አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሃ ግብር

የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ ጸታ ተኮር ሙከራዊ ጥናት (በዘጠነኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች) ተተኳሪነት

በበላይነሽ ደነቀ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም

የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ ጸታ ተኮር ሙከራዊ ጥናት (በዘጠነኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሃ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር መርሃ ግብር

የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት

በበላይነሽ ደነቀ

የጥናቱ አማካሪ

ዶክተር ብርሃኑ ቦጋለ

ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሃ ግብር

«የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ጸታ ተኮር ሙከራዊ ጥናት (በዘጠነኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት)» በሚል ርዕስ ለተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በበላይነሽ ደነቀ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ፡ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈታኞች ቦርድ አባላት፤

አማካሪ_____ፊርማ_____ቀን_____

የውጪ ፈታኝ_____ፊርማ_____ቀን_____

የውስጥ ፈታኝ_____ፊርማ_____ቀን_____

ማረጋገጫ (Declaration)

«የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ ጸታ ተኮር ሙከራዊ ጥናት (በዘጠነኛ ክፍል አሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ተተኳሪነት) » በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳንና የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም_____

ፊርማ_____

ቀን_____

ማስታወሻነቱ (Dedication)

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ማስታወሻነቱ ከህጻንነት እስከ አዋቂነት እኔን ከትልቅ ደረጃ ለማድረስ ብዙ ውጣውረድ ላየው፣ ለኔ ለኖረውና የእኔን ከዚህ መድረስ ሳያይ ጥቅምት 10 ቀን 1998 ዓ.ም. ከዚህ አለም በሞት ለተለየኝ እጅግ ለምወደው ውድ አባቴ ለአቶ ደነቀ አበጋዝ ይሁንልኝ::

ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ጀምሬ በሰላም እንዳጠናቅቅ ጤናዬን የሰጠኝ አልፋና አሜጋ የሆነው ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን፡፡

ውድ መምህሬና አማካሪዬ ዶ/ር ብርሃኑ ቦጋለ ከርዕስ መረጣው ጀምረው ጥናታዊ ጽሑፉን በጥልቀት በማንበብ የተንጋደደውን በማቃናት፣ ገንቢ አስተያየትና ጥቆማ በመስጠት፣ በተለይም የመረጃ መተንተኛ መንገዶችን ደጋግሞ በማመላከትና በመፈተሽ ላደረጉልኝ ሙያዊ እገዛ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ ስለማማከር ጥበባቸውና ችሎታቸው ልዩ አድናቆት አለኝ፡፡ የእውቀት፣ የክህሎትና የጥሩአመለካከት አባቴ በመሆናቸው ቸሩ ልዑል እግዚአብሔር ጤናና እድሜ በመስጠት ውለታቸውን ይክፈልልኝ፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን የሆኑት ዶ/ር ጌታሁን አማረ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)፣ ዶ/ር ሙሉሰው አስራቴ፣ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው፣ ደ/ር አለሙ ካሳዬ፣ ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠትና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለጥናታዊ ጽሑፉ ስኬታማነት ላደረጉልኝ የላቀ አስተዋጽኦ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ ዶ/ር ገሰሰ ታደሰ እና ዶ/ር ጌታቸው አዱኛ፣ በትልመጥናቱ የፈተና ወቅት ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት የጥናቱን አቅጣጫ በማቃናት ላደረጉልኝ የላቀ አስተዋጽኦ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ ዶ/ር ታምሬ አንዷለም የመረጃ መተንተኛ መንገዶችን በመጠቆም ላደረጉልኝ ድጋፍ ከልብ አመሰግናሁ፡፡ የኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር አቶ ኑሩ ፣ ለአማርኛ ቋንቋ መምህርት ለወ/ሮ አልማዝ ታደለ፣ ለ2008ና ለ2009 ዓ.ም. የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ የትግበራ ሂደት ላደረጉት ትብብር ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡

ወለጋ ዩኒቨርሲቲና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱን ወጪ በመሸፈን ላደረጉልኝ ድጋፍ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ መምህር አቶ ታሪኩ ነገሰ፣ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህር ዶ/ር ዘውዱ መብራ እና የአክሱም ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር ተስፋ አከለ ጥናቱን እያነበቡ ገንቢ አስተያቶችን በመስጠትና መረጃዎችን በመጠቆም ላደረጉልኝ ከፍተኛ ትብብር የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ ህልሜ እውን እንዲሆን ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ያለብኝን የቤተሰብ ሃላፊነት በመሸከም፣ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ በማድረግ ከጎኔ ለነበረሽው ለውድ እህቴ ለመምህርት ገነት ደነቀ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡

የይዘት ማውጫ

ገጽ

ማስታወሻነቱ (Dedication) 1
ምስጋና i
የይዘት ማውጫ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ vi
የስዕል ማውጫ viii
አህፅሮተ ጥናት ix
ምዕራፍ አንድ 1
መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ 1
1.2 የጥናቱ መነሻ ምክንያት 10
1.3 ዋና ዓላማ 19
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት 19
1.5 የጥናቱ ወሰን 20
የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ 22
2.1. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት 22
2.2. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት 25
2.3 ቃላትን የመማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት 27
2.4. ቃላትን የመማር ብልሃቶች ክፍፍል/ምደባ 30
2.4.1 የGu & Johnson የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል 30
2.4.2 የSchmitt የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል 31
2.4.3 የNation የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል 32
2.4.4 የOxford የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል 34
2.4.4.1 ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች 34
2.4.4.1.1 የትውስታ ብልሃቶች 34
2.4.4.1.2. አእምሯዊ ብልሃቶች 36

2.4.4.1.3. አካካሽ ብልሃቶች 39
2.4.4.2. ኢ-ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች 40
2.4.4.2.1. ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች 41
2.4.4.2.2. ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች 42
2.4.4.2.3. ማህበራዊ ብልሃቶች 43
2.5. በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አቀራረብ ላይ የሚነሱ ጭብጦች 44
2.5.1. የቃላት መማር ብልሃቶችን በተናጠል ወይስ በቅንጅት ማሰልጠን? 44
2.6 የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት 49
2.7. የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ቅደምተከተላዊ ማሕቀፍ 53
2.8. የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አስፈላጊነት 56
2.9. የብልሃት ስልጠና አይነቶች 58
2.9.1 የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና 58
2.9.2. የአንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና 58
2.9.3. የረጅም ጊዜ የብልሃት ስልጠና 59
2.10. በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎች 61
2.11. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት 64
2.12. የጥናቱ ጽንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ 72
ምዕራፍ ሦስት 74
የጥናቱ ንድፍና ዘዴ 74
3.1 የጥናቱ ንድፍ 74
3.2 የናሙና አመራረጥ 75
3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ 75
3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ 75
3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ 77
3.2.4 የመምህር አመራረጥ 78
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 79
3.3.1. ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተናዎች 80

3.4 የማስተማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት 85
3.5 ስነ ምግባራዊ ሁኔታዎች 87
3.6 የጥናቱ ሂደት 88
3.7. የመረጃ አተናተን 93
3.8 ከናሙና ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች 95
ምዕራፍ አራት 97
የውጤት ትንተናና ማብራሪያ 97
4.1 የጥናቱ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ 97
4.1.1 የጥናቱ የውጤት ትንተና 97
4.1.2 የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ 123
ምዕራፍ አምስት 136
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች 136
5.1 ማጠቃለያ 136
5.2 መደምደሚያ 140
5.3 የመፍትሔ ሀሳቦች 142
ዋቢ ጽሑፎች 147
አባሪዎች 158
አባሪ ሀ ፡ የዋናው ጥናት የመከራው ቡድን የቅድመና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት 158
አባሪ ለ፡- የዋናው ጥናት የቁጥጥሩ ቡድን የቅድመና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት 159
አባሪ ሐ፡- በዋናው ጥናት ወቅት የቃላት ፈተናው ጥያቄዎች የመለየት ብቃት 160
አባሪ መ፡- በዋናው ጥናት ወቅት የቃላት ፈተናው ክብደት ቅለት ደረጃ 161
አባሪ ሠ፡- የዋናው ጥናት የሙከራው ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት የብልሃት አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት 162
አባሪ ረ፡- በዋናው ጥናት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ 163
አባሪ ሰ፡- የዋናው ጥናት ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና 165

አባሪ ሸ፡- የዋናው ጥናት ድህረትምህርት የቃላት ፈተና 168
አባሪ ቀ፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ማሰልጠኛ መሳሪያ 171

የሠንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሠንጠረዥ 4.1፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ 98

ሠንጠረዥ 4.2፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 99

ሠንጠረዥ 4.3፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ 100

ሠንጠረዥ 4.4፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 101

ሠንጠረዥ 4.5:- የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ..... 102

ሠንጠረዥ 4.6፡- የሙከራው ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 104

ሠንጠረዥ 4.7፡- የቁጥጥሩ ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ 105

ሠንጠረዥ 4.8፡- የቁጥጥሩ ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 106

ሠንጠረዥ 4.9፡- የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ጥቅል የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቆቹ አማካይ ውጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ..... 107

ሠንጠረዥ 4.10፡- የመከራው ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ጥቅል የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቆቹ አማካይ ውጤት ልዩነት በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 108

ሠንጠረዥ 4.11፡- የመከራው ቡድን የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ 109

ሠንጠረዥ 4.12፡- የመከራው ቡድን የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 112

ሠንጠረዥ 4.13፡- የመከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ..... 115

ሠንጠረዥ 4.14፡- የመከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች

ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች

ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 116

ሠንጠረዥ 4. 15፡- የመከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ 117

ሠንጠረዥ 4.16፡- የመከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች

ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር

በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት 118

ሠንጠረዥ 4.17 በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታና በቃላት ውጤት መካከል ያለው የተዛምዶ መጠን 121

የስዕል ማውጫ

ገጽ

ስዕል1.1፡-ሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞዴል 55
ስዕል 1.2፡- የጥናቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ.....72

አህፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ መሰልጠናቸው የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ በከፊል ፍትነታዊ ምርምር መፈተሸ ነበር። ይህን ዓላማ ለማሳካትም በዱከም ከተማ የሚገኘው የኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል። በትምህርት ቤቱ ከሚገኙት አሰራ ሁለት የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች የሁለት ክፍል ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ተመርጠዋል። በመሆኑም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና እየተሰጣቸው፣ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ በተለመደው የቃላት ትምህርት አቀራረብ የቃላት ትምህርትን በአስራ አራት ሳምንታት ለ28 ክፍለ ጊዜያት እንዲማሩ ተደርጓል። መረጃዎቹ በቃላት ፈተናና በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት ተሰብስበዋል። በቃላት ፈተናና በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በየአይነታቸው ከተደራጁ በኋላ በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ (የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት፣ ዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስትና በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መለኪያ) ተተንትነዋል። በውጤት ትንተናው መሰረትም የሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድኑ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ጉልህ ልዩነት (p=0.000) አሳይቷል። በተመሳሳይ የሙከራው ቡድን የድህረትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት በልጦ ጉልህ ልዩነት (p=0.002) አሳይቷል። እንዲሁም በሙከራው ቡድን ሴትና ወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን (p=.959) አሳይቷል። ከዚህም ባሻገር በሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤትና በድህረትምህርቱ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በጣም ጠንካራ ጉልህ ተዛምዶ መኖሩን (r=.947, p= .000) ጥናቱ አመልክቷል። ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ፣ የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም፣ በሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ በተመጣጣኝ ደረጃ ችሎታቸውን ለማሳደግ ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ የበለጠ አስተዋጽኦ አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። ከዚህም ሌላ ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የብልሃት አጠቃቀምንና የቃላት ችሎታን ለማዛመድ አወንታዊ አስተዋጽኦ አለው ወደሚል መደምደሚያ ተደርሷል። ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም ስነትምህርታዊ የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፣ የወደፊት የምርምር አቅጣጫዎችም ተመላክተዋል።

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

የቃላት ትምህርት በቋንቋ ትምህርት በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር በቅድሚያ ለቃላት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ ምክንያቱም በተግባቦት ሂደት ተማሪዎች አላማቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ድርጊታቸውንና ሐሳባቸውን በተመለከተ የታቀደውን መልዕክት በተገቢው መንገድ ለሌሎች ለማስተላለፍም ሆነ ለመቀበል የቃላት እውቀታቸው ቁልፍ ሚና አለው (McCrostie, 2007; Read, 2000; Nation, 2001)፡፡ በሁለተኛ ቋንቋቸው ራሳቸውን ለመግለፅ ፈልገው መግለጫ ቃላት ሲያጡ በተግባቦት ሂደት የሚያጣድርባቸው የፍርሃት ስሜት ከፍተኛ መሆኑንና በቋንቋው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንደሚያሳድርባቸው Nyikos & Fan (2007) እና Nation (2001) ጠቁመው በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና እንዳለው አስረድተዋል፡፡

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ቃላት የቋንቋ ብቃትንና በአጠቃላይ ትምህርታዊ ስኬታማነትን ለመተንበይ ዋነኛ መሳሪያ ናቸው (Vermeer, 2001; Harmer, 1991)፡፡ Wilkins (1972) በሁለተኛ ቋንቋ መልዕክትን ለማስተላለፍና ሐሳብን በመግለጽ ሂደት የቃላት እውቀት ያለውን አስፈላጊነት ሲገልጹ፣ ያለ ሰዋስው እውቀት በተወሰነ መልኩ መግባባት ይቻላል፤ ያለ ቃላት እውቀት ግን ምንም መግባባት እንደማይቻል ጠቁመዋል፡፡ ተግባቦታዊ ክንውን ዘወትር የሚደናቀፈውም ተገቢ ቃላትን በትክክል በተገቢው አውድ ባለመጠቀም ነው፡፡ ከዚህም ያለ በቂ የቃላት እውቀት በአግባቡ መግባባት እንደማይችል መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የቃላት እውቀት ለስኬታማ ተግባቦት ዋነኛ መሳሪያ ነው (Rajaee, 2013; McCrostie, 2007; Read, 2000; Qian, 2002; Lightbown & Spada, 2006)፡፡

አንዱና ዋነኛው የቋንቋ እውቀት የቃላት እውቀት በመሆኑም ያለ ቃላት ትምህርት የቋንቋን ትምህርት ሙሉ ማድረግ አይቻልም፡፡ ለዚህም ምክንያቱም ቃላት የቋንቋ አንድ ክፍል ብቻ ሳይሆኑ መማር ማስተማርን የማከናወኛና የማሳለጫ ሁነኛ መሳሪያዎች ጭምር ናቸው (Nyikos & Fan, 2007):: የሁለተኛ ቋንቋን ለመማር የቃላት እውቀት ወሳኝ ሚና እንዳለው በንድፈ ሐሳብ አመንጪዎችና በመስኩ ተመራማሪዎች ዘንድ በስፋት ተቀባይነትን አግኝቷል (Morra & Camba, 2009; Lightbown & Spada, 2006; Nation, 2001):: Hamzah, Kafiour & Abdullah (2009)ም የቃላት ትምህርት በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴና የጥናት መስክ ትኩረት እያገኘ መምጣቱን አስረድተዋል፡፡ በተለይ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የቃላት ትምህርት ጥናት የተመራማሪዎችን ቀልብ የሳበ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ መረጃን በመጠቀምም ሆነ በማስተላለፍ ረገድ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚታየው ችግር ከቃላት እውቀት እጥረት የመነጨ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

ቃላት ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ወሳኝ ጉዳዮች በመሆናቸው ከፍተኛ የቋንቋ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችም ቢሆኑ ቃላትን መማር አለባቸው (Read, 2000)፡፡ በዚህም በዘመኑ የትምህርት ባለሙያዎች ለቃላት ትምህርት ከሰጡት ከፍተኛ ትኩረት አንጻር ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው በአግባቡ መግባባትና የቃላት ትምህርት ሂደታቸውን ለመቆጣጠር እንዲችሉ ተማሪዎችን ለመርዳት ያደረጉት ጥረት የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀትን ለማዳበር የሚያስችል ውጤታማ አቀራረብ ለመፈለግ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳደር ችሏል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የቃላት እውቀት ብያኔ ቅርጽና ነጠላ ፍቺን ከማወቅ ይልቅ የቃላት አይነቶችን መለየትንና ተገቢ ቃላትን በተገቢው አውድ ውስጥ የመጠቀም ችሎታን እንደሚያካትት ግንዛቤ በመገኘቱ ነው (Nation, 2001; Read, 2000; Lightbown & Spada, 2006)፡፡

የቃላት ችሎታ ብዙ ቃላትን ከማወቅ ባለፈ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃትንም ያካትታል (Read, 2000):: ከዚህ አኳያ በቃላት ትምህርት መስክ ቃላትን ለማስተማርና ለመማር የሚያገለግሉ አያሌ የቃላት ትምህርት አቀራረቦች፣ ቴክኒኮችና ብልሃቶች ፈልቀዋል (Hatch & Brown, 1995; Nation,

2001):: ከነዚህም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሻሻል የተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል (Nykos & Fan, 2007; Schmitt, 1997)።

በዚህም የተነሳ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ወይም ቃላትን ማስተማር ነጠላ ቃላትን ማስተማርን ብቻ የሚይዝ ሳይሆን ተማሪዎች የራሳቸውን የቃላት እውቀት በራሳቸው መንገድ ለማስፋት የሚያስችሏቸው ተገቢ ብልሃቶች ማስገንዘብን ጭምር አላማው ያደረገ ነው (Nation, 2001; Nyikos & Fan, 2007)። የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በርካታ የቃላት ክምችት እንዲኖራቸው መምህራን ተማሪዎቹን ለመርዳት የትኛው ብልሃት የቃላት እውቀታቸውን በቀላል መንገድ ለማሻሻል የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ሊያውቁ ይገባል (Oxford, 2003)::

ከቃላት ለመዳ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ዋቢ አድርገው Wong (2005) እና Nation (2001) እንዳስረዱት ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀታቸው ውስን ከሆነ በቋንቋው በአግባቡ መግባባት እንደማይችሉ ማስረዳታቸው ነው። በቂ የቃላት እውቀት ያላቸው ተማሪዎች እውቀቱ ከሌላቸው በበለጠ አንድን አዲስ ጽንሰ ሐሳብ በፍጥነት መረዳት ይችላሉ። እንዲሁም በዕለት ተዕለት የተግባቦት ክዋኔያቸው የተሻሉ ስለሚሆኑ ማህበራዊ ግንኙነታቸውም የተሳካ እንዲሆን አስተዋጽኦ አለው (Nation (2001)።

ከዚህም ሌላ የቃላት እውቀት የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ዓላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በቃላት እውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክተው Tonjes (1991)፣ Read (2000) እና Qian (2002) እንዳስረዱት የቃላት ኃይል በአንብቦ መረዳት፣ በአንብቦ መዝናናትና በመማር ስኬታማነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፤ ቃላት አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ወይንም ለማደናቀፍ ሊቆሙ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በቃላት እውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ጥብቅ ግንኙነት መኖሩን አመላካች ነው። በነባራዊው ሁኔታም ተማሪዎች በርካታ እንግዳ ቃላት ያለበትን ጽሑፍ አንብበው ለመረዳት ሲሞክሩ በርካታ መሰናክሎች ሲገጥሟቸው ይታያል። Leki & Carson (1994) በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት በቂ የቃላት እውቀት አለመኖር

በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው መሆኑ ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት ጠቁመዋል። ይህም የቃላት እውቀት በሁለተኛ ቋንቋ በአግባቡ ለመጠቀም ወሳኝ መሆኑን አመላካች ነው።

Macaro (2001) እንዳስረዱት ቃላት ቋንቋን ለመረዳትና ለማፍለቅ በጣም መሰረታዊ ቢሆኑም የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዴት መቅረብ አለበት? የሚለው ጥያቄ ለብዙ ጊዜ አወዛጋቢ ሆኖ መቆየቱን አስገንዝበዋል። አያይዘውም ከአወዛጋቢነቱ የተነሳም የተሻለ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ለመምህራን ማቅረብ አዳጋች ሆኖ መቆየቱን ጠቁመዋል። መምህራኑም የተሻለ ዘዴ ባለመጠቀማቸው ምክንያት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ለተግባቦታዊ አገልግሎት ለመጠቀም የቃላት እውቀታቸው ውስን ሆኖ ዘወትር ሲያማርሩና ቃላትን ለመማር ብዙ ጊዜ ሲያጠፉ እንደሚስተዋሉ አስረድተዋል።

Bornay (2011) እንዳስረዱት በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ታሪክ ውስጥ አብዛኛዎቹ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ለሰዋስው ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው የቃላት ትምህርትን የዘነጉ ነበሩ። አያይዘውም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ እንደማይበረታቱ፣ በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ለረዥም ዓመታት የቃላት ትምህርት ትኩረት እንዳልተሰጠውና ተዘንግቶ እንደነበረ ገልፀዋል። በዚህም የቃላት ትምህርት ይዘቶችና የቃላት መማር ብልሃቶች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሳይሰጣቸው ቆይተዋል፤ ተማሪዎችም በራሳቸው መንገድ ቃላትን እንዲማሩ ሃላፊነት አይሰጣቸውም ነበር (Coady, 1997)።

ከዚህም ሌላ Coady (1997) እንዳስረዱት ቃላትን መማር በብዙ መምህራንና ምሁራን ዘንድ ዝቅተኛ የችሎታ ደረጃ የሚጠይቅ ተግባር ነው የሚል ተገቢ ያልሆነ እይታ መኖሩ የቃላት ትምህርት ሙሉ ትኩረት እንዳይሰጠው አድርጎ ቆይቷል። Zimmerman (1997)ም የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ

ቃላትን ለማስተማርና ተማሪዎቻቸውም በራሳቸው መንገድ ቃላትን ለመማር የሚችሉባቸውን ብልሃቶች ማስገንዘብ ላይ ትኩረት ሳይሰጡ መቆየታቸውን አስገንዝበዋል።

Nation (2001) እንዳስረዱት ብዙዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ የሚገለገሉበት ሰፊ አጋጣሚ የላቸውም። በዚህም የተነሣ በቋንቋው የመጠቀማቸው ሁኔታ በአብዛኛው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተወሰነ ነው። ሆኖም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቻ የሚያገኙት ትምህርት ቋንቋውን አቀላጥፈው ለመጠቀም ስለማያበቃቸው ለአጠቃቀም ችግር ሲጋለጡ ይስተዋላል። ተማሪዎቹ ችግራቸውን አቃልለው የቃላት ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ በራሳቸው ጥረት ቃላትን መማራቸው ወሳኝ ነው። ይህ የሚሆነውም ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በተለያዩ መንገዶች ራሳቸውን ለመርዳት እንዲችሉ በሚያደርጉ ብልሃቶች የተደገፈ ትምህርት ሲያገኙ ነው።

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ከሚያግዟቸው በርካታ ነገሮች መካከል የቋንቋ መማር ብልሃቶች፣ በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶች ይገኙበታል (Oxford, 1990)። የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች የመማር ሂደታቸውን በራሳቸው እንዲቆጣጠሩና እንዲመሩ፣ የቋንቋ መማር ሂደታቸውን እንዲያፋጥኑ፣ ትምህርቱን ይበልጥ ለማቅለልና በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ስልት የሚያሳድጉበት ባህሪያት ናቸው (Oxford, 1990; 2003; Wenden & Rubin, 1987)።

የቃላት መማር ብልሃቶች ብያኔም ከዚህ ሰፊ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ብያኔ የመነጨ በመሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማር ከሚችሉባቸው መንገዶች ውስጥ የመጀመሪያውን ቦታ ይይዛሉ (Gu, 1994; Gu & Jonson, 1996; Schmitt,1997; Nation, 2001; Schmiit, 2000; Oxford, 2003):: ስለዚህ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የትምህርቱን ጫና ለመቀነስም ሆነ አዳዲስ ቃላትን በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ተገቢ የሆኑ

የቃላት መማር ብልሃቶችን ማሰልጠን በጣም ወሳኝ ነው (Pressley & McCormic, 2007)። እንደ አእምራዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እይታ አእምሯዊ እድገት በከፊል በብልሃቶች አጠቃቀም እድገት መዳበር የተወሰነ ነው። ብልሃቶችን መጠቀምን ከበቂ ልምምድ ጋር የተማሩ ተማሪዎች ብልሃቶችን በመጠቀም ልምዱ ከሌላቸው ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ ሆነው ይማራሉ (Omalley & Chamot, 1990)::

ስለሆነም የተማሪዎችን አስተሳሰብና የመማር ሂደት በራሳቸው የማያገኟቸውንና የማይጠቀሙባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች በማሰልጠን ማሻሻል ይቻላል (Pressley & McCormic, 2007)። በተጨማሪም ተማሪዎች የሚፈልጉትን ቃላት ሁሉ በክፍል ውስጥ መማርም ሆነ ማስተማር የሚቻል አይደለም:: ይህን ችግር ለማቅለል የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ማዳበር ተገቢ ነው (Oxford, 1990; O'malley & Chamot, 1990):: Han (2014) በጥናታቸው እንዳስረዱት ብልሃቶችን በመጠቀም ሂደት ተማሪዎች ሁለት አይነት ችግር ይታይባቸዋል፤ የመጀመሪያው ነጠላ ወይም ተመሳሳይ ብልሃቶችን ለተለያዩ ተግባራት በተመሳሳይ ሁኔታ በዘላቂነት መጠቀም ሲሆን፣ ሁለተኛው ብልሃቶችን ወደ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ መጠቀም አለመቻል ነው። በዚህም የተነሳ ለቃላት እውቀታቸው መዳበር ውጤታማነቱ ዝቅተኛ ነው። ይህንን ችግር ለማቅለልም ብልሃቶችን ከማሰልጠን ሂደት ጎን ለጎን ብልሃቶችን መጠቀም ያለውን ጠቀሜታና መቼ፣ እንዴትና የት መጠቀም እንዳለባቸው እንዲያውቁ የሚያስችል እውቀት ማስጨበጥ የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ የመጠቀም ችሎታቸውን ያዳብራል (Pressley & McCormic, 2007)::

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከመነሳቱ ጋር ተያይዞ የቃላት እውቀት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ ሚና እንዳለው በመስኩ ተመራማሪዎች ዘንድ እውቅና እንዲያገኝ አድርጓል። ምክንያቱም ይህ የማስተማር ዘዴ ከቅርጽ ይልቅ ትርጉም ላለው መስተጋብራዊ ተግባር አፅንየት ስለሚሰጥ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስኬታማ ተግባቦት ለማከናወን የቃላት እውቀት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑ እንዲታወቅ አድርጓል (Allen, 1983; Carter & McCarty, 1998; Schmitt

,2000)፡፡ ተግባቦታዊ አቀራረብ ከቀደሙት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንጻር ሲታይ መምህሩ እንዴት ያስተምር ከሚለው ይልቅ ተማሪዎች እንዴት ይማሩ ለሚለው የበለጠ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በሌላ አገላለጽ የተማሪዎች የቃላት እውቀት ማደግ የሚችለውም ተማሪዎች ራሳቸው የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ተዋናይ በመሆን በንቃት ሲሳተፉ ብቻ ነው ፡፡ ይህ ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተማሪዎች በራስ መር መማር (learner autonomy)ና ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረጉ ተማሪዎች ቃላትን በራሳቸው እንዲማሩ ለቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አጽንኦት ስለሚሰጥ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን መጠቀማቸው በቃላት ትምህርታቸው ስኬታማነት ላይ አስተዋጽኦ እንዳለው እንዲታወቅ አድርጓል (Tudor, 1996; Gairns & Redman, 1986; Oxford,1990)::

የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ለሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት መዳበር መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ተማሪዎች መማር ያለባቸው ስለቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችንበግልጽ ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት ለምን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደ ሚጠቀሙባቸውም ጭምር በክፍል ውስጥ መለማመድ አለባቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃቶች እውቀትና ልምድ እየዳበረ ሲሄድ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ቃላትን ለመማር ስለሚያግዛቸው ነው (OMalley & Chamot, 1990; Oxford, 1990 Oxford & Scarcella, 1994)፡፡

ይሁን እንጂ ብልሃቶችን በማስተማር ሂደት በመምህራን ላይ የሚታየው ችግር ስለብልሃቶቹ ምንነት ከመጠቆም ባለፈ ስለጠቀሜታውና ስለ አተገባበሩ ግልጽ ትምህርት አለማቅረባቸው እንደሆነ አስገንዝበዋል (Wenden, 1991; Oxford, 1990)፡፡

ቃላትን መማርን አስመልክቶ የተሰሩ ጥናቶችን ዋቢ አድረገው እንዳስረዱት ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ግልጽና የተቀናጀ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ለቋንቋው ያላቸው ተጋልጦ ዝቅተኛ በመሆኑ ብዙ ቃላትን ትርጉም ባለው አውድ በአጋጣሚ መማር ስለማይችሉ ተገቢ

የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን በራሳቸው ቃላትን እንዲማሩ መርዳት ተገቢ ነው (Brown & Perry,1991 Oxford & Crookall,1989; Oxford & Scarcella 1994)። Ellis (1985)ም ቃላትን መማር ከተማሪዎች ግለሰባዊ ልዩነት ለምሳሌ (የመማር ስልት፣ ጾታ) ወዘተ.. ጋር የተያያዘ ነው። የቃላት መማር ብልሃቶችን አጠቃቀም ለማሳደግ የሚደረጉ ማብራሪያዎችና ስልጠናዎች አላማም የትምህርቱን ሂደት በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ለማሳደግ ነው። Wenden & Rubin (1987)ም በሁለተኛ ቋንቋ ቃላት መማር ሂደት መምህራን በክፍል ውስጥ ተመሳሳይ ዘዴ በመጠቀም ቃላትን ያስተምራሉ። ነገር ግን የተወሰኑ ተማሪዎች በትምህርቱ ስኬታማ ሲሆኑ ሌሎች ግን ይወድቃሉ። ለዚህም ምክንያቱ ተመሳሳይ ዘዴ ለሁሉም ተማሪ ጠቃሚ ሊሆን አለመቻሉ ነው። ስለሆነም መምህራን ተማሪዎች በቃላት መማር ሂደት ግለሰባዊ ልዩነት እንዳላቸው ተገንዝበው የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በማስተማር በቃላት ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ መርዳት ይጠበቅባቸዋል (Ellis, 1985)።

ይህም ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በግልጽ የመማር አስፈላጊነትም የተለያዩ ንድፈ ሐሳባዊ መነሻዎች አሉት። እንደ Omalley & Chamot (1990:196) ገለጻ "አእምሯዊ ንቃት ያለው ተማሪ የበለጠ ይማራል" የሚለው የአእምሯዊ የቋንቋ መማር ንደፈ ሀሳብ የዚህ ሀሳብ ደጋፊ ነው። ይህም ተማሪዎች ልዩ ልዩ የመማር ተግባራትን በንቃት ተቀብለው በማደራጀት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር ማዛመድ የሚችሉት ልዩ ልዩ የመማር ብልሃቶችን መርጠው ሲተገብሩ ነው ከሚል መነሻ የመነጨ ነው።

ይህን ሐሳብ የሚያጠናክሩት Wlliams & Burden (1997)ም ተማሪዎች መማርን እንዴት መማር (learning how to learn) እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡ ብልሃቶችን ማወቃቸውና መተግበራቸው የትምህርቱ ዋነኛ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያግዟቸው ያስገነዝባሉ። Brown (1994)ም መስተጋብራዊ፣ ውስጣዊ ተነሳሽነትና ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብ አስፈላጊነቱ በሚወሳበት ዘመን ተማሪዎች መማርን የሚረዱ ብልሃቶችን በግልጽ እንዲገነዘቡ ማድረግ ከመማሪያ ክፍል ውጪ ጭምር ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተምሩበትን መንገድማመቻቸት እንደሆነ ጠቁመዋል።

ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በግልጽ የመማር አስፈላጊነትን የሚያጠናክረው ሌላው ሐሳብ “ተማሪዎች የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ አዳዲስ ተግባራት ማሸጋገር ይችላሉ” የሚለው አስተሳሰብ እንደሆነ Omalley & Chamot (1990፣121) ገልጸዋል። ይህም ተማሪዎች አንድ ጊዜ ብልሃቶችን ተገንዝበው መጠቀም ከለመዱ ቀድመው ከተማሯቸው ተግባራት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው አዳዲስ ተግባራት ሲያጋጥሟቸው ብልሃቶቹን በመጠቀም ይማራሉ የሚል ነው።

ቃላትን የመማር ሂደት ዘርፈ ብዙ ችሎታን የሚጠይቅ በመሆኑ ማንኛውም ተማሪ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማርበት ወቅት ከሚያጋጥሙት በጣም ፈታኝ ተግባራት አንዱና ዋነኛው ነው:: ውስብስብ ችሎታ ከመጠየቁ ጋር ተያይዞም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዘወትር የሚቸገሩበት የቋንቋ ትምህርት ይዘት እንደሆነ ይገለጻል (Read, 2000; Nyikos & Fan, 2007; Kilickaya & Krajka, 2010)።

Nation (2001)ም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት እውቀት መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ በቃላት መማር ብልሃቶች ላይ ስልጠና መስጠት መምህራን የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሻሻል የሚችሉበት ውጤታማ አቀራረብ ነው። ነገር ግን አብዛኛዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን የቃላት መማር ብልሃቶችን አስፈላጊነትና አጠቃቀም በግልጽ ስለማያስተምሯቸው ተማሪዎቹ ስለብልሃቶቹ ግንዛቤ የላቸውም። ስለተለያዩ ብልሃቶች የግንዛቤ እጥረት መኖር ደግሞ ለቃላት ትምህርት ክብደት አንዱ ምክንያት ነው (Rajaee, 2013) ።

ከ1980ዎቹ ወዲህ የስነትምህርት፣ የስነልሳንና የስነልቦና ባለሙያዎች በቃላት ትምህርት ላይ በርካታ ጥናቶች ያካሄዱ ሲሆን፣ የጥናቶቹ ውጤቶችም በቃላት ትምህርት ላይ የነበሩ አመለካከቶችን እስከመቀየር እንደደረሱ Nation (2001) እና Read (2000) ይገልጻለ። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ቃላትን መማር በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስብስብ ችሎታን የሚጠይቅ በመሆኑ የመምህሩንም ሆነ የተማሪውን ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ተግባር እንደሆነና ተገቢ ቃላትን በተገቢ አውድ በብቃት ለመጠቀም ስለሂደቱ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ግንዛቤያቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ሂደት እንደሆነ መግንዘብ ደረጃ ላይ ተደርሷል።

Nunan (1991) መምህራን ቃላትን በክፍል ውስጥ በተናጠል ከማስተማር ጎን ለጎን ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ የቃላት መማር ብልሃቶችን በምሳሌ በማስደገፍ ማስተማርና ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ስለተለያዩ ብልሃቶች ግንዘቤው ካላቸው በቃላት ትምህርቱ ሂደት በተለያየ መልኩ ራሳቸውን መርዳት ይችላሉ፤ ተገቢ ከሆኑ ብልሃቶች ጋር ይተዋወቃሉ፡፡ Hatch & Brown (1995) እና Cohen (1998)ም ቃላትን ማስተማር ቃላትን ነጥሎ ማስተማርን ብቻ የሚይዝ ሳይሆን ተማሪዎችን በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ብቁ በማድረግ በራሳቸው መንገድ የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ መርዳትን ያካትታል፡፡

ከመስኩ ባለሙያዎች ሀሳብ በመነሳት ይህ እውነታ አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋነት በሚሰጥበት የቃላት ትምህርት አውድም ሊሰራ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ ኢአፍፊትም ሆኑ አፍፊት ተማሪዎችን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውጤታማ የቃላት ትምህርት ለመስጠት ዘመናዊ የቃላት-ትምህርት የሚጠይቃቸውን ሂደቶችና ስልቶች ከመገንዘብ አልፈው መተግበርም ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረቦች የቃላት እውቀትን ሊያዳብሩ በሚችሉ መልኩ የሚተገበሩ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለዚህም መሰረታዊ ምክንያቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዘመን ወለድ የሚባሉ ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎችን በተመለከተ የሚሰጣቸው የስራ ላይ ስልጠና አለመኖሩ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ ጥናትም ቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

1.2 የጥናቱ መነሻ ምክንያት

የቃላት ትምህርት ለተግባቦታዊ ስኬት መሰረት በመሆኑ በተለያዩ የትምህርት እርከኖች ወይም ደረጃዎች በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ ሰዎች ቋንቋን እንዲማሩ ከሚያስገድዷቸው ምክንያቶች እንዱና ዋነኛው ተግባቦታዊ ብቃትን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ የቃላት አውቀት ቁልፍ

ሚና አው። ምክንያቱም ስለአንድ ነገር በአግባቡ ማዳመጥ፣ መናገር፣ እንብቦ መረዳትና መጻፍ ከቃላት እውቀት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። በቂ የቃላት እውቀት ያላቸው ተማሪዎች አንድን አዲስ ጽንሰ ሐሳብ በፍጥነት መረዳት ይችላሉ፤ በዕለት ተዕለት የተግባቦት ክዋኔያቸው የተሻለ ስለሚሆኑ ማህበራዊ ግንኙነታቸውም የተሳካ እንዲሆን አስተዋጽኦ አለው (Nation, 2001)።

Nation (2001) አንደሚያስረዱት ከ1980ዎቹ አጋማሽ ወዲህ በሚያስገርም ሁኔታ የቃላት ትምህርትን በርካታ ጥናቶችና ህትመቶች ተከናውነዋል። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ጥናቶችና ህትመቶች ተደራሽ በሆኑት ጥናታዊ መጽሔት (ጆርናሎች) ላይ የታተሙ ባለመሆናቸው ብዙ የቋንቋ መምህራን አያውቋቸውም። በመሆኑም በመምህራን የቃላት ትምህርት አመለካከትና አተገባበር ላይ ያመጡት ለውጥ በጣም ዝቅተኛ ነው። ከ1980ዎቹ በኋላ የተከናውኑ የምርምር ውጤቶች Schmitt (1997) እና Oxford (2003) እንደሚጠቁሙት የቃላት መማር ብልሃቶችን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በግልጽ ማሰልጠን በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ አዳዲስ ቃላትን በራሳቸው መንገድ በቀላሉ እንዲማሩ ይረዳቸዋል።

ከመስኩ ባለሙያዎች የምርምር ውጤት መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች በቃላት ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን በጥልቀትና በስፋት ማሰልጠን እንደሚያስፈልግ ነው። ጥሩ የቃላት መምህር ለመሆንም ሂደቱ የሚጀምረው የቃላትን ትምህርት አቀራረብ ሂደት ከመረዳት እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

Nunan (1991) ቃላትን ማስተማር ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገው ቃላትን ለመማር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ቁምር እንደ ሆነ ያስረዳሉ። ምክንያቱም ተማሪዎችቃላትን ለመማር የሚያስችሉ የቃላት መማር ብልሃቶችን የሚተዋወቁበት እድሎች ከተመቻቹላቸው በአግባቡ ሊማሩና የቃላት እውቀታቸውን ሊያዳብሩ ስለሚችሉ ነው።

በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ውጤታማና ውጤታማ ያልሆኑ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ (Gu & Johnson, 1996; Schmitt,

1997)። ውጤታማ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በተገቢው መንገድ በመጠቀም፣ የቃላትን አውዳዊ ፍቺና የርስበርስ የፍቺ ግንኙነትን የሚረዱ ሲሆኑ ውጤታማ ያልሆኑት ደግሞ የቃላት መማር ብልሃቶችን በተገቢው መንገድ የማይጠቀሙ ናቸው። በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች በማበረታታትና ሌሎች ተጨማሪ ብልሃቶችን በማሰልጠን ውጤታማ በሆኑና ባልሆኑ ተማሪዎች መካከል ያለን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ልዩነት በማቀራረብ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ማዳበር ይችላሉ (Oxford, 1990; Schmitt, 1997)።

የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን አስፈላጊነት ዙሪያ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ በተለያዩ ምሁራን ከላይ የተጠቀሱት አይነት ሐሳቦች ከመኖራቸውም በተጨማሪ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው በውጭ ሃገር የተካሄዱ ጥናቶችም የተለያዩ ውጤቶችን ያመለክታሉ።

ለምሳሌ፣ Cohen & Aphek (1980)፣ Brown & Perry (1991)፣ Yang (2014)፣ Mahdavi (2014)፣ Aktekin & Guven (2013)፣ Tassana-Ngam (2004)፣ Ronald (2001)፣ Alseweed (2000) የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ጥናት አካሂደዋል። በጥናቱ ግኝትም ብልሃቶችን በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ ቃላትን ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በድህረትምህርት የቃላት ፈተና የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ጠቁመዋል።

የምርምሮቹ ዋነኛ ክፍተት ግን የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳለው ከመግለጽ ውጭ የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ (Effect Size) ምን እንደሚመስል የገለጹት ነገር የለም።

ቀደምሲል እንደተገለጸው የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን በተማሪዎች የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ላይ አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው

የተለያዩ የምርምር ውጤቶች አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ Krzysztof (2014) እንዳስረዱት የቃላት መማር ብልሃቶችን በማሰልጠን ላይ የተደረጉ ጥናቶች መሰረታዊ ድክመቶች አሉባቸው፤

1. አብዛኛዎቹ ጥናቶች የተማሪዎችን ግለሰባዊ ልዩነትና እያንዳንዱ ብልሃት ለቃላት ትምህርት ያለው አስተዋጽኦ የተለያየ መሆኑን ከግምት ሳያስገቡ በነጠላ ብልሃቶች ወይም ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን የያዘ ውህድ አቀራረብ (mixed approach)ን ያልተከተሉና በተለይም ልዕለአእምሯዊ ብልሃቶችን ያላካተቱ በመሆናቸው ተማሪዎች የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ አዳዲስ ተግባራት በማሻገር እንዲጠቀሙና በራስ መር መማርን ለማጎልበት ጠቀሚታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ጥናቶቹ ከፍተት ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ ብልሃቶችን በተለይም ልዕለአእምሯዊ ብልሃቶችን በማካተት በተቀናጀ መልኩ በግልጽ መማርና አለመማር በቃላት ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ መፈተሽ አለበት፡፡

2. በዚህ ጥናት በክለሳ ድርሳን ክፍል 2..10 በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ተላውጦዎች እንዳሉ ተጠቁሟል፡፡ ስለሆነም Oxford (1990) እንዳስረዱት ተማሪዎች ስልጠና ቢሰጣቸውም ውጤታማ ላይሆኑ ስለሚችሉ ጥሩ የብልሃት ስልጠና ሁልጊዜ ተማሪዎች ከስልጠናው በፊት በብልሃቶች አጠቃቀም ያላቸውን የቀደመ አውቀት በመለየትና በድህረትምህርትም ስልጠናው በተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ላይ ያለውን አስተዋጽኦ በመፈተሽ ላይ ማተኮር አለበት፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በድህረ ትምህርት ተማሪዎች የሚያስመዘ ግቡት የቃላት ውጤት በርግጥም ስልጠናው የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በማሻሻሉ የተገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ መነሻ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር አብዛኞቹ ጥናቶች በቅድመትምህርትም ሆነ በድህረትምህርት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ባልተለካበት በፈተና ብቻ በተገኘ ውጤት ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ክፍተት ይታባቸዋል፡፡

በተጨማሪም በአብዛኛው በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተሰሩ በመሆናቸው በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ ውጤት ይገኝ ይሆን? የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል Carrell, Pharis & Liberto (1989)ም በልዕለ አእምሯዊ የቃላት መማር ብልሃቶች ላይ ስልጠና በመስጠት ለቃላት አውቀት መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ፈትሸዋል፡፡ በጥናቱ ውጤትም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ጠቁመዋል፡፡ O'Malley እና ሌሎች (1985) የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ እንግሊዝኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ እስያዊ (Asian) ተማሪዎችን በሙከራና በቁጥጥር ቡድን በመክፈል ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናቱ ውጤትም ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳትም ሆነ የቃላት ችሎታ ለማሻሻል የተለየ አስተዋጽኦ እንደሌለው ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የቃላት መማር ብልሃቶች የቃላት ችሎታን ለማዳበር የተለየ አስተዋጽኦ የሌላቸው መሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም የCarrell, Pharis & Liberto (1989) እና O'Malley እና ሌሎች (1985) ጥናት ውጤት Rajee (2013)፣ Alseweed (2000)፣ Aktekin & Guven (2013)፣ Mhadavi (2014)፣ Rodriguez & Sadoski (2000)፣ Ronald (2001) እና Tassana-Ngam (2004) ካገኙት የምርምር ውጤት የተለየ ወይም የሚቃረን እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን ላይ የተከናወኑት የምርምር ውጤቶች የተወሰኑት የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር የላቀ ድርሻ አለው ሲለ፣ የተወሰኑት የምርምር ውጤቶች ደግሞ የተለየ ድርሻ የለውም የሚል የሚቃረን ውጤት ማግኘታቸው ለጥናቱ መነሻ በመሆን አገልግሏል፡፡

ሌላው በሁለተኛ ቋንቋ አውድ ውስጥ በቃላት መማር ብልሃቶች ማስተማር ዙሪያ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የምርምር ትኩረት ከተሰጣቸው የተማሪዎች ባህርያት መካከል ጾታ አንዱ ነው፡፡ ለምሳሌ O'malley & Chamot (1990) በዋቢነት እንዳሰፈሩት Oxford፣ Nyikos እና Ehrman (1988) ከጾታ ጋር በተያያዘ በቋንቋ መማር ብልሃቶች ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችን ለመፈተሽ ባደረጉት የጥናት አሰሳ በጉዳዩ ዙሪያ በጣም ጥቂት ጥናቶች ብቻ ተሰርተው ተገኝተዋል፡፡ ከነዚህም

አብዛኞቹ ሴቶችና ወንዶች የሚመርጧቸውን ብልሃቶች በመለየት ላይ ያተኮሩ እንደነበሩ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ሁሉም ጥናቶች የተሰሩት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም ከዚያ በታች በሚገኙ ተማሪዎች ዙሪያ ፍተሻ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡ በተለይ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ መማር ከጸታ አንጻር በቃላት ውጤት ላይ ልዩነት መፍጠር አለመፍጠሩን በጥናት መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

በጥቅሉ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን በተካሄዱት እነዚህ ጥናቶች ላይ የታዩ ክፍተቶች በጉዳዩ ዙሪያ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም ጥናቶቹ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሻሻል አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው ቢያመለክቱም፤ በተለይም Williams & Burden (1997) እና Oxford (1990) እንዳስገነዘቡት ደግሞ ስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችን በግልጽ የማሰልጠን ውጤታማነት ከቋንቋ ቋንቋ ስለሚለያይ በሀገራችንም ጉዳዩ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

የቃላትን ትምህርት ስኬታማነት ለመፈተሽም በአማርኛ አፍራትምይሁኑ ኢአፍራት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ችሎታ፣ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ምን አንደሚመስልና የክፍል ውሰጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት ስልቶች አቀራረብ አንጻር ያለው ተገቢነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመፈተሽ በአገር ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ይህ ጥናት እንዲጠናም እንዱ ምክንያት በጥናቶቹ የተገኙት ጥቆማዎች ናቸው፡፡

ንጋቱ (2000) እና በላይነሽ (2002) አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ለመፈተሽ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ግኝትም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች (በላይነሽ፣ 2002) እና አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች (ንጋቱ፣ 2000) ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በመጠቀም ላይ የተመሰረተ አለመሆኑንና የቃላት ችሎታቸውም

ዝቅተኛ መሆኑን አሳይተዋል፡፡ ለተማሪዎቹ የቃላትና የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ ዝቅተኛ መሆን እንደምክንያት የተጠቀሱትም መምህራኑ በተማሪዎች ላይ ከሚታይ የግንዛቤ ችግር በመነሳት በክፍል ውስጥ ብልሃቶቹን በግልጽ ለማስተማር ጥረት አለማድረጋቸው እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

የጥናታቸውን ውጤት መነሻ በማድረግም በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ዘመናዊ የቃላት ትምህርት መማሪያ ስልቶችን የተከተለ እንዲሆንና የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ማዳበር እንዲችል መምህራን ተማሪዎቻቸው ከአብዛኞቹ ብልሃቶች ጋር እንዲተዋወቁ በማገዝ በራሳቸው ጥረት ቃላትን እንዲማሩ መርዳት እንደሚገባ የመፍትሄ ሐሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ይህም በቃላት ትምህርት ዙሪያ ያለውን ችግር ከማሳየቱም በተጨማሪ የተማሪዎቹን የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ በማዳበር የቃላት ችሎታቸው እንዲሻሻል ንድፈ ሀሳባዊም ሆነ ተግባራዊ ስልጠና መስጠት እንደሚያስፈልግና ለቃላት ችሎታቸው መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፤ ቢባል ምክንታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ብሩክታዊት (2001)፣ ደረበ (1999) እና እሸቱ (1997) የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ጋር ያለውን ተገቢነት ለመፈተሽ ጥናቶች አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤትም መምህራን ቃላትን ሲያስተምሩ የተለመዱትንየቃላት ማስተማሪያ ዘዴዎች አዘውትረው እንደሚጠቀሙ፣ አብዛኛው ትኩረታቸውም ፍቺና መዋቅርን ማሳወቅ ላይ እንደሆነና የቃላት መማር ብልሃቶችን ባጣመረ መልኩ ስለማያቀርቡ አቀራረቡ ተማሪዎችን አሳታፊ አለመሆኑን፣ መምህራኑም ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ስነትምህርታዊ ቴክኒኮችን በተመለከተ ምንም አይነት የስራ ላይ ስልጠና ወስደው ስለማያውቁ ከዚህ ውጪ ሌሎች የቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ስለመኖራቸው በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸውና የተማሪዎች የቃላት ችሎታም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡

የጥናታቸውን ውጤት መነሻ በማድረግም በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ዘመናዊ የቃላት ማስተማሪያ ስልቶችን

የተከተለ እንዲሆንና የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ማዳበር እንዲችል ለመምህራን ተከታታይ የሆነ የቃላት ትምህርት አቀራረብ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ሊሰጣቸው እንደሚገባ የመፍትሄ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ይህ ደግሞ መምህራን ከአዳዲስ ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስነትምህርታዊ ቴክኒኮች ጋር የተዋወቁ ባለመሆናቸው የክፍል ውስጥ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ዘመናዊ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴዎችና ብልሃቶች ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሳደግ ውጤታማ አለመሆኑን አመላካች ነው፡፡

አጥኚዋም አማርኛን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በማስተማር ልምዷ ያስተዋለችው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ በተለይም በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በቋንቋው በአግባቡ ለመጠቀም የቃላት እውቀት ችግር እንደሚገጥማቸው ነው፡፡ ለተማሪዎች የቃላት እውቀት ዝቅተኛ መሆን የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ይህ ችግር ከቃላት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጋር እንደሚያያዝም ለመረዳት ተችሏል፡፡ ምክንያቱም ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴው ሂደትን ያልተከተለና ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን ከማስተዋወቅ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አንብቡና መልመጃዎችን ስሩ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቻቸውን ፈልጉ ወዘተ.በሚል የተለመደ አካሄድ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተማሪዎችን አሳታፊ አይደለም፤ እውቀትን ከመገንባት ይልቅ አውቀትን በማስተላለፍ (ከተማሪ ተኮር ይልቅ መምህር ተኮር) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት ያለው የቃላት ትምህርት አቀራረብም በተለመደው የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተቃኘ ነው፡፡

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በመፈተሽ በተገኘው መረጃ እንደተረጋገጠውም አሁን በስራ ላይ ያለው የመማሪያ መጽሐፍም በ2004 ዓ.ም. የታተመ ሲሆን፤ አቀራረቡ «አንብቡና ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ስጡ» የሚል የተለመደውን አቀራረብ የሚከተል ነው፡፡ ይህ አቀራረብ ደግሞ ተማሪዎች መምህራን በሚያቀርቡላቸው ቃላት ላይ እንዲወሰኑና በመምህራን ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ O'malley & Chamot (1990)

እና Mhadavi (2014) እንዳስገነዘቡት ደግሞ ሁለተኛ ቋንቋን ዝቅተኛ ተጋልጦ ባለበት አካባቢ ለሚማሩ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀምና ግንዛቤ በማዳበር በራሳቸው ጥረት የቃላት እውቀታቸውን ለማሻሻል የላቀ ድርሻ አለው።

በአጠቃላይ ከላይ እንደተጠቀሰው አጥኚዋ በዚህ መልኩ ባደረገችው አሰሳ፤

- የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የመማር አስፈላጊነት ላይ የሚስማሙ ምሁራን መኖራቸውን በመገንዘቧ፣
- የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የማሰልጠን ስኬታማነት ከቋንቋ ቋንቋ በመለያየቱ በአገራችን አውድ ውጤታማነቱ መፈተሽ እንዳለበት በመረዳቷ፣
- የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን በተማሪዎች የቃላት ችሎታ ላይ አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ቢያመለክቱም ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን ላይ የተደረጉ ምርምሮች መሰረታዊ ድክመቶች ያለባቸው በመሆኑ፤
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶችን አስመልክቶ የተሰሩት ጥናቶች የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በመለየት ላይ ብቻ ያተኮሩ በመሆናቸው ብልሃቶቹን በግልጽ መማርና አለመማር ለተማሪዎች የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም መዳበር ያለውን አስተዋጽኦ የፈተሸ ሙከራዊ ጥናት ባለመኖሩ፤
- ተማሪዎች ስለቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑና ለተማሪዎች የቃላት እውቀት ችግርም ዋነኛው ምክንያት ከቃላት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጋር እንደሚያያዝ በተለያዩ ጥናቶች በመጠቆሙ፤
- በሌላ መልኩም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን ላይ የተከናወኑት የምርምር ውጤቶች የተወሰኑት የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር የላቀ ድርሻ አለው ሲሉ፣ የተወሰኑት የምርምር ውጤቶች ደግሞ የተለየ ድርሻ የለውም የሚል የሚቃረን ውጤት ማግኘታቸው ለጥናቱ መነሻ በመሆን አገልግሏል።

ከዚህ በመነሳትም አጥኚዋ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን በኢትዮጵያ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ከሚማሩት መካከል በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ተገፋፋች፡፡

በዚህም መሰረት በጥናቱ የሚከተሉት አልቦ መላምቶች ተፈትሸዋል፤

1. ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የቃላት እውቀት ልዩነት አይኖርም፡፡
2. ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት አያሳይም፡፡
3. ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የጎላ የቃላት እውቀት ልዩነት አይኖርም፡፡
4. ብልሃቶቹን በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ የለም፡፡

1.3 ዋና ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ መሰልጠናቸው የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው፡፡

1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የሚታዩባቸውን ተላውጠዎች መለየት ለመማር-ማስተማሩ ሂደት የላቀ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ ከዚህ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ስነትምህርታዊና ምርምራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡

- ስነትምህርታዊ ፋይዳው ለተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን እንዴት በቃላት ትምህርት ሂደታቸው በመጠቀም የቃላት ችሎታቸውን ሊያሻሽሉ እንደሚችሉ የሚያሳይ የብልሃት ስልጠና እንዲያገኙ ያግዛል፡፡

- ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት / መርሃትምህርት ባለሙያዎችና የማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የቃላት ተግባራትን ሲያዘጋጁ ብልሃቶቹን በግልጽ ማቅረብን እንደ አንድ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገድ ሊጠቀሙ ስለሚችሉበት ሁኔታ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት መማር ብልሃቶች ለቃላት ችሎታ መጎልበት ያላቸውን ፋይዳ በመገንዘብ ተማሪዎቻቸው በቃላት ትምህርት ሂደት ብልሃቶቹን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለማስተማር የሚያስችል ግንዛቤ ያስገኛል፡፡

- በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ሙያ የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች ስለቃላት መማር ብልሃቶች አቀራረብ በቂ ግንዛቤ ይዘው እንዲወጡ በሚደረገው ጥረት እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

- ምርምራዊ ጠቀሜታው ደግሞ ሌሎች ተመራማሪዎች በቀሪ የቃላት መማር ብልሃቶች ብሎም በሌሎች አገርኛ ቋንቋዎች የቃላት ትምህርት ላይ ለሚያደርጓቸው ጥናቶች መነሻ ይሆናል፡፡

1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቦታና ከትምህርት ቤት አንጻር ያተኮረው በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ክልል ልዩ ዞን፣ በአቃቂ ወረዳ፣ በዱከም ከተማ በሚገኝ በአመቺ ናሙና በተመረጠው ኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነው፡፡ ከክፍል ደረጃና ከተማሪዎች አንጻርም የክፍል ደረጃው በአላማ ተኮር ናሙና፣ እንዲሁም በቀላል የእጣ ናሙና በተመረጡ በ2009 ዓ.ም በሁለተኛው ወሰነትምህርት ተመዝግበው በሚማሩ የሁለት የመማሪያ ክፍሎች የዘጠነኛ ክፍል የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡

ከቃላት መማር ብልሃት አይነቶች ውስጥም መቦደን፣ በአውድ ውስጥ ማስገባት/መጠቀም (የትውሰታ ብልሃቶች)፣ ማስታወሻ መያዝ፣ መተርጎም፣ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት መጠቀም፣ መለማመድ (አእምሯዊ ብልሃቶች)፣ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ መገመት (አካካሽ ብልሃት)፣ ራስን መገምገም፣ ራስን መቆጣጠር (ልዕአእምሯዊ ብልሃቶች)፣ ከቢጤ ጋር መተጋገዝ፣ መጠየቅ (ማህበራዊ ብልሃቶች)ና ሃላፊነትን መቀበል (ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች) የሚሉትን የቃላት መማር ብልሃቶች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ በግልጽ መሰልጠናቸው የቃላት ችሎታቸውንና የብልሃትአጠቃቀማቸውን ለማዳበር የሚኖረውን አስተዋጽኦ በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ብልሃቶቹን በግልጽ መሰልጠናቸው የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር የሚኖረውን አስተዋጽኦ በተናጠልና በቃላት ችሎታና በብልሃቶች አጠቃቀም መካከል ያለውን ተዛምዶም ይፈትሻል፡፡ ብልሃቶቹም በጥቅል እንጂ በተናጠል ለቃላት ችሎታ መዳበር የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ መፈተሽ የጥናቱ ዓላማ አይደለም፡፡ እንዲሁም የተማሪዎች የቃላት ትምህርት ውጤታማነት ከተለያዩ ባህሪያቸው ጋር የሚገናኝ ቢሆንም ይህ ጥናት ብልሃቶችን በግልጽ መማር ከጸታ አንጻር በቃላት ውጤት ልዩነት መፍጠሩን በመፈተሽ ላይ አነጣጥሯል፡፡

በመጨረሻም እነዚህ ብልሃቶች ለጥናቱ የተመረጡበት መስፈርትም፣ በስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች በአብዛኛው እንደሚተገበሩ፣ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት እንዳላቸውና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተግባራዊ እንደሚደረጉ ቀደም ሲል በቃላት መማር ብልሃቶች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ግኝት ላይ በመመስረት ነው (Oxford, 1990; Gu & Johnson, 1996; Schmitt, 1997):: ከዚህም ባሻገር ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ብልሃቶች በጥምረት የቀረቡበትም Oxford (1990)፣ Alseweed (2000) እንዳስገነዘቡት ቀጥተኛ ብልሃቶች ውጤታማ የሚሆኑት በኢቀጥተኛ ብልሃቶች ሲደገፉ ወይም አንድ ላይ ተቀናጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግም ጥናቱ እነዚህን ብልሃቶች በማሰልጠን ላይ ተወስኗል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

2.1. በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በዚህም ምክንያት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ለቃላት ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ምሁራን ይናገራሉ። ለምሳሌ Candlin (1988) የቃላት እውቀት በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ እምብርት ጉዳይ ነው በማለት ያስረዳሉ። ይህን ሀሳብ በማጠናከር Nation (1990)ም ስኬታማ ተግባቦት እንዲኖር ተማሪዎች የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በሥርዓትና በጥልቀት ማወቅ አለባቸው። በስፋትና በጥልቀት ማወቃቸው ሃሳባቸውን በግልፅና በተቀላጠፈ መንገድ እንዲገልፁ ከመርዳቱም በላይ ሐሳቦችን በጥልቀት ለመመርመርና ለመረዳት ያስችላቸዋል። Harmer (1991)ም እንዳስገነዘቡት በእያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ነባራዊ ነገሮችንና እሳቤዎችን ወክለው የሚገኙትም ቃላት ናቸው። ሰዋስዋዊ መዋቅር የቋንቋውን አፅም ቢመሠርት ቃላት ደግሞ ወሳኝ የሆኑትን የቋንቋውን ብልቶች ሥጋና ደም ሆነው ሕይወት እንዲዘራ ያደርጉታል። በንግግርም ሆን በጽሑፍ ሐሳብን ለመግለጽ፣ ከሌላ አቅጣጫ የሚሠነዘሩ ሐሳቦችን አዳምጦና አንብቦ ለመረዳት፣ በአጠቃላይ ለተግባቦታዊ ክንውን መሳካት የቃላት ዕውቀት መኖር ወሳኝ ነው (Nation, 1990)።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ McCarthy (1990) የቃላት እውቀት በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና ሲያስረዱ፣ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር በጥሩ ሁኔታ የመማሩ ጉዳይ ብቻ የሚፈይደው ነገር የለም፤ ትርጉም ያለው ተግባቦት ለማከናወን መሠረታዊው ነገር የቃላት እውቀት መኖር ነው።

ተማሪዎች የቃላት እውቀታቸው ውስን ከሆነ በሁለተኛ ቋንቋቸው በአግባቡ መግባባት እንደማይችሉ ገልጸው በተለይም ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ጋር በተገናኘ ችግር እንደሚገጥማቸው አስረድተዋል። ለዚህም ምክንያቱ ስለአንድ ነገር በአግባቡ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ጥልቅ ከሆነ የቃላት እውቀት ጋር በጥብቅ የተያያዘ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በራስ የመተማመን ችግር እንዲገጥማቸውና በቋንቋው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል (Leaver, Ehrman & Shektman, 2005; Nation, 2001; Wong, 2005)

ይሁን እንጂ ቀደም ባሉት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ከስዋስው ወተርጉም ዘዴ ዘመን ጀምሮ አስከ አዳምጦ መናገር ያሉት በሙሉ ተግባቦታዊ አቀራረብ አስከመጣበት ድረስ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለቃላት ትምህርት ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠ የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ (Nation, 2001; Zimmerman, 1997)። Carter & McCarthy (1998) እና Grains & Redman (1986) እንዳስረዱት እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ለቃላት ተገቢው ትኩረት አልተሰጣቸውም። የቃላት ትምህርት ብዙውን ጊዜ የሚቀርበው ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምሮ ነው። ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የስዋስው ወተርጉም ዘዴ ዘመን በመሆኑ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው ለትርጉምና ለስዋስው ትምህርት ነበር (Zimmerman, 1997):: ለዚህም ምክንያቱ በዘመኑ ምሁራን አስተሳሰብ ቃላት በስዋስው ትምህርት ውስጥ በውስጠ ታዋቂነት አለ የሚል ነበር (Zimmerman, 1997)። ከ1950 እስከ 1970ዎቹ ቃላትን በማስተማርና በመማር ላይ የነበረው አመለካካከት ቋንቋን ማስተማር ማለት ስዋስዋዊ መዋቅርን ማስተማር ነው ተብሎ ይቆጠራል፤ በዚህም የተነሳ ቃላት የስዋስው ተገዢ ተደርጎ ስለሚቆጠር የስዋሰዋዊ መዋቅሩን ፍቺ ለማብራራት አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ከስዋስው ትምህርት ጋር ተያይዞ ይቀርባል (Macaro, 2001)::

McCarthy (1990)ም ከደምሲል በነበረው ጊዜ ቃላት በቋንቋ ትምህርት ውሰጥ ያለውን ሚና ሲገልጹ ቋንቋ ቃላትን ቢያካትትም የምንግባባው በዐረፍተ ነገር እንጂ በቃላት አይደለም የሚል እንደሆነ አስረድተዋል። ይህን ሀሳብ በማጠናከር Rudzka & Channel (1986)፣ Bornay (2011) እና Coady (1997) እንዳስረዱትም

ቀደምሲል በነበሩት አመለካከቶች ምክንያት የቃላት ትምህርትና ጥናት ትኩረት እንዳያገኝ በማድረጉ፣ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ የቃላት ትምህርት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት አይቀርብም፤ በዚህም ምክንያት የቃላት ትምህርት ተገቢነትና የቃላት መማር ብልሃት ትምህርት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ አይካተተትም፤ ተማሪዎችም በራሳቸው መንገድ ቃላትን እንዲማሩ ሃላፊነት አይሰጣቸውም:: በዚህም የተነሣ ለብዙዎቹ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ሂደት ለሚገጥማቸው ችግር መሠረቱ ቃላትን በተገቢው መንገድ አለመማራቸው ነው፡፡

ይሁን እንጂ ቃላትን መማር በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ቀላል ተግባር እንዳልሆነ ከሌሎች የቋንቋው ገፅታዎች ይልቅ ፈታኝና የመምህሩንም ሆነ የተማሪውን ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ተግባር ነው (Read, 2000):: ቃላትን ማወቅ አያሌ የቃላት እውቀት አይነቶችን ይመለከታል ለምሳሌ ፍቺን፣ የቃላት ቅርጽን፣ ፍካሪያዊና እማሪያዊ ፍቺን፡፡ ፍቺ ሰዋስዋዊ አጠቃቀምን፣ እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቺን ሲያጠቃልል ቅርጽ ደግሞ የቃላት አጻጻፍ /ስርዓተ ሆሄያትን (spelling)ና ንበትን ያጠቃልላል (Nation, 2001)፡፡ በዚህም በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዘንድ ዘወትር አስቸጋሪ የቋንቋ ክፍል እንደሆነ ይገለጻል፡፡ የቃላት አውቀት እጥረት መኖር ደግሞ ተግባቦትን ያደናቅፋል (Rajaee, 2013)፡፡ ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው፣ ቃላትን መማር ቀላል ተግባር እንዳልሆነና በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ለቃላት ተገቢው ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ነው፡፡

Nation (2001) ቀደም ሲል የነበሩት አመለካከቶች በወቅቱ ለቃላት ትምህርትና ጥናት ትኩረት እንዲሰጥ ባያደርጉም ከበርካታ አስርት አመታት በኋላ የቃላት ትምህርትና ጥናት በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በ1980ዎቹ በመዝገበ ቃላት ላይ ጥናት ከተካሄደ በኋላ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ የቃላት ጥናት እድገት እየጨመረ መጥቷል (Zimmerman, 1997)::

Scholfield's (1997) እንደሚያስረዱት በ20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ቃላትን የማስተማር ትኩረት (ፍላጎት) የመነጨው በአብዛኛው ተግባቦታዊ የቋንቋ

ማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከመምጣቱ ጋር የተያያዘ ነው። ምክንያቱም ዘዴው ከቅርጽ ይልቅ ትርጉም ላለው መስተጋብራዊ ተግባር አፅንየት ይሰጣል:: በመሆኑም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስኬታማ ተግባቦት ለማከናወን የቃላት እውቀት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑ እንዲታወቅ አድርጓል። በተጨማሪም ይህ አቀራረብ ቃላትን ለማስተማር የተለየ መንገድ ባይኖረውም ተማሪዎች የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር በራሳቸው ቃላትን መማር እንዲችሉ ትኩረት መሰጠት አለበት የሚል እምነት አለው ወይም መምህሩ እንዴት ያስተምር ከሚለው ይልቅ ተማሪዎች እንዴት ይማሩ ለሚለው የበለጠ ትኩረት ይሰጣል። በዚህም ምክንያት ቀደም ባለው ጊዜ የመዘንጋቱን ያህል ቀስበቀስ በ1990ዎቹ አካባቢ ከቃላት ማስተማሪያ ዘዴና ጥናት ጋር የተያያዙ በርካታ ጥናቶችና ህትመቶች በከፍተኛ ሁኔታ ተከስተዋል (Kojic-sabo & Lightbown, 1999)። በሁለተኛ ቋንቋ ውሰጥ ቃላትን ከማስተማር፣ ከመማርና ከቃላት መማር ብልሃቶች ጋር የተያያዙ ጥናቶችን ያካተቱ ህትመቶችም በቅርቡ ብቅ ብለዋል (Schmitt, 2000; Nation, 2001)።

2.2. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት

ብልሃት (Strategy) አንድን ጦርነት ለማሸነፍ የሚደረግ ቴክኒክና ታክቲክ ለሚለው እሳቤ ውክልና ከነበረው "ስትራቴጂያ" ከሚለው ጥንታዊ የግሪክ ቃል የመጣ ነው። ብልሃት በአሁኑ ዘመን አስተሳሰብ በተለይ በትምህርት ዘርፍ ተማሪዎች መማራቸውን ለማሳለጥ እያንዳንዳቸው የሚያደርጓቸውን ልዩባህርያት ያመለክታል Oxford, 990)። ከዚህ ጋር በተያያዘ የቋንቋ ተመራማሪዎች ብልሃት በንቁ አእምሮ ታቅዶ የሚከናወን የቋንቋ መማሪያ መንገድ እንደሆነ ያስረዳሉ (Oxford, 1990; Rubin, 1987)።

የቋንቋ መማር ብልሃቶች ግለሰቦች አንድን ሀሳብ ለመረዳት፣ መረጃ ለማከማቸት፣ አዳዲስ መረጃ ለማግኘት፣ መማርን ለመቆጣጠርና ለመገምገም ወይም አንድን የተወሰነ ተግባር ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው የተለዩ አስተሳሰቦች፣ እርምጃዎችና ስልቶች ናቸው። ስለሆነም የቋንቋ መማር ብልሃቶች በመማር ሂደት ውስጥ

የአጭር ጊዜ የትውስታ ችሎታ ውስንነትን (limitation) ለማሻሻልና መረጃን ከአጭር ጊዜ ትውስታ ወደ ረጅም ጊዜ ትውስታ አሸጋግሮ ለመጠቀም በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ በአእምሯዊ የቋንቋ መማር ንደፊ ሀሳብ እይታ የቋንቋ መማር ብልሃቶች የቀረበውን መረጃ በመፈተሽ የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታን ለማሻሻል ሁነኛ መሳሪያ ናቸው (O'mally & Chamot,1990; Pressley& McCormick, 2007)፡፡ Stern (1983) እንደሚያብራሩት ቋንቋን የመማር ብልሃት የሚለው እሳቤ በሁሉም ምሁራን ዘንድ ወጥ በሆነ መንገድ ሲገለፅና በአገልግሎት ላይ ሲውል አይታይም፡፡ ነገር ግን ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በቋንቋ ተማሪዎች በጥቅም ላይ የሚውሉ አጠቃላይ የተማሪው የአሠራር ቴክኒክ ነው፡፡

ቋንቋን የመማር ብልሃቶች የመማር አላማን መሰረት ባደረገ መልኩ በተማሪዎች የሚከናወኑና መማርን፣ እውቀት ማከማቸትን፣ ሀሳብን አስታውሶ መጠቀምን፣ መረጃ ማግኘትንና ለትምህርቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርን የሚያፋጥኑ በተማሪዎች የሚተገበሩ የአሰራር ቴክኒኮች ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የቋንቋ ተማሪው እነዚህን ብልሃቶች በመገልገል የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት የተሳካ፣ ራስ አገዝና አስደሳች በሆነ መንገድ እንዲወጣው የሚያስችሉት ናቸው፡፡ አያይዘውም ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ እነዚህን ብልሃቶች በአይነትና በተደጋጋሚ መጠቀም ከተማሪዎች የቋንቋ ብቃት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው አስረድተዋል (Wharton, 2000; Oxford, 1989)፡፡

Stern (1983)፣ Richards & Lockhart (1996) እና Wenden & Rubin (1987) የሰጡትን ብያኔ ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው ቋንቋ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ተሳትፎ ወቅት የሚያካሂዱትን ትምህርት በብዙ አቅጣጫ በመመልከት በራሳቸው ምርጫና በሚቀላቸው መንገድ እንዲማሩ የሚረዷቸው፣ በተለይ ደግሞ መምህሮቻቸውን ሁል ጊዜ ሊያገኙአቸው ስለማይችሉ ማንኛውንም ትምህርታዊ ተግባር በራሳቸው ሀይል እየሰሩ እንዲማሩ የሚያግዟቸው መንገዶች ናቸው፡፡

O'mally & Chamot (1990)፣ Rubin (1987)፣ Chamot (1987)፣ Tudor (1996) እና Oxford & Ehrman (1995) እንዳስገነዘቡት ውጤታማ የቋንቋ ተማሪዎች

የትምህርታቸውን ሂደት የሚያደናቅፉ፣ የሚያሳዩትን ለውጥና መሻሻል የሚገቱ ችግሮችንና እንቅፋቶችን ለመቋቋምና ለትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በበርካታ ብልሃቶች ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት የሚሰጡና ኃላፊነትን የሚቀበሉ፣ ሥራቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩና በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለመማር የሚሹ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥረቶች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን ከጥገኝነት ተላቅቀው፣ በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ ይረዷቸዋል፡፡

2.3 ቃላትን የመማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት

እንደ Nation (2000) የቃላት እውቀት ለተግባቦት ብቃት አስፈላጊ ነው፡፡ የቃላት እውቀት የቃላት ሆሄያት እውቀት፣ የቃላት ንበት፣ የቃላት ፍቺ እውቀት፣ የቃላት አገባብ ተገቢነት እውቀት ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም የቃላት ችሎታ ብዙ ቃላትን ከማወቅ ዘለግ በማለት የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃትንም ያካትታል (Nation, 1990)፡፡ በዚህም የተነሳ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሻሻል የተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል (Nykos & Fan, 2007; Schmitt, 1997)፡፡

Oxford & Scarcella (1994) እና Oxford (1990) እንዳስረዱት የቋንቋ መማር ብልሃት የአጠቃላይ የመማር ብልሃት ንዑስ ክፍል ሲሆን የቃላት መማር ብልሃት ደግሞ የቋንቋ መማር ብልሃት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች፣ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት በተለያየ መልኩ እገዛ የሚያደርጉ ስልቶች ናቸው፡፡ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ጽንሰ ሃሳብ የሚያጠነጥነውም ተማሪዎች የተወሰነ ውጤት ለማግኘት በንቁ አእምሮ በተለያዩ ክንዋኔዎች ሲሳተፉ የሚጠቀሟቸው የቋንቋ መማር መንገዶች ናቸው (Gu & Johnson, 1996)::

የቋንቋ መማር ብልሃቶች የቃላትን፣ የንበትን፣ የስዋስውን፣ የማንበብን፣ የማዳመጥን፣ የመናገርንና የመፃፍን ትምህርት ለማጎልበት የሚረዱ የተማሪዎች ልዩ የመማር መንገዶች ናቸው (Schmitt, 997; OMalley & Chamot, 1990):: Oxford (2003)፣

Nation (2001) እና Schmitt (1997) እንዳስገነዘቡት የቃላት መማር ብልሃቶች ብያኔም ከዚህ ሰፊ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ብያኔ የመነጨ በመሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳትና በረዥም ጊዜ ትውስታ መዝግቦ ለማቆየት ራሳቸውን ለመርዳት የሚጠቀሙባቸው የተለዩ ስልቶች ናቸው።።

Catalon (2003)ም ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች የቃላት መማር ብልሃቶች ይባላሉ በማለት ጥቅል ብያኔ ሲሰጡ Rubin እና ሌሎች (2007) ደግሞ መረጃ ማግኘት፣ ማከማቸት፣ ማስታወሰና መጠቀም የተሰኙ የመማር ሂደቶች ላይ ተፅእኖ የሚያደርሱ የተማሪዎች የቃላት መማሪያ መንገዶች ናቸው በማለት የCatalon (2003) ብያኔ በማስፋት አስረድተዋል።። የቃላት መማር ብልሃቶች ተማሪዎች ለአዳዲስ ቃላት ሲጋለጡ የቃላቱን ፍቺ ለመረዳትና ቃላቱን በዘላቂነት በአእምሯቸው ለማቆየት የሚጠቀሙባቸው የግላቸው ባህርያት ናቸው (Jurkovic, 2006)።። በአጠቃላይ የቃላት መማር ብልሃቶች የአዳዲስ ቃላትን ፍቺና የታወቁ ቃላትን ፍቺ ለመለየት፣ በረጅም ጊዜ ትውስታ ለመመዝገብና በሚያስፈልጉ ጊዜ አስታውሶ በአዳምጦ መረዳት፣ በአንብቦ መረዳት፣ በንግግርና በጽሁፍ ጊዜ አፍልቆ ለመጠቀም የሚያስችሉ የተማሪዎች ድርጊቶች ናቸው (Catalon, 2003)።።

በሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶችን ጉልህ ጠቀሜታ Mahadavi (2014) ከቻይናዎች ምሳሌያዊ አነጋገር በመነሳት እንዳስረዱት «ዓሣ እንዲበላ ስጠው! ለአንድ ቀን ዓሣ ይበላል፣ ዓሣ እንዴት እንደሚያጠምድ አስተምረው እድሜ ልኩን ዓሣ ይበላል።።» ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን ተማሪዎች ለመማር የሚፈልጉትን ቃላት ሁሉ ካለው ጊዜ፣ በእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎትና የሚማሩበት ዘዴ (መንገድ) የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ በክፍል ውስጥ በማስተማር ብቻ የተማሪዎችን የቃላት ክምችት ማዳበር አይችሉም።።

ስለዚህ መምህራን ተማሪዎች ከተወሰነ የመማሪያ ክፍለ ጊዜያቸው ውጪ ባለው ሰፊ ጊዜ በክፍል ውስጥ ያልተማሯቸውን አዳዲስ ቃላት በህይወት ዘመናቸው ሁሉ በራሳቸው መንገድ ለመማር የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች ሊያሳውቋቸው

እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡ Cohen (1998)፣ OMalley & Chamot (1990)፣ Oxford (1990) Oxford (2003)፣ Nation (2001) እና Schmitt (1997)ም የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ለሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት መዳበር መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ስለሚያግዟቸው ተማሪዎች መማር ያለባቸው ስለቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ብልሃቶችን ለምን፣ መቼ፣ የትና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸውም ጭምር በግልጽ መማርና መለማመድ አለባቸው፡፡

Gu & Johnson (1996) በተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀምና በቃላት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ በቻይና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት በብልሃት አጠቃቀምና በቃላት ችሎታ መካከል አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ጠቁመዋል፡፡ Krzysztof (2014)ም የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀምና ብልሃቶቹ ከውጤት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ለማረጋገጥ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን ከመካከለኛ-ከፍተኛ በሆነ መጠን ሲጠቀሙ በብልሃቶቹና በተማሪዎች የቃላት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን አመልክተዋል፡፡

McCarthy (1990)ም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት እውቀት መዳበር የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተካሄዱ ጥናቶች ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት ለተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም ነው፡፡ ስለሆነም ቃላትን የመማር ብልሃቶች በቃላት ትምህርት ውስጥ በተለይም ሁለተኛ ቋንቋቸውን በቂ ግብኣት በሌለበት /ለቋንቋው ያላቸው ተጋልጦ ዝቅተኛ በሆነበት አካባቢ ለሚማሩ ተማሪዎች ጉልህ ሚና ስላላቸው ተማሪዎች በግልጽ እንዲገነዘቡ ማድረግ ተገቢ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ይህን ሀሳብ በማጠናከር Oxford (1990)፣ O'malley Chamot (1990)፣ Shcmitt (1997) እና Oxford (2003)ም ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የትምህርቱን ጫና ለመቀነስም ሆነ አዳዲስ ቃላትን በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ ተገቢ የቃላት መማር ብልሃቶችን ማሰልጠን በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በRubin እና ሌሎች (2007) የቀረበ የቅርብ ጊዜ ጥናትም እንደሚያመለክተው ለሁለተኛ ቋንቋቸው ዝቅተኛ ተጋልጦ ላላቸው ተማሪዎች የቃላት መማር

ብልሃቶችን ማሰልጠን በአግባቡ ከተተገበሩ የተማሪዎችን የብልሃት አውቀት ብቻ ሳይሆን የሚያዳብሩት ተነሳሽነታቸውንና አጠቃቀማቸውንም ጭምር ነው።።

Nation (2001)ም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት በጠንካራ የቃላት ችሎታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን አስፈላጊነት በመረዳት የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ማስተማርና የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች የትኛውን ብልሃት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ማካተት እንዳለባቸው መለየት በጣም ጠቃሚ ነው።። በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ መስክ የተሰሩ በርካታ ጥናቶችም አዳዲስ ቃላትን ለመማር የቃላት መማር ብልሃቶችን መጠቀም ተማሪዎችን በቀላሉ እንዲማሩ ስለሚረዷቸው የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጠቁመዋል (Cohen, 1998; Brown & Prry, 1991; O'malley, 1987; Sokmen, 1997)::

ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች አንፃር በአጠቃላይ መምህራን ተማሪዎች ለመማር የሚፈልጉትን ሁሉንም አዳዲስ ቃላት ካለው ጊዜ፣ የቃላት ትምህርት መቋጫ የሌለው በመሆኑ፣ በእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎትና የሚማሩበት ዘዴ የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ በክፍል ውስጥ በማስተማር ብቻ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ መዳበር ይችላሉ ማለት አስቸጋሪ ነው።። ስለዚህ የመምህራን ሚና ተማሪዎቻቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች እውቀትና ልምድ እንዲያዳብሩ በማድረግ፣ እያንዳንዱ ተማሪ የሚመቸውን የመማር ብልሃት ለይቶ በመማሪያ ክፍል ውሰጥም ሆነ ውጪ እንዲገለገል መምራትና ማበረታታት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።።

2.4. ቃላትን የመማር ብልሃቶች ክፍፍል/ምደባ

2.4.1 የGu & Johnson የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል


Gu & Johnson (1996) ስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ቃላትን የመማር ብልሃቶች የ850 የቻይና ሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች በጽሑፍ መጠይቅ በመሰብሰብ አጥንተዋል።። በጽሑፍ

መጠይቁም በሰባት ዋና ዋና ምድቦች ስር በርካታ ንዑሳን የቃላት መማር ብልሃቶችን አካተው አቅርበዋል። ብልሃቶቹም በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል።

ና ዋና የቃላት መማር ብልሃቶች	ንዑሳን የቃላት መማር ብልሃቶች
ልዕለ አእምሯዊ	- ምርጫን መሰረት ያደረጉ ብልሃቶች - ዕቅድን መሰረት ያደረጉ ብልሃቶች
መገመት	- የቀደመ ልምድን መጠቀም - ስነልሳናዊ ፍንጮችን መጠቀም
መዝገበ ቃላት	- ለቁልፍ ቃለት መዝገበ ቃላት መጠቀም - ለእንግዳ ቃላት መዝገበ ቃላት መጠቀም - እግርበግር በመከተል መዝገበ ቃላት መጠቀም
ማስታወሻ መያዝ	- ፍቺ ተኮር - አገልግሎት ተኮር
ማሰላሰል	- የቃላት ዝርዝር መጠቀም - ድምፅን በማሰማት በቃል መደጋገም - በዕይታ ብቻ በመጠቀም ደጋግሞ ማሰላሰል
መረጃ መቀበል መነቃቃት	- በዕይታ መረጃ መቀበል - በማዳመጥ መረጃ መቀበል - የቃላት መዋቅርን በአእምሮ ማጥናት - ፍቺ መቀበል - አውዳዊ መረጃ መቀበል

2.4.2 የSchmitt የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል

Schmitt (1997) የጃፓን የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ 600 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚጠቀሟቸውን የቃላት መማር ብልሃቶችንና ብልሃቶቹ ለተማሪዎች ያላቸውን ጠቀሜታ በማጥናት በአምስት ምድቦች ስር የሚካተቱ 58 ዝርዝር ብልሃቶችን አቅርበዋል። ምድቦቹም **መወሰን፣ ማህበራዊ፣ ትውስታ፣ አእምሯዊና ልዕለ አእምሯዊ** ናቸው። እነዚህ አምስት ምድቦች ደግሞ እንደገና በሁለት ዋና ዋና በፍቺ ፍለጋ (Discovery strategies) እና በፍቺ ማጠናከር (Consolodating strategies) ክፍሎች ስር ተመድበዋል። በዚህ መሰረት **መወሰንና ማህበራዊ** በቃላት ፍቺ ፍለጋ ስር ሲካተቱ **ማህበራዊ፣ ትውስታ፣ አእምሯዊና ልዕለ አእምሯዊ** በቃላት ፍቺ ማጠናከር ስር ተመድበዋል። ማህበራዊ ብልሃት ለፍቺ ፍለጋም ሆነ ማጠናከር አገልግሎት ስለሚሰጥ በሁለቱም ክፍሎች ተካቷል። አከፋፈሉም የሚከተለውን ይመስላል።



መወሰን ማህበራዊ ማህበራዊ ትውስታ አእምሯዊ ልዕለ አእምሯዊ

I. የቃላት ፍቺን መፈለግ
    1. መወሰን፡- እያንዳንዱ ተማሪ ቃላትን ሲማር የሌላ ሰው ዕርዳታና ትብብር ሳይሻ በግሉ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ የሚፈልግበት ብልሃት መወሰን ይባላል፤ ለምሳሌ መዝገበ ቃላት መጠቀም፡፡
    2. ማህበራዊ፡- ተማሪዎች ለአዳዲስ ቃላት ሲጋለጡ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመረዳዳትና በመተባበር ፍቺ መፈለግ ማህበራዊ ብልሃት ይባላል፡፡
II. የቃላት ፍቺን ማጠናከር
    3. ማህበራዊ፡- በጥንድና በቡድን በመደጋገፍ የቃላትን ፍቺ ማጠናከርን ያመለክታል፡፡
    4. ትውስታ፡- ከቀደመ ልምድ ጋር አዲሱን ቃል በማዛመድ ባስፈላጊ ጊዜ አስተዋሶ ለመጠቀም የሚረዳ የቃላት መማሪያ መንገድ ነው፡፡
    5. አእምሯዊ፡- ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን አእምራቸውን በመጠቀም የሚማሩበት ብልሃት ነው፡፡
    6. ልዕለ አእምሯዊ፡- ተማሪዎች ንቁ በሆነ የአእምሮ ሂደት ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመቆጣጠር፣ ያሳዩትን ለውጥና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም ሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡

2.4.3 የNation የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል

Nation (2001፣ 218)ም ከሌሎች በተለየ ሁኔታ በጥናት ሳይሆን የራሳቸውን የቃላት መማር ማስተማር ልምድ መሰረት በማድረግ ስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች በአጠቃላይ በሦስት ምድብ ማለትም ማቀድ፣ ምንጭ (ግብዓት) መጠቀምና ሂደታዊ ብልሃቶች በማለት በሦስት ምድብ

ከፍለው አቅርበዋል። በእያንዳንዳቸው ስርም ንዑሳን ብልሃቶችን በማስቀመጥ በአጠቃላይ አስራ አንድ ብልሃቶችን አቅርበዋል።

ምድቦች	ንዑሳን ብልሃቶች
ማቀድ	- ቃላትን መምረጥ - የእውቀት ዘርፎችን መምረጥ - ደጋግሞ ማቀድ
ምንጭ	- ቃላቱን መተንተን - አውድ መጠቀም - በአፍ መፍቻና በታላሚው ቋንቋ እያገናዘቡ መማር - በአፍ መፍቻና በታላሚው ቋንቋ ተጓዳኝ ቃላትን በመተካካት መማር
ሂደት	- ማሰላሰል - ማስታወስ - ማፍለቅ

Nation እያንዳንዱ ንዑስ ብልሃት በየትኛው አጠቃላይ ምድብ ስር እንደሚገኝ በግልጽ ባለማቅረባቸው የንዑስ ብልሃቶቹን ጽንሰ ሀሳብ በአጭር ጊዜ ለመረዳት ከባድ ነው (Brown, 2000)።

ቃላትን የመማር ብልሃቶችን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መንገዶች በተለየ መንገድ ከከፈሉት ምሁራን መካከል Oxford (1990) ተጠቃሽ ናቸው። Oxford (1990) ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በማለት በመክፈል በእያንዳንዱ ሥር ሦስት ንዑሳን ብልሃቶችን ከሌሎች በርካታ ዝርዝር ብልሃቶች ጋር ለቃላት ትምህርት ተገቢ የሆኑ ብልሃቶችን በማካተት አቅርበዋል።

Ellis (1994)፣ Brown (2000) እና O'malley & Chamot (1990) እንዳስገነዘቡት እነዚህ ብልሃቶች የቅርብ ጊዜ የጥናት ውጤት በመሆናቸው፣ በብዙ ምሁራን ድጋፍ ያላቸው፣ በሌሎች ጥናቶች የቀረቡ ብልሃቶችን አካትተው የያዙ፣ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ባህሪ ከግምት በማስገባት ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ቁልፍ የሆኑ ብልሃቶችን ማለትም ልዕለ አዕምሯዊ፣ ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶችንና ማህበራዊ ብልሃቶችን ያካተተ በመሆኑ፣ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለቃላት-ትምህርት ውጤታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብልሃቶችን ለይተው ያስቀመጠና ብልሃቶቹንም በጥልቅ መረጃዎችና ምሳሌዎች አስደግፈው የሚያቀርቡ ናቸው። በተጨማሪም ቃላትን

የመማር ብልሃቶችን አተገባበር እንዳስፈላጊነቱ ምሳሌዎችን በመስጠት በግልፅ የሚያሳይና የቋንቋ ኪሂሎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ በመሆኑ ብዙ ጥናቶች እየተሰሩበት ይገኛል (Pavicic, 2008 ; Nation, 2001)።

በተጨማሪም Omall'y Chamot (1990) በOxford (1990) የቀረቡት አብዛኞቹ የቋንቋ መማር ብልሃቶች የቃላት መማር ብልሃቶች እንደሆኑ ገልጸዋል። በዚህ መሰረት ይህ ጥናትም በOxford (1990) የቀረበውን ክፍፍል መሠረት በማድረግ የተከናወነ ሲሆን፣ ለጥናቱ የተመረጡ ቃላትን የመማር ብልሃቶችም በሚከተለው መልኩ በዝርዝር ተዳስሰዋል።

2.4.4 የOxford የቃላት መማር ብልሃቶች አከፋፈል

2.4.4.1 ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

Oxford (1990) እንዳስረዱት ቀጥተኛ ብልሃቶች ተማሪዎች በቀጥታ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት እየተሳተፉ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት እንዲማሩ በቀጥታ የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው። በዚህ ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ንዑስ ብልሃቶችም የትውስታ ብልሃቶች፣ አእምሯዊ ብልሃቶችና አካካሽ ብልሃቶች ናቸው።

2.4.4.1.1 የትውስታ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ቃላትን በአእምሮው መዝግቦ በመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚረዱት ብልሃቶች ናቸው። Oxford (1990) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አንዱ መሠረታዊ ችግር በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት ወይም አገላለጾች በሌላ ጊዜ መርሳት ነው። በዚህም ተማሪዎቹ ለተለያዩ ጉዳዮች በጣም የሚጠቅሟቸውን ልዩ ልዩ የቃላት አይነቶችንና አገላለጾችን አስታውሰው መጠቀም አለመቻል ችግር ይገጥማቸዋል። የትውስታ ብልሃቶችም ተማሪዎች ይህንን ችግር በብቃት እንዲቋቋሙ ይረዷቸዋል። Oxford (1990) እንዳስረዱት ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢ

የሆነው የትውስታ ብልሃት በአእምሮ ውስጥ ምስል የመፍጠር ብልሃት ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ብልሃቶች በውስጡ ያካትታል፡፡

መቦደን፡- አዳዲስ ቃላትን ለማስታወስ በሚመች፣ ትርጉም ባለው መልኩ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንድነት በመቦደን ከአእምሮ ጋር በማያያዝ ለትውስታ የማመቻቸት ብልሃት ነው፡፡ አንድ ጊዜ የተማሩትን አዳዲስ ቃላት በቀላሉ አስታውሶ ለመጠቀም የሚያገለግል ሲሆን፣ ለምሳሌ በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸው ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ ቃላትን በአንድ ላይ፣ በቃል ክፍላቸው ለምሳሌ ስሞችን ወይም ግሶችን በአንድ ላይ፣ በፍቺ ተመሳሳይነታቸው ለምሳሌ ሞቃት፣ እሳት፣ ወይም ተቃራኒነታቸው ቀዝቃዛ፣ በረዶ፣ በአንድ ላይ መቦደን፣ ከተግባራዊ አገልግሎታቸው አንጻር ለምሳሌ ከመኪና ወይም ከማስተማር ስራ ጋር የተያያዙ ቃላትን በአንድ ላይ መቦደን፣ አንድ ሰው ስለአንድ ነገር ያለውን ስሜት ለመግለጽ የሚያገለግሉ ቃላትን ለምሳሌ መጥላት፣ መውደድ ወዘተ፣ በሰዋስዋዊ አገባባቸው ለምሳሌ አንተ፣ አንቺ፣ እሱ፣ እሷ፣ እነሱ ወዘተ .ትርጉም ባለው መንገድ በማደራጀት ከአእምሮ ጋር በማያያዝ ለትውስታ መማቻቸት፡፡ የመቦደን ብልሃት Nation (2001)፣ Schmitt(1997) እና Cohen (1990)ም ከትውስታ ብልሃቶች ተማሪዎች በአንድ ወቅት የተማሩትን ቃል በአስፈላጊ ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚረዳቸው በጣም መሰረታዊ ብልሃት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

አዳዲስ ቃላትን በዐውድ ውስጥ ማስገባት/መጠቀም፡- አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በሚሰጥ ቃላዊና ጽሑፋዊ የሃሳብ ልውውጥ ውስጥ መጠቀምና የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን በመመስረት ከቃላቱ ጋር ለተከታታይ ረጅም ጊዜያት የመዝለቅ ብልሃት ነው፡፡ አዳዲስ ቃላትን በተለያየ ዐረፍተ ነገር ውስጥ (አውድ) መጠቀም የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማስፋትና በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት ለረጅም ጊዜ አስታውሰው እንዲጠቀሙ ስለሚረዳቸው ለቃላት ትምህርት የበለጠ ጠቃሚ ነው (Gu& Johnson, 1996)::

***ሥነፍቻዊ* ካርታ፡-**የትርጉም ግንኙነት ያላቸውን ውስን ቃላት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ሊያሳይ በሚችል ስዕል ላይ መደርደር ለምሳሌ ከ"ፀጉር" ጋር የተገናኙ ቃላትን በሰው ሞንቅላት ስዕል ላይ በማደራጀት ግንኙነታቸውን በማሳየት

በአዕምሮ ውስጥ ትውስታን መፍጠር፡፡ በሌላ አገላለጽ ዋናውን ቃል መሃል ላይ በማስቀመጥ ከዋናው ቃል ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቃላት ከዋናው ቃል ጋር በቀስት በማገናኘት ቃላቱን ለረጅም ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚያስችል ብልሃት ነው፡፡ ይህ ብልሃት የተወሰኑ የቃላት ስብስቦች እንዴት እርስ በርስ ግንኙነት እንዳላቸው በግልጽ ለመረዳት ስለሚያስችልና አዳዲስ ቃላትን ለረጅም ጊዜ በአእምሮ ውስጥ መዝግቦ በማቆየት በአስፈላጊ ጊዜ አስታውሰው ለመጠቀም ውጤታማ በመሆኑ በአብዛኛው በስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች ተግባራዊ ይደረጋል (Schmitt, 1997; Brown & Perry, 1991)

ክለሳ ማካሄድ፡- በአንድ ወቅት የተማሩትን ቃላት የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር በሚል ዓላማ በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ የመከለስ ብልሃት ነው፡፡

2.4.4.1.2. አእምሯዊ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት በቀጥታ አእምሮውን በመጠቀም ተረድቶና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው፡፡ Rubin (1987)ም እንዳስገነዘቡት አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ ሲማሩ በቀጥታ አእምሯቸውን በመጠቀም የሚተገብሯቸው የአሰራር መንገዶች፣ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ወይም ችግር ማቅለያዎች ናቸው፡፡ ተማሪው በተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ተግባራት ላይ በቀጥታ የሚጠቀምባቸው መሰረታዊ አእምሯዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፤

መለማመድ፡- የንበት፣ የመጥበቅና መላላት ወዘተ ልምምድ ማድረግ፤ በአንድ አይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ ማድረግ፣ የቃላት አመሰራረትን በተደጋጋሚ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስራት ልምምድ በማድረግ፣ የቃል ክፍሎችን በመለየት ልምምድ በማድረግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ይህ ብልሃት ከአእምሯዊ ብልሃቶች በጣም መሰረታዊ ብልሃት ነው (Oxford, 1990)::

ምንጭ መጠቀም፡-በተተኳሪው ቋንቋ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለማወቅ በንግግርና በጽሑፍ መልዕክት ለማስተላለፍ የቃላት አውቀታቸውን ለማዳበር በቋንቋው የተጻፉ የታተሙ ለምሳሌ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ልቦለድ፣ መማሪያ መጽሐፍ ወዘተ. በየትኛውም ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቋንቋው የተጻፉ ጽሑፎችን በማንበብ፣ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የመሳሰሉ ምንጮችን በመጠቀም የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ፍቺና አጠቃቀም ለመረዳት የሚያገለግል ብልሃት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የአዳዲስ ቃላትን አውዳዊ አጠቃቀም ለመረዳት በቋንቋው የተጻፉ የተለያዩ ምንጮችን የመጠቀም ብልሃት ነው፡፡ እነዚህ ምንጮች ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ በቀጥታ በአውድ ውስጥ እንዲማሩና ስለተተኳሪው ቋንቋ ጠቃሚ ዳራዊ መረጃ ስለሚሰጡ ተማሪዎች ቃላቱን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ስሚረዷቸው በአብዛኛው በስኬታማ የቋንቋ ተማሪዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ (Gu & Johnson, 1996; Nation, 2001)::

መደጋገም፡- አዳዲስ ቃላትን ደጋግሞ መጻፍና ደጋግሞ ማለት (የተለያዩ ቃላቶችን በጽሑፍ ወይም በንግግር የተግባቦት ሂደት ደጋግሞ መጠቀም)፣ ቃላቱን ለብዙ ጊዜ ማዳመጥ፣ በአእምሮ ውስጥ ማመላለስና በተተኳሪው ቋንቋ የመገልገል ችሎታ ያላቸውን ሰዎች አጠቃቀም በመኮረጅ የቃላት ችሎታን ለማዳበር የሚያገለግል ብልሃት ነው፡፡ ለምሳሌ በቋንቋው የሚቀርቡ ፊልሞችን ስንመለከት በቋንቋው ተናጋሪዎች የሚቀርቡ ዐረፍተ ነገሮችን እንሰማለን፡፡ እነዚህን ዐረፍተነገሮች፣ ሐረግ ወይም ቃላት ለማስታወስ ደጋግሞ የመጻፍ ብልሃት ነው፡፡ ምክንያቱም ደጋግሞ የመጻፍ ወይም የማለት ብልሃት ዐረፍተነገሮቹን ወይም ቃላቱን በሌላ ጊዜ በትክክል ለመጠቀም ያስችላል፡፡

እንደገና ማቀናበር፡- ቀደም ሲል የተማሯቸውን ቃላት በአዲስ መልክ በማቀናጀት ትርጉም የሚሰጡ ዐረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ ደጋግሞ መልመጃዎችን መስራት፡፡

ማስታወሻ መያዝ፡- በተለያየ አጋጣሚ የሚያገኙትን የአዳዲስ ቃላትን ፍቺና አጠቃቀም በአንድ የቃላት ማስታወሻ ደብተር መዝግቦ በመያዝ ማጥናትና መለማመድ፣ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያገጥሙ አዳዲስ ቃላትን መዝግቦ በመያዝ ፍቺና አጠቃቀማቸውን ከተለያየ ምንጭ በመፈለግ የቃላት

ችሎታን ለማዳበር የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው፡፡ ተማሪዎች ማስታወሻ ሲይዙ ለምሳሌ የሁለተኛ ቋንቋ አዳዲስ ቃላትን በአፍ መፍቻ ያለውን አቻ ፍቺ በመፈለግ ማስታወሻ መያዝ፣ የቃላቱን ተመሰሳይ፣ ተቃራኒ፣ ፍካሪያዊ ፍቺ፣ የቃል ክፍላቸውንና የቃላቱን ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ወይም መዝገበ ቃላት ሳይመለከቱ ቃላቱ በራስ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ ፈልጎ መረዳት ወዘተ. ያካትታል፡፡

ማሸጋገር፡- ቀደም ሲል በአፍ መፍቻ ወይም በሌላ ቋንቋ የቀሰሙትን የቃላት ዕውቀት የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት ፍቺ ለመረዳት በቀጥታ ተግባራዊ የማድረግ ብልሃት ነው፤

መተርጎም፡- የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ቃል በመተርጎም ወይም ከአፍ መፍቻ ወደ ተተኳሪው ቋንቋ በመተርጎም የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት መጠቀም፡፡

ልሳነዋህድ መዝገበቃላት መጠቀም፡- መዝገበቃላት መጠቀም አዳዲስ ቃላት ለመማር በጣም ጠቃሚና ተጨባጭ ምንጭ ነው፡፡ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን ለመማር መዝገበ ቃላት ሲጠቀሙ ግን ልሳነ ዋህድ (በተተኳሪው ቋንቋ የተጻፈ) መዝገበ ቃላትን መጠቀም የተሻለ የቃላት እውቀታቸው እንዲሰፋ ይረዳቸዋል፡፡ ምክንያቱም ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት ሁልጊዜ የሚሰጠን ቃሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ ብቻ ነው፡፡ ልሳነ ዋህድ ወይም በቋንቋው የተጻፈው መዝገበ ቃላት ግን የቃሉን ፍቺ፣ በቃላቱ የተመሰረቱ ዐረፍተ ነገሮችን ምሳሌ፣ ተመሳሳይ፣ ተቃራኒ ፍቺና የቃል ክፍሉን ወይም ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ስለሚያካትት የቃላትን መደበኛ ፍቺና አጠቃቀም ለይተው እንዲያውቁ ስለሚረዳቸው በተለይ ቋንቋውን በጽሑፋዊ አፍልቆት ለመጠቀም ከልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት የበለጠ በጣም ጠቃሚ ብልሃት ነው (Oxford, 1990)፡፡

በርካታ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ሁልጊዜ በመዝገበ ቃላት መግቢያ የቀረበውን አጠቃቀም አያነቡትም ወይም ትኩረት አይሰጡትም፡፡ ምናልባትም ለተማሪዎች ቃላት እውቀት ማነስ አንዱ ምክንያት የቃላት አውቀትን

ሊያዳብሩ የሚችሉ ምንጮችን በተገቢው መንገድ መጠቀም አለማቻል ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይም ይህ ችግር ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ሂደት በስፋት ይስተዋላል (Sokmen, 1997)፡፡ Alseweed (2000)ም በአረብኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን በአግባቡ እንዲጠቀሙ መዝገበ ቃላት የመጠቀም ብልሃት አጠቃቀምን በክፍል ውስጥ ማስተማርና ማለመማድ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

Sokmen (1997) ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት ሰዎች ስለቋንቋው ለማወቅ መረጃ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት ተገቢ መሳሪያ ነው፡፡ በተጨማሪም Scholfield (1997) ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት ከልሳነክልኤ መዝገበ ቃላት የበለጠ ጥረት ስለሚጠይቅ ጥልቅ አእምሯዊ ሂደት እንዲከሰትና ቃላቱን በረጅም ጊዜ ትውስታ መዝግቦ ለማቆየት የተሻለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች በአግባቡ መጠቀም ስለማይችሉ በልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት የቀረቡ መረጃዎችን ለምሳሌ ምልክቶች (symbols)፣ አጽህሮተ ቃላት፣ የቃሉን የቃል ክፍል፣ የቃሉን ግንድ፣ በፊደል ተራ ቅደምተከተል ቃላትን መፈለግንና የቃላቱን ፍቺ ለማሳየት የቀረቡ ምሳሌዎችን ወዘተ በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በግልጽ ማሰልጠንና ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡

2.4.4.1.3. አካካሽ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች በቃላት ዕውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦት ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመቋቋም የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990) እንዳስገነዘቡት አካካሽ ብልሃቶች የቃላት ዕውቀት ክምችት እጥረትን ለማካካስ የሚረዱ ብልሃቶች ናቸው፡፡

ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃት የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ የመገመት ብልሃት ነው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ሁለት የተለያዩ ፍንጮችን (መረጃዎችን) ማለትም ስነልሳናዊ (በቋንቋው ያለንን እውቀት)ና ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጮችን በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገመት የሚረዱት ናቸው፡፡ ስነልሳናዊ ፍንጭ መጠቀም ማለት ለምሳሌ በንባባብ ወይም በማዳመጥ

ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን የቃል ክፍላቸውን በመለየት፣ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያን በመለየት፣ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ በመገመት መረዳት ማለት ሲሆን ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጭ (እውቀት) በመጠቀም ማለት ስለርዕሰ ጉዳዩ ያለንን የቀደመ /ዳራዊ እውቀትን ወይም አጠቃላይ እውቀትን መሰረት በማድረግ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ከአውድ በመገመት የመረዳት ብልሃት ነው። Gu & Jhonson (1996) እና Oxford (2003)ም የመገመት ብልሃት በአብዛኛው ስኬታማ (ጥሩ) የቋንቋ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚጠቀሙበት በመሆኑ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት እንዳለው አስረድተዋል።

Naiman እና ሌሎች (1978) እና Mccarthy (1990) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በማንበብ ወይም በማዳመጥ ጊዜ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥማቸው ብልህነት የተላበሰና እውቀትን መሠረት ያደረገ ግምት ይሰጣሉ። McCarthy (1990) እንዳስረዱት መገመት ሂደት ነው፤ ስኬታማ (ጥሩ) የቋንቋ ተማሪዎች በማንበብ ሂደት፣ በፈተና ወቅት ወይም በማንኛውም ሁኔታ ለሚያጋጥሟቸው ከባድ ቃላት መዝገበ ቃላት መጠቀም ወይም ሰው መጠየቅ በማይችሉበት ወይም ተገቢ በማይሆንበት ጊዜ የሚከተሉት ሂደት ነው።

2.4.4.2. ኢ-ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

Oxford (1990) በዚህ ክፍል የሚመደቡ ብልሃቶች ቀጥተኛ ባልሆነ/በተዘዋዋሪ/ መንገድ ለቃላት እውቀት መዳበር የሚያግዙ ናቸው። የተማሪውን ዘወትር የተተኳሪውን ቋንቋ ተግባራት በቀጥታ መስራትን የሚጠይቁ አይደሉም። ነገር ግን በተለያዩ መንገዶች ለቃላት ትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የትምህርታቸውን ሂደት ለመምራትና ለማመቻቸት የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው። በዚህ ስር የሚካተቱ ዋና ዋና ንዑስ ብልሃቶችም (ልዕለ አእምሯዊ፣ ስሜት-ነክ ቁጥጥርና ማህበራዊ ብልሃቶች) ናቸው።

2.4.4.2.1. ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች

ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት፣ ዝንባሌና መነቃቃት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሁም አለታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር) የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥማቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋማሉ፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነት የቋንቋው እውቀት ማነስና ለጎበረተሰቡ ባህል አዲስ መሆን በመማር ፍላጎትና በንቃት የመሳተፍ ስሜት ላይ በተወሰነ ደረጃ ጫናና የስሜት መረበሽ ማሳደራቸው የማይቀር ቢሆንም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በውስጣቸው የተፈጠረውን የመረበሽ ስሜት ለመቋቋም ይጥራሉ፡፡ ራሳቸውን እንደ አንድ የቋንቋ ተማሪ በመቁጠር በተተኳሪው ቋንቋ ፣ በህብረተሰቡና በባህሉ ላይ ቀና አመለካከት ይፈጥራሉ፡፡ እነዚህን ባህርያትም አስቀድሞ በመለየት ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃትን በተገቢው መንገድ ወደ መጠቀም ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ ዋናዋና ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ጎላፊነትን መቀበል፡- በትምህርቱ ሂደት መሳሳት እንደሚኖር በማመን ከባድ የቃላት ተግባራትን ስሜትን ተቆጣጥሮ ለማከናወን ጎላፊነትን ተቀብሎ መሳተፍ ለምሳሌ በሐሳብ ልውውጥ ሂደት ተገቢ ቃላትን መጠቀም ስለማልችል እሳሳታለሁ የሚል ስጋትን አስወግዶ ያለ ፍርሃት በንቃት መሳተፍ፤

ራስን መሸለም፡- በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ ራስን መሸለም፤ ለምሳሌ በቃላት ፈተና ጥሩ ውጤት ሲያገኙ ራስን ማድነቅ፤

አዎንታዊ ገለፃ መስጠት፡- ለራስ እእውቀት ጥሩ ግምትና አዎንታዊ መግለጫ መስጠት፣ በተለይም ከባድ የቃላት ተግባራትን ከመስራት በፊት የራስን ችሎታ ማድነቅ፤

2.4.4.2.2. ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች

የልእለ አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪው ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመቆጣጠር፣ በአጠቃላይ ያሳየውን ለውጥና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው (Oxford, 1990)። O'malley & Chamot (1990) እንዳስገነዘቡት የልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች የመማር አቅጣጫቸውን ያልለዩ፣ የመማር አቅድ የሌላቸው፣ እድገታቸውን የማይቆጣጠሩ፣ ስኬታቸውን የማይገመግሙና ቀጣይ የመማር አቅጣጫቸውን የማያውቁ ናቸው። ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማር ተገቢ የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን መምረጥ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ስለዚህ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች የቀረጹትን አላማ ለማሳካት፣ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ውጤታማነት በመገምገም የወደፊት የመማር አቅጣጫቸውን የሚወስኑበት በመሆኑ በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ማስቻል ተገቢ ነው (Oxford 1990; Schmitt, 2000)። በልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች በተማሪው የሚከናወኑ ተግባራትም፡-

የልምምድ አጋጣሚዎችን ለማግኘት መጣር፡- ለቃላት ትምህርት አመቺ ተፈጥሮአዊ አካባቢ (ሁኔታ) መፍጠር፣ ለቃላት ትምህርት ወይም ጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀት፤

ትኩረት መስጠት፡- ለቃላት ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለመማር አስቀድሞ መወሰንና በራስ ግምገማ ተገቢ የቃላት ተግባራትን መርጦ ትኩረት ለመስጠት መወሰን (መርጦ ማተኮር)፤

ማቀድ፡- ለቃላት ትምህርት የራስን ግብና አላማ ማስቀመጥ፣ ከቃላት ትምህርቱ ምን እንደሚጠብቅ /እንደምትጠብቅ አስቀድሞ የማቀድ ብልሃት ነው።

ራስን መቆጣጠር፡- ቃላትን በትክክለኛ ወይም በተሳሳተ መንገድ እየተማረ መሆኑንና የብልሃት አጠቃቀሙን በራስ በመከታተል በቃላት ትምህርት ሂደት የራስን ስህተት በራስ መለየት፤

ራስን መገምገም፡- የቃላት ትምህርቱን ውጤት በመፈተሽ ካለፈው የበለጠ መሻሻል (ለውጥ) ማሳየት አለማሳየቱን ራስን በራስ የመገምገም ወይም ተማሪዎች የቃላት መማር ሂደታቸውን የሚገመግሙበት ብልሃት ነው፡፡

2.4.4.2.3. ማህበራዊ ብልሃቶች

Oxford (1990) እንዳስረዱት እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር ቃላትን እንዲማር የሚረዱት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ቋንቋን ለመማር የሌላ ሰው ተሳትፎ አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ተማሪዎችም ለቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት በጋራ ሊሰሩ ይገባል፡፡

ስለሆነም ማህበራዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ፣ ግልፅ ያልሆነላቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን እንግዳ ቃላት ትርጉም መምህራንን ወይም ሌሎች ሰዎችን እየጠየቁ እንዲማሩ የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ብልሃቶች የቃላት ችሎታን ከማዳበር በተጨማሪ ማህበራዊ ተቀባይነትንም ያሳድጋሉ፡፡ በተማሪዎች የሚተገበሩ ማኅበራዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

በቋንቋው የመጠቀም ብቃት ካላቸው ሰዎች ጋር መተባበር፡- ተተኳሪውን ቋንቋ በብቃት ከሚናገሩ ሰዎች ጋር ህብረት(ጓደኝነት) በመመስረት የቃላት ዕውቀትን የማሻሻል ብልሃት ነው፡፡

ባህላዊ ግንዛቤን ማዳበር፡- ስለተተኳሪው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ዘይቤ ያለን ግንዛቤ በማዳበር የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት ፍቺና አጠቃቀም ችሎታን የማዳበር ብልሃት ነው፡፡

ከብጤ ጋር መተጋገዝ፡- ለጋራ አላማ ከክፍል ጓደኛ ጋር በቡድን ወይም በጥንድ በመስራት (ማጥናት) የቃላቱን ፍቺ በመለማመድ የቃላት ዕውቀትን የማሻሻል ብልሃትነው፡፡

መጠየቅ፡- የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም መምህራንን፣ የክፍል ጓደኛን ወይም ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ፣ ወይም ስህተትን ማስተካከያ የእርምት ትብብር በመጠየቅ የቃላት እውቀትን የማዳበር ብልሃት ነው፡፡

2.5. በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አቀራረብ ላይ የሚነሱ ጭብጦች

2.5.1. የቃላት መማር ብልሃቶችን በተናጠል ወይስ በቅንጅት ማሰልጠን?

በቃላት ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች መማር ያለባቸው የቃላት መማር ብልሃቶችን ጭምር ከሆነ ትምህርቱ እንዴት መቅረብ አለበት? ብልሃቶቹን እንዴት ማሰልጠን ይቻላል? የሚለው ጥያቄ ይነሳል፡፡ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ብልሃቶቹን በተናጠል በማሰልጠን ላይ ማተኮር አለበት ወይስ ብልሃቶቹን ከትምህርቱ ይዘቶች ጋር በቅንጅት በማሰልጠን ላይ ማተኮር አለበት የሚሉት ጭብጦች የቃላት መማር ብልሃቶችን ከማስተማር ጋር ተያይዘው የሚነሱ ክርክሮችና መቋጫ ያላገኙ ናቸው (O'malley & Chamot, 1990; Oxford, 1990, Wenden, 1991)፡፡ በሌላ አገላለጽ በስልጠናው ሂደት ብልሃቶቹ ብቻቸውን ተነጥለው ይቅረቡ ወይስ ከትምህርቱ ይዘቶች ጋር ተቀናጅተው ይቅረቡ የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

ብልሃቶችን ብቻ በተናጠል ማቅረብ (separete instruction) አንዱ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አቀራረብ ሞዴል ነው፡፡ በዚህ የስልጠና ሂደት የትምህርቱ ይዘት ሙሉ በሙሉ የሚያተኩረው ብልሃቶችን በማስተማር ላይ ብቻ ነው (O'malley & Chamot, 1990)፡፡ ይህን አቀራረብ የሚደግፉ ወገኖች የሚያቀርቡት ማሳመኛ ሀሳብ ብልሃቶችን ብቻ ነጥሎ ማቅረቡ ተማሪዎቹ ሙሉ ትኩረታቸውን ብልሃቶችን በማብላላት / በብልሃቶች ስልጠናው ላይ ብቻ በማድረግ

ስለብልሃቶቹ ግልጽና ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ እንዲጨብጡ/ በፍጥነት እንዲገነዘቧቸው ያስችላል የሚል ነው (Wenden (1991)። በዚህም በተመሳሳይ ሰዓት ብልሃቶችን ከቋንቋ ትምህርቱ ይዘቶች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ ተገቢ አይደለም የሚል እንደሆነ Jones እና ሌሎች (1987)፣ O'malley & Chamot (1990) እና Wenden (1991) አስረድተዋል።

ይሁን እንጂ በብልሃቶች በተናጠል በማተኮር በሚቀርበው ትምህርት የሚገኘው የብልሃቶች እውቀት የትምህርቱን ይዘቶች በመማር ሂደት ላይ በተግባር የመዋሉ ጉዳይ አጠያያቂ ነው። ምክንያቱም ብልሃቶችን ብቻ በተናጠል ማቅረቡ ተማሪዎቹ እውነተኛ የቋንቋ ተግባራትን እየሰሩ በአውድ እንዲለማመዱ እድል ስለማይሰጥ ተማሪዎቹ የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ አዳዲስ ተመሳሳይ ተግባራት እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙ ስለማያስችላቸው የተማሪዎችን በራስ መር የመማር ችሎታ በማሳደግ የቃላት ችሎታቸውን ለማሻሻል ጠቀሜታው ዝቅ ያለ ነው (Oxford, 1990; Gu & Johnson, 1996; Nation, 2001):: Oxford (1990) እንደሚያስረዱትም በመሰረቱ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና አላማም ተማሪዎች ብልሃቶችን ተጠቅመው ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ በመሆኑ ይህ አቀራረብ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው።

ሁለተኛው ቅንጅታዊ የብልሃት ትምህርት አቀራረብ (integrated instruction) ሞዴል ሲሆን በዚህ አቀራረብ ትምህርቱ ሙሉ በሙሉ ከተግባራቱ ጋር በቅንጅት ነው የሚቀርበው (O'malley & Chamot, 1990; Oxford, 1990)። ይህን አቀራረብ የሚደግፉ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያው ማሳመኛ ሀሳብ ብልሃቶችን ከቋንቋ ትምህርት ይዘቶ ጋር አቀናጅቶ ማቅረቡ ብልሃቶችን ከአውድ ውጪ ከማስተማር የበለጠ ውጤታማ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች የብልሃቶቹን ተግባራዊነት የሚረዱበትንና የሚገመግሙበትን እድል ያገኛሉ፣ እንዲሁም ብልሃቶቹን ወዲያውኑ ከክፍል ውስጥ የቋንቋ ተግባራት ጋር አቀናጅቶ እንዲለማመዱ ማድረጉ በአንዱ ይዘት አማካኝነት በተግባር የተማሩትን ብልሃት ወደ ሌሎች ተመሳሳይ አዳዲስ ይዘቶችና ተግባራት በማሸጋገር መጠቀም እንዲችሉ ይጋብዛል (Oxford, 1990)::

ይህን አቀራረብ የሚደግፉ ወገኖች የሚያቀርቡት ሁለተኛው ማሳመኛ ሀሳብ ብልሃቶችን በመማር ሂደት ተማሪዎች የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ምንነት ማወቅን ብቻ ሳይሆን የሚፈልጉት የትኛውን ብልሃት፣ መቼ፣ ለየትኛው የቋንቋ ተግባር፣ እንዴት እንደሚጠቀሙም ጭምር ነው የሚል ነው (O'malley, 1987; wenden, 1987)።

ይሁን እንጂ በዚህ አቀራረብም ተማሪዎቹን ከብልሃቶቹ ምንነት፣ ጠቀሜታና አተገባበር ጋር እንዴት ማስተዋወቅ ይቻላል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል O'malley & Chamot, 1990; Oxford, 1990) ። እነዚህ ሁለት አቀራረቦች ያሏቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ሌላ የተለየ አማራጭ መጠቀም እንደሚቻል O'malley & Chamot (1990) ጠቁመዋል። ይህም በአንድ የቃላት ትምህርት ወቅት ለአጭር ጊዜ በብልሃቶቹ ላይ ስልጠና ከተሰጣቸው/ ብልሃቶቹን ብቻ ነጥለው እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ወዲያውኑ በማስከተል የብልሃቶቹን አጠቃቀም በአውድ እንዲለማመዱ ከትምህርቱ ይዘት ጋር በቅንጅት መማር አለባቸው። በሌላ አገላለጽ ስለብልሃቶች ምንነትና ጠቀሜታ ከተማሩ በኋላ ወዲያውኑ አተገባበሩን እንዲለማመዱ የቃላት ተግባራት በማቅረብ አውዳዊ ድጋፍ በመስጠት የብልሃቶቹን አጠቃቀምና ውጤታማነት ማረጋገጥ ይቻላል። ስለዚህ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ብልሃቶቹን በተናጠልና ብልሃቶቹን ከቃላት ትምህርቱ ተግባራት ጋር በቅንጅት በማቅረብ ላይ ማተኮር አለበት (Omalley & Chamot, 1990; Oxford,1990)።

2.5.2. ብልሃቶቹን በግልጽ ወይስ በኢቀጥተኛ አቀራረብ ማሰልጠን ይገባል?

ሌላው ብልሃቶችን በተናጠልና በቅንጅት ከማሰልጠን ጋር ተያያዞ የሚነሳው ጭብጥ ብልሃቶችን በግልጽ ወይስ በኢቀጥተኛ ማቅረብ ይገባል የሚለው ተመሳሳይ ክርክር ነው (Omalley & Chamot, 1990; Oxford, 1990):: Oxford (1990) የዚህ ጥያቄ ምላሽ እንደ ብልሃቱ አይነትና እንደ ተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች የሚወሰን መሆኑን አስረድተው ግልጽና ኢቀጥተኛ የሚለውን አቀራራብ

እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡ በግልጽ አቀራረብ ትምህርቱ ለተማሪዎች ሲቀርብ ተማሪዎቹ ስለብልሃቶች ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ስለብልሃቶቹ አተገባበርና ብልሃቶቹን ስለሚጠቀሙበት አላማ በግልጽ ይማራሉ፡፡ በኢቀጥተኛ የብልሃቶች ትምህርት አቀራረብ ሞዴል ግን ተማሪዎቹ ስለሚማሩት ብልሃት ምንነት፣ ጠቀሜታና አተገባበር በግልጽ ሳይማሩ የብልሃቶቹን አጠቃቀም በተዘዋዋሪ ለማሳየት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተግባራት እየሰሩ በተዘዋዋሪ ብልሃቶቹን እንዲያውቁ የሚደረግበት ነው፡፡

Brown, Armbruster & Baker (1986) ቀደም ሲል በቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና ላይ የተሰሩ ጥናቶች የሚከተሉት ኢቀጥተኛ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና አቀራረብንና ልዕለአእምራዊ ብልሃቶችን ያላካተቱ በመሆኑ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በማዳበር የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ ተመሳሳይ አዳዲስ ተግባራት በማሻጋገር እንዲጠቀሙ ለማድረግ ያለው ጠቀሜታ ዝቅተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ የቅርብ ጊዜ የጥናት ውጤቶች በቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና ውስጥ ለተማሪዎች ስለብልሃቶቹ ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ለምን፣ መቼና እንዴት እንደሚጠቀሙበት በግልጽ ማሳውቅንና ልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች መካተት እንዳለባቸው ጠቁመዋል (Omalley & Chamot, 1990; Oxford, 1990)፡፡ ምክንያቱም የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች የመማር አቅጣጫቸውን ያልለዩ፣ የመማር አቅድ የሌላቸው፣ እድገታቸውን የማይቆጣጠሩ፣ ስኬታቸውን የማይገመግሙና ቀጣይ የመማር አቅጣጫቸውን የማያውቁ ናቸው (Omalley & Chamot, 1990; Oxford, 1990; Schmitt, 2000):: ስለዚህ በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውሰጥ የልዕለ አእምሯዊ ብልሃት መካተት በትምህርቱ ሂደት ተገቢ የሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶችን መርጠው በተገቢው መንገድ መጠቀም እንዲችሉ፣ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ውጤታማነት በመገምገም የወደፊት የመማር አቅጣጫቸውን እንዲወስኑና የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ ተመሰሳይ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ እንዲማሩ ያግዛቸዋል (O'Malley & Chamot, 1990)፡፡

ብልሃቶችን በኢቀጥተኛ ማቅረብ ይገባል የሚለው ሀሳብ አብዛኛዎቹ የትምህርቱ ተግባራት ተማሪዎች ለመማር የሚያስፈልጓቸውን ብልሃቶች ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ለማስተዋወቅ ያስችላሉ ከሚል ሀሳብ የመነጨ ነው (Omalley & Chamot, 1990; Oxford, 1990):: መምህራን እነዚህን ተግባራት ለተማሪዎች ሲያለማምዱ ምንም እንኳን ብልሃቶቹን ነጥለው ባያስተዋውቁም ብልሃቶቹን እያለማመዱ ጭምር እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ነገርግን ለማስተማሪያ በሚቀርቡት በብዙዎቹ ተግባራት ወስጥም ሆነ በማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ውስጥ በተዘዋዋሪ ተካተው የሚገኙት የቃላት መማር ብልሃቶች ካላቸው ጥልቀትና ውስብስብነት የተነሳ ላዘጋጇቸው ባለሙያ ሳይቀር በቀላሉ የሚታወቁ አይደሉም (Schmitt, 1997; Omalley & Chamot, 1990; Oxford, 1990):: በዚህም የተነሳ በዚህ አቀራረብ ላይ የሚነሳው ትችት ተማሪዎች ስለብሃቶቹ አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ ስለማያገኙ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በማዳበር በራስ መር መማርን ለማሳደግ ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው (Oxford, 1990; Gu & Johnson, 1996)::

ከላይ የቀረበውን ትችት በማጠናከር Chamot (2005)ም እንዳስረዱት በኢቀጥተኛ ሞዴል ተማሪዎች ብልሃቶችን ለምን፣ መቼ፣ እንዴትና የት እንደሚጠቀሙበት በግልጽ ስለማይማሩ ብልሃቶቹን አዳብረው ወደ ተለያዩ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ እንዲጠቀሙበት አያግዛቸውም፡፡ በዚህም የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽ ዝቅተኛ ነው፡፡ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ዋነኛ አላማ ደግሞ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ማዳበር በመሆኑ ተማሪዎች ብልሃቶቹን ተገንዝበው ይተገብሯቸው ዘንድ በግልጽ መማር አለባቸው (O'malley & Chamot, 1990; Wenden, 1991)፡፡

በዚህም የተነሳ በርካታ ምሁራን የብልሃት ትምህርት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየገጠሙት ያሉትን ትችት ለማስወገድ ዋናው ጉዳይ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና ኢቀጥተኛ ከሚሆን ይልቅ የቃላት መማር ብልሃቶቹን አጠቃቀም ግንዛቤ ለመፍጠር ተማሪዎቹ የብልሃቶችን ምንነት፣ ጠቀሜታና አተገባበር የሚለዩበት ገላጭ ደረጃ (declarative)፣ የብልሃቶቹን አጠቃቀም የሚያሳዩበት ደረጃ (procedural) እና ብልሃቶቹን ለምን፣ እንዴትና መቼ እንደሚጠቀሙ የሚያስረዱበት ጽብረቃዊ

ደረጃ (conditional) ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግ ግልጽ ማብራሪያና ምሳሌ እየቀረበላቸው በግልጽ ቢማሩ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዳለውና በቋንቋ ስርዓተ ትምህርትና በማስተማሪያ መሳሪያ ውስጥም መካተት እንዳለበት ይጠቁማሉ (Nation, 2001; Oxford, 1990)።

2.6 የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት

እንደ አእምሯዊ የቋንቋ መማር ንድፈ ሃሳብ አራማጆች እይታ የቋንቋ መማር ብልሃቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ውስብስብ አእምሯዊ ክሂል ነው። አያይዘውም በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ብልሃቶችን በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ ከሆነ በትምህርቱ ሂደት የሚገጥማቸውን ችግር በራሳቸው በማቅለል ቋንቋውን አቀላጥፈው መጠቀም ይችላሉ (Mitchell, Myles, & Marsden, 2013)።

ስለሆነም በአእምሯዊ የቋንቋ መማር ንደፈ ሀሳብ ውስጥ የቋንቋ መማር ብልሃቶች በጣም መሰረታዊ ናቸው። በማህበራዊ ግንባታ የቋንቋ መማር ንደፈ ሀሳብ እይታም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም እንደ ከፍተኛ የአእምሮ ስራ ይቆጠራል፣ ለምሳሌ መረጃን መተንተን (analysis)፣ ያገኙትን መረጃ ከቀደመ እውቀት ጋር ማያያዝ (synthesis)፣ ማቀድና መገምገም ወዘተ. ብልሃቶችን የመጠቀም ሁኔታ ከፍተኛ የአእምሮ ስራ የሚጠይቅ በመሆኑ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በማህበረ ባህላዊ አውድ ውስጥ የተሻለ ችሎታ ባላቸው ሰዎች ድጋፍ የሚያዳብሩት ነው (Oxford & Schraman, 2007)::

በዚህም የቃላት መማር ብልሃቶችን በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞዴል በግልጽ ማሰልጠን ለግንዛቤ ማደግ ማህበራዊ መስተጋብር መሰረታዊ ሚና አለው በሚለው በVygotsky (1978) የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ (Social Constructivist Theory) ላይ የተመሰረተ ነው። በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች እይታ መሰረትም አንድ ሰው በግሉ ከሚማር ይልቅ የተሻለ እውቀት፣ ግንዛቤና ክህሎት ባላቸው ሰዎች እየታገዘ ቢማር የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል። ለምሳሌ የሚያስቡትን ማጋራትና በሃሳብ ላይ መወያየት አስተሳሰብንና መማርን

ለማነቃቃትና ለማጎልበት ያግዛሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ ግንዛቤ ያድጋል (Lantolf, 2006)::

ይህን ሀሳብ በመጋራት Oxford & Schraman (2007) እንዳስረዱት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የማህበረ ባህላዊ (socio cultural) ጽንሰ ሀሳብ የእድገት መጠን ክፍተትን (Zone of Proximal Development (ZPD)) በመሙላት ሂደት ስኬታማ ተማሪዎች ጥያቄ መጠየቅ፣ የተሻለ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር (ለምሳሌ የቋንቋ መምህራንን፣ አፍፊት ተናጋሪዎችን መጠየቅ፣ የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህል ግንዛቤ ማዳበርና በቡድን መስራት) ወዘተ ማህበራዊ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ፤ በመጨረሻም የተሻለ ችሎታ ባላቸው ሰዎች የተደረገላቸው ሙያዊ እገዛ የእድገት መጠን ክፍተት (ZPD)ን መሙላት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

Lantolf (2006) እንደሚያስረዱትም፣ የአንድን ሰው የችሎታ የእድገት መጠን ክፍተት ((ZPD) ማጥበብ አጠቃላይ እእምሯዊ እድገትን (general cognitive development) ወይም ግንዛቤን ለማሳደግ ይረዳል የሚለው የVygotsky (1978) እይታ የተማሪዎችን ስኬታማነት እውን ለማድረግና የሚታዩባቸውን ችግሮች ለመፍታት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በርግጥ የግንዛቤያዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብም (Cognitive Constructivist Theory) ለቋንቋ መማር ብልሃቶች አስፈላጊነት መነሻነት የራሱ የሆነ ድርሻ አለው፡፡ ምክንያቱም እውቀት ከማህበረሰብ ወደ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ከግለሰብ ወደ ማህበረሰብም ሊሸጋገር ስለሚችል ነው፡፡

የችሎታ የእድገት መጠን ክፍተት በማህበረ-ባህላዊ ስነልቦና (Psycho-socio cultural) ጥናት ታዋቂ ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን አንድ ልጅ አሁን ያለበትን የችሎታ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚኖረውን የችሎታ ደረጃም ያመለክታል (Vygotsky, 1978)፡፡ አንድ ሰው በተናጠል ከሚሰራው ተግባር ባሻገር በሌሎች ሲደገፍ በሚያከናውነው ተግባር (በሚያሻሽለው) መካከል የችሎታ ክፍተት ይኖራል፡፡ ይህ ልዩነት ነው የእድገት መጠን ክፍተት የሚባለው፡፡ ይህን የችሎታ የእድገት መጠን ክፍተት ለመሙላትም የሙያዊ እገዛ (Scaffolding) መርህ በመከተል ሙያዊ እገዛን በተግባር ማዋል ያስፈልጋል፡፡ ይህ ችሎታም ከነበረበት ዝቅተኛ ደረጃ ቀስ

በቀስ ወደ ተሻለ ደረጃ እንደሚያመራ ያመለክታል። ይህ የችሎታ መሻሻል ደግሞ ማህበራዊ መስተጋብር ይወስነዋል፤ ለማህበራዊ መስተጋብር ተገዢ ይሆናል። ይህን የችሎታ የእድገት መጠን ክፍተት ለመሙላት ብዙ ደረጃዎችንና ሂደቶችን ማለፍ ያስፈልጋል። ከሁለት ጉዳዮች አንጻርም ሊታይ ይችላል። አካላዊ /አዕምሯዊ ብስለትና ከማህበረሰብ ፋይዳ አንጻር ማየት ይቻላል። በልጆች ዘንድ አካላዊ ብስለት እየጨመረ ሲሄድና ባህሉ እንድ ሰው ለሚያከናውነው ተግባር እውቅና ሲሰጠው የችሎታው መጠን እየጨመረ ይሄዳል።

Vygotsky (1978) እንደሚያስረዱትም፣ ግንዛቤ ከገሃዱ አለም ጋር በሚደረግ መስተጋብር ይመሰረታል። በመሆኑም እድገት ከማህበራዊና ባህላዊ አውድ ተለይቶ ሊታይ አይችልም። አእምሯዊ ሂደትን መረዳት የሚቻለውም ማህበራዊ መስተጋብርን መረዳት ሲቻል ነው። የአንድ ህጻን ስነልቦናዊ እድገት የሚለካውም የሚኖርበትን ባህል መልመድ ሲችል ነው። የመገንዘብ ሂደቱም በባህሉ ውስጥ ከሚገኙ ከቀላልና ተጨባጭ ነገሮች ወደ ውስብስብና ረቂቅ ነገሮች የሚሄድ ነው።

በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አተገባበር ጊዜም ለተማሪዎች ሙያዊ እገዛ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ሙያዊ እገዛ ልጆች እድገት እንዲያሳዩና በራሳቸው መንገድ እንዲማሩ የሚደረግ ድጋፍ ወይም እገዛ ነው። ይህም ተማሪዎች/ልጆች በሚያከናውኑት የመማር ሂደት የሚደረግ ማንኛውንም የመደገፍ ተግባር የሚመለከት ነው። በሌላ መልኩም ሙያዊ እገዛ በተናጠል በሚደረግ ተግባርና በሌሎች እገዛ በሚከናወን ተግባር መካከል ያለውን የእድገት መጠን ክፍተት ለመሙላት የሚከናወን ድጋፍ ነው። በመሆኑም የእድገት መጠን ክፍተትን ለመሙላት የሚከናወነው ይህ ሙያዊ ድጋፍ የእደገት መጠን ክፍተት የመፈጸሚያ ዋነኛ ስልት ነው (Lantolf, 2006; Oxford & Schraman, 2007)።

ከተመራማሪዎቹ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ሙያዊ እገዛ የተሻለ ችሎታ፣ ብስለት ወይም እውቀት ያላቸው ሰዎች ከእነሱ ያነሰ ችሎታ፣ ብስለት ወይም እውቀት ያላቸውን ሰዎች በማገዝ የችሎታ የእድገት መጠን ክፍተቱን ለመሙላት የሚደረግ ተግባር ነው ማለት ይቻላል። ለምሳሌ መምህራን ለተማሪዎቻቸው

የሚያደርጉትንና ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን ሙያዊ እገዛ መጥቀስ ይቻላል።።

የሙያዊ እገዛ ቴክኒኮችም፤ ማሳየት፣ መምራት፣ ተግባርን በቀላል ደረጃዎች መከፋፈል፣ መመሪያ ማቅረብ፣ ማብራራት፣ ትኩረት እንዲኖር ማድረግና ማበረታታት እንደሆኑ Mehadavi (2014) ይገልጻሉ።። Oxford & Schraman (2007)ም ምሳሌዎችንና ጥያቄዎችን ማቅረብ የሙያዊ እገዛ ቴክኒክ ነው።። እንዲሁም መስተጋብርን ማበረታታትና ምጋቤ ምላሽ መስጠት የመማር ሂደትን ያመቻቻል፤ ያፋጥናል (Oxford, 1990; Oxford & Schraman, 2007)::

የቃላት መማር ብልሃቶችን በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞዴል በግልጽ ማሰልጠንን ውጤታማ ለማድረግም ቀጥተኛ ገለጻ መስጠት (direct explanation)፣ ምሪት (modelling)፣ ሙያዊ እገዛ፣ ትብብራዊ መማር፣ የሚና ሽግግር (Role change)ንና ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በእያንዳንዱ ደረጃ እነዚህን የማስተማሪያ ስለቶች ከስልጠናው ጋር በማቀናጀት በተማሪዎች ዘንድ መነቃቃትን መፍጠር ያስፈልጋል (Omalley & Chamot, 1990)።።

በመሆኑም ከአንዱ የቃላት መማር ብልሃት ወደ ሌላው የቃላት መማር ብልሃት ከመሄዳቸው በፊት እያንዳንዱ ብልሃት ለተማሪዎች ግልጽ እስኪሆን ድረስ በመምህራን ይቀርባል።። ቅደም ተከተሉም በመጀመሪያ መምህራን ሞዴል ሆነው ስለ ብልሃቶቹ አጠቃቀም ያሳዩዋቸዋል።። ከዚያ ብልሃቶቹን በተግባር እየተጠቀሙ የሚያሳዩበትና የሚለማመዱበት ተግባራት ይቀርቡላቸዋል።። በዚህ ደረጃም ተማሪዎች በግል ከሚያደርጉት ልምምድ በተጨማሪ በጥንድና በቡድን በብልሃቱ አተገባበር ላይ በጋራ እየተጋገዙ እንዲለማመዱ ይደረጋል።። በሂደቱም መምህራን ተማሪዎቹ ቀደም ሲል የተዋወቁትን ብልሃት ምን ያህል በአግባቡ እየተገበሩት እንደሆነ ይከታተላሉ።። በክትትሉም ተማሪዎቹ ከብልሃቱ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚገጥሟቸውን ችግሮች እንዲፈቱ ድጋፍ ይሰጣሉ።። ከዚያም የማለማመዱ ድጋፍም በመጀመሪያ ሰፋ ያለ ሆኖ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ተማሪዎች ተለማምደው ሃላፊነቱን ይረከባሉ (ራሳቸውን ችለው ብልሃቶቹን ወደ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ ይጠቀማሉ)።። መምህራኑም እየተከታተሉ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ፤

ብልሃቶቹን እንዲጠቀሙ ያበረታታሉ (Philip, 2005; Tassana-Ngam, 2004; Mehadavi, 2014; Omalley & Chamot, 1990)።

2.7. የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ቅደምተከተላዊ ማሕቀፍ

የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የሚመራበት ቅደም ተከተላዊ ማዕቀፍ አለው። ብልሃቶችን በግልጽ ለማሰልጠን የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን የአቀራረብ ቅድም ተከተላዊ ማዕቀፍ ሲያቀርቡ ይስተዋላል። Jones እና ሌሎች (1987) እና Omalley & Chamot (1990) የተለያዩ ምሁራን በተግባር ላይ ያዋሏቸውን የብልሃት ስልጠና አቀራረብ ቅደም ተከተሎችን አስፍረዋል። ከነዚህም ውስጥ ቋንቋን ጨምሮ ለሌሎች ትምህርቶችም ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸው Williams & Burden (1997) እንዲሁም የቃላት መማር ብልሃቶችን ለማቅረብ ተግባራዊ የተደረገው የChamot (2005) ግልጽ የብልሃቶች ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተል ይገኝበታል። ምሁራኑ ያቀረቡት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ቅደምተከተላዊ ማዕቀፍ ተጠቃሎ ሲታይ ከታች የቀረቡትን አምስት ደረጃዎች ይከተላል።

1. **ታላሚውን ብልሃት በግልጽ ማስተዋወቅ፡-** በዚህ ደረጃ ተማሪዎች አዲስ ከሚቀርበው የቃላት መማር ብልሃት ምንነትና ጠቀሜታ ጋር በግልጽ የሚተዋወቁበት ስለሆነ እንዲማሩት ከተፈለገው የቃላት መማር ብልሃት አጠቃላይ ገጽታዎች ጋር የሚተዋወቁበትና ብልሃቱን ለመተግበር የሚዘጋጁበት በመሆኑ የቃላት መማር ብልሃቶቹን መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደ ሚጠቀሙባቸው ሰፊና ጥልቅ ማብራሪያ በመምህራን ይሰጣል።

2. **ሞዴል ሆኖ ማሳየት** (Modeling)፡- ይህ ደረጃ መምህሩ በደረጃ አንድ ለተማሪዎች ያስተዋወቀው ብልሃት እንዴት በተግባር ላይ እንደሚውል እየሰራ የሚያሳይበት፣ ብሎም ተማሪዎቹ ከመምህሩ የቀረበላቸውን ተግባራዊ ትውውቅ መሰረት አድርገው የብልሃቱን አተገባበር የሚለማመዱበት ነው። በመሆኑም በማስተማር ሂደቱ መምህሩ ሞዴል በመሆን ለልምምድ የቀረበውን ታላሚ ብልሃት አጠቃቀም በተግባር ተግባራቱን እየሰራ ለተማሪዎቹ ያሳያል።


3. **ብልሃቶቹን በትብብር መተግበር፡-** በዚህ ደረጃ መምህራንና ተማሪዎች በጋራ ብልሃቶቹን በመጠቀም የቃላት ተግባራትን ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የራሳቸውን የብልሃት አጠቃቀም የመገምገም ችሎታ እንዲያዳብሩ ብልሃቶቹን በመተግበር ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮችና የወሰዷቸውን መፍትሄዎች የተማሩትን ብልሃት ምን ያህል እንደተረዱት ለመገምገም በብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ከመምህራን ጋር በጋራ በመወያየት ብልሃቶቹን ወደፊት ለመተግበር ያላቸውን ተነሳሽነት የሚገልጹበት ሁኔታም ይመቻቻል፡፡

4. **በድጋፍ ማለማመድ/ የብልሃቶቹን አተገባበር መምራት፡-** የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ክህሎት ለማዳበር ተማሪዎቹ በደረጃ አንድ ስለ አንድ የቃላት መማር ብልሃት ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ከተገለጸላቸውና በደረጃ ሁለት በመምህሩ ሞዴልነት (ምሪት)ና በደረጃ ሦስት ከመምህሩ ጋር በጋራ የተለማመዷቸውን ብልሃቶች በስፋት በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው የተለያዩ ተግባራትን እየሰሩ በራሳቸው በብልሃቱ አተገባበር በጋራ እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ብልሃቶቹን በሚተገብሩበት ጊዜ እየተከታተለ መምራት (ሰፊ ድጋፍ መስጠት) ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም የማለማመዱ ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሃላፊነቱን ለተማሪዎች በመስጠት ራሳቸውን ችለው ከተማሯቸው ብልሃቶች እንደየ አግባብነታቸው እየመረጡ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይገባል፡፡

5. **ብልሃቶቹን ወደ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ ራሳቸውን ችለው ሲተገብሩ ማበረታታት፡-** ይህ ደረጃ በዋናነት ተማሪዎቹ ብልሃቶቹን ራሳቸውን ችለው መተግበራቸውን የማጠናከር አላማ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለው የተማሯቸውን ብልሃቶች በመጠቀም የቃላት ተግባራትን በግላቸው ሲያከናውኑ ብልሃቶቹን እንደ አስፈላጊነታቸው መርጠው እንዲጠቀሙና ሙሉ ሃላፊነት እንዲሰማቸው አቅጣጫ በማስያዝ አግባብ ያለው ግብረ መልስ በመስጠት ያበረታታል፡፡

ቅደም ተከተላዊ ማዕቀፉ ያለው ሂደት በስዕላዊ መግለጫ ሲቀርብ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ስዕል 1.1.ሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞዴል (Transactional Strategy Instruction Model)



(Mehadavi, 2014, p.393 ተሻሽሎ የተወሰደ)

በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞዴሉ ሦስት ማዕዘኑ የሚያሳየው የተማሪውንና የመምህሩን ድርሻ ሲሆን፤ መጀመሪያ አካባቢም የቃላት ትምህርት ተግባራት በመምህራን የሚከናወኑ መሆናቸውንና የመምህራን ድርሻ ሰፋ ያለ መሆኑን ነው፡፡ መምህራን የቃላት መማር ብልሃቶችን ለተማሪዎች በግልጽ ያስረዳሉ፤ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው ሞዴል በመሆን ያሳያሉ፡፡ ቀስ በቀስም ተማሪዎች ብልሃቶቹን በመጠቀም በቃላት ተግባር ላይ በመምህራን የሚመራ

ልምምድያደርጋለ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች በመምህራን ሙያዊ እገዛ እየተደረገላቸው በቀረቡላቸው ብልሃቶች የቃላት ተግባራትን ይማራሉ፡፡ መምህራንም የቃላት ተግባራትን በማመቻቸትና ብልሃቶቹን ራሳቸውንችለው እንዲጠቀሙ በማበረታታት ላይ ይወሰናሉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች የመምህራንን ሃፊነት በመረከብ ብልሃቶቹን በመጠቀም የቃላት ትምህርት ተግባራቸውን ራሳቸውን ችለው (በግላቸው) ይሰራሉ (Mehadavi, 2014)፡፡

2.8. የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አስፈላጊነት

Oxford (1990) እንዳስረዱት ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩና መምህራን የመማር ሂደቱን እንዴት መማቻቸት እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው፡፡ ምንም እንኳን መማር የሰዎች ባህሪ አካል ቢሆንም በራስ መር በንቁ ንቃተ ሂሊና ለመማር የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም በስልጠና መዳበር አለበት፡፡ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩት በቂ ግብኣት በሌለበት ነው፡፡ በመሆኑም በቋንቋ ትምህርቱ ተማሪዎች የሚፈለገውና ተቀባይነት ያለው ተግባቦታዊ ብቃት ደረጃ ላይ ለመድረስ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩት ብቻ የሚገኝ ሳይሆን በትምህርቱ ሂደት የተማሪዎችን በራስመር በንቃት መሳተፍን ይጠይቃል (Oxford,1990)፡፡ ስለሆነም የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደት ስለቃላት መማር ብልሃቶች አስፈላጊነት ያላቸው ግንዛቤ እንዲጨምር፣ የትኛው ብልሃት ለየትኛው የቃላት ተግባር የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነና የተማሯቸውን ብልሃቶች ወደ አዳዲስ ተግበራት በማሸጋገር በህይወት ዘመናቸው ሁሉ መጠቀም እንዲችሉ ስለሚረዳቸው የበለጠ በሙሉ ንቃተ ሂሊና ተገቢ ብልሃቶችን መርጠው በተገቢ ቦታ መጠቀም እንዲችሉ ይረዳቸዋል (Oxford, 1990)::

ተገቢ ብልሃቶችን መጠቀም የሚችሉ ተማሪዎች ደግሞ በቃላት ትምህርቱ ሂደት የሚገጥማቸውን ችግር በመፍታት በራስ መተማመንን በማጎልበት በትምህርቱ ሂደት በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራስመር ንቁ ተሳታፊ በመሆን

ከሌሎች በተሻለ በንቃት መማር ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን የቃላት ትምህርት ችግሮች በመፍታት የቃላት ችሎታቸውን ከማዳበሩም በላይ አጠቃላዩን የቋንቋ ትምህርት ቀላል፣ ፈጣን፣ አዝናኝና ውጤታማ እንዲሆን ጉልህ አስተዋጽኦ አለው (Schmitt, 2000; Oxford, 1990; Alseweed, 2000)። የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ስልጠና የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ የሚያሻሽለው በክፍል ውስጥ (በትምህርት ዓለም) ለሚደረገው የቃላት ትምህርት ተግባር ብቻ ሳይሆን ብልሃቶቹን በማንኛውም አውድ በዘላቂ ህይወታቸው እንዲጠቀሙባቸው ነው (Tassana-Ngam, 2004; Mehadavi, 2014)።

በዚህም የተነሳ አብዛኛዎቹ የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎች ቋንቋን እንዴት መማር እንደሚችሉ ግልጽ ስልጠና መስጠትን ይደግፋሉ (Oxford, 1990)፡፡ የዚህ ስልጠና አጠቃላይ አላማም የቋንቋ ትምህርቱ የበለጠ ትርጉም ያለው እንዲሆን ለመርዳት፣ በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የትብብር መንፈስን ለማጎልበት፣ ቋንቋን ለመማር ስለሚያስችሉ አማራጮች ማስተማርና በራስ መተማመንን ለማጎልበት የሚረዱ ብልሃቶችን ማስተማርና ማለማመድ ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህን አላማዎች ለማሳካት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ንድፈሃሳዊ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ሁኔታ በተግባራዊ ልምምድ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት (Oxford, 1990; Gu, 2003)። O'Malley& Chamot (1990)ም እንደሚያስረዱት ውጤታማ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና በስልጠናው ሂደት ንድፈ ሃሳባዊ ገለጻን፣ የብልሃቶቹን አተገባበር በተግባር ማሳየትን (ሞዴሊንግ)፣ ውዲያውኑ አውዳዊ ልምምድ ማድረግንና ምጋቤ ምላሽ መስጠትን ማካተት አለበት፡፡

ቋንቋን እንዴት መማር እንደሚቻል ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ሰው የለም፡፡ ስለሆነም በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ምን ማድረግ እንደሚገባ በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ስልጠና በመስጠት ጠንካራ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል (Oxford, 1990)፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙትም በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ግልጽ ስልጠና የተሰጣቸው ተማሪዎች ስልጠና ካልተሰጣቸው የበለጠ ለትምህርታቸው ሃላፊነትን በመቀበል በንቃት በመሳተፍ ይማራሉ (O'Malley& Chamot, 1990)፡፡

2.9. የብልሃት ስልጠና አይነቶች

Oxford (1990) እንደሚያስረዱት የቃላት መማር ብልሃቶችን በሶስት የተለያዩ መንገዶች ማሰልጠን ይቻላል፤ እነዚህም በግንዛቤ መፍጠሪያ (awareness training) ስልጠና፣ በአጭር ጊዜ / በአንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና (one-time strategy training) ስልጠናና በረጅም ጊዜ የብልሃት (Long-time strategy training) ስልጠና ናቸው።

2.9.1 የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና

የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና (awareness Training) ተነሳሽነት ማሳደጊያ ወይም የማስተዋወቂያ (familarization) ስልጠና በመባል ይታወቃል። ይህ የስልጠና አይነት ተማሪዎች አጠቃላይ ስለቃላት መማር ብልሃቶች ጽንሰ ሀሳብና እያንዳንዱ ብልሃት የተለያዩ የቃላት ተግባራትን ለማከናውን ሊረዳቸው ስለሚችልበት መንገድ ግንዛቤ የሚጨብጡበት ነው። የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና ከመደበኛው የቋንቋ ትምህርት አላማጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥ ባለመሆኑ ተማሪዎች ብልሃቶቹን እውነተኛ የቃላት ተግባራትን በመስራት በተግባር የሚማሩበትና የሚለማመዱበት አይደለም። በዚህም የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና ተማሪዎች ስለቃላት መማር ብልሃቶች ጽንሰ እንዲጨብጡ በማድረግ ወደፊት የቃላት መማር ብልሃቶች እውቀታቸውን ለማስፋት እንዲነሳሱ የሚያበራታታ ቢሆንም ከመደበኛው የቋንቋ ትምህርት አላማ ጋር ተቀናጅቶ የሚቀርብ ስላልሆነ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ለማሻሻል ያለው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ነው (Oxford, 1990)።

2.9.2. የአንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና

የአንድ ጊዜ የብልሃት (one-time *Strategy* training) ስልጠና አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ብልሃቶችን ከእውነተኛ (with actual language tasks) የቃላት ተግባራት ጋር በማያያዝ ማሰልጠንና ማለማመድ ሲሆን፤ ይህ አይነቱ ስልጠና ሁልጊዜ ከመደበኛው የቋንቋ ትምህርቱ አላማ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥ ነው። የአንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና ስለ ቃላት መማር ብልሃቶች ጠቀሜታ፣ ምንነት፣

መቼ፣ እንዴት እንደሚጠቀሙበትና የራሳቸውን የብልሃት አጠቃቀም ስኬታማነት እንዴት እንደሚገመግሙ መረጃ ይሰጣል፡፡ ይሁን እንጂ የአንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና ረዘም ላለጊዜ በቅደምተከተል ከሚሰጥ የብልሃት ስልጠና ጋር የተያያዘ ባለመሆኑ ጠቃሚ የሚሆነው ተማሪዎችን ለተለየ አላማ አንድ ወይም በጣም ታላሚ (very targeted strategies) ብልሃቶችን ለይቶ ለአንድ ጊዜ ወይም ለትንሽ ጊዜ ለማሰልጠን ሲያስፈልግ ነው፡፡ ለምሳሌ የተወሰኑ የትውስታ ብልሃቶችን ለአንድ ጊዜ ከሌሎች ብልሃቶች ጋር ሳያቀናጁ ማስተማር ነው፡፡ በአጠቃላይ የአንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና እንደ ረጅም ጊዜ የብልሃት ስልጠና ከተለያዩ ምድቦች የተውጣጡ ብልሃቶችን አቀናጅቶ ረዘም ላለጊዜ በማስተማር ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ለማሻሻል ጠቀሜታው ዝቅተኛ ነው (Oxford, 1990)፡፡

2.9.3. የረጅም ጊዜ የብልሃት ስልጠና

የረጅም ጊዜ የብልሃት ስልጠና ልክ እንደ አንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና ብልሃቶችን ከቃላት ተግባራት ጋር አቀናጅቶ በማሰልጠንና በማለማመድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ስለእያንዳንዱ የቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚጠቀሙበት፣ የራሳቸውን የብልሃት አጠቃቀም እንዴት እንደሚቆጣጠሩና እንደሚገመግሙ በግልጽ ይማራሉ፡፡ የረጅም ጊዜ የብልሃት ስልጠና ልክ እንደ አንድ ጊዜ የብልሃት ስልጠና ሁሉ ከተግባራቱ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የረጅም ጊዜ የብልሃት ስልጠና በጣም ረዘም ላለጊዜ የሚሰጥና ከተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶች ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን ስለሚያካትት የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ለማሻሻል ከአንድ ጊዜ የብልት ስልጠና የበለጠ ውጤታማና ጠቃሚ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ የስልጠና አይነት ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን ሰለሚያካትት ተማሪዎች ብልሃቶቹ እርስበርስ ያላቸውን ግንኙነት በመረዳት በቃላት ትምህርቱ ሂደት የተለያዩ ብልሃቶችን በቅንጅት መጠቀም እንዲችሉ ይጠቅማል (Oxford, 1990)፡፡

O'malley & Chamot (1990) እንደሚያስረዱትም ተማሪዎች ብልሃቶችን መጠቀም ያለባቸው አንድላይ በማጣመር ስልት ነው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ብልሃት ለቃላት ትምህርቱ ያለው አስተዋጽኦና የተማሪዎች የመማር ስልትም የተለያየ በመሆኑ አንድ ነጠላ ብልሃት የቃላት ችሎታን ለማዳበር ዋስትና የለዉም። አያይዘውም በዚህም የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን በቅንጅት መያዝ አለበት። ምክንያቱም የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ አመላካች ነው (Schmitt, 2000; Nation, 2001)።

ብልሃቶችን መጠቀም ውጤታማ የሚሆነውም ለሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ተግባራት ተገቢ ግንኙነት ሲኖረው፣ ከአያንዳንዱ ተማሪ የመማር ስልት ምርጫ ጋር የሚስማማ ሲሆን፣ ተማሪዎች ብልሃቱን በተገቢው ቦታ በአግባቡ ሲጠቀሙና ከሌሎች ብልሃቶች ጋር አቀናጅተው መጠቀም ሲችሉ ነው (Schmitt, 1997; Ehrman, Leaver & Oxford, 2003)።

ይህ ይህንን ጉዳይ በተለመከተ Gu (2003) ባካሄዱት ጥናት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ውጤታማ ለመሆን ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ ብልሃቶችን መጠቀም መቻል አለባቸው፤ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች በርካታ ብልሃቶችን በውህደት የመጠቀም ልምድ የሌላቸው እንደሆኑ ጠቁመዋል። Sokmen(1997)ም ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን ማሰልጠን ያለውን ጠቀሜታ ሲያጠናክሩ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች በርካታ ብልሃቶችን በውህደት መጠቀም የሚችሉ ናቸው። ስለሆነም የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን የያዘ ውህድ አቀራረብ (mixed approach) መከተል እንዳለበት አስረድተዋል (Sokmen, 1997; Oxford, 1990; Alseweed, 2000)::

2.10. በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጠዎች

ከተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና ምርጫ ጋር ተዛምዶ ያላቸውና በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ከተማሪዎች ባህርያት፣ ከስልጠናው አቀራረብና ከማሰልጠኛ መሳሪያው ጋር የተያያዙ በርካታ ተላውጦዎች እንዳሉ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Takeuchi, Griffth, & Coyle, 2007)።

Oxford & Nyikos (1989) በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ በካሄዱት ጥናት እንደጠቆሙት በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ከተማሪዎች ባህርያት ጋር የተያያዙ በርካታ ተላውጦዎች መካከል የሚከተሉት በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህም የክፍል ደረጃ፣ ስለብልሃቶች ያላቸው የግንዛቤ /እውቀት ደረጃ፣ የህይወት ልምድ፣ ለቋንቋው ያላቸው ተጋልጦ ዝቅተኛ መሆን፣ የተማሪዎች የታላሚው ቋንቋ ችሎታ፣ የታላሚው ቋንቋ ክብደት (የሁለተኛና የአፍ መፍቻ ቋንቋ) የመዋቅር ልዩነት፣ አጠቃላይ የመማር ስልት፣ ስብዕና ባህላዊ ዳራ የመሳሰሉት ከተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና ምርጫ ጋር በእጅጉ ስለሚዛመዱ የቃላት መማር ብልሃቶችን ስልጠና ውጤታማ ለማድረግም ሆነ ለማደናቀፍ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

O'malley & Chamot (1990) እና Oxford (1990) እንደሚያስረዱት ለምሳሌ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ያላቸው ችሎታ ዝቅተኛ ከሆነ የስልጠናውን ሂደት ለመረዳት ስለሚከብዳቸው ከስልጠናው ተጠቃሚ አይሆኑም፤ ማለትም የቋንቋ ችሎታ ደረጃቸውን በሚመለከት የብልሃት ስልጠናው በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ የሚቀርብ ከሆነ በጀማሪ የትምህርት ደረጃ እያሉ ቢቀርብላቸውም በአግባቡ ሊከታተሉ ይችላሉ። በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ ግን የቃላት መማር ብልሃቶችን ጨምሮ አብዛኛዎቹን ብልሃቶች ለማቅረብ የተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታ የተሻለ ደረጃ ላይ እስከሚደርስ መጠበቅ አስፈላጊ ነው (O'malley & Chamot, 1990)። በሌላ በኩል ስለብልሃቶች የተሻለ

ግንዛቤ ያላቸውና በከፍተኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙ (Advanced learners) ተማሪዎች ከሌሎች በበለጠ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ፡፡

Okada, Oxford & Abo (1996) እና Wharton (2001) በጥናታቸው እንደጠቆሙት ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ ከሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩበት አላማ ብልሃቶችን ለመጠቀም ሌላው ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ አስረድተዋል፤ ለምሳሌ ቋንቋውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ለመጠቀም የሚማር ሰው ፈተና ለማለፍ ብቻ ከሚማረው ሰው በበለጠ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የተለያዩ ብልሃቶችን ይጠቀማል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ተነሳሽነት ከሌላቸው የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ቢሰጣቸውም ብልሃቶቹን ለመጠቀም አያግዛቸውም፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎች ብልሃት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል (Takeuchi, Griffth,& Coyle, 2007)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የታላሚው ቋንቋ ክብደት (የሁለተኛና የአፍ መፍቻ ቋንቋ የመዋቅር ልዩነት (linguistic distance) በተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል (Oxford, 1990)፡፡ Chamot (1987) ባካሄዱት ጥናት የሩሲያ (Russian) ተማሪዎች ከስፓንሽ ተማሪዎች በበለጠ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃላትን ለመማር ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል:: Politzer (1983)ም የፈረንሳይኛ፣ ስፓንሽና የጀርመን ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ለመፈተሽ ባደረጉት ጥናት የስፓንሽ ተማሪዎች ከሌሎች በበለጠ ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል፡፡ በሌላ በኩል Takač's (2008) የጀርመንኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በማነጻጸር ባደረጉት ጥናት የጀርመንኛ ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የትውስታና ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃቶችን ከእንግሊዝኛ ተማሪዎች ይበልጥ እንደሚጠቀሙ ጠቁመዋል፡፡ በአጠቃላይ በታላሚው ቋንቋ ክብደት (አንድ ቋንቋ ከሌላው ቋንቋ ያለው የመዋቅር ልዩነት)ና በተማሪዎች ብልሃት አጠቃቀም መካከል አወንታዊ ተዛምዶ አለ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ችግሮችን ለመቋቋም የበለጠ በርካታ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል (Takač's, 2008)፡፡

Oxford (1990) ቋንቋዎች እርስበርስ ያላቸው የመዋቅር ግንኙነት ሁለተኛና የውጪ ቋንቋ ለመማር ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ የሁለተኛ ቋንቋው መዋቅር ከአፍመፍቻ ቋንቋ መዋቅር ጋር ተመመሳሳይ የሆነ ቋንቋ መማር የሁለተኛ ቋንቋው መዋቅር የተለየ ከሆነው የበለጠ ለመማር ቀላል ስለሚሆን ለቋንቋ/ቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ Koda (1996) እንደሚያስረዱት ሁለቱ ቋንቋዎች ተመሳሳይ የመዋቅር ስርዓት ካላቸው የሁለተኛ ቋንቋ የቃላት እውቀትን ለማዳበር ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር ተማሪዎች ብልሃቶችን ለመጠቀም ፍላጎት የላቸውም፤ በአንጻሩ ደግሞ በሁለተኛና አፍመፍቻ ቋንቋ መካከል የመዋቅር ልዩነት ካለ በቋንቋው የተለያዩ ክሂሎችን ለማዳበር የተማሪዎች ብልሃቶችን የመጠቀም ፍላጎት ይጨምራል፡፡ ይህ ደግሞ ለቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት አወንታዊ አስተዋጽኦ አለው፡፡

በሌላ በኩል O'malley & Chamot (1990) እና Oxford (1990) የመምህራን የክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ፣ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አቀራረብ (የስልጠና መስጫ መንገድ)ና የማሰልጠኛ መሳሪያው ተገቢነት፣ የተግባራት አመራረጥና ስልጠናውን ለማቅረብ የተመረጠው ሞዴል በስልጠና ውጤታማነት ላይ ያለውን ተጽዕኖ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡ የመምህራን የክፍል ወስጥ የትምህርት አቀራረብና የግምገማ ዘዴ የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ይወስናል፤ ለምሳሌ በክፍል ወስጥ የሚቀርቡት ተግባራት ሁልጊዜ በስዋስው ትምህርት ወይም ተመሳሳይ ይዘት ላይ የሚያተኩር ከሆነ ተማሪዎች አጠቃላይ ተግባቦታዊ ብቃትን ለማዳበር የሚጠቅሙ ብልሃቶችን ከመጠቀም ይልቅ የቋንቋውን መዋቅር ለማዳበር የሚረዱ ለምሳሌ መተንተን (analysis) የመሳሰሉ ብልሃቶችን ብቻ በመጠቀም ላይ እንዲወሰኑ ያደርጋቸዋል፤ ይህ ደግሞ የተለያዩ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ ስለማያግዛቸው ተማሪዎች ስልጠና ቢሰጣቸውም የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀም ስለማይችሉ የቃላት ችሎታቸውም ሆነ የብልሃት አጠቃቀማቸው አይሻሻልም፡፡ ስለሆነም የሚቀርቡት ተግባራት የተለያዩ ብልሃቶችን ሊያለማምዱ የሚችሉ መሆን አለባቸው (Oxford, 1990)፡፡

እንዲሁም የቃላት መማር ብልሃቶች ማሰልጠኛ መሳሪያው ለተማሪዎች ተገቢ ካልሆነ ስልጠናው ውጤታማ አይሆንም ወይም በተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። Gu (2003b) እንደሚያስረዱት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ውጤታማነት በሚቀርቡት ተግባራትና በመማሪያ አውዱ ምቹነት ላይ የተመሰረተ ነው። ማለትም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ውጤታማ የሚሆነው በማስተማሪያ መሳሪያው ውስጥ ብልሃቶቹን በአውድ ሊያለማምዱ የሚችሉ ተገቢ የቃላት ተግባራት ሲቀርቡ ነው። ስለሆነም ስልጠናው ፍሬ አልባ ከሆነ የተመረጡት ተግባራት ብልሃቶቹን ለማለማመድ ተገቢ አይደሉም። ለዚህም ምክንያቱ ተማሪዎች በርካታ ተግባራትን ለመስራት በርካታ ብልሃቶችን መጠቀም ስለሚያስፈልግና የተወሰኑ ብልሃቶች ተገቢ የሚሆኑት ለአንድ/ ለተወሰነ የቃላት ተግባራት መሆኑ ነው (Gu, 2003b)።

ከዚህ በተጨማሪም O'malley & Chamot (1990) እና Oxford (1990) እንደሚያስረዱት የብልሃቶች ስልጠናው ጤታማነት በስልጠናው አቀራረብና ለስልጠናው በተመረጠው ሞዴል ተገቢነት ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ ስልጠና የሚሰጥበት መንገድ ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ ብልሃቶችን በማቅረብ ተማሪዎች እያንዳንዱን ብልሃት ለምንና መቼ አስፈላጊ እንደሆነ፣ ረዘም ላለ ጊዜ በግልጽ በማስተማርና በማለማድ ላይ የሚያተኩር ከሆነ ተማሪዎች በሙሉ ንቃተ ሂሊና የበለጠ ተገቢ ብልሃቶችን በተገቢ ቦታ መጠቀም እንዲችሉ ይመራቸዋል (Oxford, 1990)። ስለዚህ እነዚህ ተላውጦዎች ከተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ጋር በእጅጉ ስለሚዛመዱ በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በዚህም ብልሃቶችን በግልጽ የመማር ውጤታማነትም በነዚህ ተላውጦዎች ምክንያት ስለሚለያይ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ሲሰጥ እነዚህን ጉዳዮች ከግንዛቤ በማስገባት በተማሪዎች ግላዊና ቡድናዊ ፍላጎት ላይ ማነጣጠር አለበት (Oxford, 1990; O'malley & Chamot, 1990)። ,

2.11. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ የተለያዩ

አለም አቀፋዊ ጥናቶች ተካሂደዋል። Banisaeid (2013)፣ Alseweed (2000)፣ Nation (2001)፣ Rodriguez & Sadoski (2000)፣ Mahdavi (2014)፣ Yang (2014)፣ Ronald (2001)፣ Rajee (2013)፣ Mizumoto & Takeuchi (2009) የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ፣ የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀማቸውን ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ምን እንደሆነ ለመፈተሽ ጥናታቸውን አከናውነዋል። በጥናታቸው ግኝትም አማካይ ውጤትን መሰረት በማድረግ በሁለት ቡድን ነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት በመለካት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳለው አረጋግጠዋል። የብልሃት ግዛቤና አጠቃቀማቸውን በማዳበርም ብልሃቶችን መርጦ በተገቢ ቦታቸው መጠቀም እንዲችሉና የቃላት መማር ሂደታቸውን በራሳቸው እንዲቆጣጠሩም አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው አረጋግጠዋል።

Mizumoto & Takeuchi (2009)ም ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ፣ የብልሃት አጠቃቀምና ተነሳሽነት ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ በጃፓን ዩኒቨርሲቲ እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን ለ10 ሳምንት በማስተማር ጥናት አከናውነዋል። በሙከራውና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለውን ልዩነት ለማነጻጸርም ከትምህርቱ በፊትና በኋላ ተመሳሳይ የቃላት ፈተና በመስጠት፣ ተመሳሳይ የብልሃት አጠቃቀምና የተነሳሽነት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ለሙከራው ቡድን ተማሪዎች ብቻ በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት በመስጠት መረጃ ሰብስበዋል። በጥናቱ ውጤትም ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ፣ የብልሃት አጠቃቀምና ውስጣዊ ተነሳሽነት ለማሳደግ አስተዋጽኦ እንዳለው ጠቁመዋል።

Mahdavi (2014) ለቋንቋው ዝቅተኛ ተጋልጦ (ግብአት) ባለው አካባቢ ሁለተኛ ቋንቋቸውን ለሚማሩ ተማሪዎች ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት አውቀትና የብልሃት አጠቃቀምና ግንዛቤ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ በኢራን አንደኛ አመት 60 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ

ጥናት አከናውነዋል፡፡ የምርምሩ ንድፍ በሁለት ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ ተመራማሪው መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀሙበት ዘዴ በቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ተመሳሳይ የቃላት ፈተና በመስጠት ነው፡፡ እንዲሁም ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ተመሳሳይ የቃላት መማር ብልሃቶችን አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብቻ በመስጠት ነው፡፡ በመጀመሪያ ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ሰጥተው መረጃ ሰብስበው ከተነተኑ በኋላ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የውጤት ልዩነት አለመኖሩን አረጋገጡ፡፡ ከዚያም ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሙከራው ቡድን ተማሪዎች ተግባራዊ ሆነ፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎችም በተለመደው ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴ ተማሩ፡፡ በመጨረሻም በቅድመትምህርት የተሠጠው የቃላት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች ተማሪዎች በድህረትምህርት ተሰጠ፡፡

ተመራማሪው የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የተጠቀሙበት ዘዴ የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ነው፡፡ አማካይ ውጤትን መሰረት አድርገው የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም ስልጠናው በተማሪዎች የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም ላይ ያመጣውን ለውጥ ለመፈተሽም ያቀረቡትን የጽሐፍ መጠይቅ በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት አማካይ ውጤትን መሰረት በማድረግ ተንትነዋል፡፡ በውጤቱም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ከቅድመትምህርቱ አማካይ ውጤት ልዩነት እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽ ያለው መሆኑን በመግለጽ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡

Banisaeid (2013) በበኩላቸው ከአእምሯዊና ከትውስታ ብልሃቶች የትኛው ለቃላት እውቀት መሻሻል የበለጠ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመፈተሽ 60 የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በሁለት ሙከራዊ ቡድን በመክፈል ለአንዱ ቡድን የትውስታ

ብልሃቶችን፣ ለሁለተኛው ቡድን አእምሯዊ ብልሃቶችን በቀጥታ ከቃላት ተግባራቱ ጋር አቀናጅቶ ለ12 ሳምንት በማሰልጠን ንጽጽራዊ ጥናት አካሂደዋል። መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀሙበት ዘዴ በቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ተመሳሳይ የቃላት ፈተና በመፈተን ነው። በጥናቱ ውጤትም በሁለቱ ቡድኖች መካካል የጎላ ልዩነት አለመኖሩንና በአጠቃላይ ስልጠናው የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት ጠቃቀም ለማዳበር እንደሚረዳ ጠቁመዋል።

Bornay (2011) ከትውስታ ብልሃቶች ውስጥ በመቦደንና በአእምሮ ውስጥ ምስል መፍጠር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የቃላት ችሎታን ከማጎልበት አንጻርና ቃላቱን ለረዥም ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ስፓኒሽ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ አንደኛ አመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በሁለት ቡድን ከፍለው ለ12 ሳምንት በማሰልጠን ጥናት አካሂደዋል። በጥናታቸው ውጤትም ለጀማሪ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ ማሰልጠን የቃላት ችሎታቸውን ለማሻሻልና በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት በዘላቂነት አስታውሶ ለመጠቀም አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው ጠቁመዋል።

Rajee (2013) ተማሪዎችን በሁለት ሙከራዊ ቡድን በመክፈል በመደጋገም፣ መዝገበ ቃላት መጠቀም፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ከአውድ መገመት፣ ራስን መቆጣጠርና የመቦደን ብልሃቶችን ከክፍል ውስጥ የቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት ግልጽ ስልጠና በተሰጣቸውና ኢ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ተግባራቱን እየሰሩ ወይም ብልሃቶቹን በግልጽ ባልተማሩት ቡድኖች መካከል በቃላት ችሎታቸው መሻሻል ላይ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ በኢራን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዘጠነኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ንጽጽራዊ ጥናት አካሂደዋል። በጥናታቸውም የሁለት ቡድን ነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent sample t-test) ተጠቅመው ባደረጉት ትንተና ግኝትም በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ብልሃቶችን ከተግባራቱ ጋር በማቀናጀት በግልጽ የተማረው ቡድን ብልሃቶቹን በግልጽ ካልተማረው ቡድን በድህረትምህርት የቃላት ፈተና የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን፣ የተማሩትን ቃላት በሌላ ጊዜ አስታውሰው

መጠቀም እንዲችሉና የቃላት መማር ሂደታቸውን በራሳቸው እንዲቆጣጠሩ አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

Alseweed (2000) ከአውድ መገመት፣ በንባብ ሂደት አዲስ ቃል ሲያጋጥም ዝምብሎ በማለፍ (Skipping) ብልሃትና ሌሎችን እርዳታ የመጠየቅ ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃቶቹን አጠቃቀም ለማዳበር ያለውን አስተዋጸኦ ለመፈተሽ 19 የአረብኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎችን በሙከራና በቁጥጥር ቡድን ከፍለው ለስድስት ሳምንት በማሰልጠን ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸውም የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተጠቅመው ባደረጉት ትንተና ግኝትም በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ስልጠና የተሰጣቸው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ሥልጠና ካልወሰዱት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የቃላት ችሎታቸው መሻሻሉንና በንባብ ሂደት አዳዲስ ቃላት ሲገጥማቸው ብልሃቶቹን በተገቢ መንገድ መጠቀም እንደቻሉና የቁጥጥር ቡድኑ ግን በንባባ ሂደት ለሚገጥማቸው አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመፈለግ ከአውድ ከመገመት ይልቅ መዝገበ ቃላትን እንደመጀመሪያ አማራጭ እንደሚጠቀሙ በመጠቆም ብልሃቶቹን በክፍል ውስጥ በግልጽ ማሰልጠን ለተማሪዎች ጠቃሚ መሆኑን አረጋጋጠዋል፡፡

Nation (2001)ቁልፍ ቃላት የመጠቀም ብልሃትን (Keword method) በክፍል ውስጥ ማሰልጠን የተማሪዎችን በአንድ ወቅት በክፍል ውስጥ የተማሩትን ቃላት አስታውሶ የመቀምና የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ በሁለት ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና ንድፍ ላይ በመመስረት ባደረጉት ጥናት ውጤትም ከስልጠናው በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ቃላት አስታውሶ የመጠቀም ችሎታቸው መሻሻሉንና ቁልፍ ቃላትን የመጠቀም ብልሃት በአዳዲስ ቃላት ቅርጽና ፍቺ መካከል ትስስር ለመፍጠር ጠቃሚ የትውስታ ብልሃት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

Brown & Perry (1991) በስነ-ፍቻዊ ካርታ፣ የመዐደንና አዳዲስ ቃላትን በአውድ ውስጥ በመጠቀም ብልሃት ላይ ስልጠና መስጠት የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሻሻል ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ 60 አረብኛ ቋንቋ ተማሪዎችን በሙከራና

በቁጥጥር ቡድን በመክፈል ለ10 ሳምንት ሁለት የተለያዩ መምህራንን በእጣ ናሙና በመምረጥ እንዲያስተምሩ በማድረግ ጥናት አከናውነዋል። በጥናቱ ውጤትም ስልጠናው የተማሪዎችን ቃላት ችሎታ ለማሻሻል አስተዋጽኦ እንዳለው አረጋግጠዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ሁለቱ ቡድኖች በተለያየ መምህር መሰልጠናቸው በመምህር ብቃት፣ ተነሳሽነትና የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ልዩነት ምክንያት በጥናቱ ውጤት ላይ የሚመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቆጣጠር አስቸጋሪ በመሆኑ ጥናቱ ክፍተት ይታይበታል።

Rodriguez & Sadoski (2000) ማሰላሰል፣ ከአውድ መገመት፣ ቁልፍ ቃላት የመጠቀም ብልትና ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት የመጠቀም ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ በጥምረት በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃቶች ግንዛቤና አጠቃቀም ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ በአንደኛ አመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጥናት አካሂደዋል። የምርምሩ ንድፍ በሁለት ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት ፈተና ላይ የተመሰረተ ነበር። ተመራማሪው መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀሙበት ዘዴ በቅድመና ድህረትምህርት ተመሳሳይ የቃላት ፈተና በመስጠት ነው። እንዲሁም ቅድመና ድህረትምህርት ተመሳሳይ የቃላት መማር ብልሃቶችን አጠቃቀም የሚመለከት የጽሑፍ መጠይቅ ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብቻ በመስጠት ነው። በጥናቱ ውጤትም ከስልጠናው በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ ውጤት ማስመዝገባቸውንና የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም መሻሻሉን አረጋግጠዋል። በተጨማሪም በአንድ ነጠላ ብልሃት ላይ ከማተኮር የተለያዩ ብልሃቶችን በጥምረት ማሰልጠን የተሻለ መሆኑን ጠቁመዋል።

Boyle (1987) በHong kong እንግሊዝኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩ 490 የቻይና ተማሪዎች ማለትም 233 ሴትና 257 ወንድ ተማሪዎች ውስጥ 10 የተለያዩ የቃላት ፈተና አቅርበው በካሂዱት ጥናት በአጠቃላይ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን በጥናታቸው ጠቁመዋል። በሌላ በኩል Boyle (1987) የአዳምጦ መረዳት ፈተና ፈትነው በካሂዱት ጥናት ደግሞ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የቃላት ውጤት እንዳስ መዘገቡ ጠቁመዋል። Bacon (1992) ሁለት

የማዳመጥ ክሂል ተግባራትን ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አቅርበው በካሂዱት ጥናት በሴትና በንወድ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መካከል ልዩነት እንደሌለ በጥናቸው ውጤት አመላክተዋል። Nyikos (1990) በጀርመንኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት በጀርመንኛ ቋንቋ የቃላት ችሎታ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ በጥናታቸው ውጤት ጠቁመዋል።

ሁኖም የBoyle (1987)፣ Bacon (1992) እና Nyikos (1990) ጥናቶች ብልሃቶችን በግልጽ በማስተማር የሴትና የወንድ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በመተሸ የተገኘ ሳይሆን በተለምዷዊ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎችን የተለያዩ ፈተናዎችን በመፈተን የተገኙ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አላቸው።

በኢትዮጵያ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠንን የሚመለከቱ ባይሆኑም በቃላት ክሂል ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ተከናውነዋል። ቀጥሎ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ተቃኝተዋል።

ንጋቱ (2000) እና በላይነሽ (2002) አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ለመፈተሽ ጥናት አካሂደዋል። በጥናታቸው ግኝትም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች (በላይነሽ፣ 2002) እና አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች (ንጋቱ፣ 2000) የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ወይም ስለብልሃቶቹ ያላቸው ግንዛቤና የቃላት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን አሳይተዋል። ለተማሪዎቹ የቃላትና የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ ዝቅተኛ መሆን እንደምክንያት የተጠቀሱትም መምህራኑ በተማሪዎች ላይ ከሚታይ የግንዛቤ ችግር በመነሳት በክፍል ውስጥ ብልሃቶቹን በግልጽ ለማሰልጠን ጥረት አለማድረጋቸው እንደሆነ አመላክተዋል። የጥናታቸውን ውጤት መነሻ በማድረግም በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ዘመናዊ የቃላት ትምህርት መማሪያ ስልቶችን የተከተለ እንዲሆንና የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ማዳበር እንዲችል መምህራን ለተማሪዎቻቸው በቂ መረጃ በመስጠት ተማሪዎቹ ከተለያዩ

ብልሃቶች ጋር እንዲተዋወቁና ይበልጥ የሚስማማቸውን መርጠው እንዲጠቀሙ በማገዝ በራሳቸው ጥረት ቃላትን እንዲማሩ መርዳት እንደሚገባ የመፍትሄ ሐሳብ ሰንዝረዋል፡፡

ብሩክታዊት (2001)፣ ደረበ (1999) እና እሸቱ (1997) የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ከዘመናዊ የቃላት ትምህርት ስልቶች አቀራረብ ጋር ያለውን ተገቢነት ለመፈተሽ ጥናቶች አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤትም ጥናቱ በተካሄደባቸው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ቃላትን ሲያስተምሩ የተለመዱትን የቃላት ማስተማሪያ ዘዴዎች አዘውትረው እንደሚጠቀሙና የቃላት መማር ብልሃቶችን ባጣመረ መልኩ ስለማያቀርቡ አቀራረቡ ተማሪዎችን አሳታፊ አለመሆኑን፣ መምህራኑም ቃላትን የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ስነትምህርታዊ ቴክኒኮችን በተመለከተ ምንም አይነት የስራ ላይ ስልጠና ወስደው እንደማያውቁና ከዚህ ውጪ ሌሎች የቃላት ማስተማሪያ ስልቶች ስለመኖራቸው በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸውና የተማሪዎች የቃላት ችሎታም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡ ለተማሪዎች የቃላት ችሎታ ዝቅተኛ መሆን እንደምክንያት የተጠቀሱትም መምህራን ውጤታማ ያልሆኑ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ መጠቀማቸው እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

በላይነሽ (2002) እና ንጋቱ (2000) ያከናወኗቸው ጥናቶች ብሩክታዊት (2000)እና ደረበ (1999) ካከናወኗቸው ጥናቶች ጋር የሚመሳሰሉት ሁሉም በቃላት ክሂልና በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ልዩነታቸው ግን የበላይነሽ (2002) እና የንጋቱ (2000) ጥናቶች የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም በመፈተሽ ላይ ያተኮሩ ናቸው፤ብሩክታዊት (2000)፣ ደረበ (1999) እና እሸቱ (1997) ጥናቶች ግን በቃላት ትምህርት አቀራረብ ስልቶች ላይና የቃላት እውቀት ላይ ትኩረት ሰጥተው የተከናወኑ ናቸው፡፡


በአጠቃላይ ይህ ጥናት በአማርኛ በቃላት ዙሪያ ከተደረጉት አገርኛ ቀደምት ጥናቶች በዋነኛነት የሚለየው በጥናቱ አላማ ነው፡፡ ይኸውም ቀደምት ጥናቶቹ ትኩረታቸው በተለያየ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ፣ በተለያየ ቦታና የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ችሎታ ማረጋገጥ፣ የተማሪዎችን

የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መፈተሽና የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ መገምገም ነው።

ይህ ጥናት ግን ከፊል ፍትነታዊ ስልት (Quasi-experimental) ላይ ተመስርቶ የሁለት ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና በመጠቀም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀማቸውን ለማሳደግ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ቃላት ላይ ከተደረጉት ቀደምት ጥናቶች በዋነኝነት የሚለየው ተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማሰልጠን የቃላት ችሎታቸውንና የብልሃትአጠቃቀማቸውን ለማሳደግ የሚኖረውን አስተዋጽኦ፣ በጾታ መካከል ያለውን የቃላት ችሎታ በመለካቱ፣ የክፍል ውስጥ የቃላት ትምህርት አተገባበር ሂደት፣ የተማሪዎችንና የመምህራንን ሚና በግልጽ የሚያሳይ ነው።

2.12. የጥናቱ ጽንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ

ይህ ጥናት ቀጥሎ የቀረበውን ጽንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ መሰረት አድርጎ ተከናውኗል። በጥናቱ ጽንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ የሚገኙት የቃላት መማር ብልሃቶች ግልጽ ስልጠና፣ የቃላት ችሎታ፣ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታና ጾታ ናቸው። ከነዚህም የቃላት መማር ብልሃቶች ግልጽ ስልጠና ነጻ ተላውጦ ሲሆን፣ የቃላትና የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ ጥገኛ ተላውጦዎች ናቸው። እነዚህ ተላውጦዎች፣ የጥናቱ አብይ ተላውጦዎች ሲሆኑ፣ ጾታ የጥናቱ ንኡስ ነጻ ተላውጦ ነው። በዚህ ጥናት ነጻ ተላውጦው (የቃላት መማር ብልሃቶች ግልጽ ስልጠና አተገባበር በመጀመሪያ በመምህር፣ መምህርና ተማሪዎች፣ በመጨረሻም በተማሪዎች በግል ይከናወናል። ስለሆነም የጥናቱ ጽንሰ ሃሳባዊ ማሕቀፍ በስዕል ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።



ስዕል 1.2፡- የጥናቱ ጽንሰሀሳባዊ ማሕቀፍ

ይህ ጽንሰ ሀሳባዊ ማሕቀፍ በዋናነት የጥናቱን ነጻና ጥገኛ ተላውጦዎች፣ የቃላት መማር ብልሃቶችን፣ የመምህሩንና የተማሪውን ተግባራት አካቶ ከመያዝ በተጨማሪ የጥናቱን መነሻና መድረሻ የሚያሳይ ነው፡፡ ከስዕላዊ መግለጫው እንደሚታየው ስልጠናው ከስድስት ዋና ዋና የቃላት መማር ብልሃቶች የተውጣጡ ብልሃቶችን ያቅፋል፡፡ የእነዚህ ብልሃቶች ምንነት፣ ጠቀሜታና አተገባበር በመምህሩ ከተገለጸ በኋላ በመጀመሪያ በመምህሩ ሞዴልነት የቃላት ትምህርት ተግባሩ የሚጀመር ሲሆን፣ በመቀጠል በመምህሩና በተማሪዎች በጋራ ብልሃቶቹን በመጠቀም የቃላት ተግባራትን ይሰራሉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ብልሃቶቹን እየተጠቀሙ ራሳቸውን ችለው የቃላት ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ በክንውኑ ሂደት ብልሃቶቹ ተግባራቱን ለማከናወን ባላቸው ተገቢነት ላይ ያተኩራሉ፡፡ እነዚህ ክንውኖችና ሂደቶች ደግሞ የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም ችሎታ በማዳበር የቃላት ችሎታን ያሳድጋሉ፡፡

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት በአይነቱ መጠናዊ ምርምር (Quantitative Research) ሲሆን፣ ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ (Quasi-experimental) የምርምር ስልትን የተከተለም ነው። በዚሁ መሰረት በከፊል ፍትነታዊ ስልት ላይ የተመሰረተ የሁለት ቡድኖች (የቁጥጥርና የሙከራ) ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና ንድፍ (two-group-pre-test-post-test-Comparison design) ተግባራዊ ተደርጓል። በሁለት ቡድኖች ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና የምርምር ንድፍ መሰረትም የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድን ተማሪዎች አንድ አይነት ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል፤ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል። ከዚያም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በሙያዊ እገዛ (Scaffolding) መርህ በግልጽ ለማሰልጠን በተመረጠው ቅደምተከተላዊ ማሕቀፍ (በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞድል) መሰረት የቃላት መማር ብልሃቶች ግልጽ ስልጠና እየተሰጣቸው፣ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ደግሞ በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ (በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ) ቃላትን ተምረዋል። በመጨረሻም የሁለቱም ቡድኖች ተማሪዎች አንድ አይነት ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል፤ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል። አጠቃላይ የጥናቱ ንደፍ መዋቅርም የሚከተለውን ይመስላል።

ቡድን	ቅድመትምህርት ፈተና (pretest)	ስልጠና (intervention)	ድህረትምህርት ፈተና (posttest)
የሙከራ	✓	✓	✓
የቁጥጥር	✓	×	✓

3.2 የናሙና አመራረጥ

3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ጥናቱ የተከናወነው በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ክልል ልዩ ዞን፣ በአቃቂ ወረዳ፣ በዱከም ከተማ በኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ትምህርት ቤቱም የተመረጠው በአመቺ የናሙና አወሳሰድ (Convenience Sampling) ስልት ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ፍትነታዊ ስልትን የተከተለ በመሆኑ የትኛውም ትምህርት ቤት ቢመረጥ መስራት ይቻላል፡፡ ሆኖም ለአጥኚዋ የስራ አካባቢ ቅርብ ቢሆን ጥናቱን በቅርበት ለመከታተል፣ በጥናቱ የሚሳተፉ መምህራንንና ተማሪዎችን መረጃ የመስጠት ትብብር ለማግኘት በማሰብ በዱከም ከተማ የሚገኘው ኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥናቱ እንዲካሄድበት ፈቃደኛ ሆኖ ስለተገኘ ተመርጧል፡፡

3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በአመቺ ናሙና በተመረጠው በኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2009 ዓ.ም. በሁለተኛው ወሰነትምህርት በመማር ላይ ከነበሩት አስራ ሁለት የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች መካከል የሁለት የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች 9ኛC‌ና 9ኛB በቀላል እጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (Simple Random Sampling) ተመርጠዋል፡፡

ዘጠነኛ ክፍል (የክፍል ደረጃው) በዓላማ ተኮር (Purposive Sampling) የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጠ ሲሆን፣ ምክንያቶቹም የሚከተሉት ናቸው፣ በኢትዮጵያ

በአማርኛም ሆነ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠንን የተመለከተ ጥናት አልተገኘም፡፡ ምንም እንኳን የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ሊተገበር ቢችልም በአለም አቀፍ ደረጃ በሁለተኛ ቋንቋ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠንን የተመለከቱ አብዛኛዎቹ የምርምር ስራዎች የተከናወኑትና ዘዴው የቃላት ችሎታን፣ የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀምን ለማዳበር ውጤታማ እንደሆነ የገለጹት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ለዚህም ምክንያቱ ብልሃቶቹ ካላቸው ውስብስብ ባህሪ የተነሳ የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ከተማሪዎች አእምሯዊ እድገት ጋር ስለሚያያዝ፤ አብዛኛዎቹ የቃላት መማር ብልሃቶች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ በሚገኙ ተማሪዎች የተሻለ ሊተገበሩ እንደሚችሉና በሁለተኛና በውጪ ቋንቋ ትምህርት በቋንቋው የዳበረ እውቀት ለሌላቸው በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ለሚገኙ /ለጀማሪ ተማሪዎች የብልሃት ስልጠና ማቅረብ ውስብስብ የቃላት መማር ብልሃቶችን ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ይቸገራሉ፤ ስለሆነም ውስብስብ ብልሃቶች በተማሪዎች ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉት በሚማሩት ቋንቋ የዳበረ እውቀት ባላቸው ተማሪዎች ነው (O'malley & Chamot, 1990; Gu & Johnson 1996; Schmitt, 1997)፡፡ በመሆኑም ይህን አለም አቀፋዊ ሁኔታ መነሻ በማድረግ የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ እርከን የሆኑትን የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ማጥናት አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ትምህርት እርከን ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከንን አጠናቀው ከክልል አቀፍ ወደ ሀገር አቀፍ የማስተማሪያ መጽሐፍ የሚሸጋገሩበት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ደረጃ በቃላት መማር ብልሃቶች የተደገፈ ትምህርት ማግኘታቸው ለሚቀጥሉት የክፍል ደረጃዎች የቃላት ችሎታ፣ አንብቦ የመረዳትም ሆነ አጠቃላይ ተግባቦታዊ ስኬት መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በዚህ የክፍል ደረጃ መከናወኑ ተገቢ ነው፡፡ ለክፍል ደረጃው መመረጥ ተጨማሪ ምክንያቱ በበላይነሽ (2002) ጥናትም የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች

የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤና የቃላት ችሎታ ዝቅተኛ ሆኖ የታየበት መሆኑ ነው።።

ስድስተኛ፣ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ያልተመረጡበት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ተማሪዎቹ ቋንቋውን መማር የሚጀምሩት ከአምስተኛ ክፍል በመሆኑ በቋንቋው የዳበረ እውቀት ስለሌላቸው በዚህ ደረጃ ጥናቱን ማካሄድ አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል በጥናቱ ግኝቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ከሚል ስጋት ነው።። አስረኛ ክፍል ያልተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎቹ አገር አቀፍ ፈተና ተፈታኞች በመሆናቸው በጥናቱ ትግበራ ውቅት ትኩረት ሰጥተው ላይከታተሉ ስለሚችሉ በጥናቱ ግኝቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ከሚል ስጋት ሲሆን ጥናቱን በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል ላይ ለማካሄድ ደግሞ ከ10ኛ ክፍል በኋላ ተማሪዎች ከሀገር ውስጥ ቋንቋ አንድ መርጠው ስለሚማሩ በነዚህ የክፍል ደረጃዎች አሮምኛ አፍፊት ሆነው አማርኛ የሚማሩ ተማሪዎችን በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በብዛት ማግኘት አይቻልም።።

3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ

በአመቺ ናሙና በተመረጠው አዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2009 ዓ.ም. በሁለተኛው ወሰነትምህርት በመማር ላይ ከሚገኙት አስራ ሁለት የዘጠነኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች መካከል የሁለት የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና (Simple Random Sampling) ዘዴ ተመርጠዋል።። ምክንያቱም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በአንድ የክፍል ደረጃ በተለያዩ የመማሪያ ክፍሎች ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ ከየመማሪያ ክፍሉ የተወሰኑ ተማሪዎችን በእጣ በመምርጥ በአንድ ክፍል ውስጥ ለማስተማር መሞከር እጅግ አስቸጋሪ ስለሆነና የተተግባሪነት ችግር ስላለበት ነው።። በመሆኑም ይህን በእጣ የመመደብ ችግር ሊፈታ የሚችለው ካሉት የመማሪያ ክፍሎች የሁለት የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን በሙሉ (intact group) በእጣ፣ በአመቺ ናሙና ወይም በአላማተኮር የናሙና ዘዴ መርጦ በጥናቱ ተሳታፊ ማድረግ ነው።። የዚህ ጥናት ተሳታፊዎችም በዚህ መሰረት በቀላል እጣ ተመርጠዋል።።

ከተመረጡት የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎች መካከል አማርኛና ሌላ ቋንቋ አፍፊት የሆኑ ተማሪዎች ካለ ለማጣራት ጥረት ተደርጎ ከ123 ተማሪዎች መካከል 43 ተማሪዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ስለፊቱ በጥናቱ ውጤት ትንታኔ ውስጥ አልተካተቱም። እንዲሁም በጥናቱ ውጤት ትንታኔ ውስጥ ከተካተቱት 80 ተማሪዎች 7 ተማሪዎች አሟልተው መረጃ ስላልሰጡ ከጥናቱ ውጭ ሆነዋል። ስለሆነም ለጥናቱ የዋለው መረጃ የ73 ተማሪዎች ብቻ ነው። ከዚያም በቅድመትምህርቱ ፈተናዎች ያላቸው አማካይ ውጤት በድምዳሜያዊ (inferential) ስታትስቲክስ ቀመር ተሰልቶ ጉልህ የሆነ ልዩነት የሌለው ሆኖ ስለተገኘ በቀላል እጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በ9ኛC ክፍል ውስጥ ያሉት 63 ተማሪዎች በሙከራ ቡድን፣ በ9ኛB ክፍል ያሉት 60 ተማሪዎች ደግሞ በቁጥጥር ቡድን ውስጥ እንዲመደቡ ተደርጓል። በሙከራ ቡድን ከተሳተፉ ተማሪዎች አሮምኛ አፍፊት የሆኑትና አሟልተው መረጃ የሰጡት 15 ወንድ፣ 23 ሴት፣ በጥቅሉ 38 እና በቁጥጥር ቡድን ደግሞ 14 ወንድ፣ 21 ሴት፣ በጥቅሉ 35 ተማሪዎች ብቻ ናቸው።

3.2.4 የመምህር አመራረጥ

ይህ ጥናት በሁለት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገ ከፊል ፍትነታዊ ጥናት ነው። በጥናቱም ከመረጃ መሰብሰቢያዎቹ፣ ከማስተማሪያ መንገዱና መሳሪያው ውጭ ያሉ ተላውጦዎችን ለመቆጣጠር ሙከራ ተደርጓል። ለመቆጣጠር ከተሞከሩት ተላውጦዎች አንዱ የመምህር ተላውጦ ነው። በጥናቱ ውስጥ በመምህር ብቃት፣ ተነሳሽነትና የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ልዩነት ምክንያት በጥናቱ ውጤት ላይ የሚመጣውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቆጣጠር ሲባል፣ አንድ መምህርት ሁለቱንም ክፍሎች እንዲያስተምሩ ተደርጓል። መምህርቷ ለጥናቱ የተመረጡት ፣ በጥናቱ በተሳተፉት ክፍሎች ሲያስተምሩ የነበሩ በመሆናቸው ነው። ይህም ጥናቱ የሚፈጥረው የመምህር ተላውጦ እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ፣ የቁጥጥር ቡድኑ ሲማር በቆየበት መንገድ ትምህርቱን እንዲከታተል ይረዳል ተብሎ ታስቦ ነው። ይህን አስመልክቶ Seid (2012፣ 94) Jacobs & Sorensen (2010) ጠቅሰው እንደገለጹት ሁለቱም ክፍሎች በአንድ መምህር መማራቸው የጥናቱን ውስጣዊ ትክክለኛነት ለመቆጣጠር ይረዳል።

በዚህም መሰረት መምህርቷ የቁጥጥር ቡድኑን ቀደም ሲል ሲማሩበት በነበረው ዘዴ ማለትም ምንም አይነት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ሳይወስዱ በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ መሰረት (በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ)፣ የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች ደግሞ የቃላት መማር ብልሃቶችን ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት በሙያዊ እገዛ (Scaffolding) መርህ በድጋፍ በግልጽ ለማሰልጠን በተመረጠው ቅደምተከተላዊ ማሕቀፍ (በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞድል) መሰረት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና እየተሰጣቸው በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተመሳሳይ የቃላት ትምህርት (vocabulary lesson) ሁለቱንም ቡድን ከየካቲት 17 እስከ ሰኔ 3 ለአስራ አራት ሳምንታት (ለ28 ክፍለ ጊዜያት፤ በሳምንት ሁለት ክፍለጊዜ እንዲያስተምሩ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።።

መምህርቷ የቃላት መማር ብልሃቶችን ከቃላት ተግባራት ጋር አቀናጅቶ በግልጽ የማስተማሪያ ስልት አዲስ በመሆናቸው ለአምስት ቀናት (ከየካቲት 21-22፣ 24-26 ቀን 2009 ዓ.ም.) በቀን ለሁለት ሰዓት ስለቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ አተገባበር፣ ለጥናቱ ስለተመረጠው ቅድምተከላዊ ማሕቀፍ (ሞዴል)ና የስልጠናው አተገባበር በአጭሂዋ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል (ማንዋሉን አባሪ ቀ ይመልከቱ)።።

3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱን ለማከናወን ያገለገሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የቃላት ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ ነው።። የጽሑፍ መጠይቁ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀምን የተመለከተ ሲሆን፣ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብቻ ቅድመትምህርትና የተሞላ ነው።። የእያንዳንዳቸው አዘገጃጀትና አተገባበርም እንደሚከተለው ቀርቧል።።

3.3.1. ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተናዎች

አንዱ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ነው። በናሙናው ጥናትም ሆነ በዋናው ጥናት ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተናው የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በተለያየ መንገድ ለመለካት እንደሚያስችል Alderson እና ሌሎች (1995) የጠቆሙትን የተለያዩ የቃላት ፈተና አቀራረብ ስልቶችን (format) የተከተለ ሰባት ክፍሎች ያሉትና ከ30 የታረመ ነው።

የቃላት ችሎታ መለኪያ ፈተናዎቹ የተሰጡት ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ነው። የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች ትምህርቱን ከመጀመራቸው በፊት ተቀራራቢ ውጤት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። በተጨማሪም ይህ ውጤት ለሁለቱም ቡድኖች የጥናቱ የቅድመትምህርት የቃላት ችሎታ ውጤታቸው ሆኖ ተመዝግቧል። የድህረትምህርት ፈተና ዓላማ ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ሁለት አቀራረቦች ቃላትን በመማራቸው በቃላት ችሎታቸው ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ነው (ፈተናዎቹን አባሪ ሰ እና ሸ ይመልከቱ)።

ፈተናዎቹ የተዘጋጁት በአጥኚዋ ሲሆን፣ የፈተናቹን አዘገጃጀትና አተገባበር በተመለከተ የቃላት ችሎታን ለመለካት ተማሪዎች ያለበትን የክፍል ደረጃና ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሌላ ጥያቄ ማዘጋጀት ሳያስፈልግ የፈተና ጥያቄዎቹ የተወሰዱት የመርሃ ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሐፉን አላማ መሰረት በማድረግ ከመማሪያ መጽሐፉ ነው። አወሳሰዱና አዘገጃጀቱ ግን በመማሪያ መጽሐፉ ከቀረቡት ምንባቦች አዳዲስ ቃላት በመምረጥና በመማሪያ መጽሐፉ በመልመጃ የቀረቡትን ቃላት የቀረቡበትን አውድ በመቀየር ነው። ለምሳሌ በፈተናው ከቀረበው ቃል «**ሸረከተው**» የሚለው በመጽሓፉ ውስጥ የቀረበው «**ወጋው** » የሚለውን ፍቺ በመወከል ሲሆን በፈተናው ውስጥ ግን« ሸረከተው» የሚለው «**ቀደደው** » የሚለውን ፍቺ በመያዝ ነው።

ከመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጀበት ምክንያት ተማሪዎቹ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በመሆናቸው፣ የቃላት ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች የበለጠ ውስብስብ ችሎታን የሚጠይቅ በመሆኑና የተማሪዎችን ደረጃ የሚመጥኑ ቃላትን ከሌላ ቦታ መርጦ ማቅረብ አስቸጋሪ ስለሆነ የፈተናውን የይዘት ተገቢነትና አስተማማኝነት ስለሚጎዳ ነው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ቃላት በዛው ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ያሉና ለክፍል ደረጃው ይመጥናሉ ተብለው ተመዝነው የቀረቡ በመሆናቸውና ተማሪዎቹም ለነዚህ ቃላት በተለያየ መልኩ የተሻለ ተጋልጦ ስለሚኖራቸው በዚህ ምክንያት የሚፈጠረውን ተላውጦ (ለምሳሌ የፈተናው መክበድና መቅለል) ለመቆጣጠር ይረዳል፡፡ እንዲሁም በሁለቱም ፈተናዎች ሁሉም ጥያቄዎች ባለአማራጭ እንዲሆኑ የተደረገበት ምክንያት ለሚዛናዊ ውጤት አሰጣጥ ምቹ በመሆኑና ብሎም በአንጻራዊነት በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ስለሚያስችል የፈተናውን ውጤት አስተማማኝነትና ተገቢነት (validity) ከፍ ለማድረግ እንዲረዳ በማሰብ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በተለያየ መንገድ ለመለካት ምቹ በመሆኑ ነው፡፡

የፈተናውን የይዘት ተገቢነት (content validity)ና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት በጥናቱ አማካሪ፣ በክፍል ደረጃው የሚያስተምሩ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ አማርኛን በማስተማር ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት የቋንቋ መምህራንና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሁለት የስነልቦና ባለሙያዎች እንዲያዩዋቸውና እንዲገመግሟቸው ተደርጓል፡፡ ከመምህራኑ፣ ከባለሙያዎቹና ከሙከራ ጥናቱ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም መጨመር ያለባቸው ጥያቄዎች ተጨምረዋል፣ መሻሻል ያለባቸው ተሻሽለዋል፣ መወገድ ያለባቸው ተወግደዋል፣ የአሻሚነት ባህሪ የታየባቸውን አማራጮች የማስተካከል ተግባራት ተከናውነዋል (ለምሳሌ፣ የትዕዛዝ ግልጽነትና አሻሚ መልስ የያዙ አማራጮችን ማስተካከል)፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎችን ግምገማና አስተያየት መሰረት በማድረግም የቃላት ፈተናውን ተገቢነት ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡

ከዘርፉ ባለሙያዎች ሙያዊ ግምገማና አስተያየት በኋላም የፈተናውን ይዘታዊ ወጥነት (Internal Consistency) ከሚጠቁሙ የተለያዩ የአስተማማኝነት መገመቻ

ዘዴዎች ውስጥ በናሙናው ጥናት ጊዜ የቃላት ፈተናዎቹን የአስተማማኝነት ደረጃ ለመወሰን የእኩል ክፋይ ዘዴ (split-half) ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት እያንዳንዳቸው 30 ጥያቄዎችን የያዙት የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተናዎች በናሙና ጥናቱ ለ77 ተማሪዎች ቀርበው የተገኘው ውጤት ጥያቄዎቹን በተራ ቁጥራቸው መሰረት ሙሉ ቁጥሮችን በአንድ፣ ጎዶሎ ቁጥሮችን በሌላ ምድብ በማድረግ እኩል ለሁለት ተመደቡ፡፡ ከዚያም ለእያንዳንዱ/ዷ ተማሪ ከሙሉ ቁጥር ጥያቄዎች ያገኘችው /ያገኘው ውጤትና ከጎዶሎ ቁጥር ጥያቄዎች ያገኘችው/ ያገኘው ውጤት ለየብቻ ተሰልቶ ሁለት ሁለት ውጤቶች ተመዘገቡ፡፡ ሁለቱን ውጤቶች መሰረት በማድረግ ተለክቶ የቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አስተማማኝነት r= 0.701፣ የድህረትምህርቱ r= 0.889 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከ0.7 በላይ ስለሆነ አስተማማኝ መሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

በዋናው ጥናት ወቅት ለ73 ተማሪዎች በቀረቡበት ወቅት ለሁለተኛ ጊዜ አስተማማኝነታቸው በክሮንባኽ አልፋ ዘዴ (Cronbach Alpha) ቀመር ተፈትሾ የቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አስተማማኝነት r= 0.807፣ የድህረትምህርቱ የቃላት ፈተና r= 0.856 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከ0.7 በላይ ስለሆነ አስተማማኝ መሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የፈተናዎቹን አስተማማኝነት ከማስላት በተጨማሪ የእያንዳንዱ ጥያቄ የክብደት ቅለት ደረጃና ዝቅተኛ ውጤት ያገኙትን ከፍተኛ ውጤት ካገኙት ተማሪዎች የመለየት ብቃት ተሰልቷል፡፡ Alderson (2005) እንደሚያስረዱት አንድ ጥያቄ ጥሩ የክብደት ቅለት ደረጃ አለው የሚባለው ተካፍሎ የተገኘው ውጤት በ0.3 እና በ0.7 መካከል ሲሆን ነው፡፡ የተገኘው ስሌት ውጤት ከ0.3 በታች ከሆነ ጥያቄው መክበዱን የሚያሳይ ሲሆን፣ ውጤቱ ከ0.7 በላይ ከሆነ ደግሞ ፈተናው እየቀለለ መሄዱን ያሳያል፡፡ እንዲሁም አንድ ጥያቄ ጥሩ የመለየት ብቃት አለው የሚባለው ደግሞ ተሰልቶ የሚገኘው ውጤት አነሰ ቢባል ከ0.3 በታች መውረድ የለበትም፡፡

ከዚህ በታች ውጤት ያላቸው ጥያቄዎች ከፍተኛ ውጤት ያገኙትን ዝቅተኛ ውጤት ካገኙት ተማሪዎች ያለመለየት ችግር አለባቸው ተብሎ ስለሚታሰብ መስተካከል

ወይም መወገድ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ከስሌቱ በተገኘው ውጤት መሰረት በሙከራ ጥናቱ ለ77 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከቀረቡት የቃላት ፈተና ጥያቄዎች ስምንቱ ከፍተኛ የመለየት ብቃት (ከ0.50 በላይ)፣ አስራ ስምንቱ መካከለኛ (ከ0.33 እስከ 0.50) አራቱ ዝቅተኛ የመለየት ብቃት (ከ0.3 በታች) አሳይተው ነበር ፡፡ ይህ ፈተና በሙከራ ጥናቱ በተደረገው ፍተሻ ውጤቶች መነሻ ከ0.16 እስከ 0.25 የሆነ ዝቅተኛ የመለየት ብቃት የነበራቸው አራት ጥያቄዎች ላይ በተደረጉ ማሻሻያዎች በዋናው ጥናት ወቅት ለ73 ተማሪዎች ሲቀርብ ከ0.33 እስከ 0.76 የመለየት ብቃት (አባሪ ሐ ይመልከቱ) በመገኘቱ ፈተናው መካከለኛና ከፍተኛ የመለየት ብቃት ያላቸውን ጥያቄዎች ማካተቱን ያሳያል፡፡

የጥያቄዎቹ የክብደት ቅለት ደረጃ በሙከራ ጥናቱ በተደረገው ፍተሻ ሁለቱ ቀላል (0.70 በላይ)፣ ሃያ አምስቱ መካከለኛ ክብደት (0.45 እስከ 0.70)፣ ሦስቱ ከባድ (0.24-0.28) ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዚሁ በዋናው ጥናት ወቅት የጥያቄዎቹ የክብደት ቅለት ደረጃ ሲሰላ ከ0.25 እስከ 0.77 ነጥቦች (አባሪ መ ይመልከቱ) በመገኘታቸው ፈተናው ከቀላል እስከ ከባድ ጥያቄዎችን ማካተቱን ይጠቁማል፡፡ ፈተናው ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የክብደት ደረጃ ያላቸውን ብሎም ዝቅተኛ ውጤት ያገኙትን ከፍተኛ ውጤት ካገኙት ተማሪዎች የመለየት ብቃት ያላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች አካቶ በመገኘቱም የተሻለ ይዘታዊ ተገቢነት (content validity) እንዳለው አመላካች ነው፡፡

3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ በOxford (1990) ከተዘጋጁት ጥያቄዎች ለዚህ ጥናት እንዲስማማ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ አምስት ደረጃዎች ባሉት በሊከርት ስኬል የተዘጋጀና በስድስቱ ዋናዋና የቃላት መማር ብልሃቶች (በትውስታ፣ በአካባቢ፣ በአዕምሯዊ፣ በልዕለ አዕምሯዊ፣ በማህበራዊና በስሜት ነክ ቁጥጥር የቃላት መማር ብልሃት) ስር የሚመደቡ፣ በስልጠናው የተካተቱት ዝርዝር ብልሃቶችን መሰረት ያደረጉ በሙከራው ጥናት 17፣ በዋናው ጥናት 12 ዝግ

ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብቻ ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ተሞልቷል።

የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁ ዋና ዓላማ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ከመሰልጠናቸው በፊትና ከስልጠናው በኋላ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀማቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና በድህረትምህርት የቃላት ፈተና የሚገኘው ውጤት በርግጥም ስልጠናው የተማሪዎቹን የብልሃት አጠቃቀም በማሻሻሉ የተገኘ መሆኑን ወይም የስልጠናውን ውጤታማነት ለማወቅ ነው። ድህረትምህርቱም ሆነ ቅድመትምህርት የጽሑፍ መጠይቁ በመጠንም ሆነ በይዘት ተመሳሳይ ነው (የዋናውን ጥናት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቁን አባሪ ረ ይመልከቱ)።

የጽሑፍ መጠይቁን ተገቢነትና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት የጥናቱ አማካሪ፣ ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል በሚያስተምሩ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው አንድ የስነልቦና ባለሙያ እንዲያዩትና እንዲገመግሙት ተደርጓል። ከመምህራኑ፣ ከጥናቱ አማካሪና ከባለሙያዎቹ የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግም መጨመር ያለባቸው ተጨምረዋል፣ መሻሻል ያለባቸው ተሻሽለዋል፣ መወገድ ያለበቸው ተወግደዋል፣ የአሻሚነት ባህሪ የታየባቸውን በማብራራት ግልጽ የማድረግ ተግባራት ተከናውነዋል (ለምሳሌ፣ የአጠያየቅ ችግር ያለባቸው ጥያቄዎች ማስተካከል)። የዘርፉ ባለሙያዎችን ግምገማና አስተያየት መሰረት በማድረግም የጽሑፍ መጠይቁን ተገቢነት (validity) ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። ከዘርፉ ባለሙያዎች ሙያዊ ግምገማና አስተያየት በኋላም የጽሑፍ መጠይቁን አስተማማኝነት (Reliability) ለማረጋገጥ የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። በሙከራ ጥናቱ ጊዜ የቃላት መማር ብልሃት የጽሑፍ መጠይቆቹን (ቅድመ ትምህርትና ድህረትምህርት) የአስተማማኝነት ደረጃ ለመወሰን የክሮንባኽ አልፋ ዘዴ (Cronbach Alpha) ተግባራዊ ሆኗል። በዚህም መሰረት የጽሑፍ መጠይቆቹ የአስተማማኝነት ደረጃ ተለክቶ የቅድመትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ አስተማማኝነት (Reliablity) 0.716፣ የድህረትምህርቱ የቃላት

መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ 0.801 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ከ0.7 በላይ ስለሆነ አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጧል።

በዋናው ጥናት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቆቹን (ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት) የአስተማማኝነት ደረጃ ለመወሰን የክሮንባኽ አልፋ ዘዴ (Cronbach Alpha) ተግባራዊ ሆኗል። በዚህም መሰረት የጽሑፍ መጠይቆቹ የአስተማማኝነት ደረጃ ተለክቶ የቅድመትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ አስተማማኝነት (Reliability) 0.812፣ የድህረትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍመጠይቅ 0.819 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ከ0.7 በላይ ስለሆነ አስተማማኝ መሆኑ ተረጋግጧል። የጽሑፍ መጠይቁ ለቁጥጥር ቡድኑ ያልተሰጠበት ምክንያትም የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ስለማይወስዱ ባልተማሩት መለካት ስለማይቻልና በዋናነት ደግሞ የጽሑፍ መጠይቁን በሚሞሉበት ጊዜ ስለብልሃቶቹ መረጃ ስለሚያገኙ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል ከሚል ስጋት ነው። በጽሑፍ መጠይቁ የቀረቡት 12ቱም ዝርዝር ብልሃቶች ለትንተና እንዲያመች በስድስቱ ዋና ዋና የቃላት መማር ብልሃቶች ምድብ ተከፍለዋል። ማለትም በትውስታ (1-2)፣ በአካካሽ (3)፣ በአዕምሯዊ (4-7)፣ በልዕለ አዕምሯዊ (8-9)፣ በማህበራዊ (10-11) እና ስሜት ነኪ ቁጥጥር (12ኛ) የቃላት መማር ብልሃት ምድብ ተከፍለዋል።

3.4 የማስተማሪያ መሳሪያ አዘገጃጀት

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑን ቃላትን ለማስተማር በክፍል ደረጃው የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ አግልግሎት ላይ ውሏል። Gu (2003) እና Nation (2001) እንደሚያስረዱት በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተላውጠዎች አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያው ተገቢነት፣ ክብደትና ቅለት ነው፤ ለዚህም በሙከራዊ ጥናት ስልጠናው በተማሪዎች ውጤት ያመጣውን ለውጥ ለማረጋገጥ ለዚያው የክፍል ደረጃና በዚያው ስርአተ ትምህርት ውስጥ ያሉ ምንባቦችንና የቃላት መልመጃዎች መጠቀም ተገቢ ነው። ምክንያቱም መማሪያ መጽሐፉ

የተማሪዎችን ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክፍል ደረጃው ተመጥኖ የተዘጋጀ በመሆኑ ይህን ተላውጦ ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ጥናትም አዲስ የማስተማሪያ መሳሪያ በማዘጋጀት ምክንያት የሚፈጠረውን ተላውጦ ለመቆጣጠር በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ የቃላት ተግባራትን ለመጠቀም ተችሏል፡፡ መማሪያ መጽሐፉን መሰረት አድርጎ ቃላትን ለሙከራና ለቁጥጥር ቡድኑ ለማስተማር የቀረቡት የቃላት ተግባራት ግን የተለያየ የአቀራረብ ስልትን (ዘዴ) የተከተሉ ናቸው፡፡

Gu (2003b) እንደሚያስረዱት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የስልጠናው ውጤታማነት በሚቀርቡት ተግባራትና በመማሪያ አውዱ ምቹነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ማለትም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን ውጤታማ የሚሆነው ብልሃቶቹን በአውድ ሊያለማምዱ የሚችሉ ተገቢ የቃላት ተግባራት ሲቀርቡ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለሙከራ ቡድኑ የቀረቡት የቃላት ትምህርቶች የእያንዳንዱን የቃላት መማር ብልሃት አጠቃቀም በግልጽ በአውድ ለማሰልጠን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት እንዲማሩ ተደርጓል (ማሰልጠኛ መሳሪያውን አባሪ ቀ ይመልከቱ)፡፡

በትምህርቱ ጊዜም ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመደበውን ሁለት ክፍለጊዜ ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም አስቸጋሪ ነበር፡፡ ምክንያቱም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትንና የታቀዱትን ተግባራት ለመሸፈን የሚያስችል አልነበረም፡፡ ስለዚህ ከመደበኛው የትምህርት ሰዓት አንድ ክፍለ ጊዜ በማመቻቸትና አንድ ክፍለ ጊዜ ከትምህርት ሰዓት ውጭ ፕሮግራም በማስያዝ ሁለቱም ቡድን በተመሳሳይ ቦታና ጊዜ በሳምንት ሁለት ጊዜ (አንድ ክፍለ ጊዜ 40 ደቂቃ ያህል) የሙከራ ቡድኑ በተዘጋጀው መሳሪያ መሰረት የቃላት መማር ብልሃቶቹን ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት ቃላትን እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

የቁጥጥር ቡድኑ ግን መጽሐፉ የቀረቡትን ተመሳሳይ የቃላት ትምህርት ምንም አይነት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ሳይሰጣቸው በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ (በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ) መሰረት ተምረዋል፡፡

3.5 ስነ ምግባራዊ ሁኔታዎች

ጥናቱን ለማካሄድ በመጀመሪያ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትብብር ደብዳቤ ተጽፏል፡፡ ከዚያም የትብብር ደብዳቤውን በመያዝ፣ በዱከም ከተማ ከሚገኘው አዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ጋር ስለ ጥናቱ አላማ፣ ባህሪና ሂደት በመግለጽና በመወያየት ጥናቱ እንዲካሄድ ፈቃድ ተጠይቋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለጥናቱ ከተመረጡት ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር በመገናኘት የጥናቱን አላማ በማስረዳት ፈቃደኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ ትምህርት ቤቱ፣ መምህሯና ተማሪዎች ፈቃደኛ መሆናቸው ከተረጋገጠ በኋላ፣ ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች የጥናቱ አላማ በግልጽ ተነግሯቸዋል፡፡ እነሱን የሚመለከተው መረጃ ሁሉ በሚስጥር ተይዞ ለጥናቱ ዓላማ ብቻ እንደሚውልና በጥናቱ ሂደትም እስከ ጥናቱ መጨረሻ መቀጠል ካልፈለጉ አቋርጠው መውጣት እንደሚችሉ ተገልጸላቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑት ብቻ ናቸው፡፡ በጥናቱ ሂደትም ከ123 ተማሪዎች 43 ተማሪዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ ስለፈቱ በጥናቱ ውጤት ትንታኔ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ እንዲሁም በዋናው ጥናት በጥናቱ ውጤት ትንታኔ ውስጥ ከተካተቱት 80 ተማሪዎች 7 ተማሪዎች አሟልተው መረጃ ስላልሰጡ ከጥናቱ ውጪ ሆነዋል፡፡

ስለሆነም የጥናቱ ተሳታፊ የተመረጡት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱትና ከጥናቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ በሙሉ ፈቃደኝነት የተሳተፉት ተማሪዎች ብቻ ናቸው፡፡ ለምርምሩ ዓላማ የዋሉትም ሁለቱንም (ቅድመና ድህረትምህርት) የቃላት ፈተናዎች ከተፈተኑትና ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቆች ከሞሉት ኦሮምኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች ከ73 ተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ብቻ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከቃላት ትምህርት አቀራረቦቹ መለያየት ውጪ ለሁለቱም ቡድኖች እኩ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

3.6 የጥናቱ ሂደት

የዋናው ጥናት መሰረታዊ አላማ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነው። ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ጥናቱ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል።

በጥናቱ ሂደት መረጃዎቹ የሚሰበሰቡባቸው አመች ቀናት ተመርጠዋል። በቀነ ቀጠሮዎቹ ወቅትም የጥናቱን አላማ በተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያ ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችና ለጥናቱ ተግባሪ መምህርት ተሰጥቷል።

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ በሚሞሉበት ወቅት በአስራ ሁለቱ ዝርዝር የቃላት መማር ብልሃቶች መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ገለጻ ተደርጓል (ዝርዝሩ 3.8 ላይ ይመልከቱ)። በተጨማሪም ግልጽ ያልሆኑ ጽንሰ ሀሳቦች ካሉ እንዲጠይቁ በተደጋጋሚ ለማሳሰብ ተሞክሯል። ጥያቄዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግም ተጨማሪ ማብራሪያና በቂ ጊዜ ተሰጥቷል። በቃላት ፈተናው ጊዜም ይኸው ጥረትና ጥንቃቄ ተደርጓል።

በአጠቃላይ፣ ከተማሪዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ ሂደት በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት የመረጃ መዛባት እንዳይከሰትና በጥናቱ ማጠቃለያዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎች እንዳይፈጠሩ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ የማድረግ ጥረት ተከናውኗል።

በመጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን ለመለየት፣ የቃላት ፈተናውንና የጽሑፍ መጠይቁን በትክክል መሙላታቸውን ለማረጋገጥ ቅድመ ትንተና ፍተሻ ተከናውኗል። በዚህም በጥናቱ ከተሳተፉ 123 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች 43ቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ በመሆኑና 7ቱ ደግሞ ፈተናውንና የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁን አሟልተው ያልተገኙ በመሆናቸው በጥናቱ እንዳይካተቱ ተደርጓል። በፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች የትንተና ውጤት ምን እንደሚመስል ለማየት ጥረት ተደርጓል።

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በማዘጋጀት፣ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ሂደት የሚፈጠሩ ስህተቶችን ለመቀነስ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውን ጽሑፎች በመቃኘትና በባለሙያዎች በማስገምገም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ተሻሽለው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደትም አመች ሁኔታዎችን በመምረጥና በቂ ማብራሪያ በመስጠት ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹንም ከጥናቱ መላምቶችና መሰረታዊ ጥያቄዎች ጋር ለማጣጣም ጥረት ተደርጓል፡፡ የተገኙትን መረጃዎችም መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልትን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በቃላት ችሎታ መለኪያ ፈተናና በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችም ተተንትነዋል፡፡ እነዚህን ተግባራት በማከናወንም የጥናቱ ግኝቶች ተገቢነት ያላቸው እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ የጥናቱ የትግበራ ሂደትም ለሙከራው ቡድንና ለቁጥጥሩ ቡድን የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የጥናቱ ተተኳሪዎች የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በአመቺ ናሙና ከተመረጠው የአዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የሁለት የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎች በቀላል እጣ ናሙና ተመርጠው የካቲት 17 ቀን 2009 ዓ.ም. ከ2፡00–3፡00 ሁለቱም ቡድኖች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ፈተናው ታርሞና ተተንትኖ በሁለቱም ቡድን ተማሪዎች መካከል በቅድመትምህርት ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም ከሁለቱ ክፍሎች ውስጥ በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድን ውስጥ ታቅፈው የሚጠኑትን ለመለየት የቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም በ9ኛ C ክፍል ውስጥ ያሉት በሙከራ ቡድን፣ በ9ኛ B ክፍል ያሉት ተማሪዎች ደግሞ በቁጥጥር ቡድኑ ውስጥ እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በሙከራና በቁጥጥር ቡድን የሚታቀፉት ከተለዩ በኋላ የካቲት 19 ቀን 2009 ዓ.ም. ከ3፡00-4፡20 የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብቻ ቅድመትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል፡፡ እንዲሁም ከሙከራ ቡድን የተሰበሰበው የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቁ ምላሽ ተደራጅቶ ለትንተና ዝግጁ ሆኖ ተቀምጧል፡፡

ከዚያም ለጥናቱ ለተመረጡት የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት የቃላት መማር ብልሃቶችን ስልጠና በሙከራ ቡድኑ ክፍል ውስጥ ለመተግበር ለአምስት ቀናት (ከየካቲት 21- 22፣ 24-26 ቀን 2009 ዓ.ም.) በቀን ለሁለት ሰዓት ስለቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ለጥናቱ ስለተመረጠው ቅደምተከተላዊ ማሕቀፍ (ሞድል)ና የስልጠናው አተገባበር በአጭሂዋ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናው ወቅትም ከመምህሯ ለተነሱ ጥያቄዎች አስፈላጊ ምላሾች ተሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ስልጠና በተጨማሪም መምህርቷ በ2008 ዓ.ም. የሙከራ ጥናቱ በተሰራበት ጊዜ በአጥኝዋ የተዘጋጀውን አዲስ የመማሪያ ማንዋል መሰረት እድርገው በስድስት ሳምንታት ለ12 ክፍለጊዜያት ባስተማሩበት ወቅት ተግባራዊ ተሞክሮ አግኝተዋል፡፡ በዚህ የሙከራ ጥናቱ የማስተማር ሂደትም መምህርቷ ትምህርቱን ካቀረቡ በኋላ ከአጥኚዋ ጋር በተደረጉ የክፍል ውጪ ውይይቶች በሂደቱ የታዩ አንዳንድ የማስተማር ግንዘቤ ችግሮች ተቀርፈዋል፡፡

ስለዚህም ስልጠናው፣ የማስተማር ተግባራዊ ተሞክሮውና ድህረማስተማር ውይይቶቹ ተደማምረው መምህርቷ ስለመማሪያ መሳሪያው አቀራረብ ከዋናው ጥናት መካሄድ በፊት በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ አስችለዋል፡፡ ይህም በአዲሱ አቀራረብና ቀድመው በለመዱት አቀራረብ መካከል ያላቸውን የልምድ ልዩነት ስለሚያጠበው በጥናቱ ውስጣዊ ትክክለኛነት የሚኖረውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ይረዳል፡፡ ከዚህም ባለፈ በናሙና ጥናቱም ሆነ በዋናው ጥናት ወቅት በተሰጠው ስልጠና ለመምህሯ ስለምርምሩ ግንዛቤ በመፍጠር አዲሱ የአቀራረብ መንገድ ቀደምሲል ሲያስተምሩበት ከነበረው የተለመደው አቀራረባቸው ጋር ያለውን ልዩነት እንዲያጤኑትና ለየቡድኖቹ ለይተው እንዲተገብሩ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ የትኛው አቀራረብ ውጤታማ እንደሆነ የሚታወቀው በጥናቱ መጨረሻ መሆኑን ለመምህሯ በግልጽ በማሳመን አንዱን ከሌላው አበላልጠው ሳይመለከቱ ሁለቱንም በታቀደላቸው መንገድ እንዲተገብሩ የማስገንዘብ ስራ ተሰርቷል፡፡

ጥናቱን ለሚተገብሩት መምህርት የተሰጠው ስልጠና በናሙና ጥናቱ ከተሰጠው አራት ሰዓት ተኩል ወደ አስር ሰዓት ከፍ እንዲል የተደረገው የብልሃቶቹን የስልጠና አተገባበር በተገቢው ሁኔታ ተገንዝበው መተግበር ይችሉ ዘንድ ረዘም

ላለ ጊዜ ስልጠና መስጠትና ሞዴል ሆኖ የማሳየት ተግባር እንደሚያስፈልግ ከሙከራ ጥናቱ ከተገኘው ተመክሮ በመነሳት ነው፡፡ የሙከራው ቡድን ማሰልጠኛ መሳሪያ የተዘጋጀው አጥኚዋ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን አስመልክቶ በክለሳ ድርሳኑ ውስጥ ከዘረዘረቻቸው ይዘቶች በመነሳትና ርእሰ ነገሩን አስመልክቶ የመስኩ ታዋቂ ምሁራን የጻፏቸውን ጽሁፎች መሰረት በማድረግ ነው (አባሪ ቀ ይመልከቱ)፡፡

በማስከተል የካቲት 27 ቀን 2009 ዓ.ም. በተከታታይ ለሁለት ክፍለ ጊዜያት (ከ2፡00-3፡20) በስልጠናው ስለተካተቱ የቃላት መማር ብልሃቶች ምንነትና አጠቃቀም ለተማሪዎች በአጥኚዋ ሰፊ ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ በመቀጠል አጥኚዋ እንዲያስተምሩ ለተመደቡት መምህርትና ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶቹን አጠቃቀም ከትውስታ ብልሃት (መቦደን) ከሚለው በመጀመር የካቲት 29 ቀን 2009 ዓ.ም. ለሶስት ሰዓት የብልሃቶቹን አጠቃቀም ሞዴል በመሆን በተግባር አሳይታለች፡፡ ሂደቱን (አባሪ ቀ ይመልከቱ)፡፡

በጥናቱ የማስተማር ትግበራ ወቅትም በቃላት መማር ብልሃቶች ቃላትን ለተማረው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብልሃቶቹን ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት በሙያዊ እገዛ (Scaffolding) መርህ በግልጽ ለማሰልጠን ሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞድል ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሞዴል መሰረትም ብልሃቶቹን በቀጥታ መግለጽ፣ ብልሃቶቹ በቃላት ትምህርት ሂደት ያላቸውን አጠቃቀም በመምህር ምሪት (ሞዴሊንግ) ማሳየት፣ ተማሪዎችን በስፋት በመደገፍ መምህሯና ተማሪዎች ብልሃቶቹን በመጠቀም የቃላት ተግባራት በጋራ እየሰሩ ብልሃቶቹን ማስለየት፣ ተማሪዎች በራሳቸው ብልሃቶቹን የሚለዩበትን ሃላፊነት በማስፋት መጠነኛ ድጋፍ ማድረግና ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ብልሃቶቹን የሚለዩበት ተጨማሪ የልምምድ እድል መፍጠርና ብልሃቶቹን መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው ብሎም በአጠቃቀም ሂደት የገጠማቸውን ችግሮች እንዴት እንደፈቱ ጽብረቃ ማድረግንና ብልሃቶቹን ወደ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ ራሳቸውን ችለው እንዲተገብሩ ማበረታታትንና ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በቅደም ተከተል አካቷል፡፡

የብልሃት ስልጠና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየገጠሙት ያሉትን ሙያዊ ትችቶች ለማስወገድም ዋናው ጉዳይ ብልሃቶቹን መቼ፣ ለምንና እንዴት መተግበር እንደሚቻል በግልጽ ማስረዳት ነው፡፡ በመሆኑም የቃላት መማር ብልሃቶቹን አጠቃቀም ግንዛቤ ለመፍጠር ተማሪዎቹ የብልሃቶቹን ስያሜ፣ ፍይዳና አጠቃቀም የሚለዩበት ገላጭ ደረጃ (declarative)፣ የብልሃቶቹን አጠቃቀም ደረጃ (procedural) እና ብልሃቶቹን ለምን፣ እንዴትና መቼ እንደሚጠቀሙ የሚያስረዱበት ጽብረቃዊ ደረጃ (conditional) ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ ቀደም ሲል ሲማሩበት በነበረው በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ (በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ) መሰረት፤ ምንም አይነት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ሳይወስዱ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተመሳሳይ የቃላት ትምህርት ከየካቲት 17 እስከ ሰኔ 3 ቀን 2009 ዓ.ም. ለአስራ አራት ሳምንታት (ለ28 ክፍለ ጊዜያት፤በሳምንት ሁለት ክፍለጊዜ፤ አንድ ክፍለጊዜ 40 ደቂቃ) ሁለቱም ቡድኖች ተምረዋል፡፡ በዚህ በተለመደው አቀራረብ ተማሪዎች የሚሰሯቸው ተግባራት የቃላቶቹን ፍቺ ማወቅ አለማወቃቸውን የሚፈትኑ እንጂ የቃላቶቹን ፍቺ እንዴት መረዳት እንዳለባቸው ብልሃቶችን የሚተዋወቁባቸው አይደሉም፡፡ በአብዛኛው የመምህሯ ድርሻም የቃላቱን ፍቺ በትክክል መረዳት አለመረዳታቸውን መገምገምና እውቀትን ማስተላለፍ እንጂ የቃላቱን ፍቺ እንዴት እንደሚረዱ በተለይም የቃላት መማር ብልሃቶችን ተጠቅሞ የቃላት ትምህርት እንዴት እንደሚከወን አያስረዱም፡፡

ሁለቱ ቡድኖች የቃላት ተግባራትን ብቻ በተጠቀሱት ሁለት አቀራረቦች ተለያይተው ከመማራቸው ውጪ እንደመጻፍ፣ ማንበብ፣ ማዳመጥ፣ መናገርና ሌሎች ለክፍል ደረጃው የሚሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ግን በተመሳሳይ ዘዴዎች ያለምንም ማለያየት ሲማሩ ቆይተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ከመማርና ካለመማር ውጭ ለሁለቱም ቡድኖች በመምህርቷ የሚደረጉ ትምህርታዊ ድጋፎች አቻነት እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህም በጥናቱ ውስጣዊ ትክክለኛነት ተጽዕኖ የሚያሳድረውን የድጋፍ አቻነት ተዛቦት መቀነስ ያስችላል፡፡ ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ መምህራን ቢማሩ አንዱ ከሌላው የበለጠ ወይም ያነሰ የማስተማር ልምድ፣ ብቃት፣ ፍላጎት ፣ ተነሳሽነት፣ የማስተማር

ዘዴ አተገባበር ወዘተ ያለው በመሆኑ ብቻ በቡድኖቹ ውጤት ላይ ልዩነት እንዳይፈጥር በማሰብ ጥናቱ እስኪጠናቀቅም ሁለቱ ቡድኖች በአንዲት የዘጠኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ተምረዋል።

በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች ሰኔ 4 ቀን 2009 ዓ.ም. ከ8፡00-9፡00 ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል። በማስከተል የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ብቻ ከ9፡30-10፡30 ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ሞልተዋል።

3.7. የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ተማሪዎች ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ችሎታቸው ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ለማወቅ የቃላት ፈተና ተፈትነዋል። እንዲሁም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል። ነገር ግን፣ በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት የሆኑት ተማሪዎች ውጤት ለትንታኔው ስለማያስፈልግ እንዲወገድ ተደርጓል። ከዚያም የጥናቱ ተሳታፊ ሁለት ቡድኖች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት ያላቸውን የቃላት ችሎታ አቻነት ለማወቅ የተፈተኑት ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ለየቡድኖቹ በገላጭ ስታትስቲክስ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል። በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትኗል። ትምህርቱ እንደተጠናቀቀ ሁለቱ ቡድኖች የተፈተኑት ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤትም ለየቡድኖቹ በገላጭ ስታትስቲክስ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል።

በቁጥር ቡድኑና በሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶቻቸው መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥም በነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትነዋል።

ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቡድኖች ንጽጽር ባለው ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ስልት የሚመሰረቱ ቡድኖች ፍጹም ከምርጫ መዛባት (selection bias) ነጻ ሊሆኑ ስለማይችሉ የሚገኘው ውጤት በጥንቃቄ መተርጎም አለበት። ይኸውም የሁለቱን ቡድኖች ድህረትምህርት ውጤቶች ልዩነት በማየት ውጤቱን መተርጎም በቂ አይሆንም። ምክንያቱም የልዩነቱ መነሻ ከተሳታፊዎች የባህርይ ልዩነት ይሁን ካለፉበት የልምምድ ሁኔታ ልዩነት የተገኘ መሆኑን መወሰን ያስቸግራል። ስለዚህም የእያንዳንዱን ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ውጤቶች ልዩነት በማወዳደር የውጤት ትርጓሜውን መስጠት ተገቢ ይሆናል። ለዚህም በእያንዳንዱ ቡድን በቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን ለማነጻጸር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Paired-samples t-test) ተተንትኗል።

የሙከራው ቡድን የብልሃት አጠቃቀማቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለመለካት በቅድመ ትምህርትና በድህረትምህርት ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ውጤት በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት (Paired-samples t-test) ተተንትኗል። እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከጸታቸው አንጻር በድህረትምህርት የቃላት ውጤታቸው ጉልህ ልዩነት አሳይተው እንደሆነ (ስልጠናው ከጸታ አንጻር በቃላት ውጤት ልዩነት መፍጠርአለምፍጠሩን) ለመፈተሽ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (independent samples t-test) ተተንትኗል።

በጥናቱ በሁለቱም ቲ-ቴስቶች (independent samples t-test እና Paired-samples t-test) የተገኘውን የውጤት ልዩነት ጥንካሬ (Effect size) ለማረጋገጥም፣ የኮኸንስ ዲ (Cohen's d) የልዩነት ጥንካሬ መጠን አመልካች ቀመር አገልግሎት ላይ ውሏል። እንደ Muijs (2004፣139) አገላለጽ በኮኸንስ ዲ (Cohen's d) የተገኘው ውጤት የልዩነት ጥንካሬ መጠንም፣ ከ 0-0.20 ሲሆን ደካማ (weak)፣ ከ0.21-0.50 ሲሆን መጠነኛ (modest)፣ ከ 0.51-1.00 ሲሆን መካከለኛ (moderate) እንዲሁም ከ 1.00 ሲበልጥ ጠንካራ ውጤት (strong effect) ይኖረዋል። በዚህ መሰረት ከአልፋ 0.05 ያነሱ ውጤቶች በተገኙባቸው ሠንጠረገሮች፣ የተመዘገበው ጉልህ ልዩነት ምን

ያህል ጠንካራ መሆኑን ለመፈተሽ በኮኸንስ ዲ የልዩነት ጥንካሬ መጠን አመልካች ቀመር መስፈርቶች መሰረት ትንተናው ተሰርቷል።

በኮኸንስ ዲ የተገኙ ውጤቶችም፣ በ Muijs (2004) በተገለጹት አራት ደረጃዎች ውስጥ ገብተው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። በመጨረሻም ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት አጠቃላይ የብልሃት አጠቃቀም ውጤት ከድህረትምህርት የቃላት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መለኪያ (Pearson product-moment correlation) ስታትስቲክስ ተተንትኗል። በእያንዳንዱ ስታትስቲክሳዊ ቴስት ትንተናው የተካሄደውም እንደየ ባህሪው እሙኖቹ (Assumptions) መሟላታቸው ቀድሞ ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ሁሉም መረጃዎች የተተነተኑትም ኤስ ፒ ኤስ ኤስ ቨርዥን 21. (SPSS V21.0) በመጠቀም ነው።

3.8 ከናሙና ጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች

አንደኛ፣ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ በአግባቡ ለመፈተሽ የሰልጠናውን ወይም የልምምዱን ጊዜ ከ12 ክፍለ ጊዜ ወደ 28 ክፍለ ጊዜ ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ተችሏል።

ሁለተኛ፣ ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተናውን ለመስራት የተመደበው ሁለት ሰዓት ስለበዛ ወደ አንድ ሰዓት ተኩል ዝቅ ማለት እንዳለበት ልምድ ተገኝቷል። በአንጻሩ ቅድመ ትምህርትና ድህረትምህርት የጽሑፍ መጠይቁን ለመሙላት የተመደበው 40 ደቂቃ በቂ ሆኖ ስላልተገኘ ሃያ ደቂቃ መጨመር እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ተችሏል።

ሦስተኛ፣ በባዶ ቦታ እንዲሞሉ (አንቀጹን እንዲያሟሉ) የቀረበው ጥያቄ ትዕዛዙ የግልጽነት ችግር ስለተገኘበት እንደገና መስተካከል እንዳለበት መገንዘብ ተችሏል።

አራተኛ፣ በትርጉም ልዩ የሆነውን ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ /ብ፣ በሚለው ትዕዛዝ ስር ከቀረቡት ጥያቄዎች ጥያቄ 3 አማራጮቹ አሻሚ መልስ የያዙ ሆነው ስለተገኙ በጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ዘንድ መደነጋገር ስለነበረ እንደገና ተስተካክለው መቅረብ እንዳለባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

አምስተኛ፣ የሙከራ ጥናቱን የምትተገብረው መምህርት የቃላት መማር ብልሃቶችን የስልጠና አተገባበር በተገቢው ሁኔታ ተገንዝባ መተግበር ትችል ዘንድ ጥልቅና ሰፊ ስልጠና በመስጠት በቂና ተገቢ የሆነ ሞዴል ሆኖ የማሳየት ተግባር እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ስድስተኛ፣ ብልሃቶቹ ካላቸው ውስብስብ ባህሪና ከጊዜ አንጻር በርካታ ብልሃቶችን በአንድ ጊዜ ማቅረቡ የእያንዳንዱን ብልሃት ጠቀሜታና አተገባበር በአግባቡ እንዲረዱ ከእያንዳንዱ ስድስት ዋናዋና የቃላት መማር ብልሃቶች ምድብ ማለትም (ከትውስታ፣ አእምሯዊ፣ ልዕለ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ፣ አካላዊና ከስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች) ውስጥ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢ የሆኑትን መርጦ ማሰልጠን ተገቢ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረትም በሙከራ ጥናቱ ከቀረቡት 17 ዝርዝር ብልሃቶች አምስት በመቀነስ ለዋናው ጥናት አስራ ሁለት ብልሃቶች ብቻ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህን ተመክሮዎች በአግባቡ አጢኖ በዋናው ጥናት በመተግበር ጥናቱ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ሊከናውን እንደሚችል ተመክሮ ተገኝቶበታል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ተመክሮዎች በዋናው ጥናት ላይ በአግባቡ ለመተግበር መከናወን ያለባቸው ቅድመተግባራት ከወዲሁ ዝግጅት ሊደረግባቸው እንደሚገባ ልምድ ተገኝቶበታል፡፡ በዚህም መሰረት በዋናው ጥናት ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

ምዕራፍ አራት
የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

4.1 የጥናቱ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለመለካት ዋነኛ መሳሪያ የሆኑት የቃላት ፈተናዎች አማካይ ውጤቶች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (independent samples t-test)፣ በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት (paired samples t-test)ና የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶች ደግሞ በዳግም ልኬታ ናሙናዎች (paired samples t-test) ተተንትነው ቀርበዋል። የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከጸታ አንጻር በድህረትምህርት በቃላት ውጤታቸው ልዩነት አሳይተው እንደሆነ ለመፈተሽ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኖ ቀርቧል። እንዲሁም በድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ውጤትና በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መጠን መለኪያ ተተንትኗል። በተጨማሪም በእያንዳንዱ ስታትስቲክሳዊ ቴስት ፍተሻ የተካሄደው እንደየ ባህሪያቸው እሙኖቹ መሟላታቸው ቀድሞ ከተረጋገጠ በኋላ ነው።

4.1.1 የጥናቱ የውጤት ትንተና

የመጀመሪያው የትንተናው ክፍል ያተኮረው ቅድመትምህርት ወይም ለጥናቱ የተመረጡት የሁለት ቡድኖች ተማሪዎች በተለያዩ ዘዴዎች ቃላትን ከመማራቸው በፊት በቃላት እውቀታቸው መሰረታዊ ልዩነት ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን በመፈተሽ ላይ ነው። በዚህ መሰረት መረጃው በገላጭ እና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ (inferential statitics) ተተንትኗል፤ ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.1 እና 4.2 እንደሚከተለው ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 4.1፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

ቡድን	የናሙና ብዛት (n)	አማካይ ውጤት (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std. Error Mean)
የሙከራ	38	13.24	1.71	.278
የቁጥጥር	35	13.06	2.46	.416

ሠንጠረዥ 4.1 የቁጥጥሩንና የሙከራውን ቡድኖች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሰንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.24) ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.06) በ0.18 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡

እንዲሁም የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.46) ከሙከራው ቡድን ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (1.71) በ0.75 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ የሚዋዥቅ ሳይሆን የወጥነት ባህሪ የሚታይበት ወይም ተቀራራቢ ነው፡፡

በትንተናው መሰረት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.18 እንደበለጠ ተረጋግጧል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም

ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

ሠንጠረዥ 4.2፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ቡድን	ናሙና (n)	አማካይ (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
የሙከራ	38	13.24	1.71	71	.364	.717
የቁጥጥር	35	13.06	2.46			

ሠንጠረዥ 4.2 በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድኖች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱም ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ (t= .364, df= 71, p= .717) አሳይቷል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች ከመማራቸው በፊት በቃላት እውቀታቸው መሰረታዊ ልዩነት እንደሌላቸው ያሳያል፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የቃላት እውቀት ልዩነት ይኖራል?» የሚል ሲሆን፣ መላምቱ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የቃላት እውቀት ልዩነት አይኖርም» የሚል ነበር፡፡ ጥያቄውን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.3 እና 4.4 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.3፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

ቡድን	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (Mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std.Error Mean)
የሙከራ	38	16.63	3.00	.488
የቁጥጥር	35	13.60	2.77	.470

ሠንጠረዥ 4.3 የቁጥጥሩንና የሙከራውን ቡድኖች የድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (16.63) ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.60) በ3.03 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት በ0.23 በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሁለቱም ቡድኖች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ወይም የማይዋዥቅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ትንተናው የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በ3.03 እንደበለጠ አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 4.4 እንደተመለከተው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4፡- የቁጥጥሩና የሙከራው ቡድኖች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ቡድን	ናሙና (n)	አማካይ (Mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
የሙከራ	38	16.63	3.00	71	4.462	.000*
የቁጥጥር	35	13.60	2.77			

*p<0.05

ሠንጠረዥ 4.4 በቁጥጥሩና በሙከራው ቡድኖች የድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 4.462, df =71, p= .000) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የቃላት እውቀት ጉልህ ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ በበለጠ ሁኔታ የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማዳበር የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ ተሰልቶ 1.04 (Cohen's d = 1.04) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ «መካከለኛ» (Moderate) መሆኑን ያሳያል፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የቃላት እውቀት ልዩነት ይኖራል?» የሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ አወንታዊ መልስ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የቃላት እውቀት ልዩነት አይኖርም» የሚለው አልቦ መላምት ውድቅ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ

ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የቃላት እውቀት ልዩነት አለ» የሚለው ተለዋጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ከድህረትምህርቱ የቃላት ፈተና በተገኘው ውጤት መሰረት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የቃላት እውቀታቸው ለውጥ አሳይቷል፤ በፈተና የተገኘውን ውጤት ተገቢነት ለማረጋገጥም በጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው ውጤት ጋር ተነጻጽሯል፡፡ በዚሁ መሰረት ከድህረትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ በተገኘ ውጤት መሰረት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ብልሃቶቹን በክፍል ውስጥ በግልጽ ከተማሩ በኋላ አጠቃቀማቸው ለውጥ አሳይቷል፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ የተማሯቸው ብልሃቶች የድህረትምህርት ፈተና ውጤታቸው ከቅድመ ትምህርቱ ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዲኖረው አወንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህም የተማሪዎች የቃላት እውቀታቸው መሻሻል በርግጥም በክፍል ውስጥ የተማሯቸውን ብልሃቶች በመጠቀማቸው ምክንያት መሆኑን አመላክቷል፡፡

ይህንንም ይበልጥ ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ቡድን በቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ያስመዘገበውን የቃላት ፈተና ውጤት በማነጻጸር መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የሙከራ ቡድኑ በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤቶች መካከል ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 4.5 እና 4.6 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.5:- የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (Mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std.Error Mean)
ቅድመትምህርት	38	13.24	1.71	.278
ድህረትምህርት	38	16.63	3.00	.488

ሠንጠረዥ 4.5 የሙከራውን ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (16.63) ከቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.24) በ3.42 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (3.00) ከቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (1.71) በ1.29 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ርቀት ሲታይ መጠነኛ ልዩነት ያለው ቢሆንም የሚዋዥቅ ሳይሆን የወጥነት ባህሪ የሚታይበት ወይም ተቀራራቢ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በ3.39 እንደበለጠ ውጤቱ አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 4.6 እንደተመለከተው የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.6፡- የሙከራው ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ፈተና	ናሙና (n)	አማካይ (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
ቅድመትምህርት	38	13.24	1.71	37	7.385	.000*
ድህረትምህርት	38	16.63	3.00			

*p<0.05

ሠንጠረዥ 4.6 የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 7.385, df= 37, p= .000) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ከተማሩ በኋላ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው የቃላት ችሎታ የበለጠ መሻሻል ማሳየታቸውን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ስልጠናው/ የማስተማሪያ ዘዴው የቃላት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ረድቷቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደምሲል የሙከራው ቡድን ከቁጥጥር ቡድኑ የበለጠ ውጤት ማስመዝገቡን የሚያሳየውን በነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት የተገኘውን ውጤት ያረጋግጣል፡፡ በዚህም መሰረት የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ ተሰልቶ 1.43 (Cohen's d = 1.43) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ «ጠንካራ» (Strong) መሆኑን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ በቁጥጥር ቡድኑ በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤቶች መካከል ልዩነት ስለመኖሩ የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር በማድረግ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 4.7 እና 4.8 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.7፡- የቁጥጥሩ ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (Mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std.Error Mean)
ቅድመትምህርት	35	13.06	2.46	.416
ድህረትምህርት	35	13.60	2.77	.470

ሠንጠረዥ 4.7 የቁጥጥር ቡድኑን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.60) ከቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.06) በ0.54 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የድህረትምህርቱ የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.77) ከቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.46) በ0.31 በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ይሁን እንጂ ከትምህርቱ በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ወይም የማይዋዥቅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ትንተናው የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.54 እንደበለጠ ለማሳየት አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 4.8 እንደተመለከተው የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.8፡- የቁጥጥሩ ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ፈተና	ናሙና (n)	አማካይ (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
ቅድመትምህርት	35	13.06	2.46	34	1.764	.087
ድህረትምህርት	35	13.60	2.77			

ሠንጠረዥ 4.8 በቁጥጥር ቡድኑ በቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ (t= 1.764, df = 34, p= .087) አሳይቷል፡፡ ከዚህም የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ቃላትን ከተማሩ በኋላ በቃላት ችሎታቸው ጉልህ ለውጥ እንዳላመጡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ቀደምሲል በነጻ ናሙናዎች ቲ- ቴስት የተገኘው ውጤት የሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ እንደበለጠ የሚያሳውን ያረጋግጣል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት ያሳያል?» የሚል ሲሆን መላምቱ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት አያሳይም» የሚል ነበር፡፡ ጥያቄውን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፤ ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.9 እና 4.10 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.9፡- የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ጥቅል የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቆቹ አማካይ ውጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

	ናሙና	አማካይ ውጤት (Mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት
ቅድመትምህርት	38	39.82	8.23	1.33
ድህረትምህርት	38	45.42	6.30	1.02

ሠንጠረዥ 4.9 የሙከራውን ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም የድህረትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት (45.42) ከቅድመትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (39.81) በ 5.60 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (8.23) ከቅድመትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (6.30) በ1.93 በልጦ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ከትምህርቱ በኋላ የተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት እየጠበበ መሄዱን ያሳያል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት በ5.60 እንደበለጠ ውጤቱ አሳይቷል፡፡

በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠዥ 4.10 እንደተመለከተው የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.10፡- የሙከራው ቡድን ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ጥቅል የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቆቹ አማካይ ውጤት ልዩነት በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

የጽሑፍ መጠይቅ	ናሙና (n)	አማካይ (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
ቅድመትምህርት	38	39.82	8.23	37	3.366	.002*
ድህረትምህርት	38	45.42	6.30			

*p<0.05

ሠንጠረዥ 4.10 በሙከራ ቡድኑ የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 3.366, df= 37, p= .002) አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ከተማሩ በኋላ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታቸው ጉልህ ልዩነት ማሳየቱን ነው፡፡ ከዚህም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ ተሰልቶ 0.77 (Cohen's d = 0.77) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ «መካከለኛ» (moderate) መሆኑን ያሳያል፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት

ያሳያል?» የሚለው ጥያቄ አወንታዊ መልስ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም«ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከትምህርቱ በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት አያሳይም» የሚለው አልቦ መላምት ውድቅ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት ያሳያል» የሚለው ተለዋጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.9 እና 4.10 የሙከራውን ቡድን የቅድመትምህርትና ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ ጥቅል አማካይ ውጤት የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ በቃላት መማር ብልሃት የጽሑፍ መጠይቆቹ የተካተቱት የቃላት መማር ብልሃቶች ምድብ (የትውስታ፣ አካካሽ፣ አእምሯዊ፣ ልዕለ አእምሯዊ፣ ማህበራዊና ስሜትነኪ የቁጥጥር ብልሃቶች) ደግሞ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የተገኙት አማካይ ውጤቶች ልዩነት እንዳላቸው በሚከተሉት ሠንጠረገሮች (በሠንጠረዥ 4.11 እና በሠንጠረዥ 4.12) ተገልጸዋል፡፡

ሠንጠረዥ 4.11፡- የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

የቃላት መማር ብልሃቶች ምድብ	የጽሑፍ መጠይቅ	የናሙና ብዛት	አማካይ ውጤት	መደበኛ ልይይት	መደበኛ የአማካይ ስህተት
የትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀም	ቅድመትምህርት	38	7.00	1.92	.3200
	ድህረትምህርት	38	7.55	1.97	.31260
የአካካሽ ብልሃቶች አጠቃቀም	ቅድመትምህርት	38	2..89	1.22	.19882
	ድህረትምህርት	38	3.86	.81	.13158
የአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም	ቅድመትምህርት	38	12.31	2.89	.54539
	ድህረትምህርት	38	14.89	3.36	.46924
የልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች	ቅድመትምህርት	38	6.36	1.77	.29798
	ድህረትምህርት	38	7.65	1.83	.28792

አጠቃቀም					
የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም	ቅድመትምህርት	38	5.47	1.82	.36124
	ድህረትምህርት	38	7.73	2.22	.29622
የስሜትነኪ ቁጥጥር ብልሃት አጠቃቀም	ቅድመትምህርት	38	2.81	1.22	.19906
	ድህረትምህርት	38	3.65	1.25	.20407

ሠንጠረዥ 4.11 የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም የድህረትምህርቱ የትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት (7.55) ከቅድመትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (7.00) በ0.55 በልጦ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም የተማሪዎቹ ውጤት ከአማካይ ውጤቱ ያለው ልዩነት ሲታይ የድህረትምህርቱ የትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (1.97) ከቅድመትምህርቱ የትውስታ ብልሃት አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መደበኛ ልይይት (1.92) በ0.05 ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች ድህረትምህርት የትውስታ ብልሃት አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ወይም የማይዋዥቅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የድህረትምህርቱ የአካካሽ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (3.86) ከቅድመትምህርቱ አማካይ ውጤት (2.89) በ0.97 በልጦ ታይቷል፡፡ እንዲሁም ድህረትምህርቱ የአካካሽ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (.81) ከቅድመትምህርቱ የአካካሽ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (1.22) በ0.41 አንሶ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎቹ ድህረትምህርት የአካካሽ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የድህረትምህርቱ የአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (14.89) ከቅድመትምህርቱ የአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት (12.31) በ2.57 በልጦ ተስተውሏል። እንደሁም የድህረትምህርቱ የአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (3.36) ከቅድመትምህርቱ መደበኛ ልይይት (2.89) በ0.47 በልጦ ልዩነት አሳይቷል። ይሁን እንጂ ከትምህርቱ በኋላ የተማሪዎች የአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል።

ሠንጠረዥ 4.11 እንደሚያሳየው የድህረትምህርቱ የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (7.65) ከቅድመትምህርቱ የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት (6.36) በ1.28 በልጦ ተስተውሏል። የድህረትምህርቱ የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (1.83) ከቅድመትምህርቱ የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም መደበኛ ልይይት (1.77) 0.06 ልዩነት አሳይቷል። ይሁን እንጂ ከትምህርቱ በኋላ የተማሪዎቹ የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ወይም የማይዋዥቅ መሆኑን ያመለክታል።

እንዲሁም የድህረትምህርቱ የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት (7.73) ከቅድመ ትምህርቱ የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት (5.47) በ2.26 በልጦ ተስተውሏል።

እንዲሁም የድህረትምህርቱ የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (2.22) ከቅድመትምህርቱ የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም መደበኛ ልይይት (1.82) በ0.4 ልዩነት አሳይቷል። ይሁን እንጂ ከትምህርቱ በኋላ የተማሪዎቹ የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያሳያል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በሠንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የድህረትምህርቱ የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት

(3.65) ከቅድመትምህርቱ አማካይ ውጤት (2.81) በ0.84 በልጦ ተስተውሏል፡፡ የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃት አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (1.25) ከቅድመትምህርቱ የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃት የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት (1.22) በ0.03 ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ከትምህርቱ በኋላ የተማሪዎቹ የስሜትነኪ ቁጥጥር ብልሃት አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከአማካዩ ያለው ርቀት ተቀራራቢ ወይም የማይዋዥቅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከላይ በሠንጠረዥ 4.11 ከሰፈረው መረጃ የሙከራው ቡድን ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች የጽሑፍ መጠይቆቹ አማካይ ውጤቶች ከቅድመትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች አማካይ ውጤቶች ልዩነት ያላቸው መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.12 እንደተመለከተው የዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.12፡- የሙከራው ቡድን የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች	የጽሑፍ መጠይቅ	አማካይ ውጤት (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2 tailed)
የትወስታ ብልሃቶች	ቅድመትምህርት	7.00	1.97	37	1.345	.187
	ድህረትምህርት	7.55	1.92			
አካካሽ ብልሃቶች	ቅድመትምህርት	2..89	1.22	37	4.274	.000*
	ድህረትምህርት	3.86	.811			
አእምሯዊ	ቅድመትምህርት	12.31	3.21			

ብልሃቶች	ድህረትምህርት	14.89	3.87	37	3.837	.000*
ልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች	ቅድመትምህርት	6.36	1.83	37	3.421	.002*
	ድህረትምህርት	7.65	1.77			
ማህበራዊ ብልሃቶች	ቅድመትምህርት	5.47	2.22	37	5.290	.000*
	ድህረትምህርት	7.73	1.82			
ስሜትነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች	ቅድመትምህርት	2.81	1.22	37	3.081	.004*
	ድህረትምህርት	3.65	1.25			

*p<0.05

ሠንጠረዥ 4.12 የሙከራውን ቡድን የቅድመትምህርትና የድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃት ምድቦች የጽሑፍ መጠይቁቹን አማካይ ውጤቶች ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል። በዚህም መሰረት የትውስታ ብልሃቶችን በተመለከተ መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ (t=1.345, df= 37, p= .187) አሳይቷል። ይህም ተማሪዎች ስልጠና ቢሰጣቸውም የትውስታ ብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ለውጥ አለመታየቱን ያሳያል።

የአካካሽ ብልሃቶችን አጠቃቀም በተመለከተ መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ ተማሪዎች ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላበቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የአካካሽ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 4.274 df= 37, p= 0.000) አሳይቷል። ይህም ከስልጠናው በኋላ ተማሪዎች የአካካሽ ብልሃት አጠቃቀማቸው ከፍተኛ ለውጥ ማሳየቱን ያመለክታል። የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ 0.95 (Cohen's d= 0.95) ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ «መካከለኛ» (moderate) መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶችን አጠቃቀም በተመለከተም መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 3.421, df= 37, p= 0.002) አሳይቷል። ይህም ከስልጠናው በኋላ ተማሪዎች በልዕለአእምሯዊ ብልሃቶች አጠቃቀማቸው ላይ ጉልህ ለውጥ ማምጣታቸውን ያሳያል። የጉልህ ልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ 0.71 (Cohen's d = 0.71) ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ «መካከለኛ» (moderate) መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ረገድም መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 5.290, df, 37, p= 0.000) አሳይቷል። ይህም ከስልጠናው በኋላ የተማሪዎች የማህበራዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ጉልህ ለውጥ ማምጣቱን ያመለክታል። የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ 1.11 (Cohen's d = 1.11) ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ « ጠንካራ» መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶችን አጠቃቀም አስመልክቶም መረጃው በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በቅድመትምህርቱና በድህረትምህርቱ የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች አጠቃቀም የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 3.081, df, 37, p= 0.004) አሳይቷል። ከዚህም ከስልጠናው በኋላ ተማሪዎች የስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃት አጠቃቀማቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ማሻሻላቸውን መረዳት ይቻላል። የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ 0.67 (Cohen's d = 0.67) ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም «መካከለኛ» መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ከድህረትምህርቱ የቃላት ፈተና በተገኘው ውጤት መሰረት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የቃላት ችሎታቸው ተሻሽሏል፤ በፈተና የተገኘውን ውጤት ተገቢነት ለማረጋገጥም በጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው ውጤት ጋር ተነጻጽሯል። በዚሁ መሰረት ከድህረትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ

በተገኘ ውጤት መሰረት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ብልሃቶቹን በክፍል ውስጥ በግልጽ ከተማሩ በኋላ ቃላትን ለመማር በክፍል ውስጥ የተማሯቸውን ብልሃቶች አጠቃቀማቸው ተሻሽሏል። ይህም በክፍል ውስጥ የተማሯቸው ብልሃቶች የድህረትምህርት ፈተና ውጤታቸው ከቅድመትምህርቱ ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት እንዲኖረው አወንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው በግልጽ ያሳያል። ይህም የተማሪዎች የቃላት ችሎታ መሻሻል በርግጥም በክፍል ውስጥ የተማሯቸውን ብልሃቶች በመጠቀማቸው ምክንያት መሆኑን ያመለክታል።

ሦስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ « ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነላ የቃላት እውቀት ልዩነት አለ? » የሚል ሲሆን፣ መላምቱ «ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነላ የቃላት እውቀት ልዩነት የለም» የሚል ነበር። ጥያቄውን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኗል። የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማወቅም በቅድሚያ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ሴቶችና ወንዶች በቅድመትምህርት የቃላት ውጤታቸው ልዩነት ይታይባቸው እንደሆነ ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ የአማካዮቹ ንጽጽር በሠንጠረዥ 4.13 እና 4.14 የቀረበው ውጤት ተገኝቷል።

ሠንጠረዥ 4.13፡- የሙከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

ፈተና	ጾታ	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std. Error Mean)
ቅድመትምህርት	ሴት	23	13.87	1.53	.396
	ወንድ	15	12.27	1.54	.322

ሠንጠረዥ 4.13 የሙከራውን ቡድን የሴትና የወንድ ተማሪዎች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል። በሠንጠረዡ

ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሴት ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (13.87) ከወንድ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (12.27) በ1.6 በልጦ ተስተውሏል፡፡ እንዲሁም የወንድ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (1.54) ከሴት ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (1.53) በ0.01 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ይህም የሁለቱም ጸታዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቶቹ ያለው ርቀት ሲታይ የሚዋዥቅ ሳይሆን የወጥነት ባህሪ የሚታይበት ወይም ተቀራራቢ መሆኑን ያሳያል፡፡

በትንተናው መሰረት የሙከራ ቡድኑ የሴት ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በ1.6 እንደበለጠ ተረጋግጧል፡፡ በሁለቱ ጸታዎች አማካይ ውጤቶች መካከል ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.14 እንደተመለከተው የነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.14፡- የሙከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ፈተና	ጸታ	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
ቅድመት ምህርት	ሴት	23	13.87	1.534	36	3.133	.003*
	ወንድ	15	12.27	1.546			

*p<0.05

ሠንጠረዥ 4.14 በሙከራ ቡድኑ በሴትና በወንድ ተማሪዎች የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ

ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ (t= 3.133, df = 36, p=.003) አሳይቷል፡፡ በዚህም በቅድመትምህርት በወንድና በሴት ተማሪዎች የቃላት ችሎታ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም ተሰልቶ 1.03 (Cohen's d = 1.03) ሆኖ ስለተገኘ፣ የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃ «መካከለኛ» (moderate) መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህ ከታወቀ በኋላም በሙከራ ቡድኑ የሚገኙት ወንዶችና ሴቶች በአንድ ከፍል ውስጥ በተመሳሳይ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና እየተሰጣቸው ቃላትን ከተማሩ በኋላ ድህረትምህርት የቃላት ውጤታቸው ልዩነት ማሳየት አለማሳየቱን ለማወቅ በተደረገው የአማካይ ውጤቶች ንጽጽር የተገኘው ውጤት ደግሞ በሰንጠረዥ 4.15 እና 4.16 እየተነጻጸረ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4. 15፡- የሙከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

ፈተና	ጾታ	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	መደበኛ የአማካይ ስህተት (Std. Error Mean)
ድህረትምህርት	ሴት	23	16.65	3.36	.702
	ወንድ	15	16.60	2.47	.638

ሠንጠረዥ 4.15 የሙከራውን ቡድን የሴትና የወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶችና መደበኛ ልይይቶች ያሳያል፡፡ በሠንጠረዡ ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለውም አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሴት ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (16.65) ከወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት (16.60) በ0.05 በልጦ ተስተውሏል፡፡ ሆኖም በሰንጠረዥ 4.13 እንደቀረበው በቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤታቸው መካከል ከታየው 1.6 የአማካይ ውጤቶች ልዩነት

አንጻር የድህረትምህርት አማካይ ውጤታቸው ልዩነት እንደጠበበ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አባባል ውንዶቹ 12.27 ከነበረው የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና

አማካይ ውጤታቸው ወደ 16.60 ያሻሻሉት በ4.33 ሲሆን፣ ሴቶቹ 13.87 ከነበረው የቅድመትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤታቸው ወደ 16.65 ከፍ ብሎ በ2.78. መሻሻል አሳይተዋል፡፡

እንዲሁም የሴት ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (3.36) ከወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና መደበኛ ልይይት (2.47) በ0.89 በልጦ መጠነኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም የሁለቱም ጾታዎች የድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ከአማካይ ውጤቶቹ ያለው ርቀት ሲታይ የሚዋዥቅ ሳይሆን የወጥነት ባህሪ የሚታይበት ወይም ተቀራራቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከላይ በቀረበው ትንተና የሴት ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በ0.05 እንደበለጠ ውጤቱ አሳይቷል፡፡ በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን ግን ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በሠንጠረዥ 4.16 እንደተመለከተው የነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ሠንጠረዥ 4.16፡- የሙከራ ቡድኑ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት

ፈተና	ጾታ	ናሙና (n)	አማካይ ውጤት (mean)	መደበኛ ልይይት (Std.)	የነጻነት ደረጃ (df)	የ«ቲ» ዋጋ	የጉልህነት ደረጃ (sig.2-tailed)
ድህረትምህርት	ሴት	23	16.65	3.36	36	.052	.959
	ወንድ	15	16.60	2.47			

ሠንጠረዥ 4.16 በሙከራው ቡድን በሴትና በወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ያሳያል፡፡ በዚህም መሰረት መረጃው በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልቶ በድህረትምህርት የሴትና የወንድ ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመመኖሩን ውጤቱ (t=052, df= 36, p=.959) አሳይቷል፡፡ ይህም በሙከራ ቡድኑ በተሳተፉት ሴቶችና ወንዶች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ ከዚህም ሁለቱም ጾታዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ መማራቸው በመካከላቸው ያለውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ ተቀራራቢ የቃላት ችሎታ እንዲኖራቸው ሊያደርግ እንደቻለ መረዳት ተችሏል፡፡

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም « ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነላ የቃላት ችሎታ ልዩነት አለ?» የሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ አሉታዊ መልስ አግኝቷል፡፡ ምክንያቱም በድህረትምህርት በሴትና በወንድ ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አልታየም፡፡ በመሆኑም« ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነላ የቃላት ችሎታ ልዩነት የለም» የሚለው አልቦ መላምት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ «ከስልጠናው በኋላ በሙከራው ቡድን ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነላ የቃላት ችሎታ ልዩነት አለ» የሚለው ተለዋጭ መላምት ወድቅ ሆኗል፡፡

አራተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ «ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ አለ?» የሚል ሲሆን፣ መላምቱ «ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ የለም» የሚል ነበር፡፡ ጥያቄውን ለመመለስና መላምቱን ለመፈተሽ መረጃው በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መጠን መለኪያ ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.17 ተመልክቷል፡፡

በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታና በቃላት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ የተመለከቱ በርካታ ጥናቶች መሰራታቸው በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ተገልጿል። በነዚህ ጥናቶች እንደተጠቆመው (Gu & Johnson, 1996; Krzysztof, 2014) ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን ከመካከለኛ- ከፍተኛ በሆነ መጠን ሲጠቀሙ በብልሃቶቹና በተማሪዎች የቃላት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን

በማመልከት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ በጨመረ ቁጥር የቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታም ይጨምራል። በተቃራኒው ደግሞ ብልሃቶችን በተገቢ መንገድ አለመጠቀም ዝቅተኛ ውጤት ከማስመዝገብ ጋር ይዛመዳል (Lawson & Hogben, 1996)::

ከላይ ከተጠቀሰው አኳያ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ብልሃቶችን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች አጠቃላይ የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ችሎታ ለውጥ ምን አይነት ተዛምዶ እንዳለው ወይም ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የብልሃት አጠቃቀም ችሎታንና የቃላት ችሎታን ለማዛመድ ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ ተሞክሯል። በፍተሻውም የተማሪዎቹን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ለመፈተሽ የቀረበው የድህረትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ከቡድኑ ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ጋር በማጣመር ተተንትኗል። የሁለቱን የግንኙነት መጠንና አቅጣጫ ለማመልከትም፣ ከተዛምዶ መጠን መለኪያዎች ውስጥ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ 4.17 ፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መጠን መለኪያ ተግባራዊ ተደርጓል።

ሠንጠረዥ 4.17 **በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታና በቃላት ውጤት መካከል ያለው የተዛምዶ መጠን**

		ድህረትምህርት የቃላትፈተና ውጤት	ድህረትምህርት የብልሃትአጠቃቀም ውጤት
የሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት	ፒርሰንየተዛምዶ መለኪያ	1	.947*
	ጉልህነት (2-ጫፍ)		.000
	ብዛት	38	38
የሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት የብልሃት አጠቃቀም ውጤት	ፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ	.947**	1
	ጉልህነት (2-ጫፍ)	.000	
	ብዛት	38	38

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

በሠንጠረዥ 4.17 ከሰፈረው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ብልሃቶችን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች ድህረትምህርት አጠቃላይ የብልሃት አጠቃቀም ውጤትና በቃላት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መለኪያ ተሰልቶ ውጤቱ ጉልህ ሆኖ (p= .000) ተገኝቷል። የተዛምዶው አይነትና የጥንካሬ ደረጃም አዎንታዊ (positive)ና «በጣም ጠንካራ» ነው (r= .947)። ይህም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የሚማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ችሎታቸው ባደገ ቁጥር የቃላት ፍቺን የመረዳት ችሎታቸውም አብሮ እያደገ ይመጣል ለማለት ያስችላል።

የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም «ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ አለ?» የሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ አወንታዊ መልስ አግኝቷል። እንዲሁም «ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ወጤት መካከል ተዛምዶ የለም» የሚለው አልቦ መላምት ውድቅ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ « ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ አለ» የሚለው ተለዋጭ መላምት ተቀባይነት አግኝቷል።

ለማጠቃለል የጥናቱ የትንተና ውጤት ያሳየው የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላትና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው። ምክንያቱም ከስልጠናው በኋላ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል። የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤትም ከቅድመትምህርቱ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል።

ብልሃቶችን በግልጽ በተማሩት የሙከራው ቡድን ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከልም በቅድመትምህርት የነበረውን ጉልህ የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ በድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን የጥናቱ የትንተና ውጤት አመልክቷል። ብልሃቶቹን በተማሩት ተማሪዎች ድህረትምህርት የብልሃት አጠቃቀም ችሎታና የቃላት ውጤት መካከልም አወንታዊ አቅጣጫ ያለው በጣም ጠንካራና ጉልህ ተዛምዶ እንዳለ ከሙከራው ቡድን ተማሪዎች የተገኘው መረጃ የትንተና ውጤት አሳይቷል።

4.1.2 የጥናቱ የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የጥናቱን አራት መሰረታዊ ጥያቄዎች መፈተሽ ነበር። ጥያቄዎቹን ለመፈተሽም መረጃዎቹ በቃላት ፈተናና በጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ተሰብስበው በነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት፣ በዳግምልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስትና በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መጠን መለኪያ ተተንትነዋል።

የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የቃላት እውቀት ልዩነት ይኖራል?» የሚል ነበር፤ ጥያቄውን ለመፈተሽም መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በነጻናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኗል።

መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም፣ የቃላት መማር ብልሃቶቹን በውህደት በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ (ሠንጠረዥ 4. 3) ልዩነት አሳይቷል። ልዩነቱም ጉልህና መካከለኛ መሆኑ (ሠንጠረዥ 4.4) ተረጋግጧል። ከዚህም የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የዘጠነኛ ክፍል የኦሮምኛ አፍፈት ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ተፈትሾ አወንታዊ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

ከዚህ ውጤት ተነስቶም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶችን በክፍል ውስጥ በውህ በግልጽ ማሰልጠን ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ በተለየ ወይም በተሻለ ሁኔታ በተማሪዎች የቃላት ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ መሻሻል ያሳያል ማለት ይቻላል። ይህ ልዩነት የተፈጠረው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቃላት መማር ብልሃቶች በታገዘ ትምህርት የቃላት እውቀታቸውን መቼና እንዴት አቀናጅተው መጠቀም እንደሚችሉ ጽንሰሃሳባዊና ተግባራዊ ግንዛቤ በማግኘታቸው ሊሆን ይችላል ቢባልም ተጠየቃዊ ይሆናል።

የዚህ ጥናት ግኝትም Alseweed (2000)፣ Aktekin & Guven (2013)፣ Tassana-Ngam (2004)፣ Rodriguez & Sadoski (2000) እና Rajee (2013) የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ የቃላትን ችሎታ ለማሳደግ የላቀ ድርሻ እንዳለው ካገኟቸው የጥናት ውጤቶች ጋር ተደጋጋፊነት አሳይቷል። ሆኖም ከነዚህ ጥናቶች የTassana-Ngam (2004)፣ Rodriguez & Sadoski (2000)፣ Alseweed (2000) ጥናት ውጤቶች የቁጥጥር ቡድን በማካተት የተሰሩ በመሆናቸው፣ ከቀጥተኛ ብልሃቶች የተውጣጡ ከአምስት እስከ ስድስት የሚደርሱ ብልሃቶችን በማከተታቸው፣ በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በመለካታቸው ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖራቸውም፤ የTassana-Ngam (2004)ም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ፣ የተለያየ የትምህርት ደረጃ ባላቸው ማለትም ሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ አመት ሆነው ከተለያየ ትምህርት ክፍል የተውጣጡ እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ከመካሄዱ ባለፈ ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶችን ሳያካትት ከቀጥተኛ ብልሃቶች የተውጣጡ አምስት ብልሃቶችን ብቻ ራሱ ተመራማሪው በማሰልጠን የተሰራ ነው። ይሁንና ይህ የአሁኑ ጥናት ከስድስቱም ምድብ የተውጣጡ አስራ ሁለት ብልሃቶችን በውህደት ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከተመራማሪዋ ውጪ በሌላ አንድ መምህር በማስተማር የተገኘ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር የአጠናን ልዩነት አላቸው።

የRodriguez & Sadoski (2000) ጥናት በበኩሉ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የውጪ ቋንቋን በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ከመካሄዱ ባለፈ በቀጥተኛ ብልሃቶች ላይ ብቻ አተኩሮ የተሰራ በመሆኑ ከስድስቱም ምድብ (ከቀጥተኛና ከኢቀጥተኛ) የተውጣጡ ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ በማስተማር ከተገኘው ከዚህ ጥናት ውጤት ይለየዋል። የAlseweed (2000) ጥናትም ቢሆን በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ከመሆኑ ባሻገር ለስድስት ሳምንት በተሰጠ አጭር ስልጠና ብሎም በቡድን 9ና10 የሚሆኑ ተሳታፊዎችን ብቻ ይዞ የተሰራ በመሆኑ በአንጻራዊነት በሰፊ ጊዜና በበርካታ ተሳታፊዎች ትግበራ ከተገኘው ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ልዩነት እንዳለው ከግንዛቤ ማስገባት ያሻል።

የRajee (2013) ጥናትም ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በመካሄዱ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፣ ከሦስት ምድብ የተውጣጡ አምስት ብልሃቶችን ብቻ በማካተቱ፣ በቅድመትምህርትም ሆነ በድህረትምህርት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ባልተለካበት ሁኔታ በፈተና ብቻ የተገኘ ውጤት መሆኑ በርግጥም የተገኘው ውጤት ስልጠናው የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሻሻሉ የተገኘ ነው ብሎ ለመደምደም የማይቻልበትን ሁኔታ ስለሚፈጥርና በሁለት ሙከራዊ ቡድን ላይ ተመስርቶ የተሰራ ንጽጽራዊ ጥናት መሆኑ ከዚህኛው ጥናት የሚለየው መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

እንዲሁም Yang (2014)፣ Cohen & Aphex (1980) Mahdavi (2014)፣ Banisaeid (2013)፣ Brown & Perry (1991)፣ Ronald (2001) ከአንድ ምድብ የተውጣጡ ከአንድ እስከ ሦስት የሚሆኑ ብልሃቶችን በተናጠል በማሰልጠን የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የቃላት ችሎታን ለማዳበር አስተዋጽኦ እንዳለው ከሳዩባቸው ጥናቶች ውጤት ጋርም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሆኖም እንደ Ronald (2001) እና Cohen & Aphex (1980) ያሉት ጥናቶች አንድ ነጠላ ብልሃትን በማስተማር ላይ አተኩረው የተካሄዱ ከመሆናቸው ባለፈ ከሁለት ሳምንት አስከ አንድ ወር ባለ ጊዜ በተሰጠ ስልጠናና የቁጥጥር ቡድን በሌለው የአንድ ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት ውጤትና በሁለት ሙከራዊ ቡድን ውጤት ላይ ተመስርተው የተሰሩ በመሆናቸው በተሰጠው ትምህርት ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን በአግባቡ ማነጻጸር የማይቻልበትን ሁኔታ ስለሚፈጥር ይህ ጥናት በሁለት ቡድን (የሙከራና የቁጥጥር) ቅድመና ድህረትምህርት ውጤት ላይ ተመስርቶ ከተካሄደበት የ14 ሳምንት ጊዜ ጋር ልዩነት እንዳላቸው መገንዘብ ያሻል፡፡

የYang (2014)፣ Mahdavi (2014) እና Mizumoto & Takeuchi (2009) ጥናትም ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት ፈተና ውጤት ላይ ተመስርቶ በመሰራታቸው፣ በቅድመትምህርትና ድህርትምህርት ተመሳሳይ የቃላት ፈተና በመጠቀማቸውና የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም በመለካታቸው ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም፤ የMahdavi (2014) በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሁለተኛ ቋንቋን

የሚማሩ ተማሪዎች ላይ ከመካሄዱ ባለፈ ልዕለእምሯዊ ብልሃቶችን ብቻ በማስተማር የተገኘው ውጤት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የአጠናን ልዩነት እንዳለው ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል፡፡

የYang (2014) ጥናትም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የውጭ ቋንቋን በሚማሩ ተማሪዎችና አእምሯዊ ብልሃቶች ላይ ብቻ አተኩሮ ከመካሄዱ ባሻገር በታላሚ ናሙና በተመረጡ ተሳታፊዎች ላይ ተሰርቶ የተገኘ ውጤት መሆኑ የተገኘውን ውጤት በርግጥም ብልሃቶቹን በግልጽ በመማራቸው ብቻ የተገኘ ነው ብሎ ለመደምደም የማይቻልበትን ሁኔታ ስለሚፈጥር ከዚህ ጥናት ጋር የአጠናን ልዩነት እንዳለው ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል፡፡

Mizumoto & Takeuchi (2009) ጥናትም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንግሊዝኛን እንደ ውጭ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ከመካሄዱ ባለፈ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ከማዳበር ባሻገር ለቃላት ትምህርት ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽኦም በመፈተሻቸው ከዚህ ጥናት ጋር የአጠናን ልዩነት እንዳለው መገንዘብ ያሻል፡፡

የBrown & Perry (1991) ጥናትም በበኩሉ በሁለት ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት ውጤት ላይ ተመስርቶ የተሰራ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ቢኖረውም፤ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎችን ሁለት የትስውስታ ብልሃቶችን ብቻ በማስተማር የተገኘ ውጤት ከመሆኑ ባሻገር በቅድመትምህርትም ሆነ በድህረትምህርት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ባልተለካበት ሁኔታ በፈተና ብቻ የተገኘ ውጤት በመሆኑና ሁለቱ ቡድኖች በተለያየ መምህር ተምረው የተገኘ ውጤት መሆኑ ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር የአጠናን ልዩነት እንዳለው ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡

በአጠቃላይም፣ ከእነዚህ ጥናቶች አንዳንዶቹ በውጪ ቋንቋ የማስተማር አውድ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ መሰራታቸው፣ ነጠላ ብልሃቶችን በማሰልጠን ላይ በማተኮራቸው፣ በአጭር ጊዜ ስልጠና የተሰሩ በመሆናቸው፣ ሁለቱን ቡድኖች በተለያየ መምህር እንዲማሩ ተደርጎ የተካሄዱ መሆናቸው፣ በሁለት ሙከራዊ

ቡድን ላይ የተሰሩ ንጽጽራዊ ጥናት መሆናቸው፣ በቡድን ከ30 በታች የሆኑ ተሳታፊዎችን ይዘው በመሰራታቸው፣ በአንድ ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት ውጤት ላይ ተመስርተው መካሄዳቸው ይህ ጥናት ከተሰራበት አውድና የአጠናን ዘዴ ይለያቸዋል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ የዚህ ጥናት ግኝት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማዳበር የተለየ አስተዋጽኦ እንደሌለው ካሳዩበት ከCarrell, Pharis & Liberto (1989) እና O'Malley እና ሌሎች (1985) ጥናቶች ውጤት ጋር የሚቃረን ሆኗል፡፡ በጥቅሉ ግን ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የቃላት ችሎታ ለማዳበር ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ የበለጠ ውጤታማ መሆኑን የዚህ ጥናት ግኝት አሳይቷል፡፡

በመሆኑም፣ የዚህ ጥናት ግኝት፣ Mahadavi (2014) እና Oxford (1990) የሚገልጹትን ሀሳብም የሚያጠናክር ነው፡፡ ምክንያቱም የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና በሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርት ሂደት ያለው ሚና ወሳኝ እንደሆነ ምሁራኑ እንዳስገነዘቡት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ከቃላት ችሎታ ጋር አወንታዊ ተዛምዶ አላቸው፡፡ ብልሃቶችን መጠቀምን ከበቂ ልምምድ ጋር በግልጽ የተማሩ ተማሪዎች ብልሃቶችን በመጠቀም ዙሪያ ልምዱ ከሌላቸው ተማሪዎች የበለጠ ውጤታማ ሆነው ይማራሉ፡፡ በዚህ ጥናትም በብልሃቶቹ አጠቃቀም ላይ በቂ ልምምድ በማድረግ በግልጽ የተማሩት ተማሪዎች በድህረትምህርት ብልሃቶችን ካልተማሩት ተማሪዎች የበለጠ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

እንዲሁም የዚህ ጥናት ግኝት የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ ሲዳብር የቃላት እውቀታቸውም እንደሚዳብር Omalley &Chamot (1990) ከሚገልጹት ሀሳብ ጋርም ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ነው:: ምክንያቱም በዚህ ጥናት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ብልሃቶቹን በውህደት በግልጽ ከተማሩ በኋላ የብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤያቸውም ሆነ የቃላት ችሎታቸው ተሻሽሎ ታይቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የዚህ ጥናት ግኝት ውጤታማ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና በስልጠናው ሂደት ንድፈ ሃሳባዊ ገለጻን፣ የብልሃቶቹን አተገባበር በተግባር ማሳየትን (ሞዴሊንግ)፣ ትብብራዊ መማርን፣ አውዳዊ ልምምድ ማድረግንና ምጋቤ ምላሽ መስጠትን ማካተት አለበት፣ የሚሉ ምሁራንን (Oxford, 1990; Gu, 2003; O'Malley & Chamot, 1990) ሃሳብም ይደግፋል። ምክንያቱም በዚህ ጥናት የመከራው ቡድን ተማሪዎች እያንዳንዱን ብልሃት በዚህ መንገድ በግልጽ ከተማሩ በኋላ በቃላት ችሎታቸውም ሆነ በብልሃት አጠቃቀማቸው ጉልህ መሻሻል አሳይተዋል።

እንዲሁም የዚህ ጥናት ግኝት፣ O'malley & Chamot (1990) እና Oxford (1990)፣ የብልሃት ትምህርት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየገጠሙት ያሉትን ትችት ለማስወገድ የቃላት/ ቋንቋ መማር ብልሃቶች ስልጠና ኢቀጥተኛ ከሚሆን ይልቅ የብልሃቶቹን አጠቃቀም ግንዛቤ ለመፍጠር ተማሪዎቹ የብልሃቶችን ምንነት፣ ጠቀሜታና አጠቃቀም የሚለዩበት ገላጭ ደረጃ (declarative)፣ የብልሃቶቹን አጠቃቀም የሚያሳዩበት ደረጃ (procedural) እና ብልሃቶቹን ለምን፣ እንዴትና መቼ እንደሚጠቀሙ የሚያስረዱበት ጽብረቃዊ ደረጃ (conditional) ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግ በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ የቃላት ችሎታን ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፤ ከሚሉት ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው። ምክንያቱም በዚህ ጥናት የመከራው ቡድን ተማሪዎች እያንዳንዱን ብልሃት በዚህ መልኩ ከተማሩ በኋላ የብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤያቸውን በማሳደግ የቃላት ችሎታቸው ተሻሽሏል።

Sokmen (1997)፣ Oxford (1990)፣ Alseweed (2000) እና O'malley & Chamot (1990) ተማሪዎች እንደየ ግለሰባዊ ልዩነታቸው፣ ፍላጎታቸውና እንደየ ተግባራቱ አይነት ተገቢ ብልሃቶችን መርጠው በቅንጅት በመጠቀም የቃላት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ፣ ስልጠና ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ በርካታ ብልሃቶችን የያዘ ውህድ አቀራረብ (mixed approach) በመከተል ረዘም ላለ ጊዜ መሰጠት እንዳለበት ከሚገልጹት ሐሳብ ጋርም ተደጋጋፊ ነው። ምክንያቱም በዚህ ጥናት የመከራው ቡድን ተማሪዎች ከተለያየ ምድብ የተውጣጡ ብልሃቶችን ለ14 ሳምንት

በውህደት በግልጽ ከተማሩ በኋላ የብልሃት አጠቃቀማቸውም ሆነ የቃላት ችሎታቸው እንደተሻሻለ ለመገንዘብ ተችሏል።

በተጨማሪም የዚህ ጥናት ግኝት፣ በሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ትምህርታቸው ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች በርካታ ብልሃቶችን በውህደት መጠቀም የሚችሉ ናቸው፤ ከሚሉ ምሁራን (Sokmen, 1997) ሀሳብ ጋርም ይመሳሰላል።

ከዚህም ሌላ የዚህ የጥናት ግኝት፣ ከሌሎች የምርምር ውጤቶች Gu & Johnson (1996)፣ Krzysztof (2014) OMalley & Chamot (1990) ጋር በሚመሳሰል መልኩ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ከቃላት ችሎታ ጋር ቁርኝት አለው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም ማስረጃው የቃላት ፍቺን የመረዳት አማካይ ውጤት ሲጨምር የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤትም ጨምሮ መስተዋሉ ነው። ከዚህ በመነሳትም የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ለቃላት ችሎታ መሰረታዊ ጉዳይ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም።

በሌላ መልኩ የዚህ ጥናት ግኝት፣ በቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ወቅት ግልጽና ቅንጅታዊ የብልሃት ትምህርት አቀራረብ ሞዴል በመጠቀም አተገባበሩን እንዲለማመዱ የቃላት ተግባራት በማቅረብ አውዳዊ ድጋፍ መስጠት የብልሃት አጠቃቀምን በማዳበር የተማሩትን ብልሃት ወደ ተመሳሳይ አዳዲስ ተግባራት አሸጋግሮ በመጠቀም የቃላት ችሎታን ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽኦ አለው፤ ከሚለው ከOmalley & Chamot (1990) እና Oxford (1990) ሃሳብ ጋርም ይስማማል። ምክንያቱም በዚህ ጥናት ተማሪዎቹ ብልሃቶቹን ከቃላት ተግባራቱ ጋር በማቀናጀት በግልጽ ከተማሩ በኋላ የቃላት ችሎታቸውም ሆነ የብልሃት አጠቃቀማቸው ተሻሽሏል። ከዚህም ግልጽና ቅንጅታዊ የብልሃት ትምህርት አቀራረብ ሞዴል የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ግንዛቤ በማሳደግ የቃላት ችሎታን ለማዳበር ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመገንዘብ ተችሏል።

በመሆኑም ከዚህ የጥናት ግኝት በመነሳት የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን ቃላትን በማስተማር ሂደት ስነትምህርታዊ አንድምታ (educational implication) እንዳለው መረዳት ይቻላል። ምክንያቱም የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት አውቀት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች በአግባቡ ከተተገበረ ይህን ችግራቸውን ለመፍታት ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ በበለጠ ሁኔታ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ለማየት ተችሏል።

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ «ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት ያሳያል?» የሚል ነበር፤ ይህንንም ለመገንዘብ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በዳግም ልኬታ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኗል።

መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየው፣ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርቱ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት በልጦ (ሠንጠረዥ 4.9) ልዩነት አሳይቷል። ልዩነቱም ጉልህ መሆኑ (ሠንጠረዥ 4.10) ተረጋግጧል። ከዚህም፣ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች ግንዛቤና አጠቃቀም ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ ተፈትሾ አወንታዊ ውጤት እንዳለው ለመረዳት ተችሏል። ይህ የውጤት ልዩነትም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን በተለየ ሁኔታ የቃላት መማር ብልሃቶችን ግንዛቤና አጠቃቀም ለማሻሻል የሚረዳ መሆኑን ያመላክተ ነው ማለት ይቻላል።

የዚህ ጥናት ውጤት ግኝትም Mahdavi (2014)፣ Banisaeid (2013)፣ Aktekin & Guven (2013)፣ Alseweed (2000)፣ Mizumoto & Takeuchi (2009)፣ Tassana-Ngam (2004) እና Cohen & Aphex (1980) ካገኙት የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነው። ምክንያቱም ውጤቶቹ ያሳዩት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ ጉልህ

አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የተመራማሪዎቹ የጥናት ግኝቶች ከዚህ የጥናት ውጤት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከተገኘው ውጤት በመነሳትም የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ ረገድ ስነ ትምህርታዊ አንድምታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ስልጠናው በአግባቡ ከተተገበረ የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች ግንዛቤና አጠቃቀም ችግር በመፍታት በኩል ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደቻለ ውጤቱ አሳይቷል፡፡

ሦስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ «ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የነላ የቃላት ችሎታ ልዩነት ይኖራል?» የሚል ነበር፤ ይህንንም ለመፈተሽ መረጃው በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡

መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም፣ በቅድመትምህርት የሙከራው ቡድን የሴት ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት፣ ከወንድ ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ልዩነት አሳይቷል፤ ልዩነቱም ጉልህ እንደሆነ (ሠንጠረዥ 4.14) ተረጋግጧል፡፡ በአንጻሩ፣ በድህረትምህርት የሴት ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት፣ ከወንድ ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ቢገኝም ጉልህ ልዩነት እንዳላሳየ (ሠንጠረዥ 4.16) ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማስተማር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ ተቀራራቢ ችሎታ እንዲኖራቸው በማድረግ ከተለምዷዊ ዘዴዎች ልዩነት መፍጠር መቻሉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስለሆነም፣ የዚህ ጥናት ግኝትም፣ Tassana-Ngam (2004)፣ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረውን የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ልዩነት በማሻሻል ሁለቱም ጾታዎች ተቀራራቢ የቃላት ችሎታ እንዲኖራቸው በማድረግ የላቀ ድርሻ እንዳለው ካገኙት

የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አሳይቷል፡፡ ሆኖም ይህ ጥናት በውጪ ቋንቋ የማስተማር አውድ የተለያየ ችሎታ ባላቸው ማለትም ከሁለተኛ፣ ከሦስተኛና ከአራተኛ አመት ከተለያየ ትምህርት ክፍል የተውጣጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አምስት ብልሃቶችን በማስተማር ላይ አተኩሮ የተካሄደ መሆኑ ይህ ጥናት ከተሰራበት አውድና የአጠናን መንገድ ይለየዋል፡፡

በሌላ በኩል የዚህ ጥናት ግኝት Catalan (2003) ፣ Oxford (1990)፣ O'malley & Chamot (1990) እና Yin (2008) የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በመማር የሚገኝ ውጤት ከተማሪዎች ጾታ ጋር ተዛምዶ ስላለው ተማሪዎች ስልጠና ቢሰጣቸውም ጾታ በተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ላይ ልዩነት ስለሚፈጥር እኩል ተጠቃሚ እንደማይሆኑ ከሚገልጹት ሀሳብ ጋር የሚቃረን ሆኗል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የተለያዩ ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማስተማር ከተለምዷዊ ዘዴዎች በተለየ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ ተቀራራቢ የቃላት ችሎታ እንዲኖራቸው ሊያደርግ እንደቻለ ወይም የሁለቱንም ጾታዎች የቃላት ችሎታ ማጎልበት እንደሚችል ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም ከስልጠናው ሁለቱም እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ የዚህ ጥናት ግኝት Griffith (2003)፣ Nyikos (1990) እና Young (1996) ብልሃቶችን በግልጽ በመማር በሚገኝ ውጤት የተማሪዎች ጾታ ጉልህ ልዩነት እንደማይፈጥርና ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር በመካከላቸው ያለውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ ተቀራራቢ ችሎታ እንዲኖራቸው የማድረግ አስተዋጽኦ እንዳለው ከገለጹበት የጥናት ውጤቶች ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት ውጤት ጾታ በተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር በድህረትምህርት የቃላት ችሎታቸው እንዲለያይ አላደረገም፡፡ በሌላ አገላለጽ ከስልጠናው ሁለቱም እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ውጤቱ አሳይቷል፡፡

በሌላ መልኩ የዚህ ጥናት ግኝት Oxford (1990)፣ O'malley & Chamot (1990)፣ Ellis (1994)፣ Tassana-Ngam (2004) የጠቀሷቸው Oxford (1986) እና Oxford & Ehrman (1987) ከማህበራዊ ስነልሳን ንድፈ ሀሳብ ጋር በተያየዘ በተሰሩ የጥናት ውጤቶች በአጠቃላይ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ሴቶች ከወንዶች በበለጠ ብልሃቶችን በስፋት ስለሚጠቀሙ ከወንዶች የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ካሳዩት ጥናቶች ውጤትና የተወሰኑት ደግሞ ወንዶች ከሴቶች በበለጠ ተገቢ ብልሃቶችን መርጠው ስለሚጠቀሙ ከሴቶች የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ Ellis (1994) ካገኙት ጥናቶች ውጤት ጋር ይቃረናል። ምክንያቱም በዚህ ጥናት በቅድመትምህርቱ የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረው ጉልህ ልዩነት በድህረትምህርቱ የቃላት ፈተና አልተደገመም።

Nyikos (1990) በጀርመንኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት በጀርመንኛ ቋንቋ የቃላት ክምችት ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ ካገኙት ውጤትና በተመሳሳይ Boyle (1987) ሁለት የተለያየ የማዳመጥ ክሂል ፈተና ፈትነው በካሄዱት ጥናት ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የቃላት ችሎታ እንዳላቸው ካገኙት የጥናት ውጤትጋርም ይቃረናል። እንዲሁም ከጾታ ልዩነት አንጻር Boyle (1987) እንግሊዝኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የቻይና ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሴቶች ከወንዶች የላቀ የቃላት ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ካገኙት ውጤት ጋርም ይቃረናል። ምክንያቱም በዚህ ጥናት ከስልጠናው በኋላ የሴቶቹ ብልጫ እንደተጠበቀ ቢሆንም ጉልህ ልዩነት አላሳየም። እነዚህ ጥናቶች ብልሃቶችን በግልጽ ከማስተማር ውጭ የተሰሩ መሆናቸው ከዚህ ጥናት ውጤት ጋር ላለመስማማታቸው አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

በአንጻሩ ደግሞ የዚህ ጥናት ግኝት Bacon (1992) ሁለት የማዳመጥ ክሂል ተግባራትን አቅርበው በወንድና በሴት ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መካከል ልዩነት እንደሌለ ካገኙት ጥናት ውጤት ጋር ይመሳሰላል። ሆኖም በነዚህ ጥናቶች የተገኘው ውጤት ብልሃቶችን በግልጽ ከማስተማር ጋር ተያይዞ የተገኘ ውጤት ሳይሆን በተለምዷዊ ዘዴዎች የተማሩ ተማሪዎችን የተለያዩ ፈተናዎችን በመፈተን የቃላት ችሎታቸውን በመለካት የተገኘ መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ስለሆነም፣ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማስተማር ከተለምዷዊ ዘዴዎች በተሻለ ሁኔታ፣ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማቀራረብ የሁለቱንም የቃላት ችሎታ ማሳደግ በመቻሉ ቃላትን ለማስተማር ተግባራዊ ቢደረግ የላቀ አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ ተችሏል።

አራተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ« ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ችሎታና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ አለ?» የሚል ነበር፤ ይህንንም ለመፈተሽ መረጃው በፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መጠን መለኪያ ስታትስቲክስ ተተንትኗል።

መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው፣ ብልሃቶችን በግልጽ በተማሩት ተማሪዎች ድህረትምህርት አጠቃላይ የብልሃት አጠቃቀም ውጤትና ድህረትምህርት የቃላት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ በስታትቲክስ ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል፤ የተዛምዶው አይነት (አቅጣጫ)ና የጥንካሬ ደረጃም አወንታዊና በጣም ጠንካራ እንደሆነ (ሠንጠረዥ 4.17) ተረጋግጧል። ይህን ውጤት መሰረት በማድረግም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከቃላት ውጤት ጋር ዝምድና አለው ለማለት ይቻላል።

ስለሆነም፣ የዚህ ጥናት ግኝትም Gu & Johnson (1996)፣ Krzysztof(2014) እና (Schmitt, 1997) ተማሪዎቹ የቃላት መማር ብልሃቶቹን ከመካከለኛ-ከፍተኛ በሆነ መጠን ሲጠቀሙ በብልሃቶቹና በቃላት ችሎታ መካከል አወንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ከሳዩበት የጥናት ውጤቶች ጋር ተመሳሳይነት አለው። ምክንያቱም በዚህ ጥናት

ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩት ተማሪዎች ድህረትምህርት የብልሃት አጠቃቀም ውጤት ከድህረትምህርቱ የቃላት ውጤትጋር ያለው ተዛምዶ ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህም የተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ችሎታ ሲጨምር የቃላት ችሎታቸውም አብሮ እንደሚጨምር ለመገንዘብ ተችሏል። ሆኖም እነዚህ ጥናቶች በውጪ ቋንቋ የማስተማር አውድ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ አተኩሮ የተካሄዱ በመሆናቸው ይህ ጥናት ከተሰራበት አውድ የተለየ መሆኑ ከግንዛቤ ሊገባ ይገባል።

እንዲሁም የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ የቃላት ውጤትን አመላካች መሆኑን ካሳዩት የ Schmitt (2000) እና Nation (2001) ጥናቶች ውጤት ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ ተገኝቷል።

የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ፣ የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ ረገድ ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ የበለጠ ሆኖ የተገኘው ዘዴው ባለው ባህሪ ይመስላል። ምክንያቱም ሙያዊ እገዛን፣ ምጋቤ ምላሽን፣ ኃላፊነትን በሂደት ማሸጋገርን (የሚና ሽግግርን)ንና ትብብራዊ መማርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በራስመተማመንን ለማሳደግ የተሻለ ነው። ይህ በራስ የመተማመን ሁኔታ ደግሞ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ብልሃቶቹን ተጠቅሞ አንድን ቃል በጥልቀት ለመመርመርና ትርጉም ለመስጠት ያስቻለ ነው ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይም የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የአማርኛ ኢ-አፍፊት ተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ የቃላት ችሎታቸውን ለማዳበር አወንታዊ አስተዋጽኦ ያለው ስለሆነ በቃላት ትምህርት ሂደት ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ ቢተገበር የተሻለ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሔ ሀሳቦች

5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማዳበር የሚኖረውን አስተዋጽኦ፣ ለመፈተሽ አልሞ የተነሳ ሲሆን፣ ዓላማውን ዳር ለማድረስ በጥናቱ የተፈተሹት መላምቶች የሚከተሉት ነበሩ፤

በጥናቱ የተፈተሹ የምርምሩ አልቦ መላምቶች፡-

1. ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ በሙከራ ቡድን እና በቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች መካከል ጉልህ የቃላት እውቀት ልዩነት አይኖርም፡፡
2. ከቃላት መማር ብልሃቶቹ ስልጠና በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከስልጠናው በፊት ከነበራቸው ጉልህ ልዩነት አያሳይም፡፡
3. ከስልጠናው በኋላ በሙከራ ቡድኑ ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል የጎላ የቃላት እውቀት ልዩነት አይኖርም፡፡
4. ብልሃቶቹን በተማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀምና የቃላት ውጤት መካከል ተዛምዶ የለም፡፡

እነዚህን የምርምሩን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ፣ መላምቶቹንና ዓላማዎቹን ለመፈተሽም ጥናቱ በሚከተለው መንገድ ተከናውኗል፡፡

የጥናቱ ስልት በሁለት ቡድኖች ቅድመትምህርትና ድህረትምህርት ከፊል ፍትነታዊ የምርምር ንድፍ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ጥናቱን

ለማከናወን በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ክልል ልዩ ዞን፣ በአቃቂ ወረዳ፣ በዱከም ከተማ የሚገኘው የኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ተመርጧል፡፡ በተመረጠው የኦዳ ነቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2008 እና በ2009 ዓ.ም በመማር ላይ ካሉ አስራ ሁለት የዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ የሁለት መማሪያ ክፍል ተማሪዎች ተመርጠው እንደ ቅደምተከተላቸው የሙከራውና የዋናው ጥናት ተሳታፊዎች ተደርገዋል፡፡

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገሉት መሳሪያዎች የቃላት ፈተናና የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆኑ፣ የሁለቱም መሳሪያዎች ተገቢነት እንደ አስፈላጊነቱ በቋንቋ መምህራን፣ በስነልቦና ባለሙያዎችና በጥናቱ አማካሪ ተገቢነታቸው ተፈትሿል፡፡

ከዋናው ጥናት በፊትም በሙከራው ጥናት ተፈትሸው ተገቢ ማስተካከያ ተደርጎባቸዋል፡፡ ከአስተማማኝነታቸው አንጻርም የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ በሆነው በክሮንባኽ አልፋ ተለክተው አስተማማኝ መሆናቸው ተረጋግጦ ተግባር ላይ ውለዋል፡፡

በመቀጠል የሁለቱም የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎች ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነው የተገኙት አማካይ ውጤቶች በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት ተሰልተው፣ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የቃላት ችሎታ ልዩነት ባለመገኘቱ ለጥናቱ በእጣ በተለዩበት ሁኔታም በ9ኛC ክፍል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች የሙከራ ቡድን፣ በ9ኛB ክፍል ያሉት ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ሆነው ተለይተዋል፡፡ በመቀጠል የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ብቻ ቅድመትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል፡፡

ከዚያም የማስተማሪያ መሳሪያ (ማንዋል) ለሙከራው ቡድን ተማሪዎች የብልሃት ስልጠና ለመስጠት የቃላት መማር ብልሃቶችን በሙያዊ እገዛ (Scaffolding) መርህ በድጋፍ በግልጽ ለማሰልጠን በተመረጠው ቅደምተከተላዊ ማዕቀፍ (በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞድል) መሰረት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን የቃላት ትምህርት ከብልሃቶቹ ጋር በማቀናጀት ከተዘጋጀ በኋላ በጥናቱ አማካሪ፣ 9ኛ ክፍል

በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ዩኒቨርሲቲ በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገምግመው አገልግሎት ላይ ውለው በሙከራው ጥናት ተገቢነታቸው ተፈትሿል። ከዚያ በኋላ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በተዘጋጀው ማንዋል በሽግግራዊ የብልሃት ትምህርት ሞድል መሰረት የቃላት መማር ብልሃቶቹን በተናጠልና ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት ግልጽ ስልጠና እየተሰጣቸው፣ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ደግሞ በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ (በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ) በትምህርት ቤቱ በክፍል ደረጃው በማስተማር ላይ በሚገኙት በአጥኝዋ ስልጠና በተሰጣቸው አንዲት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህርት ለአስራ አራት ሳምንታት (ለ28 ክፍለጊዜያት) ሁለቱም ቡድኖች ቃላትን ተምረዋል።

በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች በባለሙያዎች የተገመገሙና በሙከራው ጥናት ተገቢነታቸው የተፈተሸ ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ተፈትነዋል። የሙከራው ቡድን ተማሪዎችም ድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀምመለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ሞልተዋል።

በሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በቅድመትምህርትና በድህረትምህርት ለመተንተን ደግሞ ገላጭ ስታትስቲክስና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ አገልግሎት ላይ ውለዋል። ገላጭ ስታትስቲክስ የመረጃዎቹን አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ለማነጻጸር ያገለገለ ሲሆን፣ ድምዳሜያዊ ስታትስቲክሱ ደግሞ በዳግም ልኬት ናሙናዎች ቲ-ቴስት፣ በነጻ ናሙናዎች ቲ-ቴስት የልዩነቱን ጉልህነትና የልዩነቱን የጥንካሬ ደረጃ ለማረጋገጥ ያገለገለ ሲሆን፣ ፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት የተዛምዶ መጠን መለኪያ ደግሞ በድህረትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ውጤትና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ያለውን የተዛምዶ መጠን ለመለካት አግልግሏል።

ከውጤት ትንተናው መረዳት እንደተቻለውም፣ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት የቁጥጥሩ

ቡድን ተማሪዎች የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፤ የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም መካከለኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በሙከራው ቡድን ተማሪዎች ድህረትምህርት የተሞላው የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤትም ከቅድመትምህርቱ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፤ የልዩነቱ የጥንካሬ ደረጃም መካከለኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

ብልሃቶችን በተማሩት የሙከራው ቡድን ሴትና ወንድ ተማሪዎች ድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤት መካከልም ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ አመላክቷል፡፡ ከዚህም ባሻገር ብልሃቶቹን በተማሩት ተማሪዎች ድህረትምህርት የብልሃት አጠቃቀም ችሎታና የቃላት ውጤት መካከልም አወንታዊ አቅጣጫ ያለው በጣም ጠንካራ ጉልህ ተዛምዶ መኖሩን ውጤቱ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይም የጥናቱ ውጤት ያሳየው የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማሳደግ ከተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከልም የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ በተመሳሳይ መንገድ የሁለቱንም ጾታዎች የቃላት ችሎታ በማሳደግ ከተለመደው ዘዴ በተሻለ ሁኔታ አወንታዊ ለውጥ ማምጣት እንደሚችልና የብልሃት አጠቃቀምንና የቃላት ችሎታን ለማዛመድም አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም፤ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን ቃላትን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ቢውል ሚናው የላቀ ነው፡፡ ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም ቀጥሎ መደምደሚያ፣ ስነትምህርታዊ የመፍትሄ ሀሳቦችና የወደፊት የምርምር አቅጣጫዎች ቀርበዋል፡፡

5.2 መደምደሚያ

በጥናቱ የውጤት ትንተና መሰረት ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በድህረትምህርት ያስመዘገቡት የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታቸው አማካይ ውጤት በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ፣ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማሰልጠን የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም በማሳደግ የቃላት ችሎታን ለማጎልበት የላቀ ድርሻ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይህም፣ ብልሃቶችን በግልጽ መማር ከቃላት ችሎታ ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለው ስለሚያሳይ ቃላትን ለማስተማር ተግባር ላይ ሊውልና በስፋት ሊሰራበት ይገባል፤ የሚል አንድምታ አለው፡፡

የሙከራው ቡድን ተማሪዎች በድህረትምህርት ያስመዘገቡት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት፣ በቅድመትምህርት ካስመዘገቡት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ውጤት በላቀ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን ከቃላት ተግባራት ጋር በማቀናጀት በግልጽ ማስተማር የተማሪዎችን የብልሃት ግንዛቤና አጠቃቀም ችግር ለመፍታት ጉልህ የላቀ ድርሻ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይህም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ መማር ከብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው መሆኑን ስለሚያሳይ በቃላት ትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የቃላት መማር ብልሃቶች ግንዛቤና አጠቃቀም ለማጎልበት ተግባር ላይ ሊውልና በስፋት ሊሰራበት ይገባል የሚል አንድምታን ያሳያል፡፡

ብልሃቶች በግልጽ የተማሩት የሙከራው ቡድን ሴት ተማሪዎች በቅድመትምህርት ያስመዘገቡት የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት፣

ወንድ ተማሪዎች ካስመዘገቡት የቃላት ችሎታ አማካይ ውጤት በልጦ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል። በድህረትምህርት ደግሞ ሴት ተማሪዎች ያስመዘገቡት የቃላት ችሎታ አማካይ ውጤት፣ ብልጫው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደ ቅድመትምህርቱ ጉልህ ሆኖ አልተገኘም።

ስለዚህ የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማስተማር በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል የነበረውን የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ ተቀራራቢ የቃላት ችሎታ እንዲኖራቸው/በተመጣጣኝ ደረጃ ችሎታቸው እንዲጎለብት በማድረግ ከተለምዷዊ የቃላት ማስተማሪያ ዘዴዎች ልዩነት ፈጥሯል። ይህም ለተተግባሪነቱ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ይጠቁማል።

ብልሃቶቹን በግልጽ በተማሩት ተማሪዎች ድህረትምህርት አጠቃላይ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ውጤትና በድህረትምህርት የቃላት ችሎታ አማካይ ውጤት መካከል አወንታዊ አቅጣጫ ያለው በጣም ጠንካራ ተዛምዶ ታይቷል፤ተዛምዷቸውም በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። ይህም የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ የሚማሩ ተማሪዎች የብልሃት አጠቃቀም ችሎታቸው ባደገ ቁጥር የቃላት ፍቺን የመረዳት ችሎታቸውም አብሮ እያደገ መምጣቱን ለመረዳት አስችሏል። ስለዚህ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የብልሃት አጠቃቀምንና የቃላት ችሎታን ለማዛመድ አወንታዊ አስተዋጽኦ ስላለው በቃላት ትምህርት ሂደት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የሚጠቁም አንድምታ አለው።

5.3 የመፍትሔ ሀሳቦች

በጥናቱ ግኝት መሰረት፤ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ከተማሩ በኋላ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታቸው አማካይ ውጤት በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ከቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል። ለዚህም፣ ብልሃቶችን በግልጽ ማስተማር ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል።

ስለዚህ፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ፍቺ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ በቃላት ትምህርት የማስተማር ዘዴዎቻቸው ውስጥ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው መማርን ይከውኑ ዘንድ የሚረዷቸውን የተለያዩ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማስተዋወቅን በመጠቀም ቢያስተምሩ የተማሪዎች የቃላት ፍቺን የመረዳት ችሎታ የሚሻሻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በተለይም ተማሪዎቻቸው በቃላት መማር ብልሃቶች ቃላትን በሚማሩበት ሂደት ስለብልሃቶቹ አጠቃቀም የድጋፍ ተሞክሮዎችን በማጋራትና ራሳቸውን ችለው በብልሃቶቹ የቃላት ተግባራትን በመከወን ተግባራዊ ተሞክሮዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል እድል በመፍጠር የተማሪዎቹን በራስ መር መማር በማጎልበት የቃላት ችሎታቸውን ማሻሻል ይችላሉ። ለዚህ ደግሞ በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች ብሎም የብልሃቶቹን አተገባበርና ብልሃቶቹ ያሏቸውን ፋይዳዎች መምህራኑ የሚገነዘቡባቸው አጫጭር የስራ ላይ ስልጠናዎች በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች መሰጠት ይኖርበታል።

ከዚህም ሌላ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ለመሆን ለሚሰለጥኑ አዲስ ሰልጣኞች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚሰጧቸው ስልጠናዎች ስለቃላት መማር ብልሃቶች ጭምር ማስተማርና ማሰልጠን ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ሰልጣኞቹ ራሳቸው ብልሃቶቹን የመተግበር ብቃት እንዲኖራቸው ተገቢ ትምህርት በመስጠት ብሎም በቃላት የማስተማር ስነዘዴዎች ውስጥ የብልሃቶቹን አተገባበር ጭምር በማካተት በእውቀትና በክህሎት የተሻሉ እንዲሆኑ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተትምህርት/መርሃትምህርትት ባለሙያዎችና የመማሪያ ማስተማሪያመጻሕፍት አዘጋጆች የቃላት ትምህርትን ሲያዘጋጁ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽማቅረብን እንደአንድ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገድ ቢጠቀሙበትና ተግባራቱንም የተለያዩ ብልሃቶችን በግልጽ ለማለማመድ የሚያስችል አቀራረብ ተከትለው ቢያዘጋጁ የተማሪዎች የቃላት ፍቺን የመረዳት ችግር ሊቀንስ፣ የብልሃት አጠቃቀማቸው ሊሻሻልና በሴትና በወንድ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መካከል የነበረው ልዩነት ሊቀራረብ / በተመሳሳይ ሊጎለብት ይችላል፡፡

በጥናቱ ግኝት መሰረት፤ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ከወሰዱ በኋላ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የተማሯቸውን ብልሃቶች የመጠቀም ችሎታቸው አማካይ ውጤት ከቅድመትምህርቱ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም አማካይ ወጤት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በቃላት ትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀምና ግንዛቤ ለማሳደግ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች በሚሰጣቸው ስልጠናና በሚዘጋጁት የቃላት ተግባራት መሰረት ብልሃቶቹን በአግባቡ በመተግበር ለውጤታማነቱ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶቹን አውቀው (consciously) በቃላት ትምህርት ሂደት መጠቀማቸው የቃላት ትምህርታቸውን ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመከወንና በራስመር መማርን በማጎልበት ራሳቸውን ለመርዳት ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝበው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ብልሃቶችን የሚተዋወቁበትንና የሚተገብሩበትን ልምድ ለማዳበር መጣር ይጠበቅባቸዋል::

በጥናቱ ግኝት መሰረት፤ በቅድመትምህርት የሙከራው ቡድን ሴት ተማሪዎች ያስመዘገቡት የአማርኛ ቋንቋ ቃላት እውቀት አማካይ ውጤት፣ ወንድ ተማሪዎች ካስመዘገቡት የቃላት እውቀት አማካይ ውጤት በልጦ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በድህረትምህርት ደግሞ ሴት ተማሪዎች ያስመዘገቡት የቃላት እውቀት አማካይ ውጤት፣ ወንድ ተማሪዎች ካስመዘገቡት የቃላት እውቀት አማካይ ውጤት በልጦ ቢስተዋልም፣ ከወንዶቹ ያላቸው ልዩነት ግን ጉልህ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለዚህ፣ ምንም እንኳን የተለያዩ ግለሰባዊ ልዩነቶች ያሏቸውን ተማሪዎች ፍጹም በእኩልነት

የሚያስተናግድ የማስተማር ስልት ባይኖርም የቃላት መማር ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማስተማር በሴትና በወንድ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ የሁለቱንም ጾታዎች የቃላት ችሎታ በማጎልበት ከተለምዷዊ ዘዴዎች ልዩነት ፈጥሯል። ስለሆነም፣ ብልሃቶችን በውህደት በግልጽ ማስተማር የሴትና ወንድ ተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በማመጣጠን በተመሳሳይ መንገድየሁለቱንም ጾታዎች የማሳደግ ሚና ስላለው፣ መምህራን፣ የስርዓተትምህርት/መርሃትምህርት ባለሙያዎች የቃላት ትምህርት አቀራረባቸውን ከዚህ አንጻር ቢቃኙ የተሻለ ይሆናል።

ጥናት ትኩረት ያልተሰጣቸውና በስፋት ያልተዳሰሱ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የወደፊት የጥናት ጥቆማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በዚህ ጥናት ግኝት መሰረት፣ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶቹን በግልጽ ከተማሩ በኋላ የአማርኛ ቃላትን ፍቺ የመረዳት ችሎታቸው አማካይ ውጤት በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ከቁጥጥሩ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል። ይሁን እንጂ የቃላት መማር ብልሃቶቹ በተናጠል በቃላት ችሎታ ላይ ያላቸው አስተዋጽኦ አልተፈተሸም። በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች የቃላት መማር ብልሃቶቹ በተናጠል የቃላት ፍቺን በመረዳት ችሎታ ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ በተመለከተ ጠለቅና ሰፋ ያለ ጥናት አካሂዶ መፈተሽ ያስፈልጋል። ይኸውም የትኛው ብልሃት ወይም የትኞቹ ብልሃቶች በቃላት ችሎታ ላይ የበለጠ አስተዋጽኦ እንዳለው/እንዳላቸው ጥልቅና ሰፊ ጥናት ያስፈልጋል።

እንዲሁም የዚህ ጥናት ውጤት የተገኘው በአማርኛ ቋንቋ አውድ ውስጥ በተተገበረ የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ በማስተማር በመሆኑና የብልሃቶች ስልጠና ውጤታማነት ደግሞ ከቋንቋ ቋንቋ ስለሚለያይ ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን በመማር አውዶች ውስጥም ብልሃቶቹ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ችግር ለመፍታት የሚኖራቸው አስተዋጽኦ ቢፈተሽ የብልሃቶቹን የቋንቋ ወሰን ተሻጋሪነት ሚናና ባህርያት ለማወቅ ያስችላል።

በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውጤት በአንድ የክፍል ደረጃ በውስን የመማሪያ ክፍሎች ብቻ ተተግብሮ የተገኘ ከመሆኑ አኳያ ውስንነት ስለሚኖረው በሌሎች የክፍል ደረጃዎችና በርከት ባሉ ናሙናዎች ረዘም ላለጊዜ ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴን ተከትሎ በመተግበር የቃላት መማር ብልሃቶቹ የቃላት ችሎታን ለማጎልበት ያላቸውን ሚና በጥልቀት ለማወቅ በቀጣይ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ጥናት ግኝት መሰረት፣ የሙከራው ቡድን ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶቹን በግልጽ ከተማሩ በኋላ የቃላት ችሎታቸውም ሆነ የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀማቸው ጨምሮ ታይቷል፡፡ ሆኖም በዚህ ጥናት የተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ችሎታ ከቃላት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ የተፈተሸው ከአጠቃላይ የቃላት መማር ብልሃቶቹ ጋር ያለው ተዛምዶ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች እያንዳንዱ ብልሃት ከቃላት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገው በOxford (1990) ከቀረቡት ስድስት ዋናዋና ምድቦች የተውጣጡ አሰራ ሁለት ብልሃቶችን ብቻ በማሰልጠን ላይ በመሆኑ በጥናቱ ውጤት ላይ የራሱ ውስንነት ስለሚኖረው በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች የተማሪዎችን ግለሰባዊ ልዩነት ከግምት ወስጥ በማስገባት ከስድስቱም ምድብ የተውጣጡ (mixed) ወይም በርካታ (multiple tyepes of strategies) ብልሃቶችን በማካተት በተለይም ልዕለ አእምራዊ ብልሃቶችን በስፋት በማካተት በሰፊ የጊዜ ገደብ የቃላት መማር ብልሃቶቹ የቃላት ችሎታን፣ የተማሪዎችን በራስ የመተማመንና በራስ መር መማርን ለማጎልበት ያላቸውን አስተዋጽኦ ጠለቅና ሰፋ ያለ ጥናት በማካሄድ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ጥናት ግኝት መሰረት፣ የሙከራው ቡድን ሴትና ወንድ ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶቹን በግልጽ ከተማሩ በኋላ በድህረትምህርት የቃላት ፈተና አማካይ ውጤታቸው መካከል ጉልህ ልዩነት አልታየም፤ ይሁን እንጂ የዚህ ጥናት ውጤት በጥቂት ናሙና ላይ ተተግብሮ የተገኘ ከመሆኑ አኳያ ውስንነት ስለሚኖረው

በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች በርከት ባሉ ናሙናዎች ተመሳሳይ የአጠናን ዘዴን ተከትሎ በመተግበር የቃላት መማር ብልሃቶቹን በግልጽ ማሰልጠን/ማስተማር በመካከላቸው የነበረውን የቃላት ችሎታ ልዩነት በማጥበብ የሁለቱንም ጸታዎች የቃላት ችሎታ በተመሳሳይ መንገድ ለማሳደግ ያለውን አስተዋጽኦ በጥልቀት ለማወቅ በቀጣይ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ቢሰጣቸውም በተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ላይ ልዩነት ከሚፈጥሩ ወይም በስልጠናው ውጤታማነት ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ በርካታ ተላውጦዎች ጸታ፣ የክፍል ደረጃ፣ ተነሳሽነት፣ የሁለተኛ ቋንቋ ክብደት፣ ቋንቋውን የሚማሩበት አላማ፣ የተማሪዎች ባህላዊ ዳራ፣ ለብልሃቶቹ ያላቸው ግንዛቤ ከመሳሰሉት ተላውጦዎች መካከል በዚህ ጥናት የተፈተሸው ጸታ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም በሌሎች ቀጣይ ጥናቶች እነዚህ ተላውጦዎች በተማሪዎች የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀምና በቃላት ትምህርት ውጤታማነት ላይ የሚፈጥሩትን ልዩነት ወይም በነዚህ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ ትኩረት ሰጥቶ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ዋቢ ጽሑፎች

በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2002) ፡፡ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን የመማር ብልሃቶች ፍተሻ፡፡ ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2004) ፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሐፍ 9ኛ ክፍል*፡፡ዱባይ፡ የአል-ጉራር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፣

ብሩክታዊት ተስፋይ፡፡ (2001) ፡፡ በመቀሌ ከተማ በሚገኙ ሦስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የቃላት ትምህርት አተገባበር ፍተሻ፡፡ ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

እሸቱ አጋ፡፡ (1997) ፡፡ በአዲስ አበባ በሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ የቃላት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ግምገማ፡፡» ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

ንጋቱ አሰፋ፡፡ (2000) ፡፡ በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ምርምራ፡፡ ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

ደረበ ሙሉ፡፡ (1999)፡፡ «በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቃላት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፡፡» ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

Ahmed, M. (1989). *Vocabulary Learning Strategies*. In P. Meara (ed.) Beyond Words pp. 3_14. London: BAAL/CILT.

Aktekin, N. and Guven, S. (2013). Examining the Impact of Vocabulary Strategy Training on Adult ESL Students. *Mersian Univrsity Journal of the facalty of Education*, Vol.9, Issue 2, pp.339-352.

Alderson, J. C., Clapham, C. & Wall, D. (1995). *Language Test Construction and Evaluation*. Cambridge: Cambridge University Press.

Alderson, J.C. (2005). *Diagnosing Foreign Language Proficiency: The interface between Learning and Assessment*. New York: The Tower Building.

Allen, V.F. (1983). *Techniques in Teachining Vocabulary*. Oxford: Oxford Univrsity Press.

Alseweed, M.A. (2000). *The Effects of Proficiency and Training on the Word-Solving Strategies of Arab EFL Readers.(* Unpublished Ph.D. Dessertaion).Universityof Essex, Colchester.

Bacon, S. (1992). The Relationship between Gender, Comprehension, Processing Strategies, and Cognitive and Affective Response in Second-Language Listening. *Modern Language Journal*. 76: 160-178.

Banisaeid, M. (2013). Comparative Effect of Memory and Cognitive Strategies Training on ESL Intermediate Learners Vocabulary Learning. *International Journal of English Language Teaching.* Vol. 6, N. 8.

Bornay, N. (2011). Explicit Strategy Training in Vocabulary Learning for beginning Spanish Students. *International Review of Social Sciences and Humanities.* Vol. 4. Issue 3.

Boyle, J.P. (1987). Sex Differences in Listening Vocabulary. *Language Learning*. 37(2), 273- 284.

Brown, A. L., Armbruster, B. B., and Baker, L. 1986. The role of Metacognition in Reading and Studying. In J. Orasanu (Ed.), *Reading comprehension: From Research to Practice* pp. 49-75. Hillsdale, N.J.: Erlbaum.

Brown, C. and Perry, F.L. (1991). Acomparison of Three Learning Strategies for ESL Vocabulary Learning. *Research and Teaching ELT Journal*, Vol. 25, No. 2, pp. 655-670.

Brown, H.D. (2000). *Principles of Language Learning and Teaching.* Cambridge: Cambridge University Prentice-Hall.

Brown, H.D. (1994). *Principles of Language Learning and Teaching.* Cambridge: Cambridge University Prentice-Hall.

Candlin, C.N. (1988). Preface. In Ronald Carter and M. McCarthy (eds.) *Vocabulary and Language Teaching*. London: Longman.

Carrell, P.L, Paris, B.G and Liberto, J.C. (1989). Metacognitive Strategy Training for ESL Vocabulary Learning. *A Journal of Research In Language Studies*, Vol.23, No.3, PP. 647- 668.

Carter, R. and McCarthy, M. (1998). *Vocabuly and Language Teaching*. London: Longman.

Catalon, R, M. J. (2003). Sex Differences in L2 Vocabulary Learning Strategies. *International Journal of Applied Linguistics*, 13(1), 54-57.

Chamot, A. U. (1987). The learning strategies of ESL Students. *Learner strategies in Language Learning*, 71-83.

Chamot, A .U. (2005). Language Learning Strategy Instruction: Current Issues and Trends. *Annual Review of Applied Lingustics*, Vol.25, N0.2, pp.112-125.

Channel, J. (1988). Psycholinguistic Consideration in the Study of L2 Vocabulary Acquisition In R. Carter, and M. McCarthy (eds.*). Vocabulary and Language Teaching pp.229-378*. London: Longman.

Coady, J. (1997). L2 Vocabulary A quisition: A Synthesis of Research. In J.Coady and Th.Hukin (Eds.), *Second Language Vcabulary Aquisition: A Rational for Pedagogy pp.273-91*. Cambridge: Cambridge University Press.

Cohen, A. (1990). *Language Learning: Insights for Learners, Teachers, and Researchers*. Boston: Newbury House, Heinle & Heinle

Cohen, A. (1998). *Strategies in Learning and Using a Second Language*. London: Longman:

Cohen, A. and Aphek, E. (1980). Retention of Second Language Vocabulary Overtime: Investigating the Role of Mnemonic Associations. *System*. Vol.8, pp.221-235.

Ehrman, M.E, Leaver, B.L. and Oxford, R. (2003). Abrief over view of individual difference in Second Language Learning. *System: An International Journal of Educational Technology And Applied Linguistics*. Vol.31, No.4, pp.313-330.

Ellis, R. (1994). *The Study of Second Language Aquisition.* New York: Oxford Univrsity Press.

Ellis, R. (1985). *Undestanding Second Language Aquisition*. New York: Oxford Univrsity Press.

Fan, M. (2003). Frequency of use, Perceived, usefulness, an Actual usefulness of Second Language Vocabulary Strategies:A study of Hong Kong Learners. *Modern Language Journal*, 8 , 222-224

Gairns, R. and S.Redman. (1986). *Working with Words: A Guide to Teaching and Learning Vocabulary*. Cambridge: CUP.

Gillen, J., & Hall, N. (2003). The emergence of early child hood literacy. *Handbook of early childhood literacy*, 3-12.

Gu, Y. (1994). Vocabulary Learning Strategies of Good and Poor Chinese ESL Learners. In N. Bird, P. Falvey, A.B.Tsui, D.M. Allison and McNeill (Eds.). *Language and Learning pp. 376- 401*. Uk: University of Hong Kong.

Gu, Y. (2003).Vocabulary Learning in a Second Language: Person, Task, Context and Strategies. Teaching English as a Second Language. *TESOL Quarterly*, 7(2).

Gu, Y. and Johnson, R.K. (1996). *Vocabulary Learning Strategies and Language Learning out comes.* Uk: University of Hong kong.

Griffiths, C. (2003). Patterns of language learning strategy use. *System*, *31*(3), 367- 383.

Hamzah, M.S.G, Kalipour,R. & Abdullah, S.K. (2009).Vocabulary Learning Strategies of Iranian under graduate ESL Studens and its relation to their vocabulary Size. *European Journal of Social Science*, Vol.11, pp.39-50

Han, Y. (2014). *Foreign Language Vocabulary Learning Strategies: Patterns of use among college students.* (Unpublished PhD Dissertation). Submitted to the Graduate Faculty of Auburn University. Auburn: Alabama.

Harmer, J.(1991*). The Practice of English Language Teaching*. New York: Longman Group UK Limited.

Hatch, E.and Brown, C. (1995). *Vocabulary, Semantic & Language Education.* Cambridge : Cambridge University Press.

Jurkovic, V. (2006). Vocabulary Learning Strategies in an ESP Context. *TESOL Quarterly,* 2 (1), 23-32

Jones, B. F., Palincsar, A. S., Ogle, D. S., and Carr, E. G. (1987). *Strategic Teaching and Learning: Cognitive instruction in the Content areas.* Alexandria, Va.: Association for Supervision and Curriculum Development.

Kilickaya, F. and KrajkaC, J. (2010).Comparetive usefulness of on line and Traditional Vocabulary Learning. *TOJET,* 9 *(*2), 55-63.

Koda, K. (1996). L2 Word recognition Research: A critical review. *The Modern Language Journal*, Vol.*80* (4), 450-460.

Kojic-Sabo, I. and Lightbown, P.M. (1999). Students' Approaches to Vocabulary Learning and their Relationship to Success. *The Modern Language Journal*. 83 (ii):176-192.

Krzysztof, K. (2014). Investigating the Relationship between the use of Vocabulary Learning Strategies and English Language attainment of Adam Mickiewicz University EFL students. *Poland Journal of Social Studies*. Vol. 2 (3), 273-291.

Lantolf, J. P. (2006). Sociocultural theory & L2: State of the art. *Studies in Second Language Acquisition, 28*(01), 67-109.

Lawson, J.M. and Hogben, D. (1996). The Vocabulary-Learning Strategies of Foreign Language Students. *Language Learning*. 46 (1):101-135.

Leaver, B. L, Ehrman, M. & Shekhtman, B. (2005). *Acheiving success in Second Language Aquisition.* UK: Cambridge Univrsity Press.

Leki, L. and Carson, J.G. (1994). Students Perception of English for Academic Purpose Writting Instruction Writting Needs Across The Disciplines. *TESOL Quarterly*, 28, 81- 101.

Lightbown, P.M. and Spada, N. (2006). *How Language are Learned.* New York: Oxford University Press.

Macaro, E. (2001). *Learnining Strategies in Foreign and Second Languge Class room*. London: Continuum.

Mahdavi, M. (2014). Metacognitive Strategy Training and Vocabulary Learning in an Input- Poor Enviroment. *International Journal of Multidispilinary and Current Research.*Vol.2

McCarthy, M. (1990).*Vocabulary*. Oxford: Oxford University Presss.

McCrostie, J. (2007).Exammining Learner Vocabulary Note Books. *ELT Journal*, 61(3), 24

Mitchell, R., Myles, F., & Marsden, E. (2013). *Second Language Learning Theories*. Routledge.

Morra, S. and Camba, R. (2009). Vocabulary Learning in Primary School Children: Working Memory and Long -term Components. *Jouenal of Expermental Child Psychology*, 104 (2), 156-178.

Muijs, D. (2004). *Doing Quantitative Research In Education*. London: Sage Publications.

Mizumoto A., &. Takeuchi, O. (2009). Examining the Effectiveness of Explicit instruction of Vocabulary Learning Strategies with Japanese EFL University Students. *Language Teaching Research*, 13(4), 425-449.

Naiman, N.Frohlich, M.stern, H.H.and Todesco, A. (1978). *The Good Language Learner*. Toronto, Ontario Institute for Studies in Education.

Nation, P. (1990). *Teaching and Learning Vocabulary*. New York: Newbury House Publisher.

Nation, P. (2000). Learning Vocabulary in Lexical Sets: Dangers and Guidelines. *TESOL Journal*. 9 (2): 6-10.

Nation, P. (2001). *Learning Vocabulary in Another Language.* Cambridge: Cambridge Univrsity Press.

Nunan, D. (1991). *Language Learning Methodology*. London: PrenticeHall.

Nyikos, M. (1990). Sex-Related Differences in Adult Language Learning: Socialization and Memory Factors. *The Modern Language Journal*. 74(iii): 274-287.

Nyikos, M. and Fan, M. (20007). Areview of Research on Vocabulary Learning Strategies. In A. Cohen and Macaro (Eds.), *Language Learner Strategies (pp.251-273).*Oxford: Oxford Univrsity Press.

Okada, M., Oxford, R. L., & Abo, S. (1996). Not all alike: Motivation and Learning Strategies among Students of Japanese and Spanish in an Exploratory Study. *Language Learning Motivation: Pathways to the new century,* 105-119.

O'mally, J.M. and Chamot A.U. (1990). *Learning Strategies in Second Language Acquisition.* Cambridge: Cambridge University Press.

O'mally, J.M. (1987) .The Effects of Training in the Uses of Learning Strategies on Acquiring English as a Second Language, In A. wenden and J.Rubin (eds.*). Learner Strategies in Language Learning (PP.372-392).* New York: Prentice-Hall International.

O'Malley, J.M., Chamot, A.U., Russo, P., & Kupper, L. (1985). Learning Strategies Applications with Students of English as a Second Language. *TESOL Quarterly*. 19 (3): 557-584.

Oxford, R. (1990). *Language Learning Strategies*: What Every Teacher Should Know. New York: Newbury House Publishers.

Oxford, R. (2003). Toward A more Systematic Model Pf L2 Learner Autonomy. In Palfreyman, P. and Smith, R. (Eds.). *Learner Autonomy Across Culture: LanguageEducation Perspectives, (pp.75-91).* Great Britain: Pagrave Macmillan.

Oxford, R. and Crookall, D. (1989). Research on Languge Learning Strategies: Methods, Findings and Instructional Issues. *The Modern Language Journal*, 73(iv), 404-419.

Oxford, R. and Ehrman, Medline E. (1995).Adults Language Learning Strategies in an Intensive Foreign Language in the United States. *System: An International Journal of Educational Technology and Applied Linguistics.* London: Bergamann Press Ltd.Vol.23, No.3, pp.359-

Oxford, R. and Nyikos, M. (1989). Variables Affectining Choice of Language Learning Strategies by Univrsity Students. *Modern Languge Journal, 73*, 291-300.

Oxford, R. and R.C. Scarcella. (1994). ASecond Language Vocabulary learning Among Adults: State of the Art in Vocabulary Instruction. *System*.Vol.22, No. 2, pp.213-14.

Oxford, R., & Schramm, K. (2007). Bridging the gap between Psychological and Sociocultural Perspectives on L2 Learner Strategies. In Cohen, A. D., & Macaro, E. (Eds.). (2007). *Language earner Strategies: Thirty years of research and practice*. Oxford, UK: Oxford University Press.

Oxford, R. (1989). Use of Language Strategies: A Synthesis of Studies with Implications Strategy Training. *An International Journal of Educational Technology and Applied Linguistics*. Vol.23, No.3, pp.359-385. London: Bergmann Press Ltd.

Pavicic´, V. (2008). *Vocabulary Learning Strategies and Foreign Language Acquisition.* London: Cromwell Press Ltd.

Philip, B. (2005.). *Towards a Social-Motivational Metacognitive Strategy Instruction Model: Theory and Practice*. (Unpublished PhD Thesis). Universitiy Kebangsaan: Malaysia, Bangi.

Politzer, R. L. (1983). An exploratory study of self-reported language learning behaviors and their relation to achievement. *Studies in second language acquisition, 6*(1), 54-68.

Pressley, M., & McCormick, C.B. (2007). *Child and Adolescent Development for educators*. New York, NY: The Guilford Press.

Qian, D. (2002). Investigating The Relation ship Between Vocabulary Knoweledge and Academic P erformance: An Assessment Perspective. *Language Learning*, 52(3), pp.513-536.

Rajaee, M. (2013). The Effect of Strategy Training on the Vocabulary Development of ESL Learners in Public High School of Iran. *Theory and Practice in Language Studies, Vol.3*. No.11, pp.2061-2066.

Read, J. (2000). *Assessiing Vocabulary*. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C. and C.Lockhart.(1996). *Reflective Teaching in Second Language Classroom.* Cambridge: Cambridge Univrsity Press.

Rodríguez, M. and Sadoski, M. (2000). Effect of Rote, Context, Keyword, and Context/ Keyword Methods on Retention of Vocabulary in EFL Classrooms. *Language Learning*. 50 (2): 385-412.

Ronald, J. (2001). Learning about Learning from Dictionaries. *The Modern Language Journal.* 79 (I), 15-28.

Rubin, J.(1987). Learner Strategies: Theoretical Assumption, Research History and Typology. In A. wenden and J. Rubin (eds.). *Learner Strategies in Language Learning. (pp.107-160).* Cambridge: Cambridge University Press.

Rudzka, B.and Channel, J. (1986).The Words You Need: More Words You Need. *English Language Teaching*.Vol,40, No.1, pp.75-76 .

Scarcella, R. C., & Oxford, R. L. (1992). *The Tapestry of Language Learning: The Individual in the Communicative Classroom.* Boston: Heinle and Heinle.

Schmitt, N. (1997). Vocabulary Learning Strategies. In N.Schmitt and M.McCarthy (Eds.). *Vocabulary: Discription, Acquisition and Pedagogy pp. 199-228.* Cambridge: Cambridge University Press.

Schmitt, N. (2000). *Vocabulary in Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Scholfield, P.J. (1997). Vocabulary Reference Works in Foreign Language Learning. In Schmitt, N. and McCarthy, M. (Eds.), *Vocabulary: Description, Acquisition and Pedagogy* (pp. 279-302). Cambridge: Cambridge University Press.

Seid Mohammed. (2012). *Effects of cooperative learning on Reading Comprehension achievement in EFL and Social Skills of grade 10 Students* .(Unpublished

doctorial dissertation). Addis Ababa University, School of Graduate Studies, Addis Ababa.

Sokmen, A. J. (1997).Current Trends in Teaching Second Language Vocabulary. In N.Schmitt and M. McCarthy (Eds.), *Vocabulary: Discription, Aquisition and Pedagogy* pp.237-58). Cambridge: Cambridge University Press.

Stern, H.H. (1983). *Fundamental Concepts of Language Teaching*. Oxford: Oxford University *Press.*

Stoffer, I. (1995) *University Foreign Language Students' Choice of Vocabulary Learning Strategies as Related to Individual Difference Variables*.(Unpublished PhD Dissertation). University of Alabama.

Takač, V. P. (2008). *Vocabulary Learning Strategies and Foreign Language Acquisition.* Vol. 27. Multilingual matters

Takeuchi, O., Griffiths, C., & Coyle, D. (2007). Applying Strategies to Contexts: the Role of Individual, Situational, and Group Differences. In A. D. Cohen, & E. Macaro (Eds.), *Language Learner Strategies: Thirty Years of Research and Practice* pp.69-92. Oxford, UK: Oxford University Press.

Tassana-Ngam, I. (2004). *The Effect of Vocabulary Learning Strategies Training on Thai University Students'Word Retention in Second Language Classroom*. (Unpublished PhD Dissertation). Kasetsart University of Essex, Bangok, Thailand.

Tonjes, M.J. (1991). *Secondary Reading, Writing, and Learning.* Boston: Allyn and Bacon.

Tudor, Ian. (1996*). Learner-Centeredness as Language Education*. Cambridge: Cambridge University Press.

Vermeer, A. (2001). Breadth and Depth of Vocabulary in Relation to L1/ L2 Acquisition and Frequence of Input. *Applied Psycholinguistics*, 22, (2), 217-234.

Vygotsky, L.S. (1978). *Mind in Society: The Development of Higher Psychological processes.* Cambridge, MA: Harvard University Press

Wenden, A. (1987). Conceptual Background and Utility. In A. wenden. And J.Rubin (eds.*). Learner Strategies in Language Learning (pp.234-398).* Cambridge: Cambridge University Press.

Wenden, A. (1991).*Learner Strategies for Learner Autonomy*. New York: Prentice -Hall International (UK) Ltd.

Wenden, A.and J.Rubin. (1987). *Learning Strategies in Language Learning.* New York: Prentice Hall International (UK) Ltd.

Wharton, G. (2000). Language Learning Strategy: Use of Bilingual Foreign Language Learners in Singapore. *Language Learning .A Journal of Research in Language Studies.* University of Michigan: Blackwell Publishers.Vol.5o, Nos.1-3, pp.203.243.

Wilkins, D.A. (1972). *Linguistics in Language Teaching*. London: Edward Arnold.

Williams, M.and Burden, R. (1997). *Psychology for Language Teachers*: *Asocial Constructivist Approac*h. Cambridge: Cambridge University Press.

Wong, M. (2005). Language Learning Strategies and Language Self-efficacy Investigating the Relationship in Malasia. *RELC Journal*, 36 (3), 245-269.

Yang, C. (2014). Vocabulary Learning Strategy Instruction with Chinese EFL Learners: An Intervention Study. *International Review of Social Sciences and Humanities* Vol. 6, No. 2, pp. 186-200.

Young, M.C. (1996). *Listening Comprehension Strategies Used by University Level Chinese Students Learning English as a Second Language. (*Unpublished Ph.D Dissertation). University of Essex, Colchester.

Yin, C. (2008). *Language Learning Strategies in Relation to Attitudes, Motivations, and Learner Beliefs: Investigating Learner Variables in the Context of English as a Foreign Language in China.* (Unpublished PhD Dissertation). University of Maryland, College Park

Zhao, N. (2009). Metacognitive Strategy Traning and Vocabulary Learning of Chinese College Studens. *Journal of English Language Teaching. Vol.2, No.4*

Zimmerman, C.B. (1997).Historical Trends in Second Language Vocabulary Instruction. In J. Coady and T. Huckin (Eds.). *Second Language Vocabulary Acquisition: A rational for Pedagogy, pp.5-19.* Cambridge: Cambridge Univerrsity Press.

አባሪዎች

አባሪ ሀ ፡ የዋናው ጥናት የመከራው ቡድን የቅድመና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት

የተማሪው መ/ቁ	ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት	ድህረ ትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት
1	13	18
2	13	14
3	12	17
4	13	18
5	11	15
6	12	13
7	12	11
8	12	15
9	11	17
10	12	15
11	13	13
12	14	14
13	9	16
14	12	16
15	11	15
16	15	16
17	11	11
18	12	15
19	15	22
20	15	17
21	14	20
22	12	17
23	15	15
24	13	18
25	15	19
26	15	16
27	15	20
28	16	14
29	15	14
30	15	22
31	12	23
32	13	16
33	14	14
34	14	18
35	11	16
36	16	23
37	15	20
38	15	19

አባሪ ለ፡- የዋናው ጥናት የቁጥጥሩ ቡድን የቅድመና ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት

መለያ ቁጥር	ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና ውጤት	ድህረትምህርት የቃላት ፈተና ወጤት
39	10	10
40	10	11
41	12	13
42	12	11
43	12	12
44	12	11
45	13	12
46	10	11
47	10	12
48	13	14
49	11	13
50	11	11
51	12	10
52	11	11
53	11	13
54	12	13
55	10	14
56	13	11
57	12	15
58	11	11
59	13	14
60	12	14
61	16	20
62	14	18
63	14	14
64	16	14
65	15	16
66	14	16
67	16	19
68	14	12
69	14	11
70	17	16
71	16	16
72	19	18
73	19	19

አባሪ ሐ፡- በዋናው ጥናት ወቅት የቃላት ፈተናው ጥያቄዎች የመለየት ብቃት

የጥያቄ ቁጥር	ከከፍተኛ የመለሱት	ከዝቅተኛ የመለሱት	የመለየት ብቃት
1	13	5	0.61
2	16	7	0.56
3	12	5	0.58
4	12	3	0.75
5	10	4	0.6
6	13	5	0.61
7	11	5	0.54
8	14	6	0.57
9	9	4	0.55
10	12	3	0.75
11	11	6	0.45
12	8	6	0.33
13	11	7	0.36
14	13	5	0.61
15	10	4	0.6
16	15	5	0.76
17	9	3	0.66
17	10	4	0.6
18	12	4	0.6
19	8	4	0.5
20	11	6	0.45
21	9	5	0.44
22	12	5	0.58
23	13	6	0.53
24	13	5	0.61
25	9	4	0.55
26	11	7	0.36
27	13	4	0.69
28	12	7	0.41
29	14	6	0.57
30	10	4	0.6

አባሪ መ፡- በዋናው ጥናት ወቅት የቃላት ፈተናው ክብደት ቅለት ደረጃ

የጥያቄ ቁጥር	በትክክል የመለሱት ብዛት	የክብደት ቅለት
1	49	0.67
2	34	0.46
3	51	0.69
4	43	0.58
5	37	0.50
6	50	0.68
7	28	0.38
8	56	0.77
9	35	0.47
10	41	0.56
11	32	0.43
12	18	0.25
13	48	0.65
14	39	0.53
15	29	0.39
16	43	0.58
17	33	0.45
18	31	0.42
19	40	0.54
20	36	0.49
21	28	0.38
22	50	0.68
23	37	0.50
24	35	0.47
25	42	0.57
26	32	0.43
27	30	0.41
28	41	0.56
29	38	0.52
30	46	0.63

አባሪ ሠ፡- የዋናው ጥናት የሙከራው ቡድን ቅድመና ድህረትምህርት የብልሃት አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት

መለያ ቁጥር	ቅድመትምህርት	ድህረትምህርት
1	37	49
2	48	41
3	41	47
4	42	49
5	24	45
6	34	36
7	43	30
8	40	45
9	50	47
10	52	45
11	37	35
12	39	41
13	34	46
14	27	46
15	37	45
16	47	46
17	31	28
18	40	42
19	41	54
20	53	47
21	45	52
22	30	47
23	42	43
24	50	49
25	50	50
26	36	45
27	48	52
28	48	41
29	34	41
30	49	55
31	35	55
32	45	45
33	52	38
34	36	47
35	34	45
36	29	56
37	31	51
38	22	50

አባሪ ረ፡- በዋናው ጥናት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅ

በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፡-

ማሳሰቢያ ፡- ውድ ተማሪዎች የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ «የቃላት መማር ብልሃቶችን በግልጽ ማሰልጠን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታና የብልሃት አጠቃቀም ለማዳበር ያለው አስተዋጽኦ» በሚል ርዕስ ለሚካሄድ ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በዚህ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ አላማ አይውልም፡፡ በመሆኑም መጠይቁን በምትሞሉበት ጊዜ ማንንም ሰው ሣታማክሩ በመመለስና ለምትሰጡት መልስ ታማኝ በመሆን ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት የበኩላችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ በመጨረሻም ውድ የትምህርት ጊዜያችሁን መሥዋዕት በማድረግ ላደረጋችሁልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡

ክፍል አንድ ፡- የግል ሁኔታ

ክፍል ————— ዕድሜ ————— ፆታ —————

የት/ቤት ስም ————— አፍ መፍቻ ቋንቋ —————

ክፍል ሁለት፡- የጽሑፍ መጠይቅ መመሪያ

ከዚህ በታች እንግዳ(አዳዲስ) ቃላትን ለመማር የሚያግዙ ብልሃቶችን የሚገልፁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ዐረተፍ ነገር በጥሞና አንብበሽ (ህ) የተጠቀሰውን ብልሃት አጠቃቀምሽን(ህን) አስመልክቶ ከቀረቡት ሁልጊዜ ፣ አብዛኛውን ጊዜ ፣በመጠኑ ፣ በፍፁራሽ ከሚሉት አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መርጠህ(ስ) ከምርጫው ፊት ለፊት በሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ “✓” ምልክት በማድረግ መልሽ(ሽ)፡፡ ለእያንዳንዱ ሐሳብ ትክክል ወይም ስህተት መልስ የለውም፡፡ እያንዳንዳችሁ በታማኝነት መርጣችሁ የምትመልሱት መልስ ነው ትክክለኛ መልስ ስለሆነም ይህ ፈተና ስላል ሆነ እውነተኛ አጠቃቀምሽን(ህን) የሚገልፀውን መርጠሽ(ህ) መልሽ(ስ)፡፡

የመመዘኛዎች መግለጫ

5 -ሁል ጊዜ እጠቀማለሁ

4 - አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ

3 - በመጠኑ እጠቀማለሁ

2- አብዛኛውን ጊዜ አልጠቀምም

1.በፍፁራሽ አልጠቀምም

ተ.ቁ	የቃላት መማር ብልሃቶች(vocabulary learning strategies)	5	4	3	2	1
1	የተማርኳቸውን ቃላት ለማስታወስ፣ በቃል ክፍላቸው (ለምሳሌ፣ ስሞችን በአንድ ወገን፣ግሶችንና ቅጽሎችን በሌላ ወገን፣ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውን ለምሳሌ፣ ማዘን፣ መከፋት፣ በትርጉም ተቃራኒነታቸው ወዘተ.. ባንድ ላይ እመድባቸዋለሁ(የትውስታ ብልሃት)					
2	አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ ዐረፍተ ነገር እየመሰረትኩ አጠናለሁ (የትውስታ ብልሃት)					
3	በንባብ ሂደት (ለምሳሌ፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት ፣መጽሐፍ ወዘተ.) ሳነብ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመረዳት የህይወትልምዴን /አጠቃላይ እውቀትን በመጠቀም፣ የቃላቱን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በመፈለግና የቃል ክፍሉን በመመልከት ከአገባባቸው እገምታለሁ፡፡ (የአካካሽ ብልሃት)					
4	የአማርኛን ቃል ተመሳሳይ ትርጉም ወዳለው ኦሮምኛ ቃል በቀጥታ ተርጉሜ አገናዝባለሁ (ለምሳሌ፣ «አንበሳ» የሚለውን ቃል «ሌንጫ ብሎ መተርጎም) የአእምሯዊ ብልሃት)					
5	የቃላት እውቀቴን ለማዳበር ልሳነ ዋህድ(የአማርኛ) መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ (የአእምሯዊ ብልሃት)					
6	ጠቃሚ ናቸው ብዬ የማስባቸውን አዳዲስ ቃላት ተመሳሳይ ፣ተቃራኒ ፍቺ፣ፍካሪያዊ፣ እማሪያዊ ፍቺ እና አጠቃቀም በመፈለግ በማስታወሻ ደብተሬ አደራጅቼ በመያዝ አጠናለሁ፡፡ (የአእምሯዊ ብልሃት)					
7	በአጻጻፍ አንድ ሆነው በንበት በሚለያዩ ቃላት (ለምሳሌ፣ ላልተውና ጠብቀው በሚነበቡ) ቃላት ላይ ልምምድ አደርጋለሁ ፣ የተማርኳቸውን ቃላት እንደገና በማቀናበር የተለያዩ ዐረፍተ ነገሮችን እየመሰረትኩ እለማመዳለሁ፣					
8	በቃላት ትምህርቴ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ (መሻሻል) ማሳየት አለማሳየቴን ለማረጋገጥ ራሴን በራሴ እገመግማለሁ					
9	የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመረዳት የተከተልኩት መንገድ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መሆኑን በማረጋገጥ ስህተቴን በራሴ እለያለሁ፤					
10	ያልገባኝን ወይም እርግጠኛ ያልሆንኩበትን ቃል ትርጉም መምህሬን ፣ጓደኞቼን ወይም ሌሎች ሰዎችን ጠይቄ እረዳለሁ					
11	የቃላት ችሎታዬን ለማዳበር ከጓደኞቼ ጋር በመተባበር በጥንድ ወይም በቡድን እለማመዳለሁ/ እሰራለሁ					
12	የአማርኛ ቃላትን ስማር ለአዳዲስ ቃላት የምሰጣቸው ፍቺዎች ትክክል ላይሆኑ ቢችሉም በትምህርት ሂደት መሳሳት ያለ በመሆኑ ያለፍርሃት መከራዬን እቀጥላለሁ፤					

አባሪ ሰ፡- የዋናው ጥናት ቅድመትምህርት የቃላት ፈተና

የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የቃላት ችሎታን በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ቅድመትምህርት ፈተና (30 ነጥብ)

መለያቁጥር -------ክፍል -------የአፍ መፍቻ ቋንቋ------ ጾታ------- የትምህርት ቤት ስም----------የተፈቀደው ጊዜ አንድ ሰዓት ተኩል

አጠቃላይ መግለጫ፡- ይህ ፈተና የቃላት እውቀትን ለመለካት የተዘጋጀ ነው፡፡ ጥያቄዎቹም በዐ.ነር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተመሰሳይ ፍቺ መፈለግን፣ በትርጉም ልዩ የሆነውን ቃል መለየትን፣ ያልተሟሉ ዐረፍተ ነሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላትን፣ያልተሟላ አንቀጽን በተገቢ ቃላት ማሟላትን፣ጠብቆ ወይም ላልቶ በመነበብ የተለያየ ፍቺ የሚሰጡ ቃላትን መለየትና ፍካሪያዊ ፍቺ መፈለግ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ፈተናው ሰባት ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል አንድ 4 ጥያቄዎች፣ በክፍል ሁለት 4 ጥያቄዎች፣ በክፍል ሦስት 6 ጥያቄዎች፣ በክፍል አራት 4 ጥያቄዎች፣ በክፍል አምስት 6 ጥያቄዎች፣ በክፍል ስድስት 4 ጥያቄዎችና በክፍል ሰባት ሁለት ጥያቄዎች ተካትተዋል፡፡ ሁሉንም ጥያቄዎች በትዕዛቸውዛ መሰረት ትክክለኛ መልሳቸውን መርጣችሁ በማክበብ መልሱ፡፡

መመሪያ አንድ፡- ከስሩ ከተሰመረበት ቃል ጋር በፍቺ የሚመሳሰለውን ቃል / ሐረግ የያዘውን ፊደል በመምርጥ አክብቢ /ብ፡፡

1.ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል <u>በቁሙ</u> ሲታይ በጽሑፍ የቀረበን የቋንቋ ጥበብ ይመለከታል፡፡ ሀ. በተዘዋዋሪ ለ. በደፈናው ሐ. በዝርዝር መ. በጥልቀት

2.ጋሬጣው የአለሚቱን ቀሚስ <u>ሸረከተው</u> ፡፡
ሀ. ገረደፈው ለ. ቀደደው ሐ. ከካው መ. መዘዘው

3. ገመቹ እናቱ በመኪና መገጨታቸውን ድንገት ሲሰማ <u>ጉልበቱ ቁጠማ ሆነበት</u>፡፡ የተሰመረበትን አባባል ከሚከተሉት የትኛው ይተካዋል?

ሀ. ደከመ ለ. ለመለመ ሐ . ተብረከረከ መ. ደነገጠ

4. ስነ-ጽሑፍ የሰው ልጅ በህይወቱ ከሚያልፍበት ውጣ ውረድ ይቀዳል፡፡

ሀ. ይወሰዳል ለ. ይጻፋል ሐ. ይጨመቃል መ. ይከወናል

መመሪያ ሁለት፡- በፍቺ ልዩ የሆነውን ቃል የያዘውን ፊደል በመምርጥ አክብቢ /ብ፡፡

5. ሀ. ስንክሳር ለ. ችግር ሐ. መከራ መ. ድሎት

6. ሀ. መንቀፍ ለ.መተቸት ሐ. ማውገዝ መ. መደገፍ

7. ሀ. አርታኢ ለ. አድማጭ ሐ. አንባቢ መ. ተደራሲ

8. ሀ. አሳረገ ለ. ቋጨ ሐ. ጨረሰ መ. ከፈተ

መመሪያ ሦስት፡- ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ዐረፍ ነገሩን ሊያሟላ የሚችለውን ተገቢ ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ ፡፡

9. ጦርነቱ እያደር ----------ስለመጣ መክሶ መቋቋም እንደማይችል ተገነዘበ፡፡

ሀ. እየተፋፋመ ለ. እየከሰመ ሐ. እየተፍረከረከ መ. እየጎረፈ

10. ዳባ ፍቅረኛው ድንገት ወደ ዱባይ ስለሄደች ሆዱ----------፡፡

ሀ. ወላወለ ለ. ወሰነ ሐ. ተሸበረ መ. ደነደነ

11. ገመቹ በወንድሙ ላይ የፈጸመውን አሳዛኝ ድርጊት የአካባቢው ሰው ስለሰማበት ----

ሀ. ተንቆራጠጠ ለ. ተከፋ ሐ. ተንቀባረረ መ. ተሸማቀቀ

12. በረሃብ የተጠቃ ወገኑን ---------- ቆርጦ ተነሳ ፡፡

ለ. ለማጥገብ ለ. ለማካካስ ሐ. ለመታደግ መ. ለማጉረስ

13. አውሮፕላኗ ----------ሄደች፡፡

ሀ. እየበረረች ለ. እየሮጠች ሐ. እየፈጠነች መ. እየተጣደፈች

14. ጎርፉ ዛፉን ----------፡፡

ሀ. አንጠለጠለው ለ. ገነደሰው ሐ. ፈነቀለው መ. ጎመደው

መመሪያ አራት ፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ቀጥተኛ(መዝገበ ቃላዊ) ፍቻቸውን የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ

15. መረን ፣ሀ. አይናፋር ለ. ቁጡ ሐ. ልቅ መ. ብልሀ

16. ጥገት ፣ሀ. ጊደር ለ. ያልወለደች ላም ሐ. የማትታለብ ላም መ. የምትታለብ ላም

17. ሾመ ፣ሀ. ሻረ ለ. መረጠ ሐ. አጸደቀ መ. አነሳ

18. አሞካሸ .ሀ. አቆላመጠ ለ. አጥላላ ሐ. አወደሰ መ. አመሰጋገነ

መመሪያ አምስት፡- ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥንቃቄ በማንበብ የተጓደሉትን ቃላት ከምንባቡ በፊት ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንቀጹን ሊያሟላ የሚችለውን ተገቢ ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ ከቁጥሮቹ ጎን ባለው ክፍት ቦታ አስፍሪ/ር፡፡

ሀ. ማጥ ለ. ደባ ሐ. ባዝራ መ. አግቦ ሠ . መሰሪ ሰ. አልባሌ

ሰውዬው19 ይምሰል እንጂ፣ የዋዛ አይደለም፡፡ ሀበትን በተመለከተ 20 ከድንጉላ አለው፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል? በጎ የማያስብ 21 ነው፡፡ በሰው ላይ 22 ይፈጽማል፣23 መናገር ይወዳል፡፡ ይህ ደግሞ መልሶ እራሱን 24 ውስጥ ስለከተተው መውጫ አጥቶ ሲኳትን ይታያል፡፡

መመሪያ ስድስት፡- በእያንዳንዱ የጥያቄ ቁጥር ትይዩ ከተሰጡ አራት አማራጭ ቃላት መካከል በውስጡ በሚገኝ ድምፅ ጠብቆ ወይም ላልቶ መነበብ ምክንያት የተለያየ ፍቺ የሚሰጠውን ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ

25. ሀ. ሴሰኛ ለ. አዛባ ሐ. ቀዘፈ መ. ፋቀ

26. ሀ. ንስሃ ለ. አለኝታ ሐ. ፈራና መ. አጠና

27 ሀ.ወጥ ለ. ናዳ ሐ. ፈር መ. ግዑዝ

28 ሀ. ወገረ ለ. ዘመመ ሐ. ድህነት መ. ገሞራ

መመሪያ ሰባት ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ፍካሪያዊ ፍቻቸውን የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ

29. ተልባ ፣ሀ.የቅባት እህል ለ. ጥራጥሬ ሐ. ጊዜ አይቶ የሚከዳ መ. ታማኝ

30. ቤት.፣ሀ. ትዳር ለ. የሰውልጅ መኖሪያ ሐ. ጣሪያና ጊድጊዳ ያለው መ. ማረፊያ

አባሪ ሸ፡- የዋናው ጥናት ድህረትምህርት የቃላት ፈተና

የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የቃላት ችሎታን በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ድህረትምህርት ፈተና (30 ነጥብ)

መለያ ቁጥር -------ክፍል -------የአፍ መፍቻ ቋንቋ------ጸታ --------የትምህርት ቤት ስም----------የተፈቀደው ጊዜ አንድ ሰዓት ተኩል

አጠቃላይ መግለጫ፡- ይህ ፈተና የቃላት እውቀትን ለመለካት የተዘጋጀ ነው፡፡ ጥያቄዎቹም በዐ.ነር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተመሰሳይ ፍቺ መፈለግን፣ በትርጉም ልዩ የሆነውን ቃል መለየትን፣ ያልተሟሉ ዐረፍተ ነሮችን በተገቢ ቃላት ማሟላትን፣ያልተሟላ አንቀጽን በተገቢ ቃላት ማሟላትን፣ጠብቆ ወይም ላልቶ በመነበብ የተለያየ ፍቺ የሚሰጡ ቃላትን መለየትና ፍካሪያዊ ፍቺ መፈለግ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ፈተናው ሰባት ንዑሳን ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል አንድ 6 ጥያቄዎች፣ በክፍል ሁለት 4 ጥያቄዎች፣ በክፍል ሦስት 6 ጥያቄዎች፣ በክፍል አራት 2 ጥያቄዎች፣ በክፍል አምስት 6 ጥያቄዎች፣ በክፍል ስድስት 4 ጥያቄዎችና በክፍል ሰባት አራት ጥያቄዎች ተካትተዋል፡፡ ሁሉንም ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሰረት ትክክለኛ መልሳቸውን መርጣችሁ በማክበብ መልሱ፡፡

መመሪያ አንድ፡- ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ዐረፍ ነገሩን ሊያሟላ የሚችለውን ተገቢ ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ ፡፡

1. ጦርነቱ እያደር ----------ስለመጣ መክቶ መቋቋም እንደማይችል ተገነዘበ፡፡

   ሀ. እየተፋፋመ ለ. እየከሰመ ሐ. እየተፍረከረከ መ. እየጎረፈ

2. ዳባ ፍቅረኛው ድንገት ወደ ዱባይ ስለሄደች ሆዱ----------፡፡

   ሀ. ወላወለ ለ. ወሰነ ሐ. ተሸበረ መ. ደነደነ

3. ገመቺ በወንድሙ ላይ የፈጸመውን አሳዛኝ ድርጊት የአካባቢው ሰው ስለሰማበት ----

   ሀ. ተንቆራጠጠ ለ. ተከፋ ሐ. ተንቀባረረ መ. ተሸማቀቀ

4. በረሃብ የተጠቃ ወገኑን ---------- ቆርጦ ተነሳ ፡፡

ለ. ለማጥገብ ለ. ለማካካስ ሐ. ለመታደግ መ. ለማጉረስ

5. አውሮፕላኗ ----------ሄደች፡፡

ሀ. እየበረረች ለ. እየሮጠች ሐ. እየፈጠነች መ. እየተጣደፈች

6. ጎርፉ ዛፉን ----------፡፡

ሀ. አንጠለጠለው ለ. ገነደሰው ሐ. ፈነቀለው መ. ጎመደው

መመሪያ ሁለት ፡- ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ቀጥተኛ(መዝገበ ቃላዊ) ፍቻቸውን የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ፡፡

7. <u>መረን</u> . ሀ. ልቅ ለ. ብልሀ ሐ. አይናፋር መ. ቁጡ

8. <u>ጥገት</u> . ሀ. የምትታለብ ላም ለ. ያልወለደች ላም ሐ. የማትታለብ ላም መ. ጊደር

9. ሾመ .ሀ. አጸደቀ ለ. አነሳ ሐ. ሻረ መ. መረጠ

10. <u>አሞካሸ</u> . ሀ. አጥላላ ለ. አቆላመጠ ሐ. አመሰጋገነ መ. አወደሰ

መመሪያ ሦስት፡- ከስሩ ከተሰመረበት ቃል ጋር በፍቺ የሚመሳሰለውን ቃል / ሐረግ የያዘውን ፊደል በመምርጥ አክብቢ /ብ፡፡

11. ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል <u>በቁሙ</u> ሲታይ በጽሑፍ የቀረበን የቋንቋ ጥበብ ይመለከታል፡፡ ሀ. በዝርዝር ለ. በጥልቀት ሐ. በተዘዋዋሪ መ. በደፈናው

12. ጋሬጣው የአለሚቱን ቀሚስ <u>ሸረከተው</u> ፡፡

ሀ. ቀደደው ለ. ገረደፈው ሐ. መዘዘው መ. ከካው

13. ገመቹ እናቱ በመኪና መገጨታቸውን ድንገት ሲሰማ <u>ጉልበቱ ቁጠማ ሆነበት</u>፡፡የተሰመረበትን አባባል ከሚከተሉት የትኛው ይተካዋል?

ሀ. ደነገጠ ለ. ተብረከረከ ሐ . ለመለመ መ. ደከመ

14. ስነ-ጽሑፍ የሰው ልጅ በህይወቱ ከሚያልፍበት ውጣ ውረድ <u>ይቀዳል</u>፡፡

ሀ. ይከወናል ለ. ይጨመቃል ሐ. ይጻፋል መ. ይወሰዳል

መመሪያ አራት ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ፍካሪያዊ ፍቻቸውን የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ

15. ተልባ. ሀ.ታማኝ ለ. ጥራጥሬ ሐ. ጊዜ አይቶ የሚከዳ መ. የቅባት እህል

16. ቤት. ሀ. ማረፊያ ለ. የሰውልጅ መኖሪያ ሐ. ጣሪያና ጊድጊዳ ያለው መ. ትዳር

መመሪያ አምስት፡- ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥንቃቄ በማንበብ የተጓደሉትን ቃላት ከምንባቡ በፊት ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንቀጹን ሊያሟላ የሚችለውን ተገቢ ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ ከቁጥሮቹ ጎን ባለው ክፍት ቦታ አስፍሪ/ር፡፡

ሀ. ማጥ ለ. ደባ ሐ. ባዝራ መ. አግቦ ሠ . መሰሪ ሰ. አልባሌ

ሰውዬው 17 ይምሰል እንጂ፣ የዋዛ አይደለም፡፡ ሀበትን በተመለከተ 18 ከድንጉላ አለው፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል? በጎ የማያስብ 19 ነው፡፡ በሰው ላይ 20 ይፈጽማል ፣ 21 መናገር ይወዳል፡፡ ይህ ደግሞ መልሶ እራሱን 22 ውስጥ ስለከተተው መውጫ አጥቶ ሲኳትን ይታያል፡፡

መመሪያ ስድስት፡- በእያንዳንዱ የጥያቄ ቁጥር ትይዩ ከተሰጡ አራት አማራጭ ቃላት መካከል በውስጡ በሚገኝ ድምፅ ጠብቆ ወይም ላልቶ መነበብ ምክንያት የተለያየ ፍቺ የሚሰጠውን ቃል የያዘውን ፊደል በመምረጥ አክብቢ/ብ፡፡

23. ሀ. ፋቀ ለ. አዛባ ሐ. ቀዘፈ መ. ሴሰኛ

24. ሀ. ንስሃ ለ. አለኝታ ሐ. ፈራና መ. አጠና

25. ሀ. ግዑ ለ. ናዳ ሐ. ፈር መ. ዝወጥ

26 ሀ. ወገረ ለ. ዘመመ ሐ. ድህነት መ. ገሞራ

መመሪያ ሰባት፡- በፍቺ ልዩ የሆነውን ቃል የያዘውን ፊደል በመምርጥ አክብቢ /ብ፡፡

27. ሀ. ድሎት ለ. መከራ ሐ. ችግር መ. ስንክሳር

28. ሀ. መደገፍ ለ.ማውገዝ ሐ. መተቸት መ. መንቀፍ

29. ሀ. ተደራሲ ለ. አንባቢ ሐ. አድማጭ መ. አርታኢ

30. ሀ. ከፈተ ለ. ጨረሰ ሐ. ቋጨ መ. አሳረገ

አባሪ ቀ፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ማሰልጠኛ መሳሪያ

ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለጥናቱ ተግባሪ መምህር የተዘጋጀ የማስተማሪያ መሳሪያ (ጽሑፍ)

ለጥናቱ የተመረጡት መምህርት ይህን ማንዋል በመጠቀም የቃላት መማር ብልሃቶችን ስልጠና በሙከራ ቡድኑ ክፍል ውስጥ ለመተግበር ለአምስት ቀናት (ከየካቲት 21- 22፣ 24-26 ቀን 2009 ዓ.ም) በቀን ለሁለት ሰዓት በአጥኚዋ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መግቢያ የዚህ ክፍል ዋና አላማ መምህሯ/ሩ የቃላት መማር ብልሃቶቹን ተጠቅማ ቃላትን እንድታስተምር/ እንዲያስተምር ስለቃላት መማር ብልሃቶች ምንነትና ጠቀሜታ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራት/ እንዲኖረው ለመርዳት ነው፡፡

1.**የቃላት መማር ብልሃቶች ብያኔ፡-** የቃላት መማር ብልሃቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማር እና መዝግቦ ለማቆየት ራሳቸውን ለመርዳት የሚጠቀሙባቸው ስልቶች ናቸው፡፡

2. **የቃላት መማር ብልሃት አይነቶች**

ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

ቀጥተኛ ብልሃቶች ተማሪዎች በቀጥታ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት እየተሳተፉ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የተተኳሪውን ቋንቋ ቃላት እንዲማሩ በቀጥታ የሚያግዟቸው /የሚጠቀሙባቸው/ ብልሃቶች ናቸው፡፡ ቃላትን ለመማር ተገቢ የሆኑ ቀጥተኛ ብልሃቶችም የትውስታ ብልሃቶች፣ አእምሯዊ ብልሃቶች እና አካካሽ ብልሃቶች ናቸው፡፡

የትውስታ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት በአዕምሮ መዝግቦ በመያዝ እና የረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር በአስፈላጊው ጊዜ አስተውሶ ለመጠቀም የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢ የሆነው የትውስታ ብልሃት **በአዕምሮ ውስጥ ምስል የመፍጠር ብልሃት** ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ብልሃቶች በውስጡ ያካትታል ለምሳሌ፡-

1.መቦደን፡- ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንድነት በመቦደን ከአዕምሮ ጋር በማያያዝ ለትውስታ የማመቻቸት ብልሃት ነው፡፡ አንድ ጊዜ የተማሯቸውን አዳዲስ ቃላት በቀላሉ አስታውሶ ለመጠቀም ለምሳሌ በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸው /ተያያዥነታቸው ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ ቃላትን በአንድላይ፣ በቃል ክፍላቸው ለምሳሌ ስሞችን ወይም ግሶችን በአንድ ላይ፣ በፍቺ ተመሳሳይነታቸው ለምሳሌ ሞቃት፣ እሳት፣ ወይም ተቃራኒነታቸው ቀዝቃዛ፣ በረዶ፣ በአንድ ላይ መቦደን፣ አንድሰው ስለአንድ ነገር ያለውን ስሜት ለመግለጽ የሚያገለግሉ ቃላትን በአንድ ላይ ለምሳሌ መጥላት፣ መውደድ ወዘተ፣ በሰዋስዋዊ አገባባቸው ለምሳሌ አንተ፣ አንቺ፣ እሱ፣ እሷ፣ እነሱ ወዘተ .ትርጉም ባለው መንገድ በማደራጀት ከአዕምሮ ጋር በማያያዝ ለትውስታ መማቻቸት፡፡

2. አዳዲስ ቃላትን በዐውድ ውስጥ ማስገባት፡- አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በሚሰጥ ቃላዊ እና ጽሑፋዊ የሃሳብ ልውውጥ ውስጥ መጠቀም ወይም የተለያዩ ዐ.ነገሮችን በመመስረት ከቃላቱ ጋር ለተከታታይ ረጅም ጊዜያት የመዝለቅ ብልሃት ነው፡፡ አዳዲስ ቃላትን በተለያየ ዐ.ነገር ውስጥ (አውድ) መጠቀም የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ለማስፋትና በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት ለረጅም ጊዜ አስታውሰው እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል፡፡

አእምሯዊ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው የተተኳሪውን (የሁለተኛ) ቋንቋ ቃላትን በቀጥታ በመጠቀም ተረድቶ እና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ተማሪው በተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ተግባራት ላይ በቀጥታ የሚጠቀምባቸው መሰረታዊ አዕምሮታዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው፤

1.**መለማመድ፡-** የንበት፣ የመጥበቅና መላላት ወዘተ ልምምድ ማድረግ፤ በአንድ አይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ ማድረግ፣ የቃላት አመሰራረትን በተደጋጋሚ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስራት ልምምድ በማድረግ፣ የቃል ክፍሎችን በመለየት ልምምድ በማድረግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ይህ ብልሃት ከአእምሯዊ ብልሃቶች በጣም መሰረታዊ ብልሃት ነው

2..**ማስታወሻ መያዝ፡-** በተለያየ አጋጣሚ የሚያገኙትን የአዳዲስ ቃላትን ፍቺና አጠቃቀም በአንድ የቃላት ማስታወሻ ደብተር መዝግቦ በመያዝ ማጥናትና መለማመድ፣ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያገጥሙ አዳዲስ ቃላትን መዝግቦ በመያዝ ፍቺና አጠቃቀማቸውን ከተለያየ ምንጭ በመፈለግ የቃላት ችሎታን ለማዳበር የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው፡፡ ተማሪዎች ማስታወሻ ሲይዙ ለምሳሌ የአማርኛ ቋንቋ አዳዲስ ቃላትን በአፍ መፍቻ ያለውን አቻ ፍቺ፣ ተመሰሳይ ፣ተቃራኒ፣ ፍካሪያዊ ፍቺ ፣ የቃል ክፍሉንና የቃላቱን ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ወይም መዝገበ ቃላት ሳይመለከቱ ቃላቱ በራስ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ ወዘተ. ያካትታል

3. **መተርጎም፡-** የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ኦሮምኛ ቃል በመተርጎም ወይም ከአፍ መፍቻ (ከኦሮምኛ) ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚጠቀም ብልሃት ነው፡፡

4. **ልሳነዋህድ መዝገበቃላት መጠቀም፡-** መዝገበ ቃላት መጠቀም አዳዲስ ቃላት ለመማር በጣም ጠቃሚ እና ተጨባጭ ምንጭ ነው፡፡ ተማሪዎች መዝገበ ቃላት ሲጠቀሙ ልሳነ ዋህድ (በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈ መዝገበ ቃላትን) መጠቀም

የተሻለ የቃላት እውቀታቸው እንዲሰፋ ይረዳቸዋል፡፡ ምክንያቱም ላሳነ ክልኤ (ለምሳሌ ከአሮምኛ ወደ አማርኛ ወይም ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛና ኦሮምኛ) መዝገበ ቃላት ሁልጊዜ የሚሰጠን ቃሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ ብቻ ነው፡፡ ልሳነ ዋህድ ወይም በአማርኛ የተጻፈው መዝገበ ቃላት ግን የቃሉን ፍቺ፣ በቃላቱ የተመሰረቱ ዐረፍተ ነገሮችን ምሳሌ ፣ ተመሳሳይ ፣ ተቃራኒ ፍቺ እና የቃል ክፍሉን ወይም ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ስለሚያካትት የቃላትን መደበኛ ፍቺ እና አጠቃቀም ለይተው እንዲያውቁ ስለሚረዳቸው በተለይ ቋንቋውን በጽሑፋዊ አፍልቆት ለመጠቀም በጣም ጠቃሚ ብልሃት ነው፡፡

አካካሽ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች በቃላት ዕውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦት ሂደት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመቋቋም የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃት

1. **የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ የመገመት ብልሃት ነው፡፡** እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ሁለት **የተለያዩ ፍንጮችን (መረጃዎችን) ስነልሳናዊ (በቋንቋው ያለንን እውቀት) እና ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጮችን** በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን **ትርጉም ለመገመት የሚረዱት** ናቸው፡፡ **ስነልሳናዊ ፍንጭ** መጠቀም ማለት ለምሳሌ በንባባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን የቃል ክፍላቸውን በመለየት፣ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያን በመለየትና ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ መገመት ማለት ሲሆን **ኢ-ስነ ልሳናዊ ፍንጭ (እውቀት) በመጠቀም** ማለት ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ያለንን የቀደመ /ዳራዊ እውቀትን ወይም አጠቃላይ እውቀትን መሰረት በማድረግ የአዳዲስ ቃላት ፍቺ ከአውድ በመገመት መረዳት ነው፡፡

ኢ-ቀጥተኛ ቃላትን የመማር ብልሃቶች

በዚህ ክፍል የሚመደቡ ብልሃቶች ቀጥተኛ ባልሆነ/በተዘዋዋሪ/ መንገድ ለቃላት ዕውቀት መዳበር የሚያግዙ ናቸው፡፡ የተማሪውን ዘወትር የተተኳሪውን ቋንቋ

ተግባራት በቀጥታ መስራትን የሚጠይቁ አይደሉም፡፡ ነገር ግን በተለያዩ መንገዶች ለቃላት ትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የትምህርታቸውን ሂደት ለመምራት እና ለማመቻቸት የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ ሁለት ብልሃቶች **ልዕለ አዕምሮታዊ፣ ማህበራዊ ብልሃቶችና ስሜትነኪ የቁጥጥር ብልሃቶች ቀርበዋል**

ልዕለ አዕምሯዊ ብልሃቶች

ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመቆጣጠር፣ በአጠቃላይ ያሳየውን ለውጥ እና የትምህርቱን ውጤት ለመገምገም የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃት ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች የመማር አቅጣጫቸውን ያልለዩ፣ የመማር አቅድ የሌላቸው፣እድገታቸውን /መሻሻላቸውን የማይቆጣጠሩ፣ ስኬታቸውን የማይገመገሙና ቀጣይ የመማር አቅጣጫቸውን የማያውቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ ብልሃት ተማሪዎ የቀረጹትን አላማ ለማሳካት፣ የተጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ውጤታማነት በመገምገም የወደፊት የመማር አቅጣጫቸውን የሚወስኑበት በመሆኑ በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ማስቻል ተገቢ ነው፡፡ በልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች በተማሪው የሚከናወኑ ተግባራትም፡-

1.ራስን መቆጣጠር፡- ቃላትን በትክክለኛ ወይም በተሳሳተ መንገድ እየተማረ መሆኑን በራስ በመከታተል በቃላት ትምህርት ሂደት የራስን ስህተት በራስ መለየት፤

2. ራስን መገምገም፡- የቃላት ትምህርቱን ውጤት በመፈተሽ ካለፈው የበለጠ መሻሻል (ለውጥ) ማሳየት አለማሳየቱን ራስን በራስ የመገምገም ወይም ተማሪዎች የቃላት መማር ሂደታቸውን በራሳቸው የሚገመግሙበት ብልሃት ነው፡፡

ማህበራዊ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር ቃላትን እንዲማር የሚረዱት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ቋንቋን

ለመማር የሌላ ሰው ተሳትፎ አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ተማሪዎችም ለቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት በጋራ ሊሰሩ ይገባል። ስለሆነም ማህበራዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ፣ ግልፅ ያልሆነላቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን እንግዳ ቃላት ትርጉም መምህራንን ወይም ሌሎች ሰዎችን እየጠየቁ እንዲማሩ የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው። በተማሪዎች የሚተገበሩ ማኅበራዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው።

1. **መጠየቅ**፡- የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም መምህራንን፣ የክፍል ጓደኛን ወይም ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ የቃላት እውቀትን ማዳበር።

2. **ከብጤ ጋር መተጋገዝ**፡- ከክፍል ጓደኛ ጋር በቡድን ወይም በጥንድ በመስራት (ማጥናት) የቃላቱን ፍቺ በመለማመድ የቃላት ዕውቀትን ማሻሻል።

ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች

ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት፣ ዝንባሌና መነቃቃት ጋር የተያያዙ ናቸው። ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሁም አሉታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር) የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው። Oxford (1990) እንዳስረዱት ስኬታማ (ጥሩ) የቋንቋ ተማሪዎች ስለመማር ስሜታቸውና ዝንባሌያቸው እንዴት እንደሚቆጣጠሩ የሚያውቁ ናቸው። አይይዘውም መጥፎ ስሜት ለውጥን ሊገታ ይችላል ጥሩ ስሜት ደግሞ መማርን ይበልጥ ስኬታማ (ውጤታማ)ና አስደሳች ሊያደርገው ይችላላ። ለቃላት ትምህርት ውጤታማነት የሚያግዙ ስሜት ነክ ቁጥጥር ብልሃቶችም የሚከተሉ ናቸው።

ጎላፊነትን መቀበል፡- በትምህርቱ ሂደት መሳሳት እንደሚኖር በማመን ከባድ የቃላት ተግባራትን ስሜትን ተቆጣጥሮ ለማከናወን ጎላፊነትን ተቀብሎ መሳተፍ ለምሳሌ በሐሳብ ልውውጥ ሂደት ተገቢ ቃላትን መጠቀም ስለማልችል እሳሳታለሁ የሚል ስጋትን አስወግዶ ያለ ፍርሃት በንቃት መሳተፍ፤

ክፍል ሁለት፡- የዚህ ክፍል አብይ አላማ መምህሯ/መምህሩ የቃላት መማር ብልሃቶቹን ተጠቅማ /ተጠቅሞ ቃላትን እንድታስተምር/ እንዲያስተምር ለመርዳት ነው፡፡

❖ የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና አተገባበር ቅደም ተከተል

የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ የሚመራበት ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ (ቅደም ተከተል) አለው፡፡

ደረጃ 1፡- ታላሚውን ብልሃት ማስተዋወቅ/ (Explain the strategy)፡-

ተማሪዎች አዲስ ከሚቀርበው የቃላት መማር ብልሃት/ቶች ምንነት፣ ጠቀሜታ እና አተገባበር ጋር በግልጽ የሚተዋወቁበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የእያንዳንዱ የቃላት መማር ብልሃቶች ምንነት፣ ብልሃቶቹን መቼ? እንዴት? ለምን? እንደሚጠቀሙባቸው ሰፊና ጥልቅ ማብራሪያ መስጠት፡፡

ደረጃ 2፡- ሞዴል ሆኖ ማለማመድ/ ማሳየት (Modeling)፡- በትምህርቱ ሂደት መምህሩ ሞዴል በመሆን ለልምምድ የቀረበውን ታላሚ ብልሃት አጠቃቀም በተግባር ተግባራቱን (መልመጃዎችን) እየሰራ ለተማሪዎቹ ማሳየት

ደረጃ 3፡-ብልሃቶቹን በትብብር መተግበር ፡- በዚህ ደረጃ መምህራንና ተማሪዎች በጋራ የቃላት መማር ብልሃቶችን በመጠቀም የቃላት ተግባራትን ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የራሳቸውን የብልሃት አጠቃቀም የመገምገም ችሎታ እንዲያዳብሩ ብልሃቶቹን በመተግበር ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮችና የወሰዷቸውን መፍትሄዎች የተማሩትን ብልሃት ምን ያህል እንደተረዱት ለመገምገም በብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ከመምህራን ጋር በጋራ በመወያየት የትኛው ክፍል እንዲከለስላቸው እንደሚፈልጉ፣ ብልሃቶቹን ወደፊት ለመተግበር ያላቸውን ተነሳሽነት የሚገልጹበት ሁኔታም ይመቻቻል፡፡

ደረጃ 4፡-በድጋፍ ማለማመድ/ የብልሃቶቹን አተገባበር መምራት (Scaffolding instruction)፡-

የተማሪዎችን የብልሃት አጠቃቀም ክህሎት ለማዳበር ተማሪዎቹ በደረጃ አንድ ስለ አንድ የቃላት መማር ብልሃት ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ ከተገለጸላቸውና በደረጃ ሁለት በመምህሩ ሞዴልነት (Modeling)ና በደረጃ ሦስት ከመምህሩ ጋር በጋራ የተለማመዷቸውን ብልሃቶች በስፋት በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው የተለያዩ ተግባራትን እየሰሩ በራሳቸው በብልሃቱ አተገባበር በጋራ እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ብልሃቶቹን በሚተገብሩበት ጊዜ እየተከታተሉ መምራት (ድጋፍ መስጠት) ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም የማለማመዱ ድጋፍ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሃላፊነቱን ለተማሪዎች በመስጠት ራሳቸውን ችለው ከተማሯቸው ብልሃቶች እንደየ አግባብነታቸው እየመረጡ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይገባል፡፡

ደረጃ 5.፡-ብልሃቶቹን ወደ አዳዲስ ተግባራት እያሸጋገሩ ራሳቸውን ችለው ሲተገብሩ ማበረታታት፡- ይህ ደረጃ በዋናነት ተማሪዎቹ ብልሃቶቹን ራሳቸውን ችለው መተግበራቸውን የማጠናከር አላማ ያለው፡፡ በመሆኑም በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለው (Independently) የተማሯቸውን ብልሃቶች በመጠቀም ወይም ወደ አዳዲስ ተግባራት በማሸጋገር የቃላት ተግባራትን በግላቸው ሲያከናውኑ ብልሃቶቹን እንደ አስፈላጊነታቸው መርጠው እንዲጠቀሙና ሙሉ ሃላፊነት እንዲሰማቸው አቅጣጫ በማስያዝ አግባብ ያለው ግብረ መልስ በመስጠት ያበረታታል፡፡

- የቁጥጥር ቡድኑ ግን በስልጠናው ሂደት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ተመሳሳይ የቃላት ተግባራት ምንም አይነት የቃላት መማር ብልሃቶች ስልጠና ሳይሰጣቸው (በተለመደው የቃላት ማስተማሪያ ዘዴ/በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት አቀራረብ) ይማራል፡፡

በዚህ በተለመደው አቀራረብ ተማሪዎች የሚሰሯቸው ተግባራት የቃላቶቹን ፍቺ ማወቅ አለማወቃቸውን የሚፈትኑ እንጂ የቃላቶቹን ፍቺ እንዴት መረዳት እንዳለባቸው ብልሃቶችን የሚተዋወቁባቸው አይደሉም፡፡ በአብዛኛው የመምህሯ/ሩ

ድርሻም የቃላቱን ፍቺ በትክክል መረዳት አለመረዳታቸውን መገምገምና እውቀትን ማስተላለፍ እንጂ የቃላቱን ፍቺ እንዴት እንደሚረዱ በተለይም የቃላት መማር ብልሃቶችን ተጠቅሞ የቃላት ትምህርት እንዴት እንደሚከወን አያስረዱም፡፡

በመጀመሪያ የቃላት መማር ብልሃቶችን ለተማሪዎች ለማስተዋወቅ የሚከተሉት ተግባራት በእያንዳንዱ ብልሃት ትምህርቱ እስኪ ጠናቀቅ በቅድሚያ ይከናወናሉ፤

- ተማሪዎችን ውጤታማ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን የቃላት መማር ብልሃቶች እንዲገልጹ መጠየቅ ፣
- ውጤታማ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች በሰሌዳ ላይ መጻፍ፣
- ተማሪዎች የሰጡትን መልስ በአስራ ሁለቱ ብልሃቶች ስር መመደብ
- ስለእያንዳንዱ ብልሃት ምንነት፣ ጠቀመሜታና አተገባበር ግልጽ ማብራሪያ መስጠት፡

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል አንድ፡- አዳዲስ ቃላትን በአውድ መጠቀም

- **አዳዲስ ቃላትን በአውድ መጠቀም፡-** ይህ ብልሃት በአንድ ወቅት የተማራችኋቸውን ወይም ያጋጠሟችሁን ቃላት ፍቺ ለረሯም ጊዜ አስታውሳችሁ ለመጠቀምና ቃላት በተለያየ አውድ ውስጥ ሲገቡ ያላቸውን ፍቺም እንድትረዱ ስለሚያግዛችሁ የቃላት ችሎታችሁን ለማስፋት የሚረዳችሁ ብልሃት ነው፡፡
- **አዳዲስ ቃላትን በአውድ የመጠቀም ብልሃትን** ለመጠቀመም አዳዲስ ቃላትን ትርጉም በሚሰጥ ቃላዊና ጽሑፋዊ የሃሳብ ልውውጥ ውስጥ መጠቀም ወይም የተለያዩ ዐ.ነገሮችን በመመስረት ከቃላቱ ጋር ለተከታታይ ረጅም ጊዜያት የመዝለቅ ብልሃት ነው፡፡
- **አዳዲስ ቃላትን በአውድ የመጠቀም** ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት ከመማሪያ መጽሐፋችሁ የተወሰኑ ቃላትን በመውሰድ በተለያየ አውድ

(ዐ.ነገር) ውስጥ እያስገባሁ አሳያችኋለሁ፡፡ እባካችሁ ከመማሪያ መጽሐፋችሁን ገጽ-- ላይግለጡና ተከታተሉኝ፡፡ ምሳሌ፡- ተጧጧፈ
ጦርነቱ እያደር ተጧጧፈ፡፡ ተጋጋለ
ገበያው ተጧጧፈ፡፡ ደራ

- **ብልሃቱን በጋራ በመጠቀም የሚከተሉትን ቃላት በተለያየ አውድ ውስጥ እንጠምባቸዋለን፡፡**

ተግባራት፡- ተዘፈቀ፣ ዘፈዘፈ

ልጁ ውሃ ውስጥ ተዘፈቀ፡፡ ገባ፣ ተነከረ፣ ሰጠመ

ልጁ የማይወጣው ጣጣ ውስጥ ተዘፈቀ፡፡ መከራ፣ እዳ ውስጥ ገባ

አበበ ልብሱን ውሃ ውስጥ ዘፈዘፈ፡፡ ነከረ፣ ለብዙ ሰዓት ውሃ ውስጥ አቆየ

አበበ ዛፉን ዘፈዘፈው፡፡ በብዛት ቆረጠ፣ ከመረ

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል በቀላሉ አስታውሳችሁ ለመጠቀም ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? የአዳዲስ ቃላትንበአውድ የመጠቀም ብልሃትን መቼና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

- **አዳዲስ ቃላትን በአውድ የመጠቀም** ብልሃትን በመጠቀም ቀደም ሲል የተማሯችኋቸውን ቃላት ፍቺ ሌላ ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ቃላቱን በተላየየ አውድ (ዐ.ነገር) ውስጥ በማስገባት አሳዩ፡፡ ብልሃቱን በምትጠቀሙበት ጊዜ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ፤
ተግባራት፡- መስክ፣ ሙዳይ፣ አሳረገ (የዘጠነኛ ክፍል መማሪ መጽሓፍ ገጽ፣103)
-ብልሃቱን እንዴት እንደተጠቀማችሁበት በተግባር የሚያሳየኝ?
- **የተማራችሁትን አዳዲስ ቃላትን በተለያየ አውድ የመጠቀም ብልሃት በመጠቀም በግላችሁ** የተማራችኋቸውን ቃላት ለረዥም ጊዜ አስታውሶ

ለመጠቀም የሚከተሉትን ቃላት በተለያየ ዐ.ነገር ውስጥ በማስገባት በግላችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡ ተግባራት፡-ንብ፣ እስስት፣ ርግብ፣ ቋንጣ፡፡
-ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄዎች ያሏት/ያሉት?

እኔ በናንተ ኮርቻለሁ፣ እናንተም በራሳችሁ ልትኮሩ ይገባል፡፡ የተማራችሁትን ቃላት ፍቺ ለመረዳትና በዘላቂነት በአእምሯችሁ መዝግቦ ለማቆየት አይነተኛ ብልሃቶች ተጠቅማችኋል፡፡

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል ሁለት፡- የመቦደን ብልሃት

- .መቦደን፡- ይህ ብልሃት በአንድ ወቅት የተማርሻቸውን/ የተማርካቸውን ቃላት ሌ ላጊዜ አስታውሰሽ/ህ ለመጠቀም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንድነት በመቦደን ከአእምሮሽ/ህ ጋር በማያያዝ ለትውስታ ለማመቻቸት የሚጠቅምሽ/ህ ብልሃት ነው፡፡
- የመቦደን ብልሃትን ለመጠቀምም ለምሳሌ በርዕስ ጉዳይ ግንኙነታቸው /ተያያዥነታቸው ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ ቃላትን በአንድላይ፣ በቃል ክፍላቸው ለምሳሌ ስሞችን ወይም ግሶችን በአንድ ላይ፣ በፍቺ ተመሳሳይነታቸው ወይም ተቃራኒነታቸው፣ አንድሰው ስለአንድ ነገር ያለውን ስሜት ለመግለጽ የሚያገለግሉ ቃላትን በአንድ ላይ በመመደብ መጠቀም ትችያለሽ/ህ

- የመቦደን ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት ከመማሪያ መጽሐፋችሁ ከዚህ በፊት የተማራችኋቸውን የተወሰኑ ቃላት ፍቻቸውን ከሰራሁ በኋላ ሌላ ጊዜ አስታውሼ ለመጠቀም በቃል ክፍላቸውና በስዋሰዋዊ አገባባቸው እየቦደንኩ አሳያችኋለሁ፡፡ እባካችሁ ከመማሪያ መጽሐፋችሁን ገጽ--ላይግለጡና ተከታተሉኝ፡፡ ተግባራት፡- አደናቀፈ ተደናቀፈ፣ ድንቅፍቅፍ፣ አደናቃፊ፡፡

ለምሳሌ1 **በቃል ክፍል**

ግስ	**ቅጽል**
አደናቀፈ	ድንቅፍቅፍ
ተደናቀፈ	አደናቃፊ

ምሳሌ 2 በስዋስዋዊ አገባባቸው

አንተ፣ እሱ፣ እነሱ

አንቺ፣ እሷ፣ እናንተ፣ እኛ፣ እኔ

- **ብልሃቱን በጋራ በመጠቀም የሚከተሉትንቃላት ፍቻቸውን ካሰየን በኋላ በፍቺ ተመሳሳይነታቸውና ተቃራኒነታቸው እንመድባቸዋለን፤**
  ተግባራት፡- ሞቃት፣ በረዶ፣ እሳት፣ ቀዝቃዛ፣

በፍቺ ተቃራኒነት	**በፍቺ ተመሳሳይነት**
ቀዝቃዛ፣ በረዶ	እሳት፣ ሞቃት

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል በቀላሉ አስታውሳችሁ ለመጠቀም ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? የመቦደን ብልሃትን መቼና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

- **የመቦደን ብልሃትን በመጠቀም** ቀደም ሲል የተማሯችኋቸውን ቃላት ፍቺ ሌላ ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ፍቻቸውን ከሰራችሁ በኋላ በቃል ክፍላቸው መድቡ፡፡ ብልሃቱን በምትጠቀሙበት ጊዜ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ፤

  ተግባራት፡- ጠፊ፣ ተጣጣፊ፣ አጣጣፊ፣ ማጣጣፍ

-ብልሃቱን እንዴት እንደተጠቀማችሁበት በተግባር የሚያሳየኝ?

- **የተማራችኋቸውን የመቦደን.ብልሃቶች በመጠቀም ወይም የራሳችሁን ሌላ የመቦደን ብልሃት በመፍጠር ለምሳሌ** ቃላትን በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸው፣ ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ቃላት እንድ ላይ በመቦድን ወዘተ ወደፊት ለናንተ የሚመቻችሁን ብልሃት በመጠቀም ተግባራትን ስሩ። ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄዎች ያሏት/ያሉት?
  ተማሪዎች ዛሬ ትልቅ ስራ ሰርታችኋል። የተማራችሁትን ቃላት ፍቺ በዘላቂነት በአእምሯችሁ መዝግቦ ለማቆየት የመቦደን ብልሃቶችን በመጠቀም አሳይታችኋል።

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል ሦስት፡-.መለማመድ

- ***መለማመድ፡-*** የመጥበቅና መላላት በአንድ አይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ ማድረግ፣ የቃላት አመሰራረትን በተደጋጋሚ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስራት፣ የቃል ክፍሎችን በመለየት ልምምድ በማድረግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚጠቀማችሁ ብልሃት ነው። ይህ ብልሃት ከአእምሯዊ ብልሃቶች በጣም መሰረታዊ ብልሃት ነው።

- የመለማመድ ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት ከመማሪያ መጽሐፋችሁ የተወሰኑ ቃላት በመውሰድ ጠብቀው ሲነበቡና ላልተው ሲነበቡ ያላቸውን ፍቺ አየሰራሁ አሳያችኋለሁ። እባካችሁ ከመማሪያ መጽሐፋችሁን ገጽ 125- ላይግለጡና ተከታተሉኝ። ተግባራት፡- ሰባ፣ አካፋ፣ ጠላት
  ጫልቱ <u>ሰባ</u> ብር አበደረችኝ። ላልቶ ሲነበብ
  በጉ በጣም <u>ሰባ</u>። ጠብቆ ሲነበብ
  አበበ ደለሉን በ<u>አካፋ</u> አነሳው። ጠብቆ ሲነበብ
  ዝናቡ <u>አካፋ</u>። ላልቶ ሲነበብ

- **ብልሃቱን በጋራ በመጠቀም በሚከተሉት ቃላት ላይ ልምምድ በማድረግ ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፊቺ እናሳያለን፡፡ ተግባራት፡- አያት፣ ጠላት፣**

  ጫልቱ አያት አላት፡፡

  ጫልቱ ጠፍታ ስትሄድ ባለቤቷ አያት፡፡

  ገመቺ ባለቤቱን በጣም ጠላት፡፡

  ገመቺ ብዙ ጠላት አለው፡፡

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል ፍቺ ለመረዳት ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? በቃላት መጥበቅና መላላት ላይ ልምምድ የማድረግንብልሃትን መቼና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

- **የመለማመድ ብልሃትን በመጠቀም በተመሰሳይ ፊደል በተገነቡና በንበት በመለያየታቸው የያዙትን ፍቺ በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆናችሁ አሳዩ፡፡ ብልሃቱን በምትጠቀሙበት ጊዜ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ፤ ተግባራት፡- አጠና፣ አዳኝ፣ ዋና፣ አለ፣አባይ (የዘጠነኛ ክፍል መማሪ መጽሓፍ 103)**

-ብልሃቱን በምትጠቀሙበት ጊዜ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ፤

--ብልሃቱን እንዴት እንደተጠቀማችሁበት በተግባር የሚያሳየኝ?

- **የመለመማድ ብልሃት በመጠቀምወይም የራሳችሁን የመለማመድ ብልሃት በመፍጠር ለምሳሌ በቃላት አመሰራረት ላይ ልምምድ በማድረግ፣ የቃል ክፍሎችን በመለየት ልምምድ በማድረግ ወዘተ.. ወደፊት ለናንተ የሚመቻችሁን ብልሃት በመጠቀም በግላችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡**

  ተግባራት፡- ይመራል፣ እንስራ፣ ቀና፣ መጋዝ፣ ገና(ገጽ፣131)

  -ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄ ያሏት/ያሉት?

እኔ በናንተ ኮርቻለሁ፤ እናንተም በራሳችሁ ልትኮሩ ይገባል፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚያስችላችሁን አይነተኛ የመለማመድ ብልሃቶች ተጠቅማችኋል፡፡

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል አራት፡-መተርጎም

- **መተርጎም፡-** የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ኦሮምኛ ቃል በመተርጎም ወይም ከአፍ መፍቻ (ከኦሮምኛ) ወደአማርኛ ቋንቋ በመተርጎም የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚጠቀም ብልሃት ነው፡፡
- **የመተርጎም** ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት የቃላቱን ፍቺ በአማርኛ ለመረዳት ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ አየተረጎምኩ አሳያችኋለሁ፡፡ እባካችሁ ከመማሪያ መጽሐፋችሁን ገጽ-- ላይግለጡና ተከታተሉኝ፡፡ **ምሳሌ፡-**
  ስንዴ--ቀመዲ
  ገርበ---ገብስ
  ፈጠራ--ከለቁ
- **ብልሃቱን በጋራ በመጠቀም የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ለመረዳት ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ እየተረጎምን እንሰራለን፡፡**
  ተግባራት፡- በጠፍ ጨረቃ፣ ሀፍረትለበሰ፣ እጣፋንታ፣ ተውኔት፣ ውሃ አጣጭ (መማሪያ መጽሐፍ ገጽ፣96 ተውነት ከሚለውምንባብ ውስጥ የተወሰደ)

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል ፍቺ ለመረዳት ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? የመተርጎም ብልሃትን መቼና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

- **የመተርጎም** ብልሃትን በመጠቀም የሚከተሉትን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመረዳት በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ወደ ኦሮምኛ በመተርጎም አሳዩ፡፡ ብልሃቱን በምትጠቀሙበት ጊዜ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ፤
  ተግባራት፡- ማጨቅ፣ ፋይዳ፣ እንዲያገግም፣ ሳቢያ (የዘጠነኛ ክፍል መማሪ መጽሐፍ ገጽ፣ 124)

--ብልሃቱን እንዴት እንደተጠቀማችሁበት በተግባር የሚያሳየኝ?

- **የመተርጎም ብልሃት በመጠቀም ወይም የራሳችሁን የመተርጎም ብልሃት በመፍጠር ለምሳሌ** ከኦሮምኛ ወደ አማርኛ ወይም ወደሌላ ቋንቋ በመተርጎም ለወደፊት ለናንተ የሚመቻችሁን የመተርጎም ብልሃት በመጠቀም ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ፍቺ ለመረዳት በግላችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

  ተግባራት፡- ጉሮኖ፣ መታደግ፣ አፎት ወዘተ

  -ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄ ያሏት/ያሉት?

  ተማሪዎች ዛሬ ትልቅ ስራ ሰርታችኋል፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የመተርጎም ብልሃትን ተጠቅማችኋለሁ፡፡ የቃላትን ፍቺ የመረዳት ሂደታችሁን ለመቆጣጠር የቁጥጥርና የመገምገም ብልሃቶችን ተጠቅማችኋል፡፡

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል አምስት፡- ማስታወሻ መያዝ

- **ማስታወሻ መያዝ፡-** በተለያየ አጋጣሚ የምታገኙትን የአዳዲስ ቃላት ፍቺና አጠቃቀም በአንድ የቃላት ማስታወሻ ደብተር መዝግቦ በመያዝ ማጥናትና መለማመድ፣ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያገጥሙ አዳዲስ ቃላትን መዝግቦ በመያዝ ፍቺና አጠቃቀማቸውን ከተለያየ ምንጭ በመፈለግ የቃላት ችሎታን ለማዳበር የሚጠቅማችሁ ብልሃት ነው፡፡
- **ማስታወሻ በመያዝ ብልሃት ለመጠቀም** ተማሪዎች ማስታወሻ ሲይዙ **ለምሳሌ** የአማርኛ ቋንቋ አዳዲስ ቃላትን በአፍ መፍቻ ያለውን አቻ ፍቺ፣ ተመሰሳይ ፣ተቃራኒ፣ ፍካሪያዊ ፍቺ ፣ የቃል ክፍሉንና የቃላቱን ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ወይም መዝገበ ቃላት ሳይመለከቱ ቃላቱ በራስ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ መዝግቦ በመያዝ ማጥናትን ወዘተ. ያካትታል፡፡
- **ማስታወሻ የመያዝ** ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት ከመማሪያ መጽሐፋችሁ **ዳግመኛ ቃልኪዳን** የሚለውን ግጥም እያነበብኩ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት በማስታወሻ ደብተሬ መዝግቤ ተመሳሳይና

ፍካሪያዊ ፍቻቸውን እየፈለኩ አሳያችኋለሁ፡፡ እባካችሁ ከመማሪያ መጽሐፋችሁን ገጽ81ላይ ግለጡና ተከታተሉኝ፡፡

ምሳሌ፡- አርማ--መለያ

ክንዴን አፈርጥሜ-- ክንዴን አጠንክሬ
በርኩማ---መቀመጫ፣ መኖሪያ

- ብልሃቱን በጋራ በመጠቀም ዳግመኛ ቃልኪዳን የሚለውን ምንባብ እያነበብን የሚያጋጥሙንን አዳዲስ ቃላት በማስታወሻ ደብተራችን በመያዝ ፍካሪያዊ ፍቻቸውን እንፈልጋለን፡፡ (መማሪያ መጽሐፍ ገጽ፣81)

  ተግባራት፡- ቀንዲል፣
  በአሞጵር ታጥቂ፣
  ወገቤን አጥብቂ፣

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል ፍቺ ለመረዳት ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትን መቼና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

- ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትን በመጠቀም የሚከተሉት ቃላት በኦሮምኛ ቋንቋ ያላቸውን አቻ ፍቺ፣ በአማርኛ ቋንቋ ተመሳሳይ፣ ተቃራኒ ፍቺና አጠቃቀማቸውን በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆናችሁ በመፈለግ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግባችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

  -ብልሃቱን በምትጠቀሙበት ጊዜ ጥያቄ ካላችሁ ጠይቁ፣

  ተግባራት፡- ፍትህ፣ መንቀፍ፣ ጠረን፣ መታደግ፣ ማገገም፣ ነደለ፣ ቱጃር፣ ቅራቅንቦ፣ (መማሪያ መጽሐፍ ገጽ፣)

  --ብልሃቱን እንዴት እንደተጠቀማችሁበት በተግባር የሚያሳየኝ?

- ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትን በመጠቀም ወይም የራሳችሁን ማስታወሻ የመያዝ ብልሃት በመፍጠር ለሚከተሉት ቃላት እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቻቸውን፣ የቃል ክፍላቸውን፣ተቃራኒፍቻቸውንና ስዋስዋዊ አጠቃቀማቸውን

ከተለያየ ምንጭ በመፈለግ፣ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግባችሁ በግላችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

-ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄዎች ያሏት/ያሉት?

ተግባራት፡-ንብ፣ ምስጥ፣ ድንጋይ፣ ጉቶ፣ አህያ፣ ቋንጣ

ተማሪዎች ዛሬ ትልቅ ስራ ሰርታችኋል፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት ማስታወሻ የመያዝ ብልሃትን ተጠቅማችኋለሁ፡፡ የቃላትን ፍቺ የመረዳት ሂደታችሁን ለመቆጣጠር የቁጥጥር፣ የመገምገምና ሃላፊነትን የመቀበል ብልሃቶችን ተጠቅማችኋል፡፡

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል ስድስት፡-ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት መጠቀም

የዚህ ክፍል ዋና አላማ ተማሪዎች ልሳነዋህድ(አማርኛ-አማርኛ) መዝገበ ቃላት እንዴት እንደሚጠቀሙ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ አማርኛ መዝገበ ቃላት(2006 ዓ.ም፣ ገጽ፣ XXVi--XXVii) ውስጥ በቀረበው መመሪያ መሰረት ማሰልጠን ነው፡፡

የልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት አጠቃቀም ስልጠና ዋና አላማ፤

- ✓ ተገቢ የሆነ የልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት አጠቃቀምን ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የቃላት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ለመርዳት
- ✓ ተማሪዎችን ከልሳነ ዋህድ (አማርኛ-አማርኛ) መዝገበ ቃላት አጠቃቀምጋር ለማስተዋወቅና የልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት አጠቃቀም ክሂላቸውን የሚያዳብሩበት ሁኔታ በመፍጠር በተለይም ቃላትን ከተገቢ ፍቻቸው ጋር ማዛመድ እንዲችሉ ለመርዳት ነው፡፡
- ✓ ተማሪዎች ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜ በራስ መተመማናቸውን ለመገንባትና አንድ ጊዜ ስላጋጠሟቸው ወይም በክፍል ውስጥ ስለተማሯቸው አዳዲስ ቃላት ተጨማሪ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ የቃላት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው፡፡

- **ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት መጠቀም፡-** አዳዲስ ቃላት ለመማር በጣም ጠቃሚና ተጨባጭ ምንጭ ነው፡፡ ተማሪዎች መዝገበ ቃላት ስትጠቀሙ ልሳነ ዋህድ (በአማርኛ-አማርኛ) ቋንቋ የተጻፈ መዝገበ ቃላትን መጠቀም የተሻለ የቃላት እውቀታችሁ እንዲሰፋ ይረዳቸዋል፡፡ ምክንያቱም ልሳነ ክልኤ (ለምሳሌ ከአሮምኛ ወደ አማርኛ ወይም ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛና አሮምኛ) መዝገበ ቃላት ሁልጊዜ የሚሰጠን ቃሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ያለውን አቻ ፍቺ ብቻ ነው፡፡

- **ልሳነ ዋህድ ወይም አማርኛ-አማርኛ** መዝገበ ቃላት ግን የቃሉን ፍቺ፣ በቃላቱ የተመሰረቱ ዐረፍተ ነገሮችን ምሳሌ፣ ተመሳሳይ፣ ተቃራኒ ፍቺና የቃል ክፍሉን ወይም ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ስለሚያካትት የቃላትን መደበኛ ፍቺና አጠቃቀም ለይታችሁ እንድታውቁ ስለሚረዳችሁ በተለይ ቋንቋውን በጽሑፋዊ አፍልቆት ለመጠቀም በጣም ጠቃሚ ብልሃት ነው፡፡

- **ልሳነዋህድ መዝገበ ቃላት የመጠቀም** ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ አማርኛ መዝገበ ቃላት(2006 ዓ.ም፣ ገጽ፣3) የተወሰኑ ቃላትን ወስጄ አሳያችኋለሁ፡፡እባካችሁ ከተሰጣችሁ መዝገበቃላት ኮፒ ገጽ3 አውጡና ተከታተሉኝ ፡፡

ምሳሌ፡- ሀሳብ (ስ) 1.በአእምሮ ውስጥ የሚቀረጽ፣ የሚታቀድ፣ የሚመላለስ ጽንሰሀሳብ፣ ግንዛቤ

2. ስጋት፣ ጭንቀት፣ 3. አላማ፣ እቅድ፣ ፍላጎት 4. አስተያየት፣

1. <u>ሃሳብ</u> የሆነብኝ የልጄ ነገር ነው፡፡ በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ሀሳብ የሚለው ቃል የያዘውን ፍቺ የሚያሳየው ተራ ቁጥር ሁለት ላይ ያለው ነው፡፡

2. በዚህ ጉዳይ ላይ <u>ሃሳብህ</u> ምንድን ነው፡፡ በዚህ ዐ.ነገር ወስጥ ሐሳብ የሚለው ቃል የያዘው ፍቺ 4 ላይ የተገለጸውን ነው፡፡

3. በሚቀጥለው አመት ያቋረጥኩትን ትምህርት የመቀጠል <u>ሃሳብ</u> አለኝ፡፡ በዚህ ዐ.ነገር ውሰጥ ደግሞ ሀሳብ የሚለው ቃል የያዘው ፍቺ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተገለጸውን ነው፡፡

- **ብልሃቱን በጋራ በመጠቀም የሚከተሉት ቃላት በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ በጋራ እየፈለግን እንሰራለን፡፡**

ተግባራት ፡- ሀሳቡን አነሳ፣ 1.ያቀረበውን ሃሳብ ተወ፣ ቀየረ 2.ሀሳብ አመነጨ፣ አቀረበ

ምሳሌ1.አበበ ሚስት የማግባት <u>ሀሳቡን አነሳ</u>፡፡ ሀሳብ የሚለውቃል በዚህ ዐ.ነገር የያዘው በተራቁጥር 1 የተገለጸውን ነው፡፡

2. አበበ የትምህርት ጥራት ስለሚሻሻልበት መንገድ ጥሩ <u>ሀሳብ አነሳ</u>፡፡ ተራቁጥር 2

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል ፍቺ ለመረዳት ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? ልሳነዋህድ መዝገበቃላት የመጠቀም ብልሃትን መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

- **ልሳነ ዋህድ መዝገበቃላት የመጠቀም ብልሃትን በመጠቀም የሚከተሉት ቃላት በመዝገበቃላቱ ውስጥ የያዙትን ፍቺ ከፈለጋችሁ በኋላ ዐ.ነገር መስርቱባቸውና በዐ.ነገሩ ውሰጥ የያዙት ፍቺ በመዝገበ ቃሉ ውሰጥ የትኛው ተራቁጥር ላይ እንደሚገኝ በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆናችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡**

ተግባራት፡- በሰና፣ ቋፍ፣ ደብዛ፣ ተከነ፣ አበለ፣ቆረጠ፣ መጠጠ፣ ሰፈረ፣ቀና (*መማሪያ መጽሃፍ ገጽ*፣172-173)

- **ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት በመጠቀም ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን፣ የቃል ክፍላቸውንና ስዋስዋዊ አጠቃቀማቸውን በመፈለግ፣ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግባችሁ በግላችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡**

ተግባራት፡-ከፈተ፣ ገለጠ፣ ለመለመ፣ መስክ፣ ተተራመሰ፣ ቃረመ፣ ሰየመ፣አታለለ፣ አታላይ፣ መለስአለ፣ ተመለሰ

-ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄ ያሏት/ያሉት?

ተማሪዎች ዛሬ ትልቅ ስራ ሰርታችኋል፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት ልሳነዋህድ መዝገበቃላት የመጠቀም ብልሃትን ተጠቅማችኋል፡፡ የቃላትን ፍቺ የመረዳት ሂደታችሁን

የቃላት መማር ብልሃት ስልጠና ክፍል ሰባት፡- አካካሽ ብልሃቶች

- **አካካሽ ብልሃቶች፡-** እነዚህ ብልሃቶች በቃላት ዕውቀት ማነስ ምክንያት በተግባቦት ሂደት የሚያጋጥማችሁን ችግር ለመቋቋም የሚጠቅሟችሁ ብልሃቶች ናቸው፡፡ ለቃላት ትምህርት የበለጠ ተገቢነት ያለው አካካሽ ብልሃትም፡-
- **የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ የመገመት ብልሃት ፡-** የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ የመገመት ብልሃትን ለመጠቀም ተማሪው ሁለት የተለያዩ ፍንጮችን (መረጃዎችን) ስነልሳናዊ (በቋንቋው ያለውን እውቀት) እና ኢ-ስነልሳናዊ ፍንጮችን በመጠቀም የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም ለመገመት የሚረዳ ብልሃት ነው፡፡
- ስነልሳናዊ ፍንጭ መጠቀም ማለት ለምሳሌ በንባባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን የቃል ክፍላቸውን በመለየት፣ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያን በመለየትና ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ መገመት ማለት ሲሆን **ኢ-ስነ ልሳናዊ ፍንጭ (እውቀት) በመጠቀም** ማለት ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ያለንን የቀደመ /ዳራዊ እውቀትን ወይም አጠቃላይ እውቀትን መሰረት በማድረግ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአውድ በመገመት መረዳት ነው፡፡
- **የመገመት ብልሃትን እንዴት እንደምጠቀምበት** ከመማሪያ መጽሐፋችሁ **አካባቢያችን** የሚለውን ምንባብ ካነበብኩ በኋላ የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ያላቸውን ፈቺ ስነልሳናዊ ፍንጮችን ለምሳሌ የቃላቱን ተቃራኒ ፍቺ በመፈለግ፣ የቃል ክፍሉን በመለየት፣ ቅድመና ድህረግንድ ቅጥያን በመለየት የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ፍቺ በመገመት

አሳያችኋለሁ፡፡ እባካችሁ ከመማሪያ መጽሐፋችሁን ገጽ--120 ላይ ግለጡና ተከታተሉኝ፡፡

ተግባራት፡-

ተዝረክርኮ

ብክለት

የምናልመው

ፋይዳ

የተቀናጀ

- የመገመት ብልሃትን በጋራ በመጠቀም ተውኔት የሚለውን ምንባብ ካነበብን በኋላ ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ያላቸውን ፍቺ በጋራ እየፈለግን እንሰራለን፡፡

ተግባራት፡-

ትዕይንት፣

ሙዳይ፣

መድረክ፣

የገሃድ አለም፣

ክዋኔ፣

አሳረገ፣

ብልሃቱን በምትተገብሩበት ጊዜ ምን ችግር ገጠማችሁ? ያጋጠማችሁን ችግር እንዴት ፈታችሁት? የተማራችሁትን ቃል ፍቺ ለመረዳት ብልሃቱ ጠቃሚነው? ብልሃቱ ለመተግበር አስቸጋሪ ነው? ከክፍል ጓደኞችህ ስለቃላት ትምርትሽ/ህ ምን ተማርሽ/ክ? ከአውድ የመገመት ብልሃትን መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደምትጠቀሚ/ም ታውቂያለሽ/ህ?

የመገመት ብልሃትን በመጠቀም ክረክር የሚለውን ምንባብ ከነበባችሁ በኋላ የሚከተሉት አዳዲስ ቃላት ፍቺ በምንባቡ መሰረት የያዙትን አገባባዊ ፍቺ በግላችሁ ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

-ብልሃቶቹን በተመለከተ ጥያቄ ያሏት/ያሉት?

ተግባራት፡-ለአብነት፣ ታዳሚ፣ ይሰይማሉ፣ ቀሰረ፣ ብይን፣በጸጋ፣ በጥሞና፣ ሙዳ፣ይቃርማሉ፣ አይነፍጉም (የዘጠነኛ ክፍል መማሪ መጽሓፍ ገጽ፣ 171)

እኔ በናንተ ኮርቻለሁ፤ እናንተም በራሳችሁ ልትኮሩ ይገባል፡፡ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የሚያስችላችሁን አይነተኛየመገመት ብልሃቶች ተጠቅማችኋል፡፡

ማስታወሻ፡-ትምህርቱ እስኪጠናቀቅ (በእያናዳንዱ ሂደት) ተማሪዎች እንዲጠይቁ መፍቀድ፣ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፣ ለተማሪዎች ብልሃቶቹን የመጠቀምን አላማ ማስታወስ (የቃላት ፈቺን ለመረዳትና የቃላት መማር ሂደትን መቆጣጠር) ፡፡ ኢቀጥተኛ ብልሃቶቹን የችግር መፍቻ ብልሃቶቹን በእያንዳንዱ ደረጃ ማካተት ማለትም የቁጥጥር፣ የመገምገም፣ ማህበራዊና ሃላፊነትን የመቀበል ብልሃቶችን)